# ነፀብራቅ



ከአስግድ መኮንን

PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

© አሰግድ መኮንን 2002 ዓ.ም

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
All Rights Reserved

## ምስጋና

ከዚህ ዘመን ይልቅ ያለፈው ዘመን ለምን ተሻለ ብለህ አትናገር፡፡ የዚህን ነገር በጥብቅ አትጠይቅምና?
መፅሐፈ መክብብ ምዕራፍ 6:10

ሁሉ በእርሱ ሆነ ያለ እርሱ ግን የሆነም ያልሆነም

አንዳችም ነገር የለም

ስጀምር ከእኔ ጋር ነበርህ ፡ ስጨርስም ከእኔ

አልተለየህኝምና ክብር ምስጋና ለአንተ ይሁን ፣

አሜን፡፡



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

## የደራሲው ቀደምት ስራዎች

1 ኮብላይ 1990 ዓ.ም.

2 ጥብቅ ምስጢር 1999 ዓ.ም.

3 ነፀብራቅ 2002 ዓ.ም.

## ያልታተሙ የደራሲው ስራዎች

4 ጥብቅ ምስጢር ክፍል ሁለት

5 ዴር ሱልጣን 2000 ዓ.ም.

6 ስውር ህሊና 1996 ዓ.ም.

7 የጠረፉ ንጉስ 1992ዓ.ም.



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

## ማውጫ ገጽ

መግቢያ ...... 3
መቅደም ............... 6
ምዕራፍ = 1 የሃውልቱ ምስጢር : 15
ምዕራፍ = 2 የተደበቀው ሴራ : 25
ምዕራፍ = 3 የደርግ ውድቀት መዘዝ : 31
ምዕራፍ = 4 መፈንቅለ መንግስቱ ከሸፈ : 44
ምዕራፍ = 5 አስማሪ ሸፍቷል : 53
ምዕራፍ = 6 የመረጃ ሸምበሉ ተያዘ : 68
ምዕራፍ = 7 የመአህድ ምስጢር : 72
ምዕራፍ = 8 የሰላ ድንጋዩ ጦርነት : 83
ምዕራፍ = 9 የወረራዉ እቅድ ጥናት : 85
ምዕራፍ = 10 30 ደቂቃ በደብርብርሃን : 89
ምዕራፍ = 11 ወህኒ ቤቱ ተሰበረ : 105
ምዕራፍ = 12 የናዝሬቱ ሽማግሌ : 110
ምዕራፍ = 13 የፕሮፌሰሩ ንግግር : 126
ምዕራፍ = 14 ጀግኖች ናቸዉ : 147
ምዕራፍ = 15 ከጠበቃዉ ማስታወሻ : 163
ምዕራፍ = 16 የፕሮፌሰሩ እዉነተኛ ታሪክ : 180
ምዕራፍ = 17 የጥቁር አንበሳው ዶክተር 195



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

# መግቢያ

በአለማችን ቀደምት ታሪክ ከአላቸው አገራት መካከል አንዷ ኢትዮጵያ እንደነበረች ቅዱስ መጽሐፍ ሳይቀር ምስክርነት ይሰጣል::በዚህ ረጅም የታሪክ ሂደቷም የመንግስት ስርዎ አመጣጥ በነበረው የስልጣን ተቀናቃኝነት በጨቋኞችና በነፃነት ፈላጊዎች መካከል በነበረው ትግል የብዙ ሰዎች ህይወት በምክንያት ነገር ግን ያለዋጋ ሲከፈል ኖሯል:: አብዛኛው ታሪካችንም የሰላም የስልጣን ሽግግር ሳይሆን የመንግስት ግልበጣ በመሆኑ አገራችንም በነበራት የስልጣኔ ጉዳና ከመቀጠልና አለም ከደረሰባት ደረጃ ከመድረስ ይልቅ ከመጣችበት በብዙ እርቀት ወደኋላ እንድትገሰግስ አድርጓታል:: ለነጻነት ለታገሉም የትግላቸውን ምክንያት መርምሮ በመረዳት የጠበቀውን ማነቆ ከማላላት ይልቅ መሪዎቻችን የላላዉን በማጥበቅ ተቀናቃኞቻቸውን ሲጥ ለማድረግ ሲታገሉ ኖረዋል::

ያም በመሆኑ በኢትዮጵያ የስልጣን ለውጥ ከሰላም ሽግግር በተሻለ የጠመንጃው ግልበጣ እንደ ቀላል መንገድ እየተመረጠ ሊመጣ ችሏል:: በዚህ መጽሐፍም የምንመለከተው ይህንኑ እውነታ ነው::: እንደውሽማ ሞት ተሸፋፍኖ ያለፈውንና በ1984 ዓ.ም ተሞክሮ ያልተሳካውን የመፈንቅለ መንግስት ሙከራና ያስከተለውን የመበቃቀል ሂደት በአጭር በአጭሩ ለመግለጽ ተሞክሯል::

በዚህ ታሪክ በአለም ዙሪያ የፖለቲካ ሊቃውንትና ጸሐፊያን ብዙ ያሉበትና የጻፉበት ቢሆንም ትክክለኛውን እውነታ አግኝተውታል የሚል እምነት የለኝም:: ይህ ዝብርቅርቅ የታሪክ ሂደት በዚህ መልኩ ቢተላለፍ ለቀጣዩ ትውልድም የመበቃቀል ውርስን ሊያወርስ ይችላል የሚል ግምት ስለአለኝ አንዳንድ ሰዎች ባይቀበሉትም እውነታኛውን ታሪክ ለመግለጽ ሞክሪያለሁ:: ያም ሆኖ ግን ዝርዝሩን በሙሉ ያካተተ ነው የሚል እምነት የለኝም:: ምናልባትም በመረጃ እጥረት ምክንያት የቀሩትንና ታሪኩን እያወቁ ለመስጠት ፍቃደኛ ያልነበሩ ባለታሪኮችን ከዚህ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

መጽሐፍ በኋላ በድጋሚ ማግኘት ከተቻለ እንደ ክፍል ሁለት ሆኖ ሊቀርብ ይችላል:: ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በዚህ መጽሀፍ የሰፈሩት አሳቦች በሙሉ በወቅቱ ከነበሩት እውነተኛ ባለታሪኮች በቃለመጠይቅ የተወሰዱ ሆነው ከቴክኒክና ከቋንቋው በቀር ምንም የሃሳብ ለውጥ ያልተደረገባቸውና ቃል በቃል የተወረሱ አለዚያም የሰፈሩ ናቸው::

አንዳንዶቹ ባለታሪኮች ስማቸው እንዳይጠቀስባቸው በማሳሰባቸው ታሪኩ ብቻ በንጽጽር ተወስዷል::በሌላ በኩል ግን አንዳንድ ጊዜ ይሆናል ብለን ያሰብነው ሳይሆን ይቀርና ፍፁም ሊሆን አይችልም ብለን የገመትነው ሆኖ ስናገኘው እራሳችንን እስከመጠራጠርእንደርሳለን::በዚህ መፅሐፍ ውስጥም የሚገጥመን ክስተት የዚህ ተመሳሳይ ታሪክ ነው:: የደርግ መንግስት ውድቀትን ተከትሎ ኢህአዴግ አገሪቷን ከተረከበበት ከ1983 ዓ.ም መጨረሻ ጀምሮ በኢትዮጵያ ውስጥ ያልተለመደና አዲስ የሆነ የብሔሮች ግጭት ተከስቶ እንደነበር ይታወቃል::

በነበረው የሽግግር ወቅትም በብዛት ችግር ይደርስበት የነበረው የአማራው ብሔር ሲሆን የችግሩ ምክንያትም ገዢዎች ትተውለት የሄዱት የተጠያቂነት እዳ ነበር:: እዳውን እንዲከፍሉ የተበየነባቸው በደሉን አድርሰዋል የተባሉት ቤተሰቦች ሳይሆኑ በየክልሉ ተሰራጭቶ ይኖር የነበረው ደሃ የብሔሩ ተወላጅ ነበር::

እነዚህ ሁኔታዎች ወደአገር አቀፍ ወይም ብሔርአቀፍ በመቀየራቸውም እና አማራው በአማራው ላይ በመነሳቱ የሽግግር መንግስቱን በኃይል ለመጣል በሰሜን ሸዋ ቀላማ አካባቢ ጦርነት ይ ጀመራል:: ይህም በመንግስት ሚዲያዎች ሳይቀር መሰማት ጀመረና በስውር የሚያንቀሳቅሰዉ ሃይል የመላው አማራ ህዝብ ድርጅት እንደሆነ ደርሼበታለሁ ሲል መንግስት ከሰሰ:: የሽግግር መንግስቱ ይህንን ይበል እንጂ የህዝብ አስተያየት ግን እስከ አሁንም ድረስ ፕሮፌሰሩ አያደርጉትም . . . የሚል ነው::

በሌላ በኩል ስለኢንጂነር ኃይሉ ሻውል በጥብቅ ምስጢር መጽሐፌ የነበረኝ መረጃ ትክክል እንዳልነበር በመጨረሻዋ ሰዓት



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

በመረዳቴ አንባቢን ይቅርታ ለመጠየቅ ተገድጃለሁ።ስህተት የተፈጠረበትምክንያትም ጥብቅ ምስጢር የተፃፈው በሰማንያዎቹ መጨረሻ ሲሆን የታተመውም ደግሞ በምርጫ ዘጠና ሰባት መጨረሻ ላይ ስለነበር ነው። በመጽሐፉ የሰጠሁት የላቀ ክብር ልክ እንዳልነበር በርካታ አስተያየቶችና ትችቶች ደርሰዉኛል። ከዚህ በተጨማሪ ስለኢንጂነሩ መሰረታዊ ባህሪና ማንነት እናውቃለን ያሉ ግለሰቦችም በመረጃ ጭምር አስተያየት ሰጥተውኛል። ኢንጅነሩን በ2001 ዓ.ም ቃለ መጠይቅ ባደረግኩላቸው ወቅት ከራሳቸዉ አስተያየት ልገነዘብ የቻልሁት ይህንኑ ነበር።

ሁለት ቀን የፈጀ ረጅም ቃለመጠይቅ አድርጌላቸው የነበረው ጥፋተኛ ነኝ ብለዉ መንግስትን ይቅርታ ጠይቀው ከእስር ከተለቀቁ በኋላ ሲሆን በነበረን ቆይታ በአማራውና በመአህድ ላይ የነበራቸውን አስተሳሰብም በመጠኑ ልረዳ ችያለሁ። ይህንን ለማረጋገጥም ይህን መፅሐፍ ያነበበ ሊረዳ ይችላል ብዬ እገምታለሁ። መልካም ንባብ ....... ።

ደራሲዉ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

# ቅድመ ታሪክ

ከአዲስ አበባ ከተማ ወጣ ብሎ በስተሰሜን ምእራብ በኩል በሚገኝ እና በእምነበረድ በተገነባ አንድ ዘመናዊ ህንፃ ውስጥ በርከት ያሉ የደርግ ከፍተኛ የጦር መኮንኖች ተሰብስበዋል:: ህንፃው በከፍተኛ ጥናትና ጥንቃቄ የተመሰረተ ሲሆን ባለሰባት ፎቅና እጅግ ዘመናዊም ነው:: ከምድር ቤቱ ሁለተኛው የመሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ ከተሰባሰቡት ሰባት የደርግ የመረጃ ኃላፊ መኰንኖች መካከል አንድ የህክምና ምሁርም አብረዋቸው ተቀምጧል:: ቤቱ የተቀባው ቀለም ነጭ ሲሆን የመቀመጫ ወንበሮቹ ከጥቁር ቆዳ የተሰሩ አግዳሚ ፎቴዎች ነበሩ:: ከሞላላው ጠረጴዛ ግራና ቀኝ በተቀመጡት ወንበሮች ሶስት ከአንድ ፊት አራት ደግሞ በተቃራኒው የመምሪያው ሃላፊዎች የተቀመጡ ሲሆን እነሱን ከሚያገናኘው መካከል ላይ ሁለቱን ለማየት በሚያስችል መልኩ ተጋባዥ ምሁሩ ተቀምጠዋል:: መኮንኖቹ ከዚ ህ ምሁር አንዳች እርዳታ እንደሚጠብቁ ሁሉ የሁሉም እይታ ያለው ከሳቸው ላይ ነበር::

የሀገሪቱ ፕሬዝዳንት ኰሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም በምዕራቦች የስለላ ሠራተኞች ተጠልፈው ከሀገር ወጡ ከተባለበት ጊዜ ጀምሮ የደርግ ስርዓት ተንኰታኩቶ ኢህአዲግና ሻዕቢያ አገሪቷን ሲቆጣጠሩ ከፍተኛ የሀገሪቱ ባለሥልጣኖች አብዛኛዎቹ ተገድለዋል አለዚያም ከሀገር ተሰደዋል:: አንዳንዶቹም «ጉድ» በሚያሰኝና በሚያስገርም ሁኔታ እጃቸውን ሰጥተው ዘብጥያ ወርደዋል:: ያመለጡትም ቢሆኑ ገና በመታደን ላይ ናቸው::

እነዚህ የወቅቱ የዓለም ዜናዎች ነበሩ:: ከፍተኛ የጦር መኰንኖች ከዚህ የመሰብሰባቸው ምክንያትም እጃቸውን ላለመስጠት የቆረጡና የተበተነውን የጦር ኃይል መልሰው በማሰባሰብ በሽግግር መንግስቱ ላይ መፈንቅለ መንግስት አድርገው የሻቢያና የኢህአዲግ ጥምር አገዛዝን ለማስወገድ የተደራጁ መሆናቸውን ቢገልጹም በራስ የመተማመን ሃይላቸው ልክ እንደነጠላ ሳስቶ ከመካከላቸው ካሉት ምሁር የሃሳብ ድራብ አስፈልጓቸዋል::

ከአራቱ መኰንኖች መካከል የደርግ የደህንነት ኃላፊ የነበሩት ኰሎኔል ቁጠጥብጥ አመላቸው ፋታ የነሳቸው ይመስል ሲበዛ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ተጣድፈዋል። ድርጅቱ የተቋቋመው በ1984 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ ሲሆን የመጀመሪያ ስራውም የተበታተኑትን የጦር ከፍተኛ መኰንኖች በማሰባሰብ እራሱን ከጥቃት መከላከልና አገሪቷን ከጥፋት ለማዳን፣ በየክልሉ ያሉትን የጐሣ ግጭቶች ከገበሬው ጋር በመመሣጠር እንዲቀዘቅዙ በማድረግ ብሔር ብሔረሰቦችን ለማስማማት በገበሬው ውስጥ ሰርጐ መግባት የሚል አጀንዳ ያጠቃለለ ነው።

ይህ ሁኔታ ደግሞ ፈታኝና ጥበብንም የሚጠይቅ ከመሆኑ በተጨማሪ ይህንን ለማድረግ በድርጅቱ ውስጥ የተለያዩ የብሔረሰብ አባላት የሆኑ መኰንኖችን ማቀፉ ስለማይቀር ምስጢር በመጠበቁ በኩል አስቸጋሪ ፈተና መግጠሙ የማይቀር ነው። በደህንነት ሹሙ በቀኝ በኩል የተቀመጡት የባህር ኃይል የፖለቲካ መምሪያ ኃላፊ ጄኔራል የነበራቸው የስራ ኃላፊነት የተበታተነውን ጦር መልሰው በማሰባሰብና አንድ ከፍተኛ ኃይል በማደራጀት ለመፈንቅለ መንግስቱ ቀደም ሲል የነበረውን ልዩ ኰማንዶ ኋይል እንደገና ማሰልጠን ነበር። ይህ ኰማንዶ የኢህአዴግና የሻዕቢያ መሪዎችን ምኒሊክ ቤተመንግስት እንደተቀመጡ ያለአንዳች ተኩስ ጠባቂዎቹን አንገታቸውን እያነቀ በመጣል ወደቤተመንግስቱ ዘልቆ በመግባት ይገባና ሁለቱን ፕሬዘዳንቶች በስብሰባው ላይ እንዳሉ በቀጥጥር ስር ያውላቸዋል።

በግራ በኩል ያሉት የደርግ የፀጥታ ኃላፊ የሌተናል ኰሎኔልነት ማዕረግ የነበራቸውና የሶስተኛው ክፍለ ጦር አዛዥ የነበሩት መኮንን በከተማው ውስጥ ለአለው አስር ሺህ ወታደር ልዩ መመሪያ የሚሰጡ ናቸው። አራተኛው የሻለቃነት ማዕረግ አላቸው። አምስተኛው የፖሊስ የፖለቲካና የፀጥታ ኃላፊ የነበሩ መኰንን ሲሆኑ የሻቃነት መአረግ አላቸው ። በተቃራኒ የተቀመጡት ሶስት ሰዎችም የተለያየ ማዕረግና ኃላፊነት ነበራቸው።ከነኚህ የጦር መኮንኖች የመገናኛ ጠርዝ ላይ የተቀመጡት ምሁርም የህክምና ፕሮፌሰር ነበሩ። የጦር መኮንኖቹ በሳምንት ሁለት ጊዜ እየተሰበሰቡ ስለጠቅላላው ሁኔታ የሚነጋገሩ ሲሆን የመረጃ ሪፖርትም ይለዋወጣሉ።የፀጥታ ኃላፊው የውይይቱ ዋና አላማ ያደረጉት በመላ ሃገሪቱ ስለተከሰቱት ግጭቶችና በብዛት እየደረሰ ስላለው የሰዉ እልቂት አሰቃቂነት ስለነበር በፕሮፌሰሩ በኩል ተቀባይነት ያገኘ ነበር።በተለይ በጐሳዎች መካከል የተነሳው የከረረ ግጭት ፕሮፌሰሩን ብቻ ሳይሆን የሁሉንም መኰንኖች መንፈስ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

በጭንቀት ወጥሮ የያዘ እደነበር ከውይይታቸው ለመረዳት ይቻላል፡፡

«ዋናው ነገር የብሔሮችን ግጭት እንዴት አድርገን እናብርድ የሚለው ነው፡፡ በአሁኑ ሰዓት አንዳንድ ባለስልጣኖች እንደ ከፍተኛ ስልት እየተጠቀሙበት ያለው መንገድ ብሔርን ከብሔር እያጋጩ እርስ በርስ እያስተራረዱ በዚህ መካከል ያገሪቱን ሀብትና ንብረት እየዘረፉ ማጋዝ ነው፡፡ እንደምታውቁት ፋብሪካዎች እየተነቀሉ ዕቃዎቻቸው እየተወሰዱ ማዕድኖቻችንም ለባእዳን እጅ መንሻ ተሰጥተው እየተመዘበሩ ናቸው፡፡ ቅርሶቻችንም በኃይማኖት አባት ነን በሚሉት አስመሳዮች ሳይቀር ፅላትና ንዋየ ቅዱሳት ጭምር ከየገዳማትና ከየአድባራቱ እየተዘረፉ ናቸው፡፡ እነኝህን ሁኔታዎች የማቆም ግዴታ አለብን፡፡ መከልከል ባንችል ዘራፊዎቹን ማስወገድ ይቻላል፡፡ በአሁኑ ሰዓት የበግ ለምድ ለብሰው የቀበሮ ባህታዊነታቸውንእያሳዩን ናቸው» አሉ ኰሎኔሉ፡፡

«እንዴት አድርገን ነው ማስወገድ የምንችለው?፡፡ » ሲሉ ጠየቁ የፀጥታ ኃላፊው፡

«ማንኛውንም ህገወጥ ንግድ የሚያራምድ ነጋዴ ይመታል፡፡ ተቀባይ ከሌለ ሌባ ሊኖር ስለማይችል ነጋዴዎቹ ይመታሉ» ጄኔራሉ መለሱ፡፡

«ይህንን አደረግን ማለት እኮ በቀጥታ ጦርነት ከፈትን ማለት ነው፡፡ ያውም ስንቅና ትጥቅ ሳይኖረን፡፡ የሚያዋጋን ኃይልም ሳናዘጋጅ» ሻምበሉ ሃሳቡን ተቃወሙ፡፡ «ሌላ መንገድ መመረጥ አለበት፡፡ ይሄኛው እንደ አማራጭ ይሁንና በሌላ በኩል መንቀሳቀስ አለብን» አስጠነቀቁ፡፡

"ወደመፈንቅለ መንግስቱ ከመግባታችን በፊት በርካታ ሰዎችን እናሰለጥናለን፡፡ የምናሰለጥናቸው ሰዎችም ሙሉ ስልጠና ያስፈልጋቸዋል፡፡ ምንም እንኳን የሰለጠኑ ኮማንዶዎች ናቸው ብለን ብናምንም እደገና መታየት ይኖርባቸዋል » አሉ የፀጥታ ሹሙ፡፡ በክፍሉ ውስጥ ለመጠነኛ ጊዜ ዝምታ ከነገሰበት በኋላ የደህንነት ሹሙ ንግግር ጀመሩ፡፡

«መልካም ነው፡፡ ቁጥሩ ወደ አምስት መቶ የሚጠጋውን



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ከማንዶ ኃይላችንን በአስር ሺህ የሰለጠነ የከተማ ውስጥ ተዋጊ))
ጄኔራሉ ጣልቃ ገቡ::

«እኛአሰልጥነን እስከምናዘጋጅ ድረስ ሴላችንን ሊደርሱበት ይችላሉ:: በመላ ከተማው በየተሰማሩ ሲቪል ደህንነቶች:: ሚስጥራችንከተደረሰበት ልንቋቋማቸው አንችልም:: እንከላከላቸው ብንልም እንኳን ብዙ አንገፋም:: ስለዚህ ሌላ በአጭር ቀናት ውስጥ ሊጠናቀቅ የሚችልበትን መንገድ መፈለጉ የተሻለ ይመስለኛል» ብለው ሁሉንም በየተራ ተመለከቷቸው:: ሁለቱን ጠርዝ ከሚያገኘው ሰፍራ ላይ የተቀመጡት የህክምና ምሁር ሁለቱም ወገኖች የሚነጋገሩትን ከመፃፍ በስተቀር ምንም አይናገሩም::

«እንግዲያው ሁሉንም ነገር እስከምናጠናቅቅ ድረስ መፈንቅለ መንግስቱን እናዘገየዋለን» አሉ ኰሌኔሉ::

«በሱ እስማማለሁ:: ማንኛውም ነገር በጥድፊየ መጀመር የለበትም » አሉ የህንነት ሹሙ::

«ሰልጣኞች ሰልጥነው ወደ ግዳጅ ከመግባታቸው በፊት ነገሩ ግልፅ ተደርጐላቸው የፖለቲካ ትምህርት ይሰጣቸው:: ስለ ኤህአዴግ አላማና ምንነት ማወቅና መረዳት አለባቸው:: ኢህአዴግ አስራ ሰባት አመት የተዋጋው እራሱን ለመግንጠል እንጂ የኢትዮጵያን ህዝብ ነፃ ለማውጣት እንዳልነበር ማወቅና መረዳት አለባቸው» አሉ ጀነራሉ::

«ይህንን በተመለከተ የአንድ ሣምንት ትምህርት ይበቃል:: በሌላ በኩል የምንመለምላቸው ኃይሎች ሴቶች ቢሆኑ ይመረጣሉ:: በሰሌላ በኩል እያሰለጠንን በከተማው የምናሰማራቸው ኃይሎች ወደተራ ነፍስ ግድያና ዝርፊያ አልፈው እንዳይገቡም መጠንቀቅ አለብን:: ሁሉንም ትምህርት እንደጨረሱ ቀጥታ ወደ ግዳጁ ከማስገባታችን በፊት የፖለቲካ ትምህርት በቅድሚያ እንደሚያስፈልጋቸው አምናለሁ» ሲሉ መለሱ የፀጥታ ሹሙ::እንደገና ዝምታ ሆነ:: የሁሉም አእምሮ በሃሳብ ሰመመን ተውጦ እይታቸው ወደምሁሩ አቅጣጫ ሆነ::



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ምሁሩ ግን አጎንብሰው እየዓፉ ነበሩ:: ዝምታው ሲበዛባቸው ሳይሆን አይቀርም መጻፋቸውን አቋረጡና ቀና ብለው በግራና በቀኛቸው ያሉትንና ግራ የተጋቡ የሚመስሉትን የጦር መኮንኖች አንድ ግዜ ወደግራቸው መልሰው ወደቀኝ አንገታቸውን በሥግዚዟር ይመለከታቸው ጀመር::

«ብዙ ሆዳሞች አሉ:: ብዙ ውትፍትፍ አድርባዮች ከኛ መሃል ሰርገው ገብተዋል:: ስለዚህ በዚህ አቅማችን መፈንቅለ መንግስት ከፊትን ማለት ጅልነት ነው:: አንድም አይነት እርምጃ መውሰድ አንችልም:: ልንራመድ የምንችልበት መንገድ ምልመላውን በመቀጠል በበቂ ሁኔታ ወታደራዊ ስልጠና መስጠት ብቻ ነው:: በተቻለ መጠን እንማን እንደሚመለመሉና እንደሚሰለጥኑ ማወቅ አለብን::

ከሥራ የተፈናቀሉና በቤተሰባቸው ላይ ጉዳት የደረሰባቸው ወገኖች በስልጠናው ቢካተቱ ይመረጣሉ:: በተለይ ቤተሰቦቻቸው የተገደሉባቸው ሰዎች ይጠቅሙናል:: ከዚያ በኋላ የመፈንቅለ መንግስቱ ተግባር በልዩ ኰማንዶ በሚጀምርበት ወቅት በዚህ መልኩ ያሰለጠናቸው ኃይሎች ደግሞ ቤት ለቤትና በከተማ ውስጥ የሽምቅ ውጊያ በመክፈት የመንግስት ኃይል እንዳይንቀሳቀስ ወጥረው በመያዝ ይረዱናል » አሉ ጀኔራሉ::

«ትክክል የሆነ አሳብ ነው ብዬ አምናለሁ:: ቀድመን የመፈንቅለ መንግስት እርምጃ መውሰዱ በህዝብም በኩል አመኔታን ያሳጣናል:: በኛ ላይ ያለው የህዝብ አመለካከት ገና አልተቀየረም:: እኛን እንደጠረኛ እና የዲሞክራሲ ፀር እንደሆንን አድርገው እየሰበኩት ናቸው:: በሌላ በኩልም እነሱ ራሳቸው ጥቃት እየፈፀሙበት በእኛ እያመካኙ ስለሆነ ለጊዜው ህዝብ ላይቀበለን ይችላል:: ብዙ ራስ እና ብዙ ምላስ ስለአላቸው ህዝቡን አሳምነውታል:: በዚያም ላይ የምዕራቡና የምስራቁን አለም በተለያዩ ጥቅም እየደለሉት ናቸው:: ቀጥ ብለው መቆም የማይችሉ ሽባዎች ስለሆኑ እምነታቸው ያለው በምዕራቦቹ ላይ ነው:: በነሱ ምርኩዝነት ቆመዋል:: የውጭ ኃይሎቹም ሲጠ ብቀትና ሲያልሙት የነበረው ይህንኑ ነበር:: ወኔ ቢስ የሆነች



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

በራሷ የማትተማመን ኢትዮጵያን ማየት:: በሞሳድና በሲ.አይ.ኤ እያደኑ ያጠቃናል:: ከድንገተኛ መፈንቅለ መንግስት ውጭ ምንም ነገር ማካሄድ የለብንም:: እስከዚያው ድረስ ሁሉም ነገር በሚስጥር መያዝ አለበት:: የኢህአዴግና የሻዕቢያ አላማ ለነኝህ ጠላቶቻችን እኛን ባርያ አድርገው ለማስገዛት ነው:: በአሁኑ ሰዓት ለሃገር የሚቀረቀሩትን ወገኖች ማስመታትና እርስ በርስ ማጫረሱን ስራዬ ብለው ይዘውታል:: በተለይ የአማራ ብሔር የሆኑትን በቅድሚያ ከኢትዮጵያ መሬት ካጠፉ በኋላ ሌሎቹንም በተለያዩ ዘዴዎች አዳክመው ባርያ አድርገው መግዛታቸው የማይቀር ነው»በማለት ንግግራቸውን አጠቃለሉ የደህንነት ሹሙ::

የሁሉም አስተሳሰብ የተለያየ ባይሆንም «በየትኛው ቢጀመር ይሻላል» የሚለው ሀሳብ ብዙ ጊዜ አነታርኳቸዋል:: የእለቱን ስብሰባ መቋጫ ያበጁለት በመካከላቸው የነበሩት የህክምና ምሁር ነበሩ:: ለብዙ ሰዓታት በተደረገው የመኮንኖቹ የተወዛገበ ውይይት አንድም ጊዜ ጣልቃ በመግባት አስተያየትም ሆነ አሳብ ሳይሰጡ ቆይተው በመጨረሻ ላይ ግን በማስታወሻቸው ላይ ሲያሰፍሩ የቆዩትን አረፍተነገር እየተመለከቱ በየአንዳንዱ ሃሳብ ላይ አስተያየት መስጠት ጀመሩ::

«በቅድሚያ ልገልጽላችሁ የምፈልገው እኔ ወደ መላው አማራ ሕዝብ ድርጅት ስመጣ እና ድርጅቱን በሃላፊነት ለመምራት ስረከብ በኔ በጎ ፍቃድ ሳይሆን በህዝብ ጥያቄና ግፊት እንደነበር ነው የማስታውሰው:: አዚህ ከእናንተ መካከልም የተገኘሁት በእናንተው ጥያቄና ግፊት አሳሳቢነት እንደሆነ የምታውቁት እና የምትረዱት ነው::

የእኔ ከእናንተ መካከል መገኘቴ የሳት አደጋ ሰራተኞችን ስራለመስራት እደሆነ ስረዳው እራሴን ሳይገርመኝ እንዳልቀረ ላስረዳችሁ እወዳለሁ:: ለምን ብትሉኝ እኔ የህክምና ባለሙያ እንጂ የጦር መሃንዲስ አልነበርኩም አይደለሁምም:: ይህንን እናንተም የምትረረዱት ሃቅ ነው:: እንዲያውም የኔ በዚህ መገኘት አንዳንዶችን ሳየገርማቸው እንደማይቀር እረደለሁ:: ያም ከሆን ትክክል ናቸው:: ለምን ብትሉኝ አንድ የህክምና ባለሙያ ከጦር መሃንዲሶች ጋር በፀጥታ ጉዳይ ላይ ሲሳተፍ እኔ የመጀመሪያው


PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ሳልሆን አልቀርም:: ያም ሆኖ ግን እሳትን ለማጥፋት የግድ የእሳት አደጋ ባለሙያ የሆኑ ሰው ብቻ መጠበቅ ስለሌለበት እኔም የሃገራችንና የህዝቦችን ጉዳይ አሳስቦኝ አብሬያችሁ ለመወያየትና ለመመካከር በመካከላችሁ ተገኝቻለሁ::እስከ አሁን የተነጋገራችሁትንም የየራሳችሁን አሳብ በትክክል አዳምጬ ይዣለሁ:: የቱ ይበጃል የትኛው ጠቃሚ መንገድ ነው በሚለው አሳብ ላይም አስፈላጊ በመሆኑ ሰፋ አድርገን እንድንወያይበት መደረግ ይኖርበታል:: ምንም እንኳን የጦር ባለሙያ ባልሆንምና በውሳኔው ባልሳተፍም በእስካሁኑ ውይይታችሁ ላይ ሃሳብ ላቅርብና እንናተው ተመካከሩበት::

እንደ ዋና ተካፋይ ሃሳብ አድርጋችሁ ያቀፈባችሁት የጋራ ብዬ የወሰድኩላችሁ አሳብ የመፈንቅለ መንግስቱን ስለሆነ ነው::ይህንን እቅድ እኔም ብሆን በከፊል የምቀበለው ይመስለኛል:: ያም ሆኖ ግን ከፍተኛ ስጋት አለኝ:: ለምን ብትሉኝ መፈንቅለ መንግስት የሚደረግበት መንግስት እስከአፍንጫው የታጠቀ ሰራዊት ያለው ነው:: በምን አይነት መልአካዊ ሃይል ብትጠቀሙ ነው ይህንን ኋይል አልፋችሁ ቤተ መንግስት ልትገቡ የምትችሉት? ይህ ብዙ ያሳስበኛል:: ይሳካልናል ብላችሁ በእርግጠኝነት የምትሞክሩ ከሆነ ግን በምንም ተአምር በዚህ ከተማ ውስጥ ተኩስ መከፈት የለበትም:: እኔም ብሆን በሚፈጠረው ትርምስ ደም እንደጎርፍ ይህቺን ከተማ ሲያጥለቀልቃት መመልከት አልፈልግም::

ለማጠቃለያ ያህልም አለን ብላችሁ በምትኩሩበት ልዩ ኮማንዶ ሃይላችሁ ወደቤተ መንግስቱ ዘልቃችሁ የመግባቱ ሂደት ምናልባት ከተሳካ በሁለቱም አገራት መሪዎች ላይ ምንም አይነት ጉዳት ሳይደርስባቸው በሰላም እጃቸውን ይዛችሁ በማምጣት ሁላችንንም በጋራ ሊየነጋግሩን እንዲችሉ ማድረግ አለባችሁ:: በጠረጴዛ ዙሪያ እድናነጋግራቸው የምታስችሉን ከሆነ አቅሜ የቻለውን ሁሉ ድጋፍ ለማድረግ ዝግጁ ነኝ:: መስራት ያለባችሁ የእስራኤል የደህንነት ሰራተኞች የሚሰሩትን አይነት ሥራ መሆን ይኖርበታል:: ወደፖለቲካው ያስገባኝ የብዙ ሰዎች ደም ሲፈስስ ማየቴ ነው:: ስለዚህ ለማንኛውም ነገር በቅድሚያ አስባችሁ መጠንቀቅ ይኖርባችኋላ» ምሁሩ በማስጠንቀቂያ ንግግራቸውን ሲጨርሱ አስተያየትም ሆነ አሳብ ያቀረበ ማንም ባለ መኖሩ ሰብሰበው በዚህ ተዘጋ ::



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

# ምራፍ አንድ

## የሃውልቱ ምስጢር

1996 ዓ.ም ግንቦት ሰባት ቀን ከጠዋቱ አስራ ሁለት ሰዓት ተኩል ነው ::

ከእንጦጦ ተራራ ወደታች እየነፈሰ ያለው የማለዳ ቅዝቃዜ አጥንት ድረስ ዘልቆ በመግባት ሰውነትን ያንቀጠቅጣል:: ነጫጭ ልብሳቸውን የለበሱ መእመናን የባለወልድን ቤተክርስቲያን ግቢ የመላእክት መንደር እስኪመስል ድረስ አድምቀውታል:: ከቤተመቅደሱ መግቢያ በር በስተሰሜን እንደቆምሁ የቅዳሴውን ስነስርአት እያደመጥሁ ነበር። ከቤተ መቅደሱ ወደ ውጪ እየመጣ ባለው የእጣን ሽታ አካባቢውን በሙሉ የገነት መአዛ እየናኘበት ነው::

በድምፅ ማጉያ በአራቱም አቅጣጫ የቅዳሰው ልዩ ዜማ ሲንቆረቆር መንፈስን እየጎተተ እና እያንሳፈፈ ወስዶ ሰማዬ ሰማያት አድርሶ ይመልሳል:: ወርቀዘቦ ባለለምድ ካባ የደረቡና ባለንግስ አክሊል ከራሳቸው ላይ የደፉ አንድ ካህን በደቂቃዎች ልዩነት በስተሰሜን ባለው በር ብቅ ብለው ጽናጽሉን ሲያርገፈግፉት ሿ ሿ ሿ ይልና ልዩ መአዛ ያለውን የእጣን ሽታ ሲተፋው አካባቢውን የገነት መአዛ ሲያውደው ካህኑ ወደ ውስጥ ይመለሳሉ:: የቅዳሲው ዜማ ያለማቋረጥ ይንቆረቆራል::

ከቤተ መቅደሱ በስተደቡብ ምእራብ መቃብር ቦታ ከአንድ ሃውልት አጠገብ በርካታ ሰዎቻ የሃውልቱን ዙሪያ ከብበው ቆመዋል:: በእጃቸው አብርተው የያዙት የሻማ ብርሃን የማለዳውን ደብዛዛ ብርሃን ሮዝ ከለር በመስጠት የለበሱትን ልብስ ሳይቀር ልዩ ድምቀት ሰጥቶታል:: በተለያዩ አበባዎች የተጌጠው የሃውልት ቦታ አይንን የሚስብ ነበር:: ብዙ ዋጋ የወጣበት ስለመሆኑ እራሱ ምስክርነት መስጠት ይችላል::የጋዜጠኛነት



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ባህሪዬ መስለኝ ቅዳሴውን ሳልጨርስ ሃውልቱን ከበው ወደ ተሰበሰቡበት ሰዎች ሄድኩና ከነሱ ትንሽ ራቅ ብዬ እደቆምኩ የሚደረገውን ስነስርዓት በሞባይል እያቀረብኩና እያራቅሁ ከሃውልቱ ጋር በአንድ ላይ እቀርፃለሁ።።ኢንጂመር ሃይሉ ሻውል ሻለቃ ጌታቸው መንግስቴ ሻለቃ አድማሱ መልኩ የማውቃቸው የበርካታ ሰዎች ምስል በካሜራዬ እየተመላለሰ ይገባል። ከሃውልቱ በቅርብ እርቀት ፈንጠር ብለው የቆሙና በእጃቸው ሻማ አብርተው የያዙ ሰዎችም ይታዩኛል።።አናዳንዶቹ እያለቀሱ ስለነበር የእምባ ዘለላ ከፊታቸው ሲወርድበካሜራው እስክሪን ላይ ይታየኛል።።እንዚህን ሴቶች በካሜራዬ ምስላቸውን እያየሁ ማንነታቸውን መለየት ጀመርኩ። ወይዘሮ . . . አምባሳደር እገሊት ሲስትር . . . .እነሰም አብዛኞቹ የማውቃቸው ነበሩ። ከሃውልቱ ርቀውና ተለያይተው የቆሙበት የራሳቸው የሆነ ምክንየት ነበራቸው።

ሃውልቱን ዙሪያውን ከብበው ከቆሙት ግለሰቦች ጋር ሊታረቅ የማይችል የከረረ የአለማ ጣውንትነት ነበራቸው። በየፀሎታቸው መካከል አንዳቸው አንዳቸውን በጥላቻ አይን ሲመለከቱ የካሜራዬ እስክሪን እያቀረበ ያሳየኛል። በስተምስራቅ ከአለው የጥድ ዛፍ ላይ ተደግፎ ሁሉም ነገር በትዝብት እየተከታተለ ያለ አንድ ሰዉም ነበር። ከአኩራፊዎቹ ወገን ሊሆን እንደሚችል ገመትሁ።

የመላው አማራ ህዝብ ድርጅት መሪ ከሞቱ ጥቂት ወራቶች ቀደም ብሎ ኢንጂነር ሃይሉ ሻውል መአህድን እንዲመሩ ከተመረጡ ከተወሰነ ቀናት በኋላ አፍርሰው በጥንቱ የመአህድ ቢሮ መኢአድ የተባለ ህብረብሔር ድርጅት መሰረቱ። የመአህድ ቀደምት መስራቾችና የፕሮፌሰሩ የቅርብ ወዳጆች ከምንም በላይ የተማረው የአማራ ብሔር ተወላጆች የፕሮፌሰሩን የትግል ታሪክ ለማደብዘዝና አማራውን ያለታዛቢ ለማስቀረት የተወሰደ የተንከከል ሴራ ነው ብለው አጉረመረሙ።።ለዚህም ነበር ወደ ሃውቱ በመቅረብ የእጂነሩን ፊት ላለማየት በሩቁ የቆሙት። ቅዳሴው እንደቀጠለ ነው።።በድምፅ ማጉያ የምስጋና ዜማው እየተንቆረቆረ በጆሮዬ ሲገባ ይታወቀኛል። በመቃብሩ ዙሪያ የቆሙትና በየሃውልቶቹ ላይ የተደገፉት ሰዎች ያበሯቸው ሻማዎች የሚያርገበግባቸውን የማለዳ ነፋስ እየታገሉ አንብተውና



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

አልቅሰው እንደጨው እየሟሙ በማለቅ ላይ ናቸው።ስነስርአቱን በዚህ ሁኔታ እየተከታተልን እያለን ከጠዋቱ አንድ ሰዓት ሲሆን ሁኔታው በሙሉ ተቀየረና የባለውልድ ቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ በጩኸት ይታመስ ጀመር። የሁላችንም መንፈስ ወደ ትርምሱ ተሳበ። ከስድስት የማይበልጡ ሰዎች በከፍተኛ ድምፅ እየጮሁና እየተሳደቡ ወደ ሃውልቱ በመቅረብ ላይ ናቸው።ካሜራዬን ከእነሱ ላይ አነጣጠርሁና ወደኔ አቀረብኩት። ሰዎቹን አውቃቸዋለሁ። ከፊት ቀኝ አዝማች ነቅአጥበብ በቀለ ከሳቸው በግራ በኩል የምኒሊክና የአስኳል ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ የነበረው እስክንድር ነጋ። አራት ሰዎች ደግሞ ከነሱ ኋላ ተከታትለው ሃውልቱን ከብበው ሻማ እያበሩ ወደነበሩት ሰዎች እየተጠጉ ነበር።

ከሃውልቱ በትንሽ ሜትሮች ርቀር ላይ ሁለቱም ወገን ለፍልሚየ ተዘጋጅተው ተፋጠው ቆሙ።

«ልቀቅ አንተ ወሮ በላ !! እኔ ቀኝ አዝማች በቀለ በህይወት እያለሁ!!» አሉ ሽበታም ጎፈሬ ጭንቅላታቸውን በልህ እያወዛወዙ።

«አንተ ማነህና !! » የሃይሉ ግሩፕ መልስ ሰጠ። ኢንጂነሩ እልፍ ብለው ጥጋት ይዘው እንደቀሙ የሚባለውን የሚወራውን ሁሉ ያዳምጣሉ።

«እኔ ቀኛዝማች ነቅአ ጥበብ ነኝ መአህድን በአደራ የተረከብኩት። አንተማ የሞቱለትን ድርጅት አፍርሰህ መታሰቢየቸውን አጥፍተህ የለም እነዴ? እንዴት ብትደፍር ነው ታዲያ ከኝህ ክቡር ሰው መቃብር ላይ የቆምከው? ቀና ብለው መከልከል ስለማይችሉ ይሆን ? ይህ ትልቅ ድፍረት ነው።

እኛ የጅምራቸው ዳር አድራሾች እያለን ለመአህድ የለኮሷት ሻማ አትጠፋም። ሻማዋ እንዳትጠፋ ፕሮፌሰሩ አደራ ጥለውብኛል።»
ቀኝ አዝማች ወደፊት ሲጠጉ እነኛም በእርምጃ ቀረቡና



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ተፋጠጡ:: የኢንጂነሩ ግሩፖች በእጃቸው ላይ የነበሩትን የሻማ እላቂዎች የመጨረሻ እስትንፋሳቸው ከመጥፋቱ በፊት ወደመሬት ሲጥሏቸው ሽታቸው አካባቢውን አወደው::የቤተ መቅደሱን ዙሪያ ከብቦ ያስቀድስ የነበረው ምእመን ጸሎቱን አቋርጦ ተገልብጦ መጣና የተፋላሚዎቹን መጨረሻ ለማየት ዙሪያውን ከብቦ ቆሙ:: የሁለቱም ወገን ወኔ ሞቀና ጨበጣ ተያይዘው ግብግብ ተጀመረ:: ገላጋይ ከመካከላቸው ገብቶ ከገላገሏቸው በኋላ እራቅ ብለው ይመጥናል ያሉትን ቃላት እየተመራረጡ መወራወር ሲጀምሩ ምእምናኑ ወደነበረበት ተመለሰ::

«በኚህ ሰው ሃውት ላይ እየተገናኙ መነታረክ ልማድ እየሆነባቸው ነው » የሚል አስተያየት ከየአቅጣጫው ያስተጋባ ስለነበር እይታን ከአንዱ ወደሌላው እያዘዋወርሁ አዳምጥ ጀመር:: በዚህን ግዜ ነበር አጠገቡ የነበረ የፅድ ዛፍ ተደግፎ እንደቆመ ሁሉንም ነገር በትዝብት እየተመለከተ ከነበረዉ የቅድሙ ሰው ላይ እይታዬ ያረፈው:: እርምጃዬን ወደሱ አደረግሁ:: ከነበረበት ስደርስ ወደኔ መልከት አለና በተፈጠረው ክስተት አንገቱን በቁጭት ከነቀነቀ በኋላ ትክ ብሎ እየተመለከተኝ

«እነዚህ ሰዎች አንዳንዶቹ የድርጅቱን ጥብቅ ምስጢር ሳይቀር ለኢህአዴግ አውጥተው የሸጠና ፕሮፌሰሩን ለእስር የዳረጉ ሌሎቹም የአማራ ጉባኤ አቋቁመን ታሪክ እንሰራለን በማለት የሳቸውን ታሪክ ለማገዳፍ ላይ ታች ሲሉ የነበሩ ናቸው:: አሁን ደግሞ የይገባኛል ክርክር አንስተው ሲጣሉ ስመለከት እየገረመኝ ነው:: ከቶ ማንን ለማታለል እንደሆነ አይገባኝም:: ታሪክ እራሷ የምትሰጠው ምስክርነት ስላላት ከሃፍረት በስተቀር የሚያተርፉት ስምና ዝና ሊኖር አይችልም:: ስለሆነም ከድርጅቱ ከሚያገኙጥ ጥቅም አንፃር ካልሆነ በስተቀር ለታሪክና ለህዝብ አሳቢዎች አልነበሩም ወደፊትም ሊሆኑም አይችሉም »አለና ሲናገር ራሴን ከፍና ዝቅ አድርጌ «የኔም ግምት እንደዚያ ነበር » አልኩት::

«ግምት ብቻ አይደለም ትክክል ነህ» አለኝና እጁንወደኔዘረጋ:: ከዚያም ጠበቅ አድርጎ እየጨበጠኝ ብዙ ጊዜ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

እንደሚታዋወቁ ወዳጆች አቅፎ ሰላም አለኝ:: የት እንደምንተዋወቅ ለማስታወስስ እየሞከርሁ ስመለከተው ግራ መጋባቴን አየና

«እስር ቤት እያለሁ ነው ስለአንተ እሰማ የነበረው:: አድራሻህን ለማግኘት ብዙ ሰዎችን ጠይቄ ነበር:: አሁን በአጋጣሚ እዚህ በመገናኘታችን ደስ ብኛል::» አለኝ።

ለምን ሊያገኘኝ እንደፈለገ እያሰብኩኝ «ማን ልበል?»ስል ጠየቅሁት::

ሚካኤል በለጠ እባላለሁ በፕሮፌሰሩ የክስ መዝገብ ውስጥ ከነበሩት ተከሳሾች አንደኛው ሰው ነኝ:: የአስር አመት እስራቴን ጨርሼ ከወጣሁ ገና ሁለት ወር ሊሞላኝ ነው » አለኝና እጄን በወዳጅነት ያዝ በማድረግ ከግርግሩ ለመራቅ ከቤተክርስቲኑ በስተተምስራቅ ይዞኝ ሄደ::ከአንድ የተጋደመ ግንድ ላይ እንዳረፍን ታሪኩን እንደዚህ ሲል ጀመረልኝ::

«አፅመ ርስታቸው እፎይ እንዳይልና እንዳይተኛ በሀውልታቸው ላይ ሳይቀር መደባደብ ጀምረዋል:: አንዳንዶቹም የመሰረቱትን ድርጅት አፍርሰው መታሰቢያቸውንና ስማቸውን ከነመጨረሻ የቀበሩት ግለሰቦች ናቸው:: ለሁሉም ነገር ታሪክ የራሱን እውነት የሚያወጣበት ጊዜ ይመጣ ይሆናል ብዬ እገምታለሁ:: አለኝና በሃሳብ ርቆ ሄደ ከዚያም ሃሳቡን አሰባስቦ ያለፈ ታሪኩን እንደዚህ ሲል ጀመረልኝ::

የአዲስ አበባ ወህኒ ቤት ድሮ ከረቸሌ በመባል የሚታወቀው ቦታ አሁን ደግሞ ስሙ «በእግዚአብሔር» ተብሎ በሚጠራው ክልል ውስጥ ከፕሮፌሰሩ ጋር ለዘጠኝ አመታት ያህል ቆይቻለሁ:: በዚህ የመጨረሻ ግራውንድ ከሚበላው ልዩ የእስር ቦታ ከቤተሰብና ከዘመድ ሳልገናኝ አስር አመታትን በቆየሁበት ወህኒ ቤት ያሳለፍኩት እጄን የፍጥኝ በሰንሰለት ታስሬ ከሰው እንዳልገናኝ በማድረግ ነበር:: በዚያን ወቅት ተፈጥሮ የለገሠችኝን ፀሐይ እንኳን ሳላገኝና በዓይኔ ሳላይ በትንሽ ክፍል ውስጥ ከልለው ያንን ሁሉ አመታት አሳለፍሁ:: ከእኔ ቀጥሎ ከነበረው ክፍል



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ታስረው የነበሩት ደግሞ በዕፅ ማዘዋወር ወንጀል የተከሰሱና እጅግ አደገኛ የሚባሉ ግለሰቦች ነበሩ:: በዚህ ክፍል ውስጥ ለአንድ ዓመት ያህል solitary continue በሚባል አይነት እሥር የቆየሁ ሲሆን እኔ ከታሰርበት ክፍል ፊት ለፊት ፕሮፌሰር አሥራት የታሰሩበትና በከባድ ጥበቃ ቁጥጥር ስር ያለው ትንሽ ክፍል ይገኛል:: ወደዚህ ክፍል ከልዩ ደህንነት ዘቦች በቀር ማንኛ ውም የጥበቃ ሰራተኛ መቅረብ የተከለከለ ነው::

ፕሮፌሰሩ ጠዋት 12 ሰዓት የእስር ቤቱ በር ይከፈትላቸውና ወደውጭ ይወጣሉ:: በግቢው ውስጥ ለ 30 ደቂቃ ያህል የእግር ጉዞ ከአደረጉ በኋላ ከአንዲት የእንጨት መቀመጫ ላይ አረፍ ይሉና መጽሐፍ ማንበብ ይጀምራሉ:: ከቁርስ በኃላም ከአንዲት ትንሽ በርጩማ ላይ ጸሐይ ካለበት ስፍራ ይቀመጡና የመፅፍ ንባባቸውን ይጀምራሉ:: ከቁርስ እስከ ምሳ ሠዓት ያለው ረጅም ጊዜ የንባብ ጊዜያቸው ስለ ነበር ማንም መጥቶ ከተቀመጡበት እንዲነሱ የሚጠይቃቸው የለም:: በዚህ ሁኔታ ሳይንቀሳቀሱ ለረጅም ሰዓት ይቆያሉ::

ፕሮፌሰር ከዛች ሰዓት ጀምሮ ለምሳ እስከተደወለ ድረስ ከቦታቸው ንቅንቅ ሳይሉና ከማንም ጋር ሳይናገሩ በማንበብ ብቻ ጊዜያቸውን ሲያልፉ እኔ ደግሞ ከበሩ አጠገብ በምትገኝ ትንሽ ቀዳዳ እሳቸውን እየተመለከትሁ እቀመጣለሁ:: በእንደዚህ ሁኔታ የቀኑ ኡደት የቀጠለ ቢሆንም ወደ መጨረሻው አካባቢ የፕሮፌሰር ጤና እያሳሰበኝ መጣ::

አዘወትረው ወደውጭ መውጣታቸውን አቁመዋል:: የእሳቸውን ደህንነት የማረጋግጠው በተለመደ ቦታቸው ለንባብ መቀመጣቸውን በማየት ሲሆን ከዚያች ስፍራ ከሌሉ እሰጋ ነበር:: የታሰርኩበትን ቤት በር ታከኪ በቀዳዳ ማየት የዘወትር ልማዴ እየሆነ የመጣውም የጤናቸው ሁኔታ ከጊዜ ወደ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ጊዜ ስለታወከ ወደውጭ መውጣት በማቆማቸው ነበር:: ህመማቸው ከእለት ወደ እለት እየባሰባቸው ስለነበር ምናልባትም ጠንቶባቸው ተኝተው ይሆናል የሚል ስጋት ስለነበረኝ በቀዳዳው አጨንቁሬ እውላለሁ::

በዚህ ሁኔታ የተወሰኑ አመታት አሳልፌን ሁኔታዎች የበለጠ እያስጉኝና እያስጨነቁኝ እረፍትም እየነሱኝ መጨነቅና መበሳጨት ጀመርሁ:: ትዝ ይለኛል ጥር ወር መጀመርያ 1990 ዓ. ም ፕሮፌስርን ከአይኔ በተሰወሩ በብዙ ግዜያችን በድንገት ወደ ኳስ መጫወቻው ሜዳ በዝግታ ሲራመዱ አየኋቸው:: ለምን እንደጠፉ ለማረጋገጥ የምችልበት የመጠየቂያ መንገድ ባይኖረኝም በድንገት ሳያቸው በልቤ ውስጥ የተሰማኝ ደስታ ከፍተኛ ነበር::ፕሮፌሰር ሙሉ ልብሳቸውን ለበሰው ከቀኑ ወደ አምስት ሰዓት ገደማ ይሆናል ከእስር ክፍላቸው ወጡና ቀስ ብለው በጥንቃቄ እየተራመዱ ከፊት ለፊታችን በሚገኘው የኳስ መጫወቻ ሜዳ ውስጥ በመግበት ጥቂቶች የእግር ጉዞ ሲያደርጉ ተመለከትኩ:: ሁኔታቸውን እንደተመለከትሁም ታምመው እንደነበረ ተረዳሁ:: ግምቴ ትክክል ነበር::

ፕሮፌሰር በጣም ታመዋል:: በጥኑ መያዛቸውን የሰውነት እንቅስቃሴያቸው ቀድሞ ያስረዳል::እኔ ስላልገባኝ እንጂ ለካስ ፕሮፌሰር መታመማቸው ብቻ ሳይሆን ወደ ውጭ አገር ለህክምና ሊወጡ ተዘጋጁ ተብለው ኖሯል ከክፍላቸው የወጡት::

በትንሿ ሜዳ ለአስራ አምስት ደቂቃ ያህል ሲዘዋወሩ ቆይተው ከሜዳው ወደምታስወጣው ደረጃ ተራመዱ:: እሳቸው ወደሚራመዱበት
አቅጣጫ የእግራቸውን እንቅስቃሴ በአይኔ እየተከታተልኩ እና አብሬ በሃሳቤ እየተራመድሁ እያልሁ የዘገነነኝ ሁኔታ ተፈጠረ:: ፕሮፌሰሩ እራሳቸውን በራሳቸው ተደናቅፈው ወደቁ:: በተቀመጥኩበት እያለሁ ሳይታወቀኝ በስሜት ጮኬ ተነሳሁ::ከዚህ በኋላ ምን እደንደነበረ ምን እንዳደረግሁ ትዝ የሚለኝ ነግር የለም:: ትዝ የሚለኝ ነገር ቢኖር ሁለት እጄ በአንድነት ተጣምሮ በካቴና እንደታሰረ ወደሳቸው አቅጣጫ መብረሬ ብቻ ነበር::



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

በዚያን እለት የኔ ክፍል በር ለምን በላዬ እንዳልተቆለፈብኝ የተረዳሁት ከዚህ ሁሉ በኋላ ነበር:: ለካስ በሩን ክፍት ያደረጉልኝ ፕሮፌሰርን ለአንዴና ለመጨረሻሽ ግዜ በተቀመጥኩበት ሆኜ በእይታዬ እንድሸኛቸው የሰጡኝ ፍቃድ ኖሯል:: ለአንድም ለመጨረሻም ጊዜ የተሰናበትኳቸው በዚያች እለት በዚህ ሁኔታ ነበር:: የታሰረ እጄን አንከርፍፌ ወደሳቸው ብሮጥም እኔ ከመድረሴ በፊት እራሳቸው ተነስተው ቆመው አገኘ ኋቸው:: አንድነት ተቆራኝቶ የታሰረ እጄን ለሰላምታ እየዘረጋሁ

«ምነው አደናቅፍዎት? » ስላቸው

«አዎን አደናቀፈኝ » ብለውኝ የመውደቃቸው ምክንያት የአቅም ማነስ ሳይሆን ማየት ባለመቻላቸው መሆኑን በዚህ ሁኔታ አስረዱኝ::

«ሚካኤል የአይነስውሮችን ችግር ዛሬ ገና ተረዳሁ:: የስኳር ህመሜ ከፍተኛ ደረጃ ላይ በመድረሱ አይኔን ስለጋረደኝ ማየት አቃተኝና ነው ተደናቅፌ የወደቅሁት:: ሁሉንም ነገር ለይቼ ከማላይበት ደረጃ ላይ ደርሻሁ:: አንተንም የማይህ ግማሽ ሰውነትክን ብቻ ነው:: አንተነትክን የለየሁትም በድምጽህ እንጂ አይኔ በፍፁም ለይቶ ማየት አይችልም:: ለህክምና ሊወስዱኝ መሰለኝ ወደ ውጭ ወጥቼ ሰውነቴን እያፍታተሁ እንድጠባበቅ ነግረውኝ ነው አሁን ሰውነቴን ለማፍታታት ስራመድ አደናቅፎኝ ልወድቅ የቻልኩት» አሉኝ ባዘነ ስሜተውጠው:: «እንደዚህ ሳይብስቦት እና ሙሉበሙሉ ማየት ሳይሳኖት ለምን አልታከሙም» ስል ጠየቅኳቸው:: የታሰረ እጄን ጥብቅ አድርገው በእጃቸው ያዙኝና እንደመሳቅ ካሉ በኋላ

«ስማህ ሚካእል የኔ ጉዳይ መቼ እንዲህ በቀላሉ ከዚህ ወጥቼ ለመታከም የሚያስችል ሆነና ነው:: ብዙ ችግር አለበት:: በመጀመሪያ እዚህ ያሉት የወህኒ ቤት አለቆች አውቀው ቀጥሎ የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር እንዲያውቅ ይደረጋል:: እሱ ደግሞ በተራው ለደህንት ሪፖርት አድርጎ የደህንነት ቢሮው በጉዳዩ ከመከረበት በኋላ ለጠቅላይ ሚኒስተር ጽ/ቤት ተነግሮ ከጠቅላይ ሚኒስተር ጽ/ቤት መፈቅድ አለበት:: ከዚህ በኋላ ነው ወደ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ሆስፒታል ሄጄ መታከም የምችለው:: ይኸንን ለማድረግ ደግሞ ይኸው ሃያ ቀን ፈጀ:: በዚህ መካከል ነው እንደዚህ የሆንኩት:: በየሁለት ዓመት አሜሪካ ሄጄ እንድታይ የጠቅላይ ሚኒስቴሩ ቢሮ ወስኖልኝ ነበር:: እኔ ግን ምንም ሳይደረግልኝ ይኸው አምስት ዓመት በእስር ቆይቻለሁ:: ህመሜ ጠንከር ያለ ስለሆነ እዚህ ያሉት ሀኪሞች ብቻ የሚሠሩት አይደለም:: የማየት ችግር ከሁሉም ስለሚከፋ ለስዓይኔ ነግርኩህ እንጂ የሌላው ጤናዬ ችግር ከቀን ወደ ቀን እጅግ እየባሰብኝ ነው»:

እሳቸው ይኸን ብለውኝ ሌላ ነገር ሊነግሩኝ እየፈለጉ ሳለ ፖሊስ መጥቶ አካልቦ ከፊቴ ወሰዳቸው:: ከዚያን በኃላ ፕሮፌሰርን ድጋሚ ሳላያቸው የመጨረሻ ስንብታችን ሆነ:: የማይድኑ መሆናቸውን ሲያረጋግጥ መንግስት ለሌላ የፕሮፓጋንዳ ጠቀሜታ ሲል ብቻ ወደ ውጭ ሀገር ሄደው እንዲታከሙ ፈቅጃለሁ ሲል በሚድያዎቹ ሁሉ አስነገረ::

በእንደዚህ አይነት ሁኔታ እኔና ፕሮፌሰር አስራት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ስንብት ከአደረግን በኋላ ከምን ደረጃ ላይ ደርሰው ይሆን? ተሻላቸው ወይስ ደሞ ባሰባቸው? እያልኩ ወሬ ስጠባበቅ ከሃገር በወጡ ሶስት ወር ሊሞላቸው ጥቂት ቀናት ሲቀር የሞታቸው መረዶ ወደ አገር ቤት ተሰማ:: ይህን ከባድ መርዶ ስሰማ የወደቀብኝን ሃዘንለመግፅ ይከብደኛል::

አሥራታችንን በማጣታችንህሊናችን የደማው ከእሳቸው ጋር በአንድ ላይ የተሰቃየነው ብቻ ሳንሆን እስረኛው በሙሉ ነበር ለማለት እችላለሁ:: እነዚያ ብዙ ነፍስ ያዳኑ ሺዎችን በዶክተርነት ያስመረቁ ቅዱስ እጆች ለራሳቸው ህክምና አጥተው በወህኒ ቤት አይናቸው በስኳር ህመም ታውሮ እስከ መጨረሻ አንቀላፍተዋል:: እኚህ ታላቅ ሰው የአሟሟታቸው ሚስጢር በማይታወቅ ሁኔታ ለዚህች ሀገር ሲሉ አልፈዋል::



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

እኔም አሥር ዓመት ቆይቼ ከእስር መፈታቴ ነው። ወደዚህ የመጣሁበት ምክንያቱም በዚህ ሁኔታ የተለዩኝን የትግል አባታችንና አጋራችንን የስድስተኛ የሙት ዓመታቸውን ለማሰብ ነበር:: አሁን ግን የምትመለከተው ሁኔታ መንፈሴን ክፉኛ ስለነካው ተበሳጭቻለሁ:: አለና ትንሽ ሲያስብ ቆይቶ ቀጠለ።

በፕሮፌሰር ሞት ልቡ ያልደማ ወገን የለም:: ጠላት ከገደለን ይልቅ የራሳችን ወገን ያጠናብንን መከራና መከራችንን ለማብዛት የሄድነው ርቀት የትየለሌ ነው:: በገዛ ወገኖቻችን ብዙ የግፍ አተላ ተደፍቶብናል:: በጠላትነት ከፈረጁን ወገኖች በበለጠ አሁን እኔ እኔ እየተባባሉ የሚነታረኩት ቡድኖች በእኛ ላይ ብዙ ክህደት ፈጽመውብናል ያደረሱብን በደል ከጠላት በእጥፍ ይበልጣል እንጂ አያንስም::

ከሞታቸው የበለጠ እያሳዘነኝ ያለው ሁኔታ በሰላም እንቀላፍተው ከተኙበት ስፍራ ድረስ እየመጡ አርፈው እንዳይተኙ እየተጯጯሁ አላሳርፍ ብለዋቸዋል አለኝና ከተቀመጥንበት ቦታ እንዳለን ንግግሩን በድንገት አቋርጦ ዙሪያችንን ይቃኝ ጀመር ከዚያም በድንገት ብድግ አለና ቀሪውን ታሪክ በሌላ ግዜ እተርክልሃለሁ ብሎ ተሰናብቶኝ ሄደ:: ሻምበል ሚካኤል በጀመረልኝ ረጅም ትረካ መንፈሴን ወስዶት ስለነበር የስነስርአቱ መቋጫ ምን እነደነበር እንኳን የማስታውሰው ነገር አልነበረም::ትዝ ያለኝና የማስታውሰው ቢኖር ሁለቱንም ወገኖችፖሊስ ደርሶ እየገፈታተረ ከምድረግቢው ይዟቸው መውጣቱን ብቻ ነበር።



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

# ምዕራፍ ሁለት
## የተደበቀው ሴራ

ቀኝ አዝማች ነቅአጥበብ ይህንን ይበሉ እንጅ በህዝብ አመለካከት በኩል ሲታይ ከኢንጂነሩ የተሻለ ስም አልነበራቸውም፡፡ እንዲያውም ለመአህድ መዳከምና በመጨረሻም መፍረስ የእሳቸው ወደ ኢህአዲግ ተገልብጠው መግባት ነው የሚል ሃሜት አለ፡፡

ኢንጂነሩን በተመለከተ ግን የሰዎች አስተያየት ከመደብ ልዩነት ጋር የተያያዘ ስለነበር ወደመጨረሻው አካባቢ በመአህድ መፍረስ ዙሪያና ከፕሮፌሰሩ ጋር ነበራቸው ስለሚባለው የሁለቱ ቅራኔ ሰፋ ያለ ቃለ መጠይቅ አድርጌላቸው ስለነበር የተረዳሁት ይሄንኑ ነበር፡፡እሳቸው እንደሚሉት መአህድ እንዲፈርስ የተደፈገው በህዝብ ጥያቄ ሳይሆን በእሳቸው የግል ፍላጎት ነበርያፈረሱት። ወደ ህብረብሔር ለመቀየር አስበው ሳይሆን ከፕሮፌሰሬ ጋር በነበራቸው የአስተሳሰብ እና የመደብ ልዩነት ከምንም በላይ ደግሞ ከፕሮፌሰሩ ጋር በነበራቸው የማይታረቅ ቅራኔ ነው በማለት ያምናሉ፡፡

ምክንያቱን ሲዘረዝሩም ከፕሮፌሰሩ አለባበስ ይጀምሩና በስብሰባ ላይ ሳይቀር ፕሮፌሰሩ ባህልን እና ማንነትን ከአጥንትና ከደም እያመሳከረ የሚገልፅ ካፓን የመሳሰሉትን የመኳንንት ልብስ ለብሰው ስለሚመጡ ይህ የማይዋጥላቸው ኢንጂነሩ በመድረክ ላይ እንኳዋን ከጎናቸው አይቀመጡም ነበር፡፡ ከፕሮፌሰሩ ጎን ይቀመጡ የነበሩት የመሳፍንቱና የመኳንንቱ ልጆች የሆኑ እንደነ ወይዘሮ አልማዝ ኃይለማርያም እና አምባሳደር ዬዲት እምሩን የመሳሰሉት ወይዛዝርቶችነበሩ ይላሉ አስተያየት ሰጪዎች፡፡

ይህንን ሁኔታ ደግሞ ኢንጂነሩ የማይቀበሉት ብቻ ሳይሆን ፍፁም የሚጠሉትም ነበር በማለት የጥላቻቸውን ጥንተ መሰረት በማንሳት ሲያብራሩ አፄ ኃይለ ሥላሴ ለጎበዝ ተማሪዎች የማበረታቻ ሽልማት ይሰጡ ስለነበር ከተሸላሚዎቹ ተማሪዎች መካከል ኢንጂነር ሃይሉ ሻውልም ይቀርባሉ፡፡ በዘር ሃረጋቸው ሳይሆን በጥረታቸው መድረክ ላገኙት ተማሪ ፈተናው ቀላል



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

አልነበረም:: ንጉሱም ሃይሉን ትኩር ብለው እየተመለከቱ «አንተ ደግሞ የማነህ ልጅ» በማለት ሲጠይቁ

«የሻውል ልጅ ነኝ» ብለው ይመልሱዋቸዋል::ንጉሡ የተጠራውን ሰው ስም ባለማወቃቸው ሽልማቱን ብቻ ሰጥተው የሃይሉን እጅ ሳይጨብጡ ትተው ወደሌሎቹ ተሸላሚዎች ያልፋሉ::በዚህን ግዜ የበታችነት ስሜት የተሰማቸው የዛን ግዜው ለጋ ተማሪ ነገሩን እንደዋዛ ትተውት ረስተውት አልቀሩም:: ቂም ይዘው ለአደጉት ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል የአማራውን ባህልና ጥንታዊ ማንነት ለሚያንፀባርቁት ፕሮፌሰር አስራት ፍፁም የሚመቹ አልነበሩም ይላሉ ብዙዎች::እኔም ብሆን ለኢንጅነሩ ቃለመጠይቅ በአደረግኩላቸው ወቅት ይንፀባረቅባቸው የነበረው ስሜት ከዚህ የተለዩ ነበር ለማለት አልችልም::

ስለሆነም በዚህ ዙሪያ በአንድ ወቅት አቅርቤላቸው ለነበረው ቃለ መጠይቅ የሰጡኝ መልስ በሚከተለው መልኩ ነበር::

«ኢንጂነር የአስተዳደግዎን ሁኔታ ምን ይመስል እንደነበር ሊገልፁልኝ ይችላሉ?» የኔ ጥያቄ ነበር ::

ኢንጂነሩ ሳቅ ብለው ጀመሩልኝ « አስተዳደሬ የስነልቦና ተፅእኖ ነበረበት ለማለት እችላለሁ:: እናቴ የሞተችብኝ ገና የሶስት ዓመት ልጅ እያለሁ ነበር እንደናትም እንዳባትም ሆኖ ያሳደገኝ አባቴ ነው:: አባታችን እኛን ለማሳደግ የከፈለውን መስዋእትነት ሳስታውስ አሁን ላይ ያሳዝነኛል::»

«ለአባትና ለእናትዎ ስንተኛ ልጅ እደነበሩ ቢገልፁልኝ::?»

«ለቤተሰብ አምስተኛ ልጅ መሆኔ ነው::»

«የአባትዎ ስራ ምን አንደነበርስ ሊነግረኝ ይችላሉ::?»

«አባቴ ፖስተኛ ነበር:: እንዲህ እነደ አሁኑ ሞተር ሳይክል ይቅርና ተራ ሳይክልም እንኳን በአልነበረበት ወቅት በእግሩ የአዲስ አበባ ጎዳናዎችን እያደረሰ ነበር ከአንዱ ወደሌላው መስሪያ ቤት ፖስታ ያመላልስ የነበረው::»



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

«አስተዳደግም የስነልቦና ተፅዕኖ ነበረበት ማለት ነው::?»

«አልተሳሳትክም ትክክል ነህ » የምፀት ሳቅ ሳቁ::

«ወደ መአህድ እንዴት እንደገቡ ሊነግሩኝ ይችላሉ? ከሆነስ በወቅቱ ምን ምን ችግር ገጥምዎት ነበር::? »

«በመአህድ ውስጥ ብዙ የአመለካከት ችግር የነበረባቸው ሰውዎች ገጥመውኛል:: አብዛኛዎቹ አጥንትና ደማቸውን እየቆጠሩ የሚኖሩ እና አማራ ነው ሰው ብለው የሚየምኑ አይነት ምሁራኖች ነበሩ::

«በድርጅቱ ውስጥ የእርስዎ የስራ ድርሻ ምን ነበር::?»

«የውጭ ግንኙነት አላፊ ነበርሁ:: ፕሮፌሰሩ ወደ ማአህድ ያስገቡኝ የውጭ ግንኙነት እንድሰራላቸው ነበር::»

«ከፕሮፌሰሩ ጋር አልፎ አልፎ በመካከላችሁ ያለ መግባባት ይፈጠር እደነበር ሰምቻለሁ:: የአለመግባባታችሁ ምክንያት ምን እንደነበረ ሊገልፁንልኝ ይችላሉ?»

ኢንጂነሩ ትንሽ ሲየስቡ ቆዩና ራሳቸውን በዝግታ አወዛወዘው «የለም ትዝ አይለኝም» አሉኝ በአጭሩ:: ምንም እንኳን ለዚህ ጥያቄዬ መልስ ባይሰጡኝም ቀደም ሲል በድርጅቱ ውስጥ አማራ ብቻ ነው ሰው ብለው የሚያስቡ መሁራኖች . . . ብለው ጠቅሰውልኝ ስለነበር ከተባሉት ሰዎች ዋናውና አንደኛው ፕሮፌሰሩ ስለመሆናቸው አልተጠራጠርኩም::የአጥንታቸውን ክብደትና የደማቸውን ጥራት በአለባበስ እና በአነጋገራቸው ጭምር እየመዘኑ ለሌላው የሚያሳዩትል ፕሮፌሰር አስራት እንደ ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል በተፅኖ ለአደጉ ሰዎች ተስማሚ አልነበሩም:: እናም የኢንጂነሩ መልስ ትክል ስለነበር ወደሌላ ጥያቄ ገባሁ::

«መአህድን ወደ መኢአድ ለመለወጥ ሲነሱ የገጠምዎት ችግር አልነበረም::?»

«ይህ ትክክለኛ ጥያቄ ነው:: ድርጅቱን ለመቀየር ስንቀሳቀስስ በርካታ ችግሮች ከፊት ለፊቴ ተደቅነው ነበር:: ያም ሆኖ እንቅስቃሴዬን ከመጀመሬ በፊት ቀደም ሲል አስተካክዬ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ስለነበር ሳይጠላለፍና ሳይሰናከል ያለምንም ችግር ላልፈው ቻልሁ እንጅ የለውጡን ስራ ለመስራት ስነሳ አማክሪያቸው ከነበሩት አብዛኞቹ የአማራ ብሔር ተወለጆች የአምባገነንነት ስሜት የተጠናወታቸውና በአጠቃላይ አማራ አማራ የሚሸትቱ ነበሩ ለማለት እችላለሁ:: ስለሆነም መአህድን አታፈርስም በማለት ሊታገሉኝ ሞክረው ነበር::

እነኝህን ግለሰቦች ትናንትም አውቃቸው ስለነበር ትግላቸው አላስደነገጠኝም:: ለምን ብተለኝ ከስር መሰረት አመጣጣቸው ከላይ ልጠቅስልህ እንደሞከርኩት አማራ ብቻ ነው ሰው ብለው ከሚያስቡት ወገኖችነበሩ። ነገር ግን የመከላከል አቅሙ ያልነበራቸው ናቸው:: ስለሆነም የነበራቸው ምርጫ ሁለት ሆነ:: አንድ ከኛ ጋር ተስማምተው መቀጠል ካልሆነ ደግሞ ለቅቀው መውጣት:: ስለሆነም ያልፈለጉት ተገልለዋል:: እኛን የተከተሉና እኛም የመረጥናቸውከኛጋርቀጥለዋል::መውጣት ለመረጡትም በመውጣታቸው አልተከፋንም::አማራነቱን የወደደ አማራነቱን ይዞ ወጣ::ኢትዮጵያዊነቱን የወደደ ደግሞ ከእኛ ጋር ተስማምቶ ለመስራት ቀረ::»

«ይቅርታ ያድርጉልኝና ኢንጂነር አማራ ነኝ ያለው ሁሉ ኢትዩጵያዊነቱን ክዷል ማለት ነው::? »

«እንደሱ ማለቴ አይደለም:: እኔ እያልኩ ያለሁት ከምንም በላይ አማራነቱን የሚያስቀድሙ ሰዎች ስለነበሩ እነዚህ ደግሞ ዲሞክራሲን ለማምጣት አይችሉም እና ይወገዱ ነው:: ዲሞክራሲ የሚመሰረተው ቅድሚያ በማንኛውም ሰው አመለካከት ውስጥ የእኩልነት ስሜት ሲኖር ብቻ ነው::»

((መአህድየተመሰረተዉየአማራውን የበላይነት ለማረጋገጥ ሳይሆን አማራውን ከሚደርስበትና እየደረሰበት ከነበረው ጥቃት ለመከላከል ነበር:: አሁን ግን አማራውን ሆን ተብሎ ተከራካሪና አስታዋሽ እንዳይኖረው ለማድረግ ድርጅቱን አፍርሰው መጠላያ አሳጡት:: እኛም የመከላከሉ አቅም ስላልነበረን ትተን ወጣን የሚሉ አሉ:: እርሶስ ይህንን ምን ይላሉ::?»



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

«ይሄ በፍፁም ተቀባይነት የሌለው የነሱ ብቻ አሳብ ነው:: ለምን ብትለኝ አማራው መአህድ በመፍረሱ ለጥቃት አልተጋለጠም:: አማራውን የጥቃት ሰለባ አድርጎት የነበረው እራሱ መአህድ ነበር:: መኢአድ ከተመሰረተ በኋላ ግን የአማራው ጥቃት ሙሉ በሙሉ ቆሟል ለማለት እችላለሁ:: ይህ ደግሞ ሁላችንም ያየነው ሀቅ ስለነበር መካድ አይቻልም:: »

«የለውጡ ሂደት እንዴት በአጭር ግዜ ሊሳካላችሁ ቻለ?::»

«ድርጅቱን ለመለወጥ በቅድሚያ የተንቀሳቀስነው በገበሬው ውስጥ ነበር:: ከላይ እንደገለጽኩልህ አካሄዳችን ጥንቃቄን የተከተለ ነበር:: በጎንደር ፣ በወሎ ፣ በጎጃምና በሌሎችም የአማራው ክልሎች እኔ እራሴ በገበሬው ቤት ውስጥ እያደርሁ መአህድ ወደ ህብረብሔር መለወጥ እንዳለበት አሳምኜ ነበር:: ከዚህ በኋላ የቀረው የከተማው ነዋሪ በተለይም ደግሞ የአዲስ አበባ ህዝብ ነው:: በየክልል ከተማው የነበሩትን አመራሮች በግል ጠርቼ አሳምኛቸው ስለነበር አዲስ አበባዎቹ ደገፉም ነቀፉም ፋይዳ አልነበራቸውም::»

«ሶስቱን የአማራ ክልሎች ማለትም ጎጃም፣ ጎንደር እና ወሎን ሲጠቅሱልኝ የሰሜን ሸዋን አልፈውታል። በዚያ የነበረውን ገበሬ አላማከራችሁም ነበር? ከሆነስ ለምን::? »

«ሰሜን ሸዋ ላይ ብዙ ትኩረት ባለመስጠታችን ለጊዜው አልፈነው ነበር::»

«ለምን ትኩረት አልሰጣችሁም? እንደሚባለው ከሆነ ለመአህድ መመስረትም ሆነ ከመስራቶቹ ዘጠና በመቶ የነበሩት የዚሁ ክልል ተወላጆች መሆናቸው ነበር:: አሁንም መአህድ በመፍፈሱ ያኮረፉት እና እንደ ቂም በቀል የወሰዱት የዚሁ ክልል ተወላጆች መሆናቸው ይነገራል:: ማማከሩን የነፈጋችኋቸው አይቀበሉንም ከሚል ስጋት ነበር::?»



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

«እሱም ያስኬዳል:: ቀድም ሲል እንደነገርኩህ አብዛኞቹ የዛ ክልል ተወላጆች የአስተሳሰብ ችግር የተጠናወታቸው ስለነበሩና የገበሬው አሰፋፈርም ለአዲስ አበባ ቅርብ ስለሆነ ለውጡን በምስጢር ለመያዝ ሲባል ሸዋን ለጊዜው ማለፉ አስፈላጊ ነበር::»

«የሶስቱን ጠቅላይ ግዛት ህዝቦች አሳምነው ከተመለሱ በኋላ ምን ምን እርምጃዎችን ወሰዱ?»

«አዲስ አበባ እንደተመለስሁ በሶስቱ ጠቅላይ ግዛቶች የነበሩትንአላፊዎች ስብሰባ ጠርቼ በቀጥታ የድርጅቱን ለውጥ እንደምናካሂድ ነገርኳቸው:: »

«ይህንን እርምጃ ብዙ ሰዎች እንድመፈንቃለ ፓርቲ አድርገው ወስደውለታል::እርስዎ ለዚህ ምመልስ ይሰጡኛል:?» ኢንጂነሩ ከትከት ብለው ከሳቁ በኋላ » ድርጅቱን አሳደግሁ እንጂ አልፈነቀልኩም:: መጀመርያውንም ከውጭ ከመምጣቴ በፊት መአህድን እንድመራላቸው ለመረጡኝ ሰዎች እንደምለውጠው ነግሬያቸው ተማምነንበት ነው በአላፊነት ለመምራት ወደ አገር ቤት የተመለስኩት::»

«እርስዎን ወደ ድርጅቱ ያመጡዎት ሰዎችየድርጅቱን መለወጥ ወይንም መፍርስ የማይቀበሉ ቢሆኑ ኖሮ አገር ቤት አይመለሱም ነበር ማለት ነው::?

«ይመስኛል:: ለምን ብትለኝ መጀመሪያውኑም ቢሆን መአህድን ለቅቄ የወጣሁበት ዋናው ምክንያት ፓርቲውን በመዋቅሩ ደረጃ ስለማልደግፈው ነበር » አሉኝ ኢንጂነሩ::

ይህ ብቻ አይደለም በወቅቱ ለኢንጂነሩ አቅርቤላቸው የነበረ ቃለ መጠይቅ:: ለሁለት ቀን ያህል አድርጌላቸው የነበረ ቃመጠይቅ እራሱን የቻለ አንድ ትልቅ ጥራዝ መፅሐፍ ስለሆነ እሱ ጊዜውን ጠብቆ ይወጣል:: እነዚህን እንደማጣቀሻ የወሰድኳቸው ከፕሮፌሰሩ ጋር ስለነበራቸው አለመግባባትና መአህድንም በቂም በቀል አፈረሱት ስለመባሉ አንባቢ የራሱን ግምት እንዲሰጥበት ይጠቅማል ብዬ ነው::



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

# ምዕራፍ ሦስት

## የደርግ ውድቀት መዘዝ

ከሚካኤል በለጠ በሚቀጥለው ቀጠሯችን ስንገናኝ ሙሉ ደስተኛ ሆኖነበር የጠበቀኝ:: ራስ ሆቴል ጎራ ብለን ሻይ ቡና ካልን በኋላባለፈውጀምሮልኝስለነበረውታሪክካቆመበትእንስቶእንዲህበማለ ይተርክልኝጀመር::መነሻችን የመአህድ መወለድና የፖለቲካ ዓላማው አይደለም:: ሁላችንም ብንሆን የራሳችን የሆነ መሠረትና ጅማሮ ነበረን:: የኔና የእኔ መሰል ጓደኞቼ የትግል አነሳስ በፍፁም ከመአህድ ጋር የተገናኘ አልነበረም:: መሰረቱ እንደዚህ ነው:: የደርግ መንግስት የጦር መኮንኖች ተጠራርገን ጦላይ ለተሃድሶ ከገባን በኋላ ተሸናፊ በመሆን እንገታችንን ደፍተን የአሸናፊን ጀግንነት እያወደስን መጪውን የመከራ ግዞት በራሳችን ፊርማ ላለመቀበል መመካከር የጀመርነው በዚያ በጭንቅ ሰዓት ነበር::

ከደርግ ውድቀት በኋላ የደረሰብንን የውርደት ካባ አውልቀን ለመጣል የተለምነው የራሳችን የትግል መስመር ነው ወደመጨረሻ ከመአህድ ጋር በእትብት ያቆራኘን:: ያ በወቅቱ በአፍሪካ ምድር ተወዳዳሪ አይገኝለትም እየተባለ ይነገርለት የነበረው ግዙፍ ሰራዊት በሚያስገርም እና በሚያሳዝን ሁኔታ በአንድ ጊዜ አደኢያሪክ ግንብ ከተናደ በኋላ ብዙ ሺዎች የምንቆጠር የጦር መኮንኖች በጦላይ የወታደራዊ ማሰልጠኛ ማዕከል ተሃድሶ ተብሎ ከታጎርን በኋላ ለስድስት ወራት በእስር እንድንቆይ ተደርጎ ነበር:: በዚህ እስር ቤት ደግሞ አካላዊ ብቻ ሳይሆን ስነ ልቦናዊ እና ሞራላዊ ድርጊቶች ይካሄዱ ነበር::

ይህንን የሞራል ውድቀት ለመመለስ ሲባል አንድ ሃይል መፍጠር የግድ ሆነ:: ስለሆነም በቅድሚያ የፖለቲካ ትምህርት እንደአዲስ ሀ ሁ ብለን መቁጠር ነበረብን::በሌላ በኩል ደግሞ በመጪው ዘመን ምን እንደምንመስል በህብረተሰብ ውስጥ ያለንን ቦታና ከምንም በላይ ህዝብ ከኛ ምን ይጠበቃል የሚሉትን



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ነጥቦች እንስተን እራሳችንን የምናይበት ጊዜ የገጠመን በዚህ ወቅት ነበር:: ምክንያቱም እንዚህን ነገሮች ለመነጋገርም ሆነ አንድ ግንባር ለመፍጠር የመገናኘት እድል ፈጥሮልን ነበርና ነው::

ለዚህ ተግባር ሁሉም ሰው ከዚህ የተሻለ የመሰባሰብ ዕድል ስለማይገጥመው አጋጣሚውን ለመጠቀምና የራሳችንን መበት ለማስከበርም ሆነ በኛ ሽንፈት ምክንያት በሀገራችን ላይ የደረሰውን ውርደት ለማደስ ከዚህ የተሻለ የመሰባሰብ እድ አልነበረንም:: በሌላ በኩልም በህዝብ ላይ ለሚደርስ በደል ከኛ ምን ይጠበቃ እኛስ ከዚህ ምን መማር አለብን በሀገሪቱ አሁን በፍጥነት የሚንቀሳቀስ ሀይል ለመፍጠር ከኛ የተሻለ ኃይል ከየት ሊመጣ ነው? በነዚህ እና በሌሎችም ነጥቦች ላይ በስፋት ከተመካከርን በኋላ በአንድ ነገር ተስማማን ሁላችንም የሰለጠንን ወታደሮች ነን:: ሀገርን ከመከፋፈል ለመዳን ደግሞ በቂ ሃይል አለን ብለን የወሰድነው እኛንና እራሳችንን ብቻ ነበር::

በጉዳዩ ብዙ ከተወያየን በኋላ ለተግባር ተስማማን:: ይህ አማራጭ ደግሞ ለእኛ ሁለት ወሳኝ ነጥብ የነበረው ሲሆን አንደኛ ው የደርግ ሰራዊት ወንጀል እንደሰራ ተደርጎ እስከዓለም ዳርቻ የጎደፈ ስማችንን ለማደስ ሁለተኛውና ወሳኙ ነጥብ ደግሞ ከተሃድሶ ከ ወጣን በኋላ ሊደርስብን የሚችለውን የተናጠል ጥቃት በአንድነት ለመቋቋም የቅድሚያ ዝግጅት ለማድረግ ነበር:: ተበታትነን የትም እየወደቅን የአውሬ እራት ከምንሆን እራሳችንን እየተከላከልን ታሪክ ሰርተን ማለፍ የሚል እቅድ ነበር:: እድል ገጥሞን አቅማችን መጠናከር ከቻለም ኢህአዲግን በመጣል አገሪቱን ከመከፋፈል ማዳን አለብን በሚለው ሃሳብ ሙሉ በሙሉ ተስማማን :: እነዚህን በመሳሰሉት ወሳኝና አንኳር የሆኑ ነጥቦች ላይ ለመወያየት ውስጥ ውስጡን የተጀመረው እንቅስቃሴ በሁላችንም በኩል ተቀባይነት ያገኘ ቢሆንም ብዙ ስጋቶች ነበሩበት:: እንደሰጋነዉም በመካከላችን አስጊ የነበሩ ሁኔታዎች መፈጠራቸው አልቀረም:: የተለያዩ ጥቅሞችን ልናገኝ እችላለን ብለው ያሰቡ ወገኖች ከኛው መሃል አፈንግጠው በመውጣታቸው ብዙም ሳንራመድ መፍረክረክ ተጀመረና አንዳንድ ምስጢሮች አፈትልከው ብቅ ማለት ጀመሩ::ከዚያ በኋላ አንዱ አንዱን



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ባለማመን እርስ በርስ መጠራጠር ተጀመረ:: በጠላይ የጦር ማሰልጠኛ ካምፕ ውስጥ ሆነን መወያየት ስንጀመር የገጠመን የመጀመሪያው ፈተና ይህንን የመሰለ ሲሆን አሳዛኝ ገጠመኞችን ነበር:: ምክንያቱም ሁላችንም በጦር ወንጀለኝነት ተፈረጅን ከዓለም ጫፍ እስከ ዓለም ዳረቻ በጥላቻ እንድንታደን አዋጅ የተነገረልን መሆናችንን እያወቀንና እየተረዳን ራሳችንን መሰለል መጀመራችን አሳዛኝ ብቻ ሳይሆን አሳፋሪም ነበር ለማለት እችላለሁ::

በዚህ ሁኔታ የሚፈለግ ወንጀለኛ የመንግስት ተለጣፊ በመሆን የመታነቂያ ገመዱን እየሸረበ እራሱን ይሰልላል ተብሎ ቢነገር የሚታመን አልነበረም:: የተፈራው አልቀረም የሆነው ሁሉ ሆነ:: ከትንሽ ጊዜ በኋላ ካድሬዎች በነጠላ እየከፋፈሉ « እገሌ ይህን ተናግሯል:: አንተም በጉዳዩ እጅህ እንዳለህበት ነግሮናል:: የምታምን ከሆነ ከሚደርስብህ ስቃይ ነፃ ሰው ነህ:: እውነቱን የማትናገርና የምትክድ ከሆነ ግን ከፍተኛ ስቃይ ይደርስብሃል » በማለት በጥያቄ ያጣድፉን ጀመር:: ይጠይቁን የነበረው አንዳንዱ አውነትነት ስለነበረው ከራሳችን ውስጥ መረጃዎች እንደወጡ ተረድተን ነበር:: ውይይታችንን ለተወሰነ ጊዜ አቋርጠን ቆይተን ሁኔታዎች እየቀዘቀዙ ሲመጡ እንደገና ጀመርን:: ያም ሆኖ በድጋሚ በመካከላችን መከፋፈል በመፈጠሩ

የምንጠራጠራቸውን ሰዎች ሙሉ በሙሉ ለማግለል ወሰንን:: ውሳኔያችን የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ስለነበረው ከዚያ በኋላ ወሬው ስለቀዘቀዘ እንደልብ ስንወያይ ቆይተን የተሃድሶ ጊዜው አብቅቶ ወደየ ትውልድ ቀያችን መመለሻ ጊዜያችን ተቃረበ::

ልንገናኝ የምንችልበት አድራሻ መለዋወጥ እንዳለብን ብንረዳም ለጊዜው በቃል ከመነጋገር በስተቀር የተዘረጋ መስመር አልንበረንም:: በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳለን የተሃድሶ ግዜአችን አልቆ ከጠላይ ተሰናበትን:: በሰሜን ሸዋ አካባቢ የነበርነው ግን ሁላችንም ወደመጨረሻው ተገናኝተ ስለነበር ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ ውስጥ ውስጡን ስንላላከክ ቆይተን



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ህዳር 7 ቀን 1984 ዓ.ም በደብረብረሃን ከተማ ጠባሴ በሚባለው ቀበሌ 09 መንደር ውስጥ በአንድ የጦር መኮንን ሰው ቤት ተገናኝተን የመጀመሪያ ስብሰባችንን አደረግን:: በሁለተኛው ስብሰባችን ስንገናኝ ግን ከኛ ውጪ ከገበሬው የተሰባሰበ አርሶ አደሮችም አብረውን ተካፋይ ነበሩ:: በሶስተኛው ስብሰባችን ላይ ደግሞ ከገበሬዎቹ በተጨማሪ በመንግስት ሥራ ተቀጥረው ይሰሩ የነበሩና ከኢትዮጵያ ቆዳ ፋብሪካ እና መሰል ድርጅቶች ከስራ የተባረሩ ሰዎችም ተቀላቅለውን ነበር::

በዚህ ሁኔታ በተደረገው የምስጢር ውይይት ላይ በስፍራው የተገኙት በሙሉ እቅዳችንን የተቀበሉት በልበ ሙሉነት እንደነበር አሁንም ላይ ሆኜ አስታውሰዋለሁ:: ከጠዋቱ አራት ሰዓት ላይ የተጀመረው ውይይት እስከ ምሽቱ ሁለት ሰዓት ቀጥሎ ከምሽቱ አምስት ሰአት አካባቢ ላይ በጣም በመዳከማችን መለያየት የግድ ሆነ:: በማግስቱ ብዙ ከተወያያንበት በኋላ ከስምምነት ላይ ደርሰን የቀረበው ሃሳብ በሙሉ ድጋፍ ፀድቆ ከቀኑ አስራ ሁለት አካባቢ ተለያየን::

በውይይታችን አንስተናቸው ከነበሩት አንኳር አንኳር ነጥቦች መካከል ገዥዎቹ በፈጠሩት ስህተት በራሱ በአማራው ልጆች መካከል ያለው መከፋፈል በሌሎቹ በኩል ደግሞ አማራው ብዙ ግፍ እንደሰራ ተቆጥሮ ነፍጠኛበሚል ቅፅል ስም እየተፈረጀ የጭቁኑ ህዝብ ጠላት ተደርጎ መወሰዱ ነበር:: በነዚህ ሁለት ምክንያቶች እንጥፍጣፊው ወደኛ ደርሶ እንደጀርመን ሂትለር የጦር መኮንኖች ማደኛ ወጥቶብን እንደነበር የቅርብ ግዚ ትዝታችን ነው:: በወቅቱ ሌሎችን ነገሮች ታግሰን ለመኖር ብንሞክርም እንኳን ለህይወታችን ዋስትና አልነበረንም:: ለደፈቱም ቢሆን ጥቃቱ የሚቆም ስላልመሰለን ቆርጠን ለመጋፈጥ የወሰነው ሁሉንም ነገር በዚህ መልኩ ከተመለከትን በኋላ ነበር::

ምንም እንኳን ሞት እንደአማራጭ ተደርጎ የሚወሰድ ባይሆንም እየገደሉ መሞትን እንደ አማራጭ ይዘን ነበር ወደትግሉ የገባነው:: በሁሉም በኩል የተወጠርን በመሆናችንና የቀጠሮ ጊዜ ስላልነበረን በእለቱ አንድ አስተባባሪ ኮሚቴ አቋቋምን



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

በሱ በኩል ሁላችንን ሊያገናኘን የሚችል የግንኙነት መረባችንን በሀገር አቀፍ ደረጃ ዘረጋን::

በስብሰባችን ላይ አብረውን የተገኙትና ትግሉን ለመቀላቀል የመጡት በሙሉ የፖለቲካውን አስተባባሪነት በመረከብ ወደ አዲስ አበባ በስውር ገብተው በማቴሪያልም ሆነ በኢኮኖሚ በኩል ሊያግዙን የሚችሉ የፖለተካ ድርጅቶችን እንደሚያፈላልጉ ቃል ገቡልን:: የተመረጡት ሰዎች ሊያግዘን የሚችል የፖለተካ ድርጅት ከማፈላለግ በተጨማሪ ከሌሎች ክልሎች ጋር የምንገናኝበትን መንገድ የሚፈጥር መስመር እንደሚዘረጉልን ከተነጋገርን በኋላ ወደ አዲስ አበባ እንዲሄዱ ቀን ተወሰነ::

እኔ የማውቀው የትግል አጀማመራችን አሁን በነገርኩህ መልኩ ሲሆን ከዚህ የተለየውንና ከመዐሕድ ቢሮ ጋር ያጣመረንን የግንኙነት መስመር ግን ይህ ነበር ብዬ ለመናገር አልችልም:: ለምን ብትለኝ በእለቱ ስብሰባችን ላይ ስለነበሩት ሰዎች ምንነት እና ማንነት የተረዳሁት እጅግ ዘግይቼ ስለነበር ነው::

ምንም እንኳን አላፊነት ቢኖረኝም ብዙ የማላውቃቸውና መጨረሻ የተረዳኋቸው ነገሮች ነበሩ:: በሌላ በኩል ግን ትግላችንን ለመጀመር ማንም ሰው በአጋጣሚ በእጁ የገባውን መሳሪያ ይዞ መንቀሳቀስ እንደሚኖርበትና በቀጣይነት ለሚያደርገው ትግልም ከተግባር ጋር መንቀሳቀስ እንደሚገባው እንዲያውቅ ተደርጓል።

ትጥቅን በተመለከተም በየወረዳው የሚገኙ የመሳሪያ ግምጃ ቤት መጋዘኖች ጥናት ተደርጎባቸው መሳሪያ ያለባቸው መጋዘኖች ተሰብረው አባሎቻችን ትጥቅ እንዲያገኙ ለማድረግ የምንችልበት ስልት ቀየስን:: አሳቡ ሙሉ በሙሉ በመፅደቁም የጦር መሳሪያ የሚገኝባቸው ወረዳዎች ይጠኑ ጀመር:: እቅዱን እንድናቀርብ የስራ ድርሻ የተሰጠን ሻለቃ መስፍን ታደሰ ሻምበል ደጀኔ ዝቄና እኔም እራሴ ነበርሁ:: መሳሪያ ይገኝባቸዋል ወደተባሉበት ወረዳዎች በሲቪል መልክ ለጥናት መንቀሳቀስ ስለነበረብን ስራችንን ሙሉ በሙሉ ጀመርን፡ ከእኛም



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

በተጨማሪ ከየወረዳው የመጡ መኮንንች የስራ ድርሻ ተሰጥቷቸው ስለነበር እነሱም በኀላፊነት እያስተባበሩ በቀጣይነት የሚንቀሳቀስስ ኮሚቴ ከታች ወደ ላይ እንዲዋቀርና ጠቅላላ ድርጅታዊ መዋቅር እንዲዘጋጅ ተደረገ። መዋቅራችን ከተዘረጋ በኋላ የመጀመሪያው ዙር ወታደራዊ ሀይል ወደሰሜን ሸዋ ቆላማ አካባቢዎች እንዲንቀሳቀስ እና ቦታ እንዲይዝ ተወሰነ።

ከዚያ በመቀጠል ለሁለተኛ ዙር የተደራጀው ሃይል ደግሞ ሞፈር ውሃና መርሃቢቴን ይዞ እስከ ይፋት ቆላ የአፈርና የአማራ ክልልን እንዲያገኝ ሆኖ መስመሩን በማስፋት ወደ ወሎ ግዛት ከተገናኘ በኋላ በሁለት ተከፍሎ እንዲንቀሳቀስ ሲደረግ ይህ ወታደራዊ ሃይል መነሻና መድረሻው ተወስኖ ሁለቱም ሃይል የተመረጠለትን ቦታዎች እንዲይዝ የመጨሻው ውሳኔ ተሰጠው።

የተመረጡት ቦታዎች ከተያዙ በኋላ ወደመሃል ኢትዮጵያ የተላከው አጥኚ ሃይል የተለያዩ መረጃዎችን ለሚመለከተው ክፍል የማቅረብ ስራውን በጥቂት ግዜ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ማቅረብ ጀመረ በይፋት፣በምንጃር፣በሸንከኮራ፣በቡልጋ፣በመንዝና ግሼ እንዲሁም በመርሃቤቴ ላሉት ቆላማ የወታደራዊ ቦታዎች በሙሉ እንደ እዝ መምሪያ ሆኖ የሚያገለግለው ጣቢያ ደብረብርሃን እንዲሆን ተወሰነ።

በስብሰባችን ላይ ከነበሩት ሰዎች መካከል አሁን የማስታውሳቸው ከተማ ደስታ የተባለ ሰው ሁለት መሳሪያዎችን ለመስጠት ቃል ገብተውልን ነበር። ያም ሆኖ ግን መሳሪያውን አምጥተው ያስረከቡ አያስረክቡ ያየሁት ወይንም የማውቀው ነገር አልነበረም።

በሌላ በኩል ግን ገና ስንጀምረው በቃለ መሃላ የተጀመረው የትግል ጉዞአችን ረጅምና ውስብስብ ነበር። በዚህ መልኩ የተጀመረውን ጥልፍልፍ መንገድ ሁላችንም የቃሉ ክበደት እና የትግሉ ቁርጠንነት ከምንም በላይ ደግሞ የፈተናው ብዛት የፈጠረብንን ስሜትና ጫና ተከትለን የሺህ ኪ/ሜትሩን ጉዞ በአንድ እርምጃ ሀ ብለን ለመጀመር የካቲት 5 ቀን 1984ዓ.ም



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

የከተማ ስንበት የምናደርግበት የመጨረሻው እለት ሆነ:: እቅም የፈቀደውን ዝግጅት አድርገን የስራና የሃላፊነት ድርሻችንን ከተረከብን በኋላ ደብረብርሃንን ለቅቀን ወጣን:: የትግል ጉዞአችንን ገና ከመነሻው ፈተና ገጠመውና መ/አ ዘውዱ የሚባል ሰው እኛን ለመሰለል ከውስጣችን የገባ መሆኑ በውስጥ መረጃ ሰራተኞቻችን ተደረሰበት:: ግለሰቡ እንዴት እንደገባ ባናውቀውም ከየካቲት አምስት ቀን ስብሰባችን ላይ ጀምሮ አብሮን እንደነበር አውቃለሁ:: አመጣጡ በምንና በማን በኩል እንደነበር ግን እኔ ብቻ ሳልሆን የኔ አጋሮች በሙሉ ያልተረዱት እና እስከመጨረሻውም ያልተፈታ ምስጢር እንደሆነ ቆይቷል::

መቶ አለቃ ዘውዱ ትርፍራፊ ለማግኘት ብሎ በራሱ ይመጣ ወይም ደግሞ በመንግስት ተመልምሎ የተረጋገጠ መረጃ ማግኘት ባለመቻላችን የእርስ በርስ ጥርጥሬ ውስጣችን እንዲገባ መንገድ መፍጠሩ አልቀረም:: እንቅስቃሴያችን የፈጠነና ቅፅበታዊ ባይሆንና የነበረውን ሃይል ወደ ተመደበለት የውጊያ ወረዳ ባናሰማራ ኖሮ ከደብረብርሃን ከተማ ሳናወጣ በነበርንበት ተይዘን እንደነበር ከዛሬ ላይ ሆኜ አስታውሳለሁ::

ከጥቂት ቀናት በኋላ ጦራችን ሰፍሮበት የነበረውን ቦታ አደጋ ያስከትላል ተብሎ ስለተሰጋ በአፋጣኝ እንዲቀየር ተደረገ: ወታደረዊ ሃይላችን በዚህ ፈታኝ ሁኔታ ያለፈ ሲሆን በእኔ የሚመራው አንድ ኮሚቴ በከተማ ቀርቶ ከየትም አቅጣጫ የሚመጣውን መልዕክት እየተቀበለ የሰው ሃይል በማደራጀት ለማንኛውም እንቅስቃሴ የተሟላና ሰፋ ያለ የመረጃ ማሰባሰብ ስራ እዲሰራ አላፊነት ተሰጠው::

ይህንን በመሰለው ሃላፊነት አእምሮዬ ተወጥሮ በሌላ በኩል ደግሞ ለግዳጅ የተላከው ዘማች ቡድን እምን ደረጃና በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ ስንቅም ሆነ ትጥቅ ምን እንደሚያስፈልገው የመከታተል ሃላፊነቱ በኔ ላይ የተጣለ ነበር:: ይህንን ሁሉ አላፊነት በጫንቃዬ ተሸክሜ በደብረብርሃን ከተማ እየተዘዋወርሁ በዚያ ያለውን የመንግስት እንቅስቃሴ ከማጥናት በተጨማሪ ከአዲስ አበባ ከሚመጡና ከጎጃምና ፣ ከጎንደር



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ከሚንቀሳቀሱት ሃይሎች ጋር የሚደረገውን ግንኙነት ለማጠናከር ከፍተኛ የመረጃ ስራም እሰራ ነበር።በዚህ እንቅስቃሴ ላይ እንዳለሁ ነበር አንድ መልካም አጋጣሚ መፈጠሩን ተረዳሁት። ነገሩ እንዲህ ነበር። በኮሎኔል ዳንኤልና በኮሎኔል ታደሰ እንዲሁም በአቶ ከተማ ደስታ የሚመራ የበላይ አስተባባሪ ሃይል በአዲስ አበባ ተመስርቶ በአንድ የፖለቲካ ድርጅት ደጋፊነት እየተንቀሳቀሰ ነው የሚል መረጃ ከእጁ ላይ ገባ። ይህ ሃይል መደራጀቱን የሚገልፅ ማስረጃ የደረሰኝ ወደአሰዲስ አበባ በላክነው ቡድናችን በኩል ሲሆን የአሰላለፍ ስትራቴጂውም ወደ ጫካ ገብቶ ረጅም የትግል ጉዞ ከማድረግ እና ብዙ ዘመን የሚፈጅ የትግል ስልት ከመንደፍ በተሻለ በአስር ሺህ የሚቆጠሩ የደርግ መንግስት ኮማንዶዎችን አሰባስቦ አዲስ አበባ በመግባት በምድር ጦር ግምጃ ቤት ተከማችቶ ያለውን የጦር መሳሪያ መዝረፍና መታጠቅ።

በቀጣይም የሬድዮና የቴሌቪዥን ጣቢያውን ተቆጣጥሮ መፈንቅለ መንግስት ማካሄድ የሚል ዝርዝር የያዘ ነበር። ከዚህ ቡድን ጋር ለመገናኘት ጊዜ ባለመፍጀታችን አብረን እንድንሰራ ከስምምነት ላይ ደረስንና በአጭር ጊዜ በተደረገ የማሰባሰብና የማስተባበር ሥራ ዕቅዱን ወደውጤት ለመቀየር ተቻለ። ከዚህ በኋላ የሃይል አሰላለፋችንን አንድ አድርገን በማስተባበር የተጣመረ የመረጃ እንቅስቃሴ ተዘረጋ።በዚህ ቡድን ውስጥ ለኔ የተሰጠኝ የሥራ ድርሻ መረጃዎችን እያሰባሰቡ ለበላይ አስተባባሪዎች ማቅረብ ሲሆን የመጀመሪያውን ሪፖርት አቅርቤ በወቅቱ የተሰጠኝ መልስ ያለው ሁኔታ ብዙ አስቸጋሪ እደማይሆንና ከሌላው የትግል ስልት የተሻለና የቀለለ መንገድ ይመስላል የሚል ነበር።

በዚህ ሁኔታ ሰፋ ያለ ውይይት ከአደረግን በኋላ ጦሩን በተመለከተ በሁለቱ ኮሎኔሎች በኩል ያለው እስከ 10 ሺህ የሚደርስ ልዩ ኮማንዶ ሃይ ል በቂ እንደሚሆንም ታመነበት።እንቅስቃሴ ስንጀምር አንዳንድ ያስደነቀኝ ነገር የገጠመኝ ሲሆን የኮሎኔል ዳንኤል ጉዳይ ነበር። እኝህ ሰው የመፈንቅለ መንግስት ሱስ አለባቸው እየተባለ ቅፅል ስም የተሰጣቸው መሆኑን አውቅ ስለነበር አሁን ደግሞ ለምን



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

በመፈንቅለ መንግስት ውጊያው እንዲጀመር ፈለጉ የሚለው ጥያቄ ውስጤን እየሰረሰረኝ የቅድመ መረጃ ማሰባሰቤን በስፋት ቀጠልሁ:: በሰሜን ሸዋ የተጀመረው እንቅስቃሴ በተመለከተ ማንኛውንም የደህንነት ማስጠበቅ ስራው ሙሉ በሙሉ በኔ ላይ የወደቀ በመሆኑ የነበረብኝ የስራ መጨናነቅ ከጊዜ ወደጊዜ እረፍት የነሳኝ ከመሆኑ በቀር ሁሉም ነገር በጥሩ ሁኔታ እየተጓዘ ነበር::

በሰሜን ሸዋ ቆላማ ቦታዎች የተንቀሳቀሰው ተዋጊ ሃይል ወደ አዲስ አበባ በአስቸኳይ እዲመጣ በመወሰኑ ለሻለቃ መስፍን ታደሰ በጥቂት ቀናት ውስጥ መድረስ እንዳለበት የሚገልፅ መልእክት ላኩበት: መልእክቱ እንደደረሰው ያለውን ሀይል ይዞ አዲስ አበባ የገባው በተፋጠነ ሁኔታ ነበርአዲስ አበባ እንደገባ ፈረንሳይ ለጋሲዮን አካባቢ በሚገኘው ጫካ ውስጥ በመስፈር ወታደራዊ ጥናት እያደረገ እንዲጠባበቅ ትዕዛዝ ተሰጠው:: ከዚህ በኋላ ነበር ለዘመቻው ድርጅት /ሌጅስቲክ / ድጋፍ አንድ ጠንካራ የሆነ የፖለቲካ ድረጅት መኖሩን የሰማሁት:: ብዙም ሳይቆይ ሚስጢሩ ወደውጭ እየወጣ መጣና የኋላ ድጋፍ የሆነው የፖለቲካ ድርጅት የመለው አማራ ህዝብ ድርጅት እንደሆነ የአመራሩ ቁልፍ ሰዎች ለመረዳት ቻልን:: እለ የተባለው የሠለጠነ አስር ሺህ ጦርም በአዲሰ አበባ ከተማ ዙርያ በእሉት ጫካዎች እንዲቆይ የተደረገ ሲሆን የአስፋፈሩን ሁኔታ በተመለከተም የአዲስ አበባ ከተማን በስተሰሜን ምእራብ የእንጦጦ ተራሮችን ግማሽ ጨረቃ ሰርቶ ነበር::

በአጋጣሚ ይሁን ወይም ደግሞ ታስቦበት ግንቦት ወር በኢትዮጵያ መንግስት ላይ የመፈንቀለ መንግስት ሙከራና ለውጥ ከአፄው መንግስት ጀምሮ ተካሂዶበታል:: አሁንም ደግሞ መፈንቅለ መንግስቱ የተወሰነው ግንቦት ወር ነው:: የመፈንቅለ መንግስቱ እንቅስቃሴ በሚያስገርም ሁኔታ የተፋጠነ ሲሆን የእቅዱን ዘጠና ዘጠኝ በመቶ ለማጠናቀቅ ከመቻላችንበተጨማሪ ትዝ ከሚለኝ ትውስታዬ መካከል በቤተመንግስቱ ላይ የሚካሄደው የዉጊያ ፕላን



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ዝርዝር ጥናትና የእቅዱ እስትራቴጂ ነበር:: ወደ ቤተ መንግስቱ ዘልቆ ለሚገባው አምስት መቶ ልዩ ኮማንዶ ሃይል የተመረጠለት የመግቢያ በር ለውሃ መውረጃ የተዘጋጀው የመሬት ውስጥ ለውስጥ ቱቦ ነበር:: እነዚህ በቆሻሻ ውሃ መውረጃው ቱቦ ውስጥ በልባቸው እየተሳቡ ረጅም ጉዞ ከአደረጉ በኋላ ቤተ መንግስቱ ውስጥ የሚገቡት አምስት መቶ ኮማንዶዎች ቤተ መንግስቱ ውስት ሲደርሱ የተሰጣቸው ግዳጅ በሣንጃና እጅ በእጅ ውጊያ ብቻ እዲጠቀሙ በእጃቸወ ላይ የያዙት መሳሪያ ገመድና ሳንጃ ብቻ ነበር:: ይህ ሃይል እምነት የተጣለበት በሱ ላይ ስለነበር የተከፈለው መስዋት ተከፍሎ በቀላሉ ቤተመንግስቱን መቆጣጠር እንዲችል ጥብቅ ትዛዝ ተቀብሏል::

በሌላ በኩል ግን እሱን ሊያግዝ የሚችል ቁጥሩ እስከ ሁለት ሺህ የሚደርስ ተጨማሪ ኮማንዶ የቤተ መንግስቱን ዙሪያ አጥር ተከትሎ ከውጭ ወደ ውስጥ ሊከላከል በሚያስችል መልኩ የተዘጋጀ ሲሆን ከከባድ እስከ ቀላል መሳሪያ የታጠቀ ድጋፍ ሰጪ ነበረው::የዚህ አይነት አላፊነት የተሰጠው አምስት መቶ ልዩ ኮማንዶ ኃይል በደርግ አስመራ ላይ መፈንቅለ መንግስቱን ከአከሸፋት ኮማንዶዎች የተውጣጣ ስለነበር መፈንቅለ መንግስቱንም እንደሚያሳካ ሙሉ በሙሉ እምነት የተጣለበት ነበር:: በወቅቱ እናስበው እንደነበር የኢህአድግ ሃይል በብቃት ደረጃ ሲታይ ከመሳሪያ ተኩስ ውጭ በኮማንዶ በኩል አስተማማኝ እንዳልነበር ነው::

ስለሆነም ከቤተ መንግስቱ ቀጥሎም ሬድዮና ቴሌቪዝን ጣቢያውን እንዲሁም ቴሌኮሚኒኬሽን ላይ ፈጣን ጥቃት ተሠንዝሮ የመገናኛ ተቋሞችን በአጭር ጊዜ ውስጥ በቁጥጥር ስር ለማዋል የነበረን ሃይል ከበቂ በላይ ነው የሚል ግምት ነበረን:: በሁሉም በኩል የተሰለፈውሃይል የመጨረሻውን ትእዛዝ እየተጠባበቀ ሲሆን በአስማረ ዳኜ የሚመራ ብዙም ወታደራዊ ትምህርት ያልተሰጠው አምስት መቶ የታጠቀ ሃይል በተጠባባቂነት የተመደበ ነበር:: የዚህ ሃይል አሰላለፍ በራሱ በአስማረ የሚታዘዝ ሲሆን የቦታ አሰላለፍን በተመለከተ የሰሜን



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

መውጫና መግቢያ የአዲስ አበባ አስመራ በር ተብሎ የሚጠራውን መንገድ እንዲዘጋ የተመደበ ነበር:: በአምስት ምድብ የተከፈለው የከተማ ውስጥ ተዋጊ ሃይል ወደ ተሰጠው የግዳጅ ቦታ ሲንቀሳቀስ በአምስቱ የመግቢያ በሮች የተመደበው ዘጊ ሃይል ደግሞ በየበሮቹ ላይ ሆኖ ማንኛውንም እንቅስቃሴ ያግዳል::

በዚህ ሁኔታ ሁሉ ነገር ከተጠናቀቀ በኋላ የማይቀረውና ፈታኙ ሁኔታ ለመጨረሻ ፍልሚያ ግንቦት 7 ቀን 1984 ዓ.ም ለመፈንቅለ መንግስቱ ስራ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ተጀመረ:: ግንቦት 6 ለ 7 አጥቢያ የድርጊቱ አቀነባባሪና የበላይ መሪ የነበሩት ኮሎኔል ዳንኤል በገፃቸው ላይ ያልተራጋጋ ስሜት ይታይባቸው ጀመር:: ኮሎኔሉ ከዚያን ቀን በፊት የነበራቸው ልበሙሉነትና የተረጋጋው መንፈሳቸው እንደማለዳ ጤዛ እየተነነ የጠፋ ይመስል ፊታቸው ገርጥቶ በመመልከቴ በልቤ ውስጥ የተሰያዩ ጥርጣሬዎች ተሰንቅረው ምክንያቱን በዉል ሳላውቅ ግንቦት 6 ቀን አለፈና በማግስቱ ግብቦት 7 ተተካ::

እስከ ቀኑ 12 ሰዓት ድረስ በኮሎኔሉ በኩል የተለየ ለውጥ ሳላይ ቆይቼ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ተኩል ሲሆን የበለጠ ወደአራስ ነብርነት ተቀይረው በውጊያ አፈፃፀም ውስጥ ከፍተኛ ሀይልና ድረሻ ነበራቸው ከኮሎኔል ታደሰና ከሌሎቹም አመራሮች ጋር ድንበር የዘለለ ንትርክ ውስጥ ገቡ::እንዲህ አይነት ሁኔታ በስራቸው ለነበርነው አመራሮች ግራ አጋቢ ብቻ ሳይሆን አስደንጋጭም ነበር ለማለት እችላለሁ:: እርግጥ ስለቀደመ ባህሪያቸው ሲነገር እንደምሰማው ከሆነ ኮሎኔል ዳንኤል የኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማሪም ዓይነት ቁጡና ቅብጥብጥ ባህሪ የነበራቸው እንደሆኑ ነበር:: በዚያን እለት የነበረው የኮሎኔሉ በድንገት የመቀያየር ሁኔታ ከመሰረታዊ ባህሪ የመነጨ ስላልነበር ከሰአት ወደ ሰአት እየተለዋወጠ ሄደው ወደ እውሬነት የተለወጠ ስለመሰለኝ የእቅዱ መበላሸት ታየኝና ክፉኛ ተረበሸኩ::ኮሎኔሉ የተፈጠረው አሳዛኝ ሁኔታ አስከራቸውና ይበልጥ አራስ ነብር



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ሲያደርጋቸው ስመለከት ሰማይ የተደፋብኝ ያህል እስከ ሚሰማኝ ድረስ መጭው ሁኔታ ከብረት አሎሎ ከብዶኝ አጠገቤ ከነበሩት ድንጋዬች በአንደኛው ላይ አረፍ ለማለት ተገደድሁ። ነገሩ እንዲህ ነበር። በውጊያው ላይ ይገባልናል ተብሎ የተጠበቀው አስር ሺህ ሠራዊት በተያዘለት ሰዓትና ቁጥር የተሟላ አልነበረም። በሌላ በኩልም በውሃ መውረጃ ቱቦ ውስጥ ሠርጎ ወደ ቤተመንግስቱ እንዲንቀሳቀስ የታዘዘው የኮማንዶ ኃይል ቁጥር የተጠቀሰውን ያህል ካለመሆኑ በተጨማሪ እርስ በርስ ሊያገናኝ የሚችል የሬድዮ መገናኛ አልነበረመውም።ሁሉም ነገር አይብ ላይ የተደፋ ቆሎ ሆነና የውጊያ ዕቅዱን ለማስቀረትም ሆነ ለማስቀጠል የማያስችል አስቸጋሪ ሁኔታ ተፈጠረ።

ወደቤተ መንግስቱ እንዲገባ የታዘዘው ሃይል የግንኘ ነት መሣሪያ አልተሰጠውም። የግንኙነት መሳሪያ ሳይኖረው ከቆሻሻ ቱቦ ውስጥ የገባው ልዩ ሃይል የመቀጠያም ሆነ የመመለሻ መስምሩ የተዘጋና የተቋረጠ መሆኑን ስሰማ ስሜቴ በአየር እንደተሞላ ስልቻ እየሟሸሸ ሲመጣ ታወቀኝ። በዚህ ሁኔታ ሁሉም ነገር እየጠበበ መጣና ለማስገባትም ሆነ መልሶ ለማውጣት በማይቻል መልኩየእቅዳችንን ተግባር አንቆ በመያዝ እራሱን በራሱ ጠልፎ የሚጥል ለማስገባትም ሆነ ለማስወጣት የማይችል አስቸጋሪ ቅርቃር ሆኖ ቀረ። እነዚህን ሁኔታዎች መልሶ ለማስተካከል አይደለም እንዴት ተፈጠሩ ብሎ ለመጠየቅም እንኳን ጊዜው የመሸ ነበር።

ኮሎኔል ዳንኤል በራስ የመተማመን ብቃታቸው እንደጉም እየተነነ ከፊታቸው ሲጠፋ ስመለከት ነበር ሁሉም ነገር እንዳከተመለት የተረዳሁት። በወቅቱ እንደተመለከትኳቸው ከገጻቸዉ የተገነዘብኩት ዘዴ አልባ ሆነው በአሉበት ቦታ ያለምንም መንቀሳቀስ ተገትረው መቅረታቸውን ነበር። ወደ ቤተመግስት የሄደው ሃይል በተመለከተ እንዴት ይመለስ ምንስ እያደረገ ይሆን እነኚህ ሁሉ ጥያቆዎች መልስ የሌላቸው ነበሩ። ቀጥልም አትቀጥልም ለማለት የመገናኛ መስመሩ ተቆርጧል ። ሁሉም ነገር በቀላሉ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

የማይወለድ በእግሩ በኩል ዞሮ የመጣ የበካር ሴት ምጥ ነበር የሆነው::ከዚህ በኋላ የመጨረሻ አማራጭ ተደረጎ የተወሰደው ሰዎችንእየላኩ በቃል መንገር ነበር:: በዚህ ሁኔታ ጥረት ከአደረግን በኋላ ለግዳጅ በተጠንቀቅ ይጠባበቅ የነበረው ልዩ ሃይል እንዲያፈገፍግና ወደ ዳር እንዲመለስ አደረግን:: ከለሊቱ ስድስት ሰዓት ሲሆን ከኮሎኔል ዳንኤል ጋር ሌሎች ሁለት ኮሎኔሎችን ጨምሮ እነ አቶ ከተማ ደስታ እና በርካታ ሻለቆችም በአንድ ህንፃ ውስጥ እንዳሉ በኢህአዲግ የፀጥታ ሃይሎች ተያዙ:: ከዚያ በኋላ ትዝ የሚለኝ ነገር ቢኖር አውራው እነደሞተበት ንብ እየተበታተነ በፈለጉበት አቅጣጫ እየሸሸ ያለውን ተዋጊ ሃይል መመልከቴን ብቻ ነበር::

እኔ እና ሻለቃመስፍን የራሳችንን ጦር ይዘን አዲስ አበባን ለቅቀን ስንወጣ አስማረ ዳኜም የራሱን አምስት መቶ ጦር ይዞ ወደመጣበት የተመለሰ ሲሆን እቅዱን ያበላሹትና ያን ሁሉ ችግር የፈጠሩት እነ ሻለቃ ዘርአይ እና ከሱ ጋር የነበሩ የኤርትራ ተወላጅ የነበሩ የጦር መኮንኖች መሆናቸውን የሰማሁት ወደደብረብርሃን ከተመለስኩ በኋላ ነበር::



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

# ምዕራፍ አራት
## መፈንቅለ መንግስቱ ከሸፈ

ደብረብርሃን እንደተመለስን ከሻለቃ መስፍን ጋር ለእቅዱ መበላሸት መንስኤው ምን እንደነበር ስንነጋገር የሚከተለውን አስረዳኝ፡፡ ነገሩ እንዲህ ነው፡፡ በአጠቃላይ እቅዱ እየተሰራ የነበረው ከኢህአዲግ ቢሮ ጋር በአንድ ላይ ነበር፡፡ እንዴት ብትለኝ ከኮሎኔል ዳንኤል ጋር በአንድ ላይ በመሆን የመፈንቅለ መንግስቱን እቅድ ያወጡት ሻለቃ ዘርአይና ሌሎች ስማቸውን የማላስታውሰው የኤርትራ ተወላጆች የነበሩ የደርግ የጦር መኮንኖች ሲሆኑ የኤርትራን መገንጠል የሚቃወሙ በመምሰል ሁለቱ መሪዎችን በመፈብቅለ መንግስት መወገድ እንዳለባቸው አሳቡን ያቀርባሉ፡፡እነዚህ ግለሰቦች እቅዱ ከመውጣቱ ጀምሮ እስስከመጨረሸሻዋ ደቂቃ ድረስ እየተሰራ የነበረውን የመፈንቅለ መንግስት እንቅስቃሴ ለኢህአዲግ እና ለሻቢያ የፀጥታ ሰራተኞች ያቀርቡ ነቤር ማለት ነዉ።

እነኮሎኔል ዳንኤል ሻለቃ ዘረአይና ከእሱ ጋር የነበሩትን የደርግ የጦር መኮንኖች ከመነሻው ጀምረው አብረዋቸው እንዲሰሩ ሲያደርጉ የእቅዱን አንዱ ኮፒ በእነሱ እጅ እንዲቀር ያደርጋሉ። በነሱ እጅ የቀረው አንድ ኮፒ ይላክ የነበረው ለመንግስት የፀጥታ ሰራተኞች ነበር፡፡ ይህ ስህተታቸው ይመስለኛል ኮሎኔል ዳንኤልን ወአውሬነት የቀየራቸው፡፡ በርግጥም የተሰራው ስተት የሁለት አመት ህፃን ሊፈፅመው የማይችል ስለነበር እየተናደዱ ያሉት በራሳቸዉ ስህተት ትክክል ነበሩ፡፡

እቅዳችንን እያከናወንን የነበርነው ከኢህአዲግ ቢሮ ጋር አንድ ላይ በመሆን የተጀመረዉ መፈንቅለ መንግስታችን አሁን ባየከው ሁኔታ ተጠናቀቀና እነኮሎኔል ዳንኤል እና አጋሮቻቸው ማእከላዊ ምርመራ ሲገቡ እነኮሎኔል ዳንኤል ወደ ግዞት እስር ቤት ሲወርዱ እነሻለቃ ዘርአይ እና አጋሮቹ እስር ቤት ድረስ እየሄዱ ይስቁባቸው እና ይሳለቁባቸው እንደነበር ወደመጨረሻ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

አካባቢ እኔ በታሰርኩበት ሰዓት ሰምቻለሁ:: የወደቀውን ስማችንን እንደገና ለማንሳት የነበረው አማራጭ አንድ መንገድ ብቻ በመሆኑ መጀመሪያ አቋርጠን የነበረውን የግንኙነት መስመር ለመዘርጋት ወደሁዋላ ተመልሽ እንቅስቃሴ ጀመርኩ:: በተደረገው እረፍት የለሽ ጥረት ተበታትኖ የነበረው ጦር በአጭር ግዜ ውስጥ ተመልሶ እንደነበር እንዲሰባሰብ ተደረገ:: ከትንሽ ቀናት በኋላም ሻለቃ መስፍን ታደሰንና ሌሎችንም የጦር መኮንንች ተገናኝቼ ስለጠቅላላው ሁኔታ ከተነጋገርን በኋላ ለቀጣይ ትግል እቅድ ተነደፈ:: የእቅዱ ዋና ተግባር የነበረውም የተበታተነውና መልሶ የተሰባሰበዉ የጦር ሃይል እንደገና አዲስ የሞራል ትምህርት እንዲሰጠው እና በአዲስ መልክ ለግዳጅ እንዲሰለፍ መጠናከር የሚል ነበር:: መልሶ ለማዋቀር አስቸጋሪ ፈተና የገጠመን ቢሆንም ጦራችንን በአጭር ግዜ ውስጥ አሰባሰብን የሞራል ተሃድሶ ትምህርት መስጠት ጀመርን::

በዚህ እንቅስቃሴ ላይ እያለን ነበር ከአስማረ ዳኜ ጋር በይፋ ለመገናኘት የቻልነው:: አስማረ ከደርግ መንግስት ጀምሮ በሽፍትነት የኖረና የጫካውን ህይወት ጠንቅቆ የሚያውቅ ሲሆን በተለይም በ1983 ዓ.ም በአርባ ጉጉ አካባቢ ይኖሩ የነበሩ የአማራ ብሔር ተወላጆች ላይ በደረሠው ጭፍጨፋ 15 ሰዎች ይዞ ወደስፍራው በመሄድ ታላቅ ጀብዱ የሰራነበር:: እንደሌሎቹ ሽፍቶች ሁሉ ህዝብን የሚዘርፍና የሚያስፈራራ ሳይሆን ለቸገረው የሚረዳ ለከፋው መከታ የሚሆን እንደነበር ይነገርለታል:: ከደርግ መንግስት ውድቀት በኋላ የኢህአዲግ መንግስት ወደ ሰላም እንዲመጣ እና ምህረት ተሰጥቶት በሰላም እንዲኖር ስለጠየቀው ይመለሳል::

ኢህአዲግ አካባቢውን በደንብ እንዲቆጣጠርለት ስለፈለገ የጊና አገር ወረዳ አስተዳዳሪ አድርጎ ሲሾመው ጊዜ አልወሰደበትም::አስማረ የወረዳ አስተዳዳሪነት ስልጣን ተሰጥቶት እያለ በኢህአዲግ የሽግግር መንግስት መፈንቅለ መንግስት ላይ ለመሳተፍ መፈለጉ ግራ አጋቢ ቢሆንም አንዳንድ ሰዎች እንደሚሉት ግን ቀደም ሲል አርባ ጉጉ ላይ በአደረገው ጀብዱ ከፕሮፌሰር አስራት ጋር ለመቀራረብ በመቻላቸው



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

መፈንቅለ መንግስቱ ላይ እንዲሳተፍ ጠይቀውታል የሚል ነው።

እስማረን የፈለግንበት ምክንያት በአገሪቱ ያሉትን ዋሻዎች ቀደም ሲል እንደመኖርያ መንደሩ ከማወቁ በተጨማሪ ከገበሬው ጋር በነበረው መቀራረብ እጅግ በጣም እንደሚጠቅመን ስለተረዳን ነበር። በወቀወቱ በአማራው ላይ ይደረግ በነበረው አፈናና ግድያ በመበሳጨቱ ወደ መጨረሻ አካባቢ በራሱ የወረዳ ግምጃ ቤት የነበረውን የጦር መሳሪያ በማውጣት የተወሰኑ ታማኝ ሰዎችን አስታጥቆ ወደ ጫካው በመመለስ ከእኛ ጋር አብሮ ሰርቷል።

እስማረ ከመፈንቅለ መንግስቱ በኋላ የተመለሰው ወደ አስተዳደር ስራው ስለነበር እሱን ቀርቦ ለማነጋገር የማይቻል ፈተና ስለሆነ ለተወሰኑ ግዜአቶች ከሱ የመገናኘቱን ሃሳብ አዘግይተን ሌሎች ስራዎችን በመስራት ላይ እንዳለን ከአዲስ አበባ በኩል እሱን ማግኘት የምችልበት ጥቆማ ደረሰን። ከአዲስ አበባ ወደ እስማረ የተዘረጋው መስመር ዋና መነሻው የመላው የአማራ ሕዝብ ድርጅት መሆኑን የተረዳሁት ከዚሀ በሁዋላ ነበር። በርግጥም ቀደም ብዬ እንደገመትኩት እስማረ ከመዐህደ ጋር እትብቱ የተሳሰረበትን ምክንያት በአርባ ጉጉ በወሰደው እርምጃ የፕሮፌሰሩን አንጀት በማራሱ ነበር።

ሻለቃ መሽፍን ታድሰ ከመዐህድ መሪ ጋር ከተገናኘ በኋላ የእስማረና የፕሮፌሰሩ አላማ የከረረ እና ከምንም በላይ በእምነት የተገነባ መሆኑን ስለተረዳ ለኔም ያስገነዘበኝ ይህንኑ እዉነታ ነዉ። ከዚህ በኋላ ነበር ሻለቃ መስፍን ታደሰና ሻምበል ደጀኔ ዝቁ ከያዙት ጥቂት ሀይል ጋር በራሱ በእስማረ ክልል ውስጥ መንቀሳቀስ እንዲችሉ ፕሮፌሰሩ ትእዛዝ ሰጥተውት በራሱ የመኖሪያ ቤት እስከተወሰነ ጊዜ ድረስ እንዲቆዩ ያደረጋቸው።

በወቅቱ የወረዳ አስተዳዳሪነት ስልጣኑን እንደያዘ ስለነበር ከመአህድ ቢሮ ጋር እንደልብ ለመገናኘት መንገዱ የተመቻቸ ከመሆኑም በተጨማሪ በአደራ ለተቀበላቸው ሰዎች «እኔ ለጊዜው ያለኝ ስልጣን አንዳንድ ነገሮችን ለማመቻቸት



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ይጠቅመኛል በትጥቅና በስንቅ በኩልም ብዙም የምቸገር አይመስለኝም::በአሁን ሰዓት እንደችግር የምቆጥረው የጦር ትምህርት ልምድ የሌላቸው ሰዎች ስላሉኝ እነሱን የወታደራዊ ትምህርት አለማግኘታቸው ነበር::እነኚህን የሰለጠኑ ባለሙያዎች ማግኘቴ እንደትልቅ እድል የምቆጥረዉ ስለሆነ እንደችግር አልቆጥረውም » በማለት ማረፊያ ይሰጣቸዋል:: እነሱም ከአስማሪ በቀረበላቸው ሃሳብ ሙሉ በሙሉ ተስማምተው ገበሬዎቹን በወታደራዊ ሙያ ለማሰልጠን ይስማማሉ::

በዚህ የተደሰቱት ሻለቃ መስፍንና ሻምበል ደጀኔ ዝቂ የማሰልጠን ስራ ይጀምራሉ:: እኔም በበኩሌ ተጥሎብኝ የነበረው የስራ ድርሻዬ በደበረብረሃን ከተማ ሆኜ የሰው ሃይል መመልመልና ከየወረዳው የሚመጡትን ምምሎች አንዳቸው ከሌላቸው ጋር የሚገናኙበትን መስመር በአዲስ መልክ ተቀብዬ የግንኙነት ስራውን ጀመርሁ:: በዚህ መልኩ የተወሰነ ጊዜ እንደሰራሁ አንድ ሰው ከጊና አገር ወረዳ የመጣ መሆኑን ከነገረኝ በኋላ

«ሻለቃ መስፍን ታደሰ ልኮኝ ነው የመጣሁት:: በአስቸኳይ ጊናአገር ድረስ መጥተህ በአካል እንድንገናኝ ብሎሃል» አለኝ::

ከሻለቃ መስፍን በተደረገልኝ ጥሪ መሰረት ሰኔ 10 / 1984 ዓ.ም መልእክቱን ይዞልኝ ከመጣው ሰው ጋር ወደ ጊናአገር ለመሄድ ከጠዋቱ አስራሁለት ሠዓት የደብረብርሃንን ከተማ ለቅቀን ወጣን:: በመኪና እስከ ጫጫ ድረስ ከተጓዝን በኋላ ጫጫ ከተማ ከመግባታችን በፊት አንድ ኪሎ ሜትር እርቀት ላይ ከመኪና ወርደን በምስራቅ አቅጣጫ ከዋናው መኪና መንገድ ተገንጥለን ሰንሰለታማውን የእግር ጉዞ ጀመርን::

የፀሐይ መውጫ አቅጣጫን ከፊት ለፊታችን እየተመለከትን ስንዋዝ ዉለን ከሰአት በሁዋላ ደረስን:: ሻለቃ መስፍን ከአስማሪ መኖርያ ቤት እየጠበቀኝ ስለነበር ከአስማሪ ዳኘ ጋር አስተዋወቀኝና ስለኔ አጠቃላይ ሁኔታና ማንነት በጥቅሉ አጠር አድርጎ አስረዳው::አስማሪ ዳኘ ዕድሜው በ30ዎቹ መጀመሪያ ላይ የሚገኝ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ሲሆን ቁመቱ እስከ 1.78 ሜትር የሚደርስና እና መልኩ የቀይ ዳማ ፀጉረ ሉጫ መልከመልካምና በአንድ እጁ ላይ የመመንመን ወይንም በተለምዶ «ሻባ» ተብሎ የሚጠራ መለያ ያለዉ ነው:: ከአንድ እጁ በስተቀር ሌላው አካሉ የጠነከረና የተስተካከለ ወንዳወንድ ቁመና ያለው ነበር:: በቀለም ትምህርቱ በኩል ቡዙ የገፋ ባይሆንም ሰውን የማዳመጥና የመረዳት ችሎታውን ስመለከት ጥሩ አስተዋይ ረጋ ያለና በሳል አእምሮ ያለው መሆኑን በውይይታችን ወቅት ልረዳ ችያለሁ::

አስማረን መሰረታዊ ይዘቱን ለመግለፅ በጠቅላላው በሁሉም ነገር ላይ የተረጋጋና የመቻኮል ምልክት የማይታይበት ልበ ሙሉ ተብሎ ሊጠራ የሚገባው ወንዳወንድ ባለ ግርማ ሞገስ ሰው ነው ቢባል የሚገባው ነበር:: እንደአንበሳ የሚያስፈራ ግርማ ሞገስ የከበደ እና የጠነከረ የሰውነት አቋም አለው:: ካልተቆጣ በቀር አይኖቹ ትኩር ብለው ሰውን ስለማይመለከቱ እንደነብር አይናፋር መሆኑን ልረዳ ችያለሁ::

ወደመጨረሻ አካባቢ እንደነበረኝ ግምት ከሆነ ከፕሮፌሰር አስራት ጋር ሊያግባባቸው የቻለውም ይህ ባህርይው ሊሆን ይችላል የሚል ድምዳሜ ላይ አድርሶኛል:: ለምን ቢባል ፕሮፌሰር ችኩል ሰው አይወዱም:: አስማረ ደግሞ በሁሉም ነገር ላይ ቁጥብ የሚባል ሰው ነው:: አስማረ በሱ በኩል ከኔ የማፈልገዉንና ስለራሱም ሁኔታ አንድ በአንድ ዘርዝሮ ከአስረዳኝ በኋላ ፈገግ ብሎ እየተ መለከተኝ

«እኔ ጨርሻለሁ:: እናንተ ተጫወቱ» ብሎ ቤቱን ለኔና ሻለቃ መስፍን ትቶልን ወጣ::

ከሻለቃ መስፍን ጋር በነበረን ቆይታ አስማረ ከፕሮፌሰር አስራት ጋር ስለነበረው ግንኙነትና ስለአለው አጠቃላይ አቋም ሁሉንም ነገር ለበራካታ ሰዓት በዝርዝር አስረዳኝ:: አስማ ረ የወረዳ አስተዳደር ሆኖ ለመንግስት እያገለገለ ምን ያህል አምኖት በቤቱ ተደብቆ መቆየት እንዳቻለም በውይይታችን መካከል ጣልቃ እየገባሁ ሻለቃ መስፍንን ጠይቄው ነበር:: የሠ መልስ የመንግስት አላፊነት ቢይዝም እንደማያምንበትና በአማራው ላይ የሚደርሰው ግፍ ያንገፈገፈጠው መሆኑን የሚገልፅ ሲሆን



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

አጠቃላይ የአስማረን ዕቅድና የወደፊት ሀሳብ በሚከተለው መልኩ ሊያስረዳኝ ሞክሮ ነበር።

«አስማረ ዳኜ በኢህአዲግ መንግስት ውስጥ በሥልጣን መቆየት የማይፈልግ ከመሆኑም በላይ እነሱም ለጊዜው መጠቀሚያ ሊያደረጉትእንጅ በዘላቂነት እንደማይፈልጉት በሚገባ የተረዳ ሰው ነው።በተጨማሪም በአማራው ላይ እየደረሰ ያለውን በደል ከኛ በላይ የተገነዘበ ጥሩ ህሊና ያለው አስተዋይ መሆኑን አምናለሁ። ለዚህም በቂ መረጃው እሱ የሚነግረኝ ሳይሆን በአርባ ጉጉ የሰራው ታላቅ ስራ ነው። ሥልጣኑንም በሚመለከት ላለህ ጥርጣሬ ኢህአዲግ በከሰም አካባቢ ያለውን ገበሬ ለጊዜው እንዲያረጋጋለት ያደረገው ዘዴ እንጂ ለአስማረ አስቦ አይደለም ስልጣን የሰጠው ኢህአዲግ አስማረ ያደረገውን እና እያደረገ ያለውን በሙሉ ያውቃል። እስከ አፍንጫው የጦር መሳሪያ የታጠቀዉንና በቡልጋ አካባቢ ያለውን አማራአረጋግቶለትስጨርስ

ሁሉንም ነገር መቆጣጠር በሚችልት ወቅት እንደሚያስገልለው አስማረ ተረድቷል። በተለይም ከመአህድ ጋር ያለዉን ቁርኝትና አሁን ደግሞ በመፈንቅለ መንግስቱ ላይ የነበረውን ተሳትፎ መንግስት ስለ አለማወቁ ምንም መተማመኛ አይኖርም። ይህንን ደግሞ እንደ አስማረ ያለ ንቁ አይምሮ ያለው ሰው ቀድሞ ለመተንበይ የሚቸገር አይመስለኝም። በመንግስት ከተደረሰበትና ከታወቀ ተጉለት ውስጥ በኢህዲጎች የተገደለውን አየለ ዝቄን አንስቶ የሱ እጣ እንደሚገጥመው በደንብ አስረድቶኛል። በፍፁም አያምናቸውም። ሳይቀድሙኝ እኔ ቀድሜያቸው በነሱ ግምጃ ቤት ውስጥ ባለው መሳሪያ የራሴን ጦር በተደራጀ መልኩ አስታጥቃለሁ እናንተ በወታደራዊ ስልጠናው ተባበሩኝ እንጅ በኔ በኩል በማንኛውም ነገር ላይ ምንም ችግር የለም» በማለት ስለሁሉም ነገር አንድ በአንድ አስረድቶኛል አለኝ ሻለቃ መስፍን

ሁሉንም ነገር በማሰላሰል ከገባሁበት ሰመመን የመለሰኝ «ያለህን ጥርጣሬ አስወግደው » በማለት ትከሻዬን መታ ሊያደርገኝ ነበር።ሁለታችን እየጠጨዋወጥን እያለን አስማረ ተመልሶ መጣና «እናንተን የመሰለ የጦር መኮንኖች ካገኘሁ ብዙ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

እንሰራለን። ፕሮፌሰር አስራትም በብዙ ነገር እንዲማረዱኝ ቃል ገብተውልኛል። ማንም ሰው ባይረዳኝም እንኳን እኔ ለራሴ አላንስም። አለና ከፊት ለፊታችን ከአንድ ወንበር ላይ እንደተቀመጠ በየተራ ይመለከተን ጀመር።

በርግጥም ከአነጋገሩ የተረዳሁት ቀምነገር ቢኖር ልበ ሙሉነቱንና ቆራጥነቱን ብቻ ሳይሆን በውስጡ የነበረ ወገን አፍቃሪነቱን ጭምር ነበር። የሱ ወኔ እያሞቀኝ መጣና በቆራጥነት አብረን እንደምንታገል ነገርኩት። በእርግጥም አስማረ ያነሳቸው እና ለመሸፈት የወሰነባቸውን ሁኔታዎች ከእኔ ጥርጣሬ ጋር ሳወዳድር በብዙ መንገድ እያመነኩት ልመጣ ችያለሁ፡ በወቅቱ ከፊት ለፊቴ ተቀምጦ የነበረው ያ ጀግና ሰው ከ1983 ዓ.ም ከረመት ወር ላይ ጀምሮ በአማራው ላይ በደረሰው ጭፍጨፋ የራሱን ሃይል በመያዝ በምስራቅ ኦሮሚያ ዘልቆ ታሪክ መስራቱን የተረዳሁት ወደመጨረሻ ነበር። ይህ የሚስጥር ታሪካዊ ጀግንነቱ ስላኮራቸው ሳይሆን አይቀርም ፕሮፌሰሩ በጥብቅ እንዲቆረጐት ያደርጋቸው። ከአስማረ ብዙ ነገር ነው የተረደሳሁት። ከዚህ በኋላ ነበር ጥሩ እረዳት ያገኘን መሆናችን የታወቀኝ። ጦላይ ወታደራዊ ካምፕ በተሃድሶ ላይ ሆነን እንመኝ የነበረው የዚህ አይነት ጀግና ሰው ማግኘት እንደነበር አስታውሳለሁ።

አስማረ ራሱ ለመሸፈት መነሳቱ ብቻ ሳይሆን ብዙ እሱን የሚያምኑት የታጠቁ ገበሬዎች ነበሩት። መሳሪያን በተመለከተም ከሞርታር እስከ ላውንቸር ድረስ እንደነበረው ለማወቅ ችያለሁ። መትረየስማ ለሱ በጣም ቀላል መሳሪያ ነበር ለማለት እችላለሁ። ከዚህ ውጪ ክላሽን ጨምሮ ክነሙሉ ጥይቶቻቸው በሺ የሚቆጠሩ መሳሪያዎች በራሱ ግምጃ ቤት ውስጥ ስለነበር የጦርመሳርያ ችግር የለም። ከዚህ ሌላም ሁለት ነገር አለው። መሳሪያና በወታደራዊ ሙያ ያልሰለጠነ አመራር የሌለው ብዙ ገበሬ ሀይል። ታዲያ ጥያቄው ይህንን ብዙ የገበሬ ሃይል እንዴት ነፈስ እንዝራብትና ወታደር እናደረገው የሚለው ብቻ ነው።እኛ ደግሞ ዘመናዊ መሣሪያውን ለማስተማርም ሆነ ገበሬውን



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ለማስልጠን ብቁ ነበርን:: ይህን ሃሳብ በአእምሮዬ እያሰላሰልሁ

»በዚህ በኩል ምን ያህል የምንሰራ ይመስልሃል? አሰማረ ለእኛ አላፊነት ጥሎብናል:: ስለዚህ ወደተግባር መቀየር የኛ ፋንታ አይመስልህም አለኝ መስፍን::

በርግጥም አሰማረ ወደር የማይገኝለት የጀግኖች ጀግና የሚባል መሆኑን አምናለሁ: ከአስራ አምስት የማይበልጡ ረዳቶችን አስከትሎ በመሄድ ታላቅ ጀብድ ሰርቶ ተመልሷል:: ይህንን ስሰማ የበለጠ እየኮራሁ በትና እየወደድኩት መጥቻለሁ:: ለዚህ ሰውም ታማኝ በመሆን በርካታ ገበሬዎችን ማሰልጠን እንዳለብን አምናለሁ:: ከመስፍን ጋር ብዙ ከተወያየን በኋላ የሚያሰለጥኑት ሃይሎች ወደዚህ ሲመጡ በቅድሚያ ደህንነታቸው መጠበቅ ስለሚኖርበት ወደቆላው ጊዜያዊ የማሰልጠኛ ቦታ እንዲዘጋጅ አስገነዘብኩት:: እሱም ቢሆን በኛ በኩል ገበሬውን ለማሰልጠን የሚመጡት ወታደሮች ደህንነታቸው መጠበቅ እንዳበት ያምናል የሚል መልስ ሰጠኝ መስፍን::

አያይዞም አስማረ በመጀመሪያ አፋርን በሚያዋስነው የከሰም ወንዝን ተከትሎ በአለው በርሃማ ክልል ሄዶ ቦታ ማዘጋጀት እንዳለበት ከተወያየንበት በኋላ የቦታውን አቀማመጥ እኛ ብንመርጥ እንደሚሻል አስማረ አስገነዘበን:: እንዲህ ያለው አዲስ ሃሳብ ባንድ በኩል ያስፈነደቀኝ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ሥጋት እየጫረብኝ ነበር የተቀበልኩት:: ምክንያቱም በወቅቱ ገበሬውን ወታደራዊ ትምህርት ለመስጠት የነበረንን የሰው ሃይል የአቅም ውስንነት ሙሉ በሙሉ ከማልተማመንበት ደረጃ ላይ እንዳለ ስለማውቅ ነበር:: ያም ሆኖ ግን የአስማረን ዕድል መጠቀም ከምንም በላይ የተሻለ አማራጭ ስለነበር የቀረበውን ሃሳብ ያለማወላወል ለመቀበል ተገደድሁ:: በዚህ ሁኔታ ከችግር ጋር ተያይዞ የመጣው ያልተጠበቀ ዕድል ከጠለቀ ሀሳብ ውስጥ ሰለከተተኝ በሃሳብ ተውጬ ለብዙ ሰዓት መማሰን ቀጥዬም ነበር::



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

በመጨረሻም ከሀሳቤ በመመለስ «የገጠመን ዕድል ከጠበቅሁት በላይ ስለሆነ በጣም ተደስቻለሁ ነገር ግን እስከ አሁን በማንም ድጋፍ ሳይሆን እራሴ ባለኝ አቅም ብቻ የማንቀሳቀስ በመሆኑ በጣም ተጎድቼ እንደነበር አውቃለሁ ከዚህም በተጨማሪ የሴል አዘረጋጋችን ዘዴ one to one ስለሆነ በእውነቱ ያለውን ሀይል አውቃለሁ። የዚህን ያህል ይሆናል ብዬ ለመቁጠር ወኔውም ድፌረቱም የለኝም። ግን የተቻለውን ለመሥራት ለራሴ ቃል ገባሁ። በነገሩ ብዙ ከአሰብኩበት በኋላ ወደ ደብረብርሃን ልመለስና የተወሰነ ቀን የማነቃቃት ሥራ ሠርቼ ልገልጽላችሁ » የሚል አሳብ አቀረብሁ።

መስፍን «አስማረ በአሁኑ ሰዓት ከሰዎች ጋር ያለው ሁኔታ ሳይላዩን ብቻ ስለሆነ እና ሁሉም በሥጋት ውስጥ ስለሆኑ እስ ይህንን የክረምት ወር የራሱን ሃይል በማስታጠቅ ወደ ቆላው ወርዶ ቦታውን ከያዘበኋላ ቢጠሩትም ወይ ላለማለት ወስኗል። በተቻለህ መጠን በርታ» አለኝ እጄን ጠበቅ አድርጎበወዳጅነት እየጨበጠኝ።



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

# ምዕራፍ አምስት

## አስማረ ሸፈቷል

በሁለተኛው ቀን አስማረንና እሱን ተሰናብቼ ከሰአት በኋላ ወደ ደብረብርሃን ጉዞ ጀመርሁ። ደብረብርሃን የደረስኩት በጣም መሽቶ ስለነበር ማንም ሳያገኝኝ ወደ ከተማ ዘልቄ ገባሁ። ወደ መጨረሻ ኢሀአዲግ ደብረብርሃን ከተማ የገደለው አንድ ሰውና ሌሎች አሁን ስማቸውን መግለፅ የማልፈልገው ሁለት የሻለቃ መአረግ የነበራቸው የእኛ አባሎች ደብረብርሃን ይጠብቁኝ ስለነበር ከአስማረ ዳኜ ይገፄ የተመለስኩትን መልእክት በዝርዝር ነገርኳቸው።

ከመልእክቱም በተጨማሪ የአስማረን ጠቃላላ አቋምና ሁኔታዎች በዝርዝር ስገልፅላቸው እጅግ ተደስተው ነበርያዳመጡኝ። ስለቀጣዩ ሁኔታ በሰፊት ከተወያይተንበት በኋላ በሁሉም ነገር ከስምምነት ላይ መድረሳቸውን አረጋገጥሁ። በጣም ተዳክሜ ስለነበር «እረፍት ያስፈልገኛል» ብያቸው የትውልድ መንደሬ ወደሆነችው መንዲዳ ወረዳ ከለሊቱ ስምንት ሰዓት ሲሆን ሄድሁ።

በዚያ ቆይታዬ ወቅት እንዳቀድኩት ተረጋግቼ ብዙ አላረፍኩም ነበር። አባላቶችን በመመልመል ሥራ ላይ ተጠምጄ ሌትና ቀን ስሰራ ነበር የቆየሁት። በወቅቱ ከመለመልኳቸው ሰዎችም አብዛኛዎቹ የቀድሞ ጦር አባላት ስለነበሩ ለመዝመት ፍቃደኛ መሆናቸውን በደስታ ነበር ያረጋገጡልኝ። በማንኛውም ሰዓት ስጠራቸው እንደሚነሱ ቃል ገቡልኝና የሃሳብ ልውውጥ ስናደርግ በመንዲዳ ወረዳ ለሃያ ቀን ቆይቼ ከሃያ ቀን በኋላ የተወሰኑ መኮንኖችንና የጦር አበላትን አስከትዬ እለሊት ላይ ወደ ጊናገር ጉዞ ጀመርን።

አብረዉን ከነበሩት አብዛኞዎቹ ገበሬዎች ነበሩ። ሌሊቱን ሙሉ ስንጓዝ አደርን ከንጋቱ አስራ አንድ ሰዓት ሲሆን ጊናገር ስንደርስ እነ ሻለቃ መስፍን እየጠበቁን አገኘናቸው። ያመጣናቸው ሰዎች ወደ ተዘጋጀላቸው ጊዜያዊ ማረፊያ ሲሄዱ ከመስፍንና ከአስማረ ጋር



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ስለጠቅላላው ሁኔታ ከተነጋገርን በኋላ እኔና መ/አ ተስፋዬ ሀይሌ አንድ ቤት ውስጥ ስንጫወት ዉለን ምሽት ላይ ወደ ደብረብርሃን ተመለስን። መ/አ ተስፋዬ ተሰጥቶት የነበረው የስራ ድርሻ የኢህአዲግን እንቅስቃሴንና የህዝቡን የእለት ከእለት ስሜት እየተከታተለ መረጃ እንዲየቀርብ ነበር።በደብረብርሃን ከተማ ለትንሽ ጊዜ እንዲቆይ የተደረገውም ለዚህ ሥራ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ አስማረ ከሱ ዘንድ ያደረስናቸውን ሰዎች አጥንቶ እስኪያውቃቸው ድረስ ለተወሰነ ግዜ በአለንበት ሆነን ከሱ መልስ መጠባበቅ እንደነበረብን እናውቃለን። በዚህ ሁኔታ አንድ ወር ያለፈን ቢሆንም የመጣልን መልስ አልነበረም። ስለሰዎቹ ሁኔታ መልስ ስንጠብሓ የስማረና የኢህዲግ የመጨረሻ የፍቺ ዜና በዚህ መልኩ ሰማነሁ።

አስማረ ሀይሉን አዘጋጅቶ ከአጠናቀቀ በኋላ በወረዳው ግምጃ ቤት የነበረውን ዘመናዊ መስሪያ በማውጣት ለራሱ ታማኝ ሰዎች አስታጥቆ አሳግርት በተባለው ቦታ መሽጎ ከኢህአዲግ ሰራዊት ጋር መፋጠጡን አንድ መልእክተኛ መጥቶ ነገረኝ። እየተዘጋጀንበት ያለና የምጠብቀው ቢሆንም ለምን እንደሆነ አላውቅም ዜናው ሲደርሰኝ ልቤ ክፉኛ ነበር የተረበሸው። ምናልባትም አይቀሬው አጠቃላይ ጦርነት መጀመሩን ስለተረዳሁ ይመስለኛል። አስማረ ሀይሉን ለውጊያ ዝግጁ ሆኖ እንዲጠባበቅ ትዕዛዝ በመስጠት አሳግርት ውስጥ ጊዜያዊ ቦታ ላይ የመንግስትን ጦር እየጠበቀ መሆኑንና በሻለቃ መስፍን ይመራ የነበረው አንድ ሃይል ደግሞ የመከላከያ ሽፋን እንዲሰጥ በአሳግርት ተራራማ ስፍራ ይዞ እየተጠባበቀ እንደሆነ ነበር የመጣው መልእክተኛ ያስረዳኝ።

አስማረ ዝግጅቱን አጠናቅቆ ከጨረሰ በኋላ ለጦርነት ተዘጋጅቻለሁና እንድትመጣና እንድትገጥመኝ ጋብዤሀለሁ ብሎ ለመንግስት መልእክት ሲያስተላልፍ ኢህአዲግ በበኩሉ አግባብቶ እጁን ለመያዝ የጀመረውን መጥፎ መንገድ ትቶ በሰላም ወደ አላፊነቱ እንዲመለስ ይለምነው ጀመር።

አስማረ ግን «የነብር ጅራት አይዙም ከያያም» የተባለውን ተረት ተርቶበት «ይልቅስ በፍጥነት እንድትመጣ» የሚል መልስ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ይሰጠዋል:: ኢህአዲግ የአስማረን አቋም ከተረዳ በኋላ ሁለት ብርጌድ ጦር በጊናገር ወረዳ ላይ ለማዝመት ሲንቀሳቀስ ጊዜ አልወሰደበትም:: በዚህ መልኩ ቀዝቀዝ ብሎ የተጀመረው ጦርነት እየተካረረ መጥቶ ወደ ጠቅላላ ጦርነት ተገባ:: መንግስትም ለማግባባት ይጠቀምበት የነበረውን የሰላም መንገድ ሙሉ በሙሉ በመተው የሃይል እርምጃውን በዘመናዊና በከባድ መስሪያ በመታገዝ ከባድ ጦርነት ለመክፈት ተገደደ::

በአስማረ ይመራ የነበረው የገበሬዎች ጦር በበኩሉ ጠላትን በሞተ መሬት ውስጥ በማስገባትና ቆርጦ በመምታት በአንድ ቀን ውጊያ ብቻ በርካታ የኢሃዲግ ወታደሮች ሲገደሉ ሃያ አምስት ደግሞ ከነትጥቃቸው ይማረካሉ:: መንግስት የተዋጊ ሃይሉን መጠን በማሳደግና የከባድ መሣሪያዎች ድጋፍ በመጠቀም ቢሊኮፕተር ጭምር እየታገዘ ይደበድብ ጀመር:: ከመንግስት ወታደር ጋር ፊትለፊት የውጊያ ግንባር የፈጠረው የገበሬውች ሃይል ያለምንም ስንቅ ለሳምንት ያህል የተፋለመ ሲሆን በጦርነቱ ላይም በርካታ የመንግስት ወታደሮች ተገድለው ብዙ የጦር መሳሪያ ተሰብስቦ ነበር::

አስማረ ድል ቢቀናውም ከወታደራዊ ሳይንስ አኳያ ሲታይ በዚህ መቀጠሉ የትም እንደሚያደርስ ግልጽ ነበር:: ስለሆነም ሻለቃ መስፍንና ሌሎችም የጦር መኮንኖች ሆነው ከተነጋገሩበት በኋላ የውጊ ወረዳዎች መቀየርና ማፈግፈግ እንዳለባቸው ለአስማረ ያማክሩታል:: አስማረም « ከእናንተ የጦር ሞያተኞት የዚህ ዓይነት ምክር እስኪመጣ እንጂ እስከ መጨረሻው እንቆያለን የሚል ዕቅድ አልነበረኝም:: አሁንም ቢሆን ቀደም ሲል ያዘጋጀሁት ቦታ ስላለኝ ወደዛ ለመሄደ ዝግጁ ነኝ:: ስለሆነም የዚህን ጦር ንቅናቄና የማፈግፈግ ሥልት አውጥታችሁ አፈፃፀሙን በአስቸኳይ በመጀመር ጦራችንን ከውጊያ ማላቀቅ አለባችሁ» የሚል መልስ ሰጠ::

ሻለቃ መስፍንና ሻምበል ደጀኑ ከአስማረ ባገኙት የማፈግፈግ ፈቃደኝነት በጦርነት ላይ ያለውን ሃይል በምን መንገድ ቢጠቀም ያለጉዳት ከጦርነት ነፃ እንደሚሆን የሚያስችለውን እቅድ ለመንደፍ ቦታዎች እና ሰዓሰቶችን



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ያመቻቹ ጀመር:: የመጨረሻው ንድፊ ሃሳብ ለኔ ተሰጠኝና ጦራችን ከውጊያ ተላቅቆ በሰላም የሚያስፈልግበትን ንድፍ አወጣሁ:: በዚህ ንድፍ ውስጥ የተካተቱት ዋና ዋና ነጥቦች ለቀጣይ ዘመቻ ቤት ንብረቱን ጥሎ የሚሄደውና በመጀመሪያም በአስማረ ዳኜ በኩል ተነግሮትና ወደ ትግል ለመቀላቀል ዝግጁ ሆኖ በነሱ አቅራቢያ እንዲሰፍር ተደርጎ የነበረ ተጠባባቂ ሃይል እንዴትና የት ከኛ ጋር መገናኘት እንዳለበት በውጊያ ላይ ያለው ጦራችን ከጦርነት ለማፈግፈግ ሲንቀሳቀስ የመንግስት ሠራዊት እንዳይከተለን ማሳሳቻዎችን እንዴት መጠቀም እንዳለብን እነዚህን ሁሉ በጥንቃቄ ካጠናሁ በኋላ ንድፉን አወጣሁ::

በዚህ መሰረትም ተዋጊው ሃይል በሁሉም አቅጣጫ የተጧጧፈ ጦርነት መክፈት የግድ ነበር:: በዚህ መሃል በጦርነት ላይ የነበረው ሀይል ፋታ ስለሚያገኝ ከጦርነት ይላቀቃል:: ቀጣዩ ክፍል የሽፋን ተኩስ ይሰጥ የነበረው ነው:: እሱን ቦታ እንዲለቀ ለማድረግም ቀደም ሲል ከጦርነትነፃ የሆነው ተዋጊ በርቀት በመንግስት ወታደሮች ላይ የከባድ መሳሪያ ተኩስ ይከፍታል::ሶስተኛው ከውጊያ የተላቀቀውን ጦር የመሰብሰቢያ ወይንም የመገናኛ ቦታዎችን ማዘጋጀት ነበር::

ጦራችን የመሰብሰቢያ ወረዳ ተዘጋጅቶለት በቀጠሮ ቦታ ከተገናኘ በኋላ ለነበረዉ እንቅስቃሴ የተሰራዉ ንድፍ ከአስማረ ጋር ውይይት ከተደረገበት በኋላ ለአፈፃፀም ወደ ውጊያ ትዕዛዝ ተቀይሮ ከሌሊቱ ሰባት ሰዓት ሲሆን በመንግስት ጦር ላይ ድብልቅልቅ ያለ ጦርነት በሁሉም አቅጣጫ ተከፈተ:: ከሌሊቱ ስምንት ሰአት ተኩል ሲሆን ጦራችን ይዞት የነበረውን የውጊያ ወረዳ ሙሉ በሙሉ ለቆ ወጣ::

ከዚያም ለሽፋን ወደኋላ የቀረውን ሃይል እንዲያስለቅቅ በተራራ ላይ ይጠብቅ የነበረ አነስተኛ ሀይል በከባድ መሳሪያ መደብደብ ጀመረና ከለሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ላይ ጦራችን ያለምንም ጉዳት የመጀመሪያውን የውጊያ ወረዳ ትቶ ወደ ከሰም ወንዝ በማፈግፈግ ከመንጋቱ በፊት ገኘር መሬት ይዞ ይጠባበቅ ጀመር::

ያም ሆኖ እኛን የተከተለ የመንግስሰት ሃይል አልነበረም:: ይህ ቦታ ደግሞ ለአስማረ ዳኜ ልክ እንደራሱ ቤትና እንደአባቱ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

እርስትየሚቆጥረው መሬት ነበር ለማለት ይቻላል። ለምን ቢባልም አስማረ ከአፋሮቹ ጋር በሁለት ጥብቅ ነገሮች በወዳጅነት ተቆራኝቶ የሚኖር በመሆኑ ሲሆን እሱም በአምቻና ጋብቻበሲሳ በኩልም የአፋር ህዝብ አርብቶ አደር እንደመሆኑ መጠን ከብቱ ውሃና ሣር ሲቸግረው ወደ አስማረ ይዞታ ውስጥ እያመጣ ከድርቅ እንዲከላከል መፍቀዱ ነበር።

በዚህ ሁኔታ የተመሰረተው ቤተሰባዊ ግንኙነት አስማረ ተቸግሮ መጥቶ ይቅርና እሱን ለመሰለ ሁሉ የአፋሮች ቤታቸው ክፍት ነበር። ከአፋር ባላባቶች እና የጐሣ መሪዎች ጋር መልካም ግንኙነት በመፍጠሩም እጅግ አድርጎ እንደሚያምናቸው ብቻ ሳይሆን እንደሚከራባቸውም አስማረ ዘወትር ይናገራል። አፋሮች ከሁሉም በላይ የመደጋገፍ ልምድ ስለነበራቸው አስማረ ሲመቸው ወደ ሰሜን ሸዋ አሣግርትና አንኮበር ሳይመቸው ደገሞ ወደ አፋር ክልል እየሄደ መሠወር የቆየ ልምዱ ነበር። የአፋርና የአዋሽን አዋሳኝ ለወታደራዊ ሀይሉ ማጠናከሪያና መስፈሪያ የተመቹ እንደሚሆኑ ቀደም ሲል እንደነገረኝ አስታውሳለሁ። በአፋር ወዳጆቹ ዘንድ በሺህ የሚቆጠሩ የቀንድ ከብቶች እንዳሉትና ለችግር ጊዜ ለራሱ ጦር ስንቅ እደሚሆኑት የሚተማመን ሲሆንአብዛኛውን ሃብት ያፈራውም የወረዳ አስተዳዳሪ በነበረበት ወቅት ሳይሆን በደርግ መንግስት ሽፍቶ አፋር ውስጥ በቆየበት ጊዜ ነበር።

ጦራችን የውጊያ ወረዳውን ለቅቶ ከወጣ በኋላ በከሰም ቀላ ጊዜያዊ ቦታ እንደሰፈረ ሻለቃ መስፍን ታደሰና ሻምበል ደጀኔ ዝቄ የነበራቸውን ሀይል በአንድነት በማጣመር ስለቀጣዩ ሁኔታ አመራር መስጠት ጀመሩ። ጦርነቱ ያለምንም ጉዳት በጊዜያዊ ወረዳ በመሰፈሩ በአመራሮቹ ልብ ውስጥ የነበረው ደስታ ቀላል የሚባል አልነበረም። ጦራችን ወደ አፋር ክልል ከገባ በኋላ እኔ ወደብረብርሃብ ስለተመለስሁ ለጊዜው ከነሱ ጋር ያለው ግንኙነት ተቋረጠና እስከ ታህሳስ መጨረሻ ድረስ ምንም ነገር ሳልሰማ ሌሎች ስራዎችን እየሰራሁ ቆየሁ። ለእኔ የተሰጠኝ የስራ ድርሻ አዲስ አበባና ደብረብርሃን እየተመላለስሁ በጉንደርና በጎጃም ያለውን እንቅስቃሴ በማጥናት የመገናኛ መስመር እንዲዘረጋ መንገዶችን ማመቻቸት ነበር። በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳለሁአንድ ሰው መ/አ ተስፋዬ ሀይሉ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ቤት ሥልክ ይደወልና እኔን እንደሚፈልግ መልእክት ይተዋል። መልክቱ ሲነገረኝ ሁኔታው ቢረብሸኝም የተባለውን ሰው ማግት ነበረብኝ። ከቀጠሮው ቦታ ስደርስ አንድ ጠይም ቀጭን ረዘም ያለ ልጅ እግር ሰው እየጠበቀኝ ነበር። ሰውዬው ማንነቱን ከአስተዋወቀኝ በኋላ አዲስ አበባ ለስራ እንደምፈለግ ነገረኝ። የመጠቀሚያ የምስጢር ኮድ ስለነገረኝ ስለማንነቱ ብዙም አልተጨነቅሁም።በአንድ ላንድክሩዘር መኪና ተሳፍረን ከአንድ ሰዓት ተኩል ጉዞ በኋላ አዲስ አበባ ደረስን። ከአንድ ወዳጃችን ቤት እንደገባን አፋርኛና አማርኛ ጥርት አድርጎ የሚናገር ልጅ እግር ሰው እየጠበቀን ነበር።ከድብረብርሃን አብሮን የመጣው ሰው እዛ ካገኘነው ወጣት አፋር ጋር አስተዋወቀኝና መልእክተኛው ስለመጣበት ጉዳይ እንደዚህ ሲል አስረዳኝ።

« የመጣሁት ከአስማሪ ዳኘ ተልኪ ነው። አንተን ለጥብቅ ስራ እደሚፈልግህና በአስቸኳይ ይገኝህ ወደሱ እንድመልስ አስጠንቅቆ ነው የላከኝ። ዛሬውኑ ተነስተን ጉዞ መጀመር አለብን» አለኝ

ከሰዓት በኃላ ከአዲስ አበባ ተነስተን አዋሽ አስራ ሁለት ሰዓት አካባቢ ገባን። ከዚያም አስማሪ ዳኜና የኛ ጦር አለበት ሊያደርሰኝ የሚችል ሌላ ሰው መዘጋጀቱን አስረድቶኝ አዋሽ ከተማ ለሚኖሩና የአስማሪ ወዳጆች ለሆኑ አፋሮች አስረከበኝና ሄደ። አፋሮቹ በጥሩ እንክብካቤ ከአስተናገዱኝ በኋላ ወደነ አስማሪ ለሚደረገው የእግር ጉዞ መንገድ የሚመሩኝ የአስማሪን መልእክት አመላላሾች እደሆኑ ተነገረኝ። ከጠዋቱ አንድ ሰዓት ተነስተን መትሃራ በሁለት ሰዓት ደርስን። ከመተሃራ በሚቀጥለው ቀን ወደ መልካ ሰዲቀ ጉዞ ጀምረን አዋሽን በእግር በማቋረጥ አቅማችን የቻለውን ያህል ከተጓዝን በኋላ ወደ 11 ሰዓት ገደማ መንገድ እየመራኝ ከነበረው አፋር ቤት ደረስንና አዳር እዚያው ሆነ። የአፋር ክልል ሙቀት ሌሊት ሳይቀር እንደእሳት ነሞራ ሲገርፈኝ ነበር ያደረው።

በማግስቱ ጠዋት ተነስተን ቆንጥርና ትናንሽ ቁጥቋጦዎች እየጣስን ስንጓዝ ውለን አስር ሰዓት ላይ ጦራችን ከነበረበት መድረሳችንን አፋሩ ነገረኝ። ከትንሽ ደቂቃ በኋላ ከአስማሪና



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ከመስፍን ጋር ስንገናኝ በጣም ተዳክሜ ስለነበር ሰላምታ እንደተለዋወጥን ከአፋሩ ጎጆ ቤት ታዛ ስር ተጋደምኩ። አየሩ ቀስ በቀስ እየቀዘቀዘ ስለነበር ሰውነቴን ድካሙ ሲለቀኝ ታወቀኝ። ከዚያም እሚበላ ነገር ቀማመስኩና ትንሽ አረፍ እንዳልኩ አስማረ በአዲስ አበባ እና በደብረብርሃን አካባቢ ስለነበሩት አጠቃላይ ሁኔታዎች ይጠይቀኝ ጀመር። ሁሉንም ነገር የማውቀውን ያህል ከነገርኩት በኋላ ስለወደፊቱ ምን መሥራት እንደምንችል ሰፋ አድርገን ከተወያየን።በሁዋላ « ቀሪውን ከመስፍን ጋር ተወያዩ» ብሎን ሁለታችንን ብቻ ትቶን ይዞኝ ከመጣው አፋር ጋርከቤት ወጥቶ ሄደ።እኔና መስፍን ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ያለፈበትን የውጊያ ሁኔታና በመጨረሻውም ያለበትን ደረጃ በዝርዝር ያስረዳኝ ለብዙ ሰዓት ነበር። ከምሽቱ አንድ ሰዓት አካባቢ ሲሆን በጣም ደክሞኝ ስለነበር ማረፍ እንዳለብኝ ነገርኩት እና በአፋሩ ጎጆ ውስጥ ከአንዲት የድንጋይ መደብ ላይ ጋደም ብዬ ስለቀጣዩ ሁኔታ አስብ ጀመር። ለብዙ ሰዓት ሳስብ ቆይቼ እለሊት ላይ ነበር እንቅልፍ የወሰደኝ።

ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት አካባቢ ስነቃ ሻለቃ መስፍንን ከአጠገቤ አገኘሁትና «በውጊያ የተማረኩት ወታደሮች ወዴት ነው ያሉት» ስል ጠየቅኩት።ሻለቃ መስፍን በአግራሞት እየተመለከተኝ «የጨረስናቸው መስሎህ ነው የጠየቅኸኝ? አትስጋ እንደ መንግስት ከሚያደርገው በላይ ለሶስት ወር በእንክብካቤ ይዘን አቆይተናቸው ዓላማችንን በትክክል ካስተማርናቸው በኋላ የነበራቸውን ምርጫ ጠየቅናቸው። ወደቤተሰባቸው መቀላቀል የሚፈልጉ መሆናቸውን ሲነግሩን አስማረ አዋሽ ወስዶ በባቡር አሳፍሮ ወደ አዲስ አበባ ላካቸው። መንግስት ምን እንዳደረጋቸው የሰማነውም ሆነ የምናውቀው ነገር የለም። እንደዚሁ በወሬ ደረጃ ግን አንዳንዶቹ በሥለላና በቅኝት መልክ ወደኛ ተልከው መንገድ ደርሰው ቦታ ጠፋብን ብለው እንደተመለሱ አፋሮቹ ነግረውናል። ይህንን እንተውና ወደ ዋናው ጉዳይ እንግባ » አለኝና ትንሽ ሲያስብ ቆይቶ።

«አሁን አንተ በአፋጣኝ የተጠራህበት ምክንያት ችግር ስለገጠመን ነው። ችግሩ ቶሎ መፍትሄ የሚሰጠው ስለሆነ ነው እድትመጣ ያደረግሁት። ለአራት ወር ያህል እዚህ ተቀምጠናል።



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ከዚህ በኋላ የምንቀጥል አልመሰለኝም:: እንዳንቀጥል የወሰንበት ምክንያት አንዱና ዋናው የቀለብ ችግር ነው:: እስከ አሁንድረስ በነበሩት ጠራቶች ውስጥ አስማረ በየሁለትና ሶስት ቀን የራሱን ላምና በሬ እያረደልን ከቂጣና ሩዝ ጋር ቀቅለን እየበላን ነው ያሳለፍነው:: ከብቶቹን አርዶ በመጨረሱ ሁሉም ነገር እየተመናመነ ነው:: ከአስማረ ጋር እየተነጋገርንበት ያለው ነጥብ እኛን ሊረዳ የሚችል አካል በማፈላለጉ ላይ ነው:: ድጋፍ ሰጪ የሚሆን ረጂ አካል ማግኘት እንዳለብን በወይይት ውሳኔ ላይ ተደርሷል ለዚህም ድርጅትና ግለሰብ እናገኛለን የሚል እምነት አለን:: በአሁኑ ሰዓት የቡድን መሣሪያዎች በቀላሉ ይዞ ከቦታ ወደ ቦታ ለመንቀሳቀስ የሚያስችል ትጥቅ ያስፈልጋል::

በእኛ እጅ ላይ ያሉት መሣሪያዎች 81 ሚ .ሜ 82 ሚ .ሜ ሞርተርና ሄ ካሊበር የመሣሠሉት ሲሆኑ ከነዚህ መሣሪያዎች በተጨማሪ የመገናኛ ሬዲዮኖችን መጠቀም የግድ አስፈላጊ ነው::ሬድዮኖቹ ከምላ ጎደል በእጃችን የሚገኙ ቢሆኑም እንዚህን በትክክል ለመጠቀም ሙያተኞቹ የሉንም::በተለይም መገናኛዎቹን በተመለከተ የሰለጠነ ባለሙያ ካልሆነ በቀር ማንኛ ውም ሰው የሚጠቀምባቸው አይደሉም:: እነኚህን ባለሙያዎች ለማግኘትም ሆነ በስራ ላይ ለማዋል እኔ በነገርኩት መሰረት አስማረ ትሰራልኛለህ ብሎ እምነት የጣለብህ አንተን ነው:: እኔም ብሆን ትሰራለህ ብዬ ሙሉ እምነት እጥልብሃለሁ:: እንደአላፊነትም እንደግዳጅም ይህንን ስራ እንደምትሰራ ተስፋ አደርጋለሁ » አለኝና ትክ ብሎ ተመለከተኝ::

በርግጥም የተጣለብኝ አላፊነት ቀላል አልነበረም:: በሬዲዮ ኦፕሬተርነት በኩል የሰለጠነ የማውቀው ባለሙያ ወታደር ማሰላሰል ብጀምርም ለጊዜው በፍፁም አልመጣልህ አለኝ:: በዚያ ሰዓት እንደነዚህ ያሉ ባለሙያዎችን አስቦ ማግኘት እጅግ ከባድ ነበር:: ለብዙ ሰአት ቆየሁ:: ለግዜው በአእምሮዬ የመጣልኝ ሰው አልነበረም:: የሥራው ከባድነት ቢታየኝም በተስፋ መቁረጥ ውይይታችን እንዳይጀመር ስል ብቻ ከብዙ ዝምታ በኋላ

«እሞክራለሁ:: ለማንኛውም ግን በቅድሚያ በቂ ግዜ ማግኘት ያስፈልገኛል:: በሌላ በኩልም በቂ የግንኙነት መስመር መፈጠር አለበት » :: የሚል መልስ ሰጠሁት::



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

አንገቱን በዝግታ ሲያወዛውዝ ቆየና «ይኸ በሚገባ ታስቦበታል። ከአንኮበር እስከ ደብረብርሃን ያለው ስፍራ በመኪና ስለሚከናወን ችግር የለውም። ሌላው ቀለብን በማመለከት ያለው ችግር ሲሆን በአዋሽና በመተሃራ በኩል የተዘረጉ መስመሮች አሉ። ለዚሁ ጉዳይ አስማረ በቅርብ ወደ መተሃራ እንደሚሄድ ነግሮኛል።» በማለት መስፍን በዝርዝር ሊያስረዳኝ ሞከረ። ለቀረበልኝ አሳብ በሁሉም ነገር ላይ ፈቃደኛነቴን ለመግለፅ ያህል እራሴን ከፍና ዝቅ በማድረግ አወዛወዝሁ።

በዚያን ቀን ምሽት ሙሉ ሌሊት በስብሰባ ተወጥረን አድረን ጠዋት ቁርስ ከበላን በኋላ እንደገና ስብሰባው ቀኑን ሙሉ ቀጥሎ ዋለ። በሚቀጥለውም ቀን በተመሣሣይ ሁኔታ በስብሰባ ውዬ አደርኩ።በሶስተኛው ቀን ስብሰባችንን አጠናቀቅን ወደመጣሁበት እንድመለስ ተወሰነና እኔን የሚወስደኝ አፋር በሶስተኛው ቀን ይመጣል ተብሎ እየጠበቅሁ ቢሆንም አፋሩ እስከ አኩለ ቀን ድረስ ሳይመጣ በመቆየቱ በትስግስት ለመጠበቅ ተገደድሁ። ከአሁን አሁን ይመጣል እያልን ስንጠባበቅ ልክ ከቀኑ አስር ሰአት አካባቢ ድንገተኛ የሆነ ችግር ተፈጠረና አካባቢው በውጥረት ተናወጠ። ከነበርንበት ቅርብ እርቀት ላይ ቅልጥ ያለ ተኩስ ተከፈቶ ፀጥታ የነገሰበትን በርሃማ አካባቢ በድንገት የፈነዳው ጦርነት በመሳሪያ ጩኸት እና በባሩድ ሽታ ሲያፍነው ሙቀቱ በእጥፍ የጨመረ መሰለ። በዚህ ድንገተኛ ጦርነት ምክንያት የጉዞ መስመሬ ተቀየረና እንደ አንድ ተዋጊ ወታደር ሆኜ ክላሽ ተሰጠኝ። ከተወሰነ ጦርነት በኋላ ሁለት የመንግስት ወታደሮች ተገድለው አምስት እንደተማረኩ ተኩሱ ቆመና ለጊዜዉም ቢሆን አካባቢው የተረጋጋ መሰለ።

የጦርነቱ መቀስቀስ ምክንያት ወደ አካባቢው ለስለላ ከተላኩ የኢህአዲግ ወታደሮች ጋር አስማረ በድንገት በመገናኘቱ ነበር። ለቅኝት የተላኩት እነዚህ ወታደሮች አስማረ በነበረበት ስፍራ ደርሰው እሱ ቀድሞ ስላያቸው ተኩስ በመክፈት ሁለቱን ወታደሮች ይገድላቸዋል። በርከት ያሉት ሲሸሹ አምስቱ ግን ተማርከው ነበር። የቦታ ለውጥ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ የጉዞ መስመሬ ተቀይሮ ያን አካባቢ እንድንለቅ ተደረገ። ከዚህ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

በኋላ የተሰጠኝን ክላሽ ይገፍ ከነሱ ጋር ጉዞ ጀመርኩ፡፡ ከምሽቱ ሶስት ሰዓት ገደማ ሲሆን አንድ ቦታ ይዘን ለሊቱን በዚያው አሳልፈን ጠዋት ሲነጋጋ አካባቢ እኔን ይወስዳል የተባለው አፋር መምጣቱ ተነገረኝ፡፡ የኔ ከዚያ በፍጥነት መውጣት አስፈላጊ በመሆኑ ለሥራው ማንቀሳቀሻ የተወሰነ ብር አስማረ ከሰጠኝ በኋላ ለአፋሩ በአደራ አስረከበኝ፡፡ አደራ የተሰጠሁት አፋር ተከትዬ ከቀኑ አስር ሰአት ሲሆን አካባቢውን ለቅቀን ተንቀሳቀስን፡፡

ጭው ብሎ በተዘረጋው በርሃማ የዳሎል ክልል ስንጓዝ የነበረው እንደመልአክ ሰይፍ ሙቀቱ በሚወዘገዘገው ሙቀት ውስጥ ነበር፡፡ ትናንሽ አሸዋማ ቁጥቋጦዎችን እየጣስን ስንጓዝ ውለን አመሻሽ ላይ ከአፋሩ ቤት ደርሰን ከዚያው አደርንና ጠዋት አስራ ሁለት ሰአት ሲሆን ከመኝታችን ተነስተን ጉዞ ስንጀምር ሌሊቱን ከደጋው ዝናብ ዘንቦ አድሮ ኖሮ የአዋሽ ወንዝ ከአፍ እስከ ገደፉ ጢም ብሎ ሞልቶ አገኘነው፡፡ አፋሮች ዋናተኞች ስለሆኑ በዋና መሻገር ይችላሉ፡፡ እኔ ግን አዋሽን በግርማ ሞገሱ እንደዘንዶ ሲርመሰመስ ስመለከት ደነገጥሁ፡፡በኔ ችሎታ የማይሞከር ነበር፡፡የነበረችኝን ችሎታ ደብቄ ምንም ዋና የማልችል መሆኔን ለመንገድ መሪዬ ነገርኩት፡፡ አፋሩ አብሮን ከነበረው ሰው ጋር በአፋርኛ ተነጋገረና እኔን መለስ ብሎ እየተመለከተኝ «በጀርባው አዝሎ እንደሚያሻግርህ እየነገረኝ ነው፡፡ አይዞህ አትስጋ » አለኝ ሳቅ ብሎ፡፡

በዚህን ወቅት ነበር «አፋር ለወደደው ይሞታል» የሚባለው አባባል የታወሰኝ፡፡ አያይዞም «እንኳንስ የወዳጅ ወዳጅ ሆነህ ይቅርና እንደዚሁም ባንተዋወቅ ተቸግረህ ባይ አላልፍህም» የሚል አረፍተ ነገርበአስተርጓሚያችን በኩል አከለበት፡፡ እኔን በጀርባው አዝሎ ሊያሻግረኝ ሲዘጋጅ ሁለት አፋሮች በአየር የተሞላ አቁማዳ ይዘው ብቅ አሉ ይህ ደግሞ ጥሩ አጋጣሚ ነበር፡፡ አፋሩ ሁለቱን አቁማዳዎች አንድ ላይ በገመድ አቆራኝቶ አስረና ግራና ቀኝ በሁለቱ ብብቶቼ ስር እንዲይዛቸው ካሳየኝ በኋላ እንደዚህአለኝ፡፡

«ጀማሪ ዋናተኞች በተነፋ ባሉን እንደሚለማመዱት በሁለት እጅህ ብብት ስር አስገብተህ ያዝና በእግርህ ወንዙ ጠርዝ ውስጥ ግባ»



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

በአስተርጓሚው በኩል ይህ ሲነገረኝ ከደረቴ በላይ ሥልቻው ላይ በመተኛት በሁለት እጆቼ ብብት ውስጥ ሥልቻውን አስገብቼ ወደውሃው ጠጋ አልኩ። አፋሩ በእኔ ጀርባ ላይ ሆኖ ስልቻውን ይዞ እኔን እየገፍ ለመቅዘፍ ሲሞክር ሚዛኑን መጠበቅ አቃተውና እኔን ለቆ በሌላ አቅጣጫ ሲወድቅ ስልቻው ይዞኝ ፈትለክ አለ። ያለችኝን ትንሽ ችሎታ ተጠቅሜ በመቅዘፍ አቅጣጫዬን ለማስተንከል ተፍጨረጨርኩኝ።ያለ የሌለ ችሎታዬንና ሃይሌን በመጠቀም እራሴን ከአዋሽ ላንቃ ውስጥ ለማውጣት በሞት ሽረት ትግል ላይ እያለሁ አፋሩ እንደምንም እራሱን ተቆጣጥሮ በፍጥነት እየዋኘ የደረሰልኝ የመጨረሻ ተስፋዬን ለማሟጠጥ ትንሽ ሲቀረኝ እንደነበር አስታውስሃለሁ። በኔ ላይ ተደርቦ እየቀዘፈ ከ150 ሜትር በላይ ርዝመት ያለውን የአዋሽ ወንዝ በስንት ትግልና ድካም ነበር ሊያሻግረን የቻለው። በመጀመሪያ ወደ መልካወረር ተጉዘን መልካ ወረር ስንደርስ በመኪና ወደ አዋሽ ሄድን። ከአዋሽ ወደ መተሃራ ከተጓዝን በኋላ መተሃራ ስንደርስ ምሳችንን በዚያ በላን። በእለቱ አዲስ አበባ መግባት ስለነበረብኝ

« ከዚህ በኋላ እናንተ አታስፈልጉኝም ከተማ ከተማውን ለኔ ተውት » ስላቸው በሃሳቤ ተስማሙና

«መተሃራ ካለው ተወካያችን ጋር መተዋወቅ አለብህ። ሌላ ጊዜ ስትመጣ እነሱ ጋር አርፈህ ወደኛ መልዕክት ልከህ ነው የምንቀበልህ አንተን ከነሱ ጋር እንዳገናኝህ አስማረ ነግሮል።አብረን እንሂድና አስተዋወቀንህ ትሄዳለህ » አሉኝ።

ከሰዎቹ መተዋወቁ በብዙ መልኩ ሊጠቅመኝ እንደሚችል ስለተረዳሁ ሃሳባቸውን አልጠላሁትም ነበር። አፋሩ አያይዞም «ሌላ ጊዜ ስትመጣ እነሱ ጋር አርፈህ ወደእኛ መልክት ስትልክ መጥተን እንቀበልሃለን። አንተን ከሱ ጋር እንዳስተዋውቅህ አስማረ አደራ ስላለኝ የአስማረን አደራ መወጣት ስላለብኝ ነው የማስቸግርህ። ከሰዎቹ ካስተዋወቅኩህ በኋላ ወደ አዲስ አበባ ትሄዳለህ።» ብሎኝ ወደ ተባሉት የአስማረ ወዳጆች ዘንድ ጉዞ ጀመርን።አስማረ ወዳጆች ቤት ስንደርስ በትልቅ አክብሮት ነበር የተቀበሉን። ማንኛውም መስተንግዶ ከተደረገልን በኋላ ከሁሉም ጋር ትውውቅ አድርጌ 11 ሰዓት



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

አካባቢ ተሰናብቻቸው በአንድ የጭነት መኪና ተሳፈርኩና ወደናዝሬት ጉዞ ጀመርሁ። ናዝሬት አድሬ በማግስቱ አዲስ አበባ ጠዋትላይ አዲስ አበባ ገባሁና ምንም ሳላርፍ ጉዞ ጀመርሁ።ደብረብርሃን የገባሁት ከቀኑ በሰባት ሰአት ሲሆን ከአንድ ምግብ ቤት ምሳ በላሁና ወደ ካፌ ጎራ ብዬ ቡና እየጠጣሁ አካባቢውን በጥንቃቄ እከታተል ጀመር:: የፈጠነ አለዚያም ደግሞ ዝግ ያለ ነገር አልነበረም:: ደብረብርሃን እንደዛው እንደጥንቱ እያንቀላፋች ነበረች:: ከሰዓት በኋላ የደብረብርሃን ከተማን በስጋትና በጥርጣሬ አይን በመመልት ከቀበሌቀበሌ እየተዘዋወርሁ የመሽታ ቤቶችን ሳይቀር ጎበኘሁ:: ስለእኔ ቀርቶ ስለማንኛውም ነገር ወሬ የለም:: ምሽት ላይ ማረፊያ ይገፍ ከመተኛቴ በፊት በተሰጠኝ ግዳጅ መሠረት አባሎቼን ሰብስቤ ሥራዬን ለመቀጠል ምን ማድረግ እንዳለብኝ ሳስብ አመሸሁ:: በሁለተኛው ቀን ወደ መደበኛ የማስተባብር ሥራዬ ገብቼ አባላቱን ማወያየት ስጀምር ብዙዎቹ ነገሮች 'መስመራቸውን ይዘው በጥሩ ሁኔታ እየሄዱ ነበሩ::

በሬድዮ መገናኛ ሙያ የሰለጠኑና በኔ እዝ ስር አስመራ የነበሩ ሁለት የሬድዮ መገናኛ ባለሙያዎችንም አግኝቼ አነጋገርሁ:: ምስጢሩን ባልገልፅላቸውም ሰዎቹ የተጠየቁትን ለመስራት ፍቃደኞች ነበሩ::ይህ ከሆነ ከወር በኋላ ይመስለኛል የመስፍን ቤተሰቦች ያለማረጋጋት ውስጥ መሆናቸው ተነገረኝ:: ምን እንደተፈጠረ ለመጠየቅ ወደ ሻለቃ መስፍን ቤተሰቦች ዘንድ ስደርስ ሀዘን በተሞላበት ሁኔታ እያየችኝ

«መስፍን መጣኮ» አለች ታናሽ እህቱ::

«ማን? ምንድነው የምትይው? አልገባኝም » አልኩና ስጠይቃት

አንገቷን ወደ መሬት ደፍታ «መስፍን ማታመጥቷል እኮ » አለች ደገመችና::

የምሰማውን ብጠራጠርም እውነት ነበር«መጥቶ ቤትተኝቷል ነው የምትይኝ » ስል ጠየቅኳት «አዎን» አለኝ ቀና ብላ እየተመለከተችኝ::

«ምን ዓይነት ድፍረት ነው ይኸ የት ነው ያለው? "ስላት



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

«ከእኛ ቤት የሷ የተሻለ ነው ብለን ስላሰብን እዚያ ነው ያለው»አለችኝ እየተከዘች። ምን እንደተፈጠረ ባትነግረኝም አንድ ከባድ ችግር እንደደረሰ ግን ውስጤ ነግሮኝ ነበር።

በስሜት ብቻ እየተገፋሁ የማይሰማ በድን ሰውነቴን ተሸክሜ ወደ መስፍን እህት ቤት ገሰገስሁ። ከውጭ የተቀበለችኝ እህቱ ስለበረች እስዋም እንደእህትዋ ከፊቷ ላይ መልካም ነገር አለነበብኩም። ሰላም ብላኝ ተያይዘን ወደ ቤት ገባን። ሻለቃ መስፍን ከአንድ ጓዳ ውስጥ ተኝቷል። ትኩር ብዬ ከተመለከትኩት በኋላ «ጀግኖች አርበኝነቱ በድል ተጠናቀቀና ከተማ ተመለስክ ማለት ነው? » አልኩት። ከዚያም ፊቴ በቅሬታ እንደተዋጠ ዕጄን ዘረጋሁለት። እንደነገሩ ጨበጠኝ። ነጠላ ጫማውን ከእግሩ ለማስገባት እያስተካከለ ስመለከተው ሃሳቡን መጣሉ የበለጠ አናደደኝ እና ወደጠባቧ የመኝታ ቤቱ መስኮት ተጠግቼ በመቆም እመለከተው ጀመር።

ቀና ብሎ ተመልክቶኝ «ይልቅ ቁጭ በል። እንዴት እንደማገኝህ ሳሰላስል ነው የመጣኸው።» ገርበብ ብሎ በተከፈተው የመኝታ ቤቱ መስኮት ውጭውን አሻግሮ እየተመለከተ ትንሽ ሲያስብ ቆይቶ «ታስታውስ እንደሆን የመጣህ ጊዜ አንድነገር ነግሬህ ነበር» አለኝ።

«አስማረ ወደ መተሃራ ቀለብ ለማምጣት እንደሚሄድ ነግረኸኝ ነበር።»

«ልክ ነህ። ከሦስት ቀን በፊት ሁለት ጠባቂዎቹን ይዞ መተሃራ ይሄዳል። ከዚያ ሲደርስ ምን እንደተፈጠረ አላውቅም በመሃከል ላይ ሃሳቡን ይለውጥና ወደ ቀኝ ታጥፎ በከሰም በኩል በማቆራረጥ ሸሬ የምትባል የገጠር መንደር ይሄዳል። እኔ እንደሚመስለኝ ግን የመተሃራው ተወካይ በኢህአድግ እንደተገዛና መተሃራ ከተማ ውስጥ ተኩስ እንዳይከፈት ለማድረግ ወደዚህ እንዲሄድ መንገድ ላይ ያልሆነ ነገር ሰዎች እንዲነግሩት አድርጓል ባይ ነኝ። አስማረ አቅጣጫውን ቀይሮ ወደዚያ ከሄደ በኋላ ምሽት ላይ ተነስቶ መተሃራ ከተማ ይገባል። ስንቅ እናቀብልሃለን ያሉት የመተሃራ ተወካዩቹ ለማስመሰል በአንድ ፒካፕ መኪና ከፊት



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ለፊት ስንቅ ጭነው እሱን ወደ ቀጠሩት ስፍራ ሲመጡ በሌላ ፒካፕ ቶዮታ የኢህአድግ ወታደሮችን ከበስተኋላቸው በቅርብ እርቀት አስከትለው ይመጣሉ።

አስማረ በሁኔታው ተጠራጥሮ የተቃጠሩበትን ሥፍራ ቀይሮ እየጠበቃቸው ነበር። በመጀመሪያ ስንቅ የጫነው መኪና ያልፍና ወታደሮቹን የጫነው ላንድ ክሩዘር ቶዮታ መኪና ብቅ ይላል። አስማረን ይጠብቀናል ብለው የቀጠሩበት ቦታ እሩቅ ስለነበር ወታደሮቹ አገር አማን ብለው ተዘናግተው ነበር የሚጓዙት። ምንም ባልጠረጠሩት ወታደሮች ላይ ቀድሞ ተኩስ በመክፈት ብዙዎቹን ይገድላቸዋል። በከተማዋ ዳርቻ ደፍጦ የነበረ አንድ ብርጌድ ጦር ተኩስ ከፈተና ከአስማረ ጋር የነበሩት ሁለቱየእሱ አጃቢዎች ተገደሉ። አስማረን በተመለከተ ግን የተጨበጠ መረጃ አላገኘንም። ግማሹ ቆስሎ አምልጧል ሲል፣ ግማሹ ደግሞ የለም አልተመታም እየተታኮሰ ሸሽቶ አምልጧል ይላል።

የሆነው ሆኖ መጨረሻውን ያወቀ የለም። የኢህአድግ ወታደሮች ከወደቁት ሶስት ሰዎች መሀከል አንዱን አንገቱን ቆርጠውና ራዶ ሰዓቱን ጭምር አምጥተው የከተማውን ሕዝብ እንዲሰበሰብ ከአደረጉ በኃላ «አስማረን ገለነዋል። ከዚህ በኋላ ሁሉም ነገር አበቃ» ብለው ለህዝቡ አሳውቀዋል።የሞቱት ሦስቱም ባለሽሩባ ስለነበሩ እነሱ ለህዝብ ያሳዩት እራስ የአስማረ ስለመሆኑ በእርግጠኝነት መናገር አይችሉም። ሆኖም አስማረ ስለተከበበ ሊያመልጥ አይችልም ብሎ አንበሳዬ የተባለ የከተማው ነዋሪ መናገሩን እኔ ራሴ ሰምቻለሁ» አለኝ መስፍን።

እንደዚህ ያለውን መርዶ ስሰማ በጥይት የተመታሁ ያህል ደነገጥሁና የምናገረው ስለጠፋኝ ዝም ብዬ ስመለከተው ቆየሁ፡ከዚያም ትንሽ ሲያስብ ቆየና « ይህን ወሬ እንደሰማን በአስማረ ወንድምና የቅርብ ረዳቶቹ አማካኝነት ስብሰባ አድርገን ነበር። ያም ሆኖ አንድ መፍትሄ ላይ መድረስ አልቻልንም።ሁላችንም አንድ የምናውቀው ነገር አለ። አስማረ ከሌለ ያን ጦር ለአንድ ቀን እንኳ አመራር ሰጥቶ የሚያሳድር አንድም ነፍስ ያለው ሰው አልነበረም። አስማረ በሀብትም ሆነ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

በዲፕሎማሲው በኩል ምትክ የማይገኝለት ወሳኝ ሰው ነበር:: የትም ሄዶ ቢናገር ሰውን ያሳምናል:: አሁን ግን ሁሉም ነገር የለም::በዚያም ላይ ለጠሩ የሚላስ የሚቀመስ ነገር አልነበረም:: ሁሉም ከበረዶ በላይ ቀዝቅዞና ሞራሉ ወድቆ ነበር ስብሰባ ብለን የተቀመጥነው:: ስብሰባውን የመራው የአስማረ ወንድምሲሆን እኔንም ስለሁኔታው

«ምን ሃሳብ አለህ » ሲል ጠይቆኝም ነበር::አስማረ ከሌለ ምንም እንደሌለ ውስጤ ቀደሞም ያውቅ ስለነበር ከዚህ በኋላ እዚህ መቆየትና መቀጠል ምንም ተስፋ እንደሌለው ገልጬለት ሁላችንም በቡድን ተከፋፍለን ውጊያችንን እንቀጥላለን የሚል አስተያየት ሰጠሁት::ከዚያም ወደሌሎቹ አመራሮች እየተመለከትሁ እኔ የራሴን ሀይል ይዤ በዛሬው እለት ወደሌላ ቦታ መሄድ እፈልጋለሁ:: እናንተስ? አልኳቸው:: የሁሉም አስተሳሰብ ከኔ ጋር የተለየ አልነበረም:: አስማረ ከሌለ ምንም እንደሌለ ሁሉም ቀድሞ እንደገባው ተረዳሁ:: ሁሉም እንደአመጣጡናእንደቅርበቱ ወደሌላ አቅጣጫ እንደሚሄድ ገለፀና ስንብትና የመሣሪያ ክፍፍል አድርገን ተለያየን በቃ ይኸው ነው » አለኝ መስፍን::

ይህንን የመሰለና ክብረት አሎሎ የከበደ መርዶ ከጫንቀዬ ላይ ሲወድቅብኝ አንገቴን አቀርቅሬ ለብዙ ሰዓት ሳስብ ቆየሁና አዲስ አበባ ሄዶ የሆነውን ሁሉ ለፕሮፌሰሩ አስረድቶ ሌላ አማራጭ መፈለግ እንዳለበት ሃሳብ አቀረብኩለት:: በዚህ ዙሪያ ብዙ ከተወያየንበት በኋላ በማግስቱ ጠዋትአዲስ አበባ ለመሄድ ተነሳ:: ከዚያን ዕለት ጀምሮ እኔና መስፍን ለ6 ወር ያህል አልተገናኘንም:: ከምን እንደደረሰም የደረሰኝ ምንም መረጃ አልነበረኝም:: እህቱንም አየተመላለስሀጠይቂያት የሰጠችኝ መለስ ምንም የሰማችውም ሆነ የምታውቀው ነገር እንደሌለ ነበር::



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

# ምዕራፍ ስድስት

## መረጃ ሻምበሉ ተያዘ

መጋቢት 4 ቀን 1985 ዓ.ም ነው:: ደብረብርሃን ከተማ ውስጥ ሸንቅጥ ሆቴል ተብሎ በሚታወቀው ሰፍራ በአንዱ የመኝታ ክፍል ውስጥ የኔ አጐት የሆነውን ስለሺ ይልማን ጨምሮ በርካታ ሰዎች ካርታ እየተጫወትን ነን:: አንድ ወንድና አንዲት ሴት ወታደሮች መጥተው መኝታ ክፍሉ በራፍ ላይ በመቆም « ሻምበል ሚካኤል በለጠ ስለምንፈልግህ ወደውጭ ውጣ » ብለው ይጠሩኛል::

በዚህ ግዜ ካርታውን ወደ መሬት ወረወርኩና ተነሣሁ:: ምንም ምርጫ አልነበረኝም:: የተቀባበለ መሳሪያ ከፊት ለፊቴ ተወድሮብኛል:: ከግቢው እንደወጣን መታወቃቸውን አሳዩኝና

«ለጥያቄ ትፈለጋለህ ቀጥል» የሚል ቀጭን ትዕዛዝ በሴቷ ተሰጠኝ:: ዝም ብዬ ከመቀበል ውጭ አማራጭ ስለሌለኝ ቀደምሁ:: ወንድማማቾች ቡና ቤት ፊለፊት ወደሚገኘው የክ/ሰራዊቱ ዋና የጦር ካምፕ ወሰዱኝና ለዘበኛ በተዘጋጀች ጠባብ ክፍል ውስጥ አስገብተው ከውጭ ከዘጉብኝ በኋላ ምንም ሳይጠይቁኝ ትተውኝ ሄዱ:: ከዚያ በኋላ ቀኑን ሙሉ ተመልሰው ምንድነህ ብለው አልጠየቁኝም ነበር:: መዝጊያዋን ገንጥዬ ለመውጣትና ለመጥፋት ሞክሬም ምንም ሳይሳካልኝ ቀኑን ውዬና ለሊቱንም አድሬ በማግስቱ ጠዋት አንድ ሰአት አካባቢ ጠባሴ ወደሚገኘውና በቅዝቃዜ የሚታወቀው የጦር ካምፕ በወታደርታጅቤ ተወሰድኩ:: ለምን እንደታሰርኩ ውስጤ ያውቀው ስለነበር የሚጠብቀኝ ዱላ ከወዲሁ ምን እንደሚሆን በግልፅ ይታወቃል:: ይዘውኝ የሄዱት ከሰው መካከል ስለነበር እንደማይገድሉኝ ግን እርግጠኛ ነበርሁ::

ጠባሴ እንደደረስሁ ወደ ሦስት ሰዓት አካባቢ ላይ ቀለል ባለ መልኩ በአንድ የቀድሞ የደርግ ጦር መኮንን በነበረ ሰው ምርመራ ተጀመረ:: ስሙን የማላስታውሰው አንድ የቃኝ መኰንን



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

የነበረ ሰው ነው:: በ204 የአየር ወለድ ክ/ጦር በእኔው ዕዝ ሥር አስመራ የነበረ ወታደር ነበር:: ምርመራውን የጀመረው መኮንን በየት በኩል አቆራርጦ ኢህአዲግ ውስጥ እንደገባ አላውቅም:: የሳይኮሎጂ ምሁር በሚመስል መልኩ

«የአስማረ ዳኜ ጦር ተደምስሷል:: ጥቂቶቹም አብረውት ከእርሱ ጋር ተደምስሰዋል:: አንተ ግን ለጊዜው ከዚያ አልነበርክም:: ከዚህ መልምለህ የወሰድካቸው ሰዎችም አብረው እንደተደመሰሱ ሰምተሃል»አለኝና እኔ ከደብረብርሃን መልምዬ የወሰድኳቸውን ሰዎች ስም ዝርዝር ሳይቀር አንድ በአንድ እየዘረዘረ ያስረዳኝ ያዘ::

በዚያንግዜ የተረዳሁት ነገር ቢኖር በትክክል ይህ ሰው እኔን ከኔ በላይ እንደሚያውቀኝ ነበር:: ሆኖም የሚለኝን ሁሉ ከማመን ይልቅ መካድ ነበረብኝ:: እናም እንደምንም እራሴን አረጋግቼ መመለስ ጀመርሁ::

«በመጀመሪያ ደረጃ እኔ አስማረ ዳኜ የሚባል ሽፍታ አላውቅም:: መልምዬ ወደ ሽፍትነት የላኩትም ሰው የለም::የምትለው ሁሉ ለኔ ግልጽ ስላልሆነልኝ አልገባኝም » አልኩት::ቀዝቀዝ ባለ መልኩ ጥያቄውን የጀመረው መርማሪ መኮንን ብዙም ለውጥ በማይታይበት ሁኔታ«ሽመልስ የሚባለውን ሰው የላክኸው አንተ መሆንህንም ትክዳለህ » አለኝ ፊቱን ሳይሆን ጀርባውን እንደሰጠኝ::

«እኔ ሽመልስን ለአስማረ መልምዬ አላኩም:: ሽመልስን በእርግጥ አውቀዋለሁ:: ጐረቤቴ ነው:: እሱ እንደነገረኝ ከሆነ በተለያዩ ምክንያቶች በኢህአድግ ካድሬዎች ጫና ስለሚደረግብኝ መኖር አልቻልኩም:: ወደማልታወቅበት ቦታ ሄጄ በግብርና ተቀጥሬ ለመስራት ስለፈለግሁ የሚቀጥረኝ ወይንም በቀን ሠራተኝነት የሚያሠራኝ ፈልግልኝ » ብሎ ስላስጨነቀኝ ቡልጋ ወረዳ ለሚኖር የእናቴ ወንድም በግብርና ተቀጥሮ እርሻ እያረሰ እንዲቀመጥ በደሞዝ አስቀጥሬዋለሁ:: ወደመጨረሻ ላይ አጎቴ በላከልኝ ማስታወሻ ሽመልስ በራሱ ጊዜ ወጥቶ መጥፋቱን አሳውቆኛል:: ከዚያ በኋላ ከአስማረ ጦር ተቀላቅሎ ከሆነ የኔ ውሣኔ አይሆንም:: ተቸግሮ በመረዳቱ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

እኔን የሚያስጠይቀኝ ነገርም ይኖራል የሚል እምነት የለኝም። በራሱ ውሳኔ ለወሰደው የሽፍትነት እርምጃ እኔ ተጠያቂ ልሆን እችላለሁ እንዴ » ስለው

«አንተ ብትክድም በሌላ መልኩ የአይን ምስክሮች ማረጋገጫ ሰጥተውብሃል:: » አለኝ መርማሪው መኰንን::

አሁንም ጀርባውን ሰጥቶኝ እንደቆመ ነበር:: ከዚያም ፊቱን በድንገት እየመለሰ « እኔ ሽመልስን በቀጥታ ወስጄ ከአሥማረ ጋር አስገናኘሁትም እያልኩኝ ነው?»:: አለና የፌዝ ሳቅ ሳቀብኝ::

በዚህን ግዜ እልህ ተናነቀኝና «ያም ከሆነ ደግሞ የሠራሁት የቅብብሎሽ ሥራ ነው» አልኩት:: እራሱን በዝግታ እያወዛወዘና በእግሩ መሬቱን እየደቃ ቆይቶ እንደማንኮራፋት ከአለ በኃላ

«አንተ አስማረ ዳኜን ለመጐብኘት ስትሔድ ሽመልስን ከሱ እንዳገናኘህ ተረዳ:: በተጨማሪም ሻለቃ መስፍን ከተባለው ሰው ጋር ለብቻችሁ ብዙ ተነጋግራችሁ ስታበቁ በድጋሜ ከሽመልስ ጋር ተነጋግራችኋል»አለኝ::ትክክል ነበር:: ጥያቄና መልሱ መጨረሻው እንደማያምር ብረዳም ጥሩ መልስ ላለመመለስ ከውስጥ ወደ ውጭ ሲገፋኝ ይታወቀኝ ነበር::ሰውየው ቀጠለ::

«ትሰማኛለህ? ለሻለቃ መስፍን ታደሰ ይኸንን ሰውዬ አደራ ከማለትህም በላይ ሻለቃው የሚሠጠውን መመሪያ ተግባራዊ ማድረግ እንዳለበት ለሽመልስ ለብቻው ወስደህ ነግረኸዋል:: ለብቻችሁ ተነጋግራችሁ ነበር ያልኩህ ይህንን ነው » አለኝ::የጥያቄው አመጣጥ በጣም አደገኛ ስለነበረ ሁኔታውን ማለዘብ እና ማረጋጋት እንዳለብኝ ተገነዘብሁ።

«እኔ ሻለቃ መስፍንን ያገኘሁት መትሃራ ነው:: ሻለቃ መስፍን በጣም ጓደኛዬ ስለነገበር አሞኛልና ቶሎ ድረስልኝ ብሎ መልእክተኛ ልኮ ስለጠራኝ ነው መተሃራ ድረስ ልጠይቀው የሄድኩት:: መትሃራ ስደርስ መስፍንን አገኘሁት:: አብረን ውለን ማታ እዚያ ማደር እንደማልችል ነግሮኝ አስማረ ወዳለበት ይዞኝ ሄደ:: በመጨረሻም የአስማረ ጦር ከነበረበት ምሽግ ወሰደኝ::



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

በዚያን ቀን ከዚያ አድሬ በማግስቱ ተመለስኩ የጠራኝ በከፍተኛ ሁኔታ በወባ ተይዞ ስለታመመ ስለነበር መድሐኒት እንዳመጣለት ነበር:: መድሃኒት አደረስኩለት እንጂ አስማረንም ቢሆን በፊት አላውቀውም::»

የሰጠሁት መልስ ያናደደው ለመሆኑ ከፊቱ ላይ አነበብኩ:: ከዚያ በኋላ የደረሰብኝ ዝርዝሩ ብዙ ነው:: ለክብሬ ስል ግን መናገር አልፈልግም:: ብቻ አንድ ወር ያህል ጠባሴ ጦር ካምፕ ከታሰርኩ በኋላ ለደብረብርሃን ፖሊስ ጣቢያ ተላልፌ ተሰጠሁና ወደ ወህኒ ወረድሁ:: በድምሩ 31 ቀን ጦር ካምፕ ና ፖሊስ ጣቢያ 33 ቀን በደብረብርሃን ወህኒ ቤት ታስሬ በመጨረሻም ክስ ተመሥርቶብኝ ከስድስት ወር የእስር ቤት ስቃይ በኋላ ዋስ እንዳቀርብ በፍርድ ቤት ተፈቀደልኝ:: የሁለት ሺህ ብር ዋስ ጠርቼ ተፈታሁ::

ከዚህ በኋላ ነበር በኔ ላይ የሚደረገው ክትትል በእጥፍ እየጨመረ የመጣው:: ማነቆው እየጠበበ ሲመጣ እኔም በበኩሌ ወደጫካ የመግባቱን አለማዬን ከቀን ወደቀን እየጨመርሁ መጣሁ::



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

# ምዕራፍ ሰባት

## የመአህድ ምስጢር

1984 ዓ.ም በጥር ወር ላይ የተቋቋመው የመላው አማራ ህዝብ ድርጅት መዐህድ መሪዎች እንደሚሉት በአማራው ላይ ያገርበበውን የጥፋት ደመና ለመግፈፍ እና የእሳት አደጋ ሠራተኞችን ሥራ ለመስራት የተቋቋመ ይሁን ወይም ደግሞ ሌላ አላማ ኖሮት በርግጥ በትክል ይህ ነው ብዬ ለመናገር አልችም:: ለምን ብትሉኝ መአህድን ከመነሻው ጀምሮ አላውቀውም እና ነው:: ዘር ጉሳን የማይለይ በኢህአድግ የጉሳ ፖለቲካ ያልተጠለለ በአንድ ህዝብ በአንድ ሀገርና አንድ ባንዲራ የሚያምን ነው የሚለውን የላይ መርሁን ግን በትክክል አውቃለሁ:: እኔም ብሆን ወደመአህድ የተቀላቀልኩት በሰላም መንገድ አልነበረም::

የመላው አማራ ሕዝብ ድርጅት የምሥረታ ሀሳብ አቅራቢ መሥራች አባልም አይደለሁም:: ሲመሰረትም በቦታው አልነበርኩም:: እኔም ሆንኩ የኔ መሰሎች ሁላችንም ብንሆን በራሳችን መንገድ ገዞ ጀምረን መንገዱ ወጣ ገባና አስቸጋሪ ሆኖ ለመንዝ ሲያቅተን የግድ ድጋፍ ሲያስፈለረገን ነበር የተሻለውን አማራጭ ፍለጋ ወደ መአህድ የተጠጋነው:: መአህድ በሰላም መንገድ ለመንቀሳቀስ በሽግግር መንግስቱ እውቅና ተሰጥቶት ሲመሰረት ባልኖርም ውስጠ ምስጢሩን ግን በጥንቃቄ የተረዳሁ ነኝ ብዬ መናገር እችላለሁ::

የመላው አማራ ህዝብ ድርጅት መአህድ በእንቁ መሪው ፕሮፌሰር አስራት የተመሰረተው አማራው በገኘርዎች ስላቅና የለ «አሣይህ በለው» ትዕዛዝ በየቦታው እንደበግ እየታረደ የጅብ እራት በሚሆንበት ሰዓት እንደነበረ ትክክል ነው::በተለያዩ ምክንያቶች የሰላሙን በር እንደለቀቀ አንዳንድ መረጃዎች የሚጠቁሙ ሲሆን በተለይም ደግሞ የወቅቱ የሽግግር መንግስት ፕሬዘዳንት « አማራውን በውስጡ አልፈን ስለመጣን ችግሩን ተገንዝበንለት ስላለፍን ድርድት አያስፈልገው » ሲሉ የሽግግር መንግስቱ ጠቅላይ ሚኒስተር ታምራት ላይኔ በበኩሉ «አማራውን



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

እኔ ወክያለሁ» ብሎ ከተናገረ በኋላ ሱማሌ ክልል ሄዶ «ምንትስ» እያለ ሲሰድብህ የኖረውን እና ሊገዛህ የመጣውን ነፍጠኛ የመቀበያህ ወቅት አሁን ነው» የሚል ቀጭን ሰይጣናዊ ትእዛዝ መስጠቱም እውነት ነው። ለሺህ ዓመታት ለተሰራው ግፍና የአስተዳደር በደልም ብቸኛው ተጠያቂ አማራው ብቻ ነው ተብሎም ተፈርጇል። በዚህ ሁኔታ በተፈጠረው ያለመረጋጋት ብዙ አማርኛ ተናጋሪዎች በየቦታው ጭዳ እንዲሆንም ተደርገዋል። እኔ በነበረኝ መረጃና እስከማውቀው ድረስ ከዚህ በኋላ ነበር የመላው አማራ ሕዝብ ድርጅት በሰላማዊ መንገድ ተንቀሳቅሶ የአማራውን ችግር ለመፍታት እንደማይችልና ሃይልን እንደ አማራጭ ለመጠቀም የወሰነው። የጊዜውን መከፋት ተከትሎ አብ ዛኛው የጐሣ ፖለቲካ መሪ አማራን ማግደልና ማስገደል የፖለቲካ ዓላማው ግብና የጀግንነቱ መለኪያ አድርጎ ከመውሰዱም ሌላ ባህልና ትውፊቱን ማጥፋት ሞራሉን መግደልና አስተሳሰቡን መለወጥ ለጌቶቹ ታማኝነት መገለጫነት የተሰጠው የቤት ሥራ ሆኖ በስራ ላይ እንዲውልም ተደርጎ የታየበት የታሪክ አጋጣሚ ነበር ለማለት ይቻላል።

አንዳንዶች አስተያየት ሰጭዎች እንደሚያምኑበት ከሆነ የመላው አማራ ሕዝብ ድርጅት በፕሮፌሰር አሥራት የበላይ መሪነት መወከሉ በራሱ ስሙ ብቻ አንድ አስደንጋጭ ክስተት ስለነበረ የዓለማዎቹ ተጣይነት አጠራጣሪ ነበር የሚል ነው። አስተያየት ሰጭዎቹ ሲቀጥሉም በድርጅቱ ላይ የተመዘዘበት ሾተል ወደ አፎቱ እንዲመለስ ለማድረግ የሰላሙ መንገድ ብዙም አስተማማኝ አቅም አልነበረውም። ስለዚህ ፕሮፌሰሩ ሃይልን እንደ አማራጭ ለመጪለድ ተገደዱ ይላሉ።እነዚህ ችግሮች እንዳሉ ሆነው የሰሜን ሸዋ የመአህድ ተወካይ የነበረ አንድ ወጣት ቸርችል ጎዳና ከሚገኘው የመአህድ ዋና ጽሬት ቤት ሲወጣ የኢህአዴግ ደህንነቶች እግሩን በጥይት ቀልጥመው ይጥሉታል። ይህ ወጣት ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት አልዱአለም መላኩ የሚባል ሲሆን የሰሜን ግንባር አርበኞች ንቅናቄን የመሰረተ ነው። ወጣቱ ቁስሉን በህክምና ከዳነ በኋላ

«ከአሁን በኋላ ጫካ መግባት ይሻለኛል» ብሎ ለፕሮፌሰሩ ነገራቸው።አልተቃወሙትም።እንዲያውም«አይዞህ እኔ አለሁልህ። አንተ ብቻ በርታ እንጅ ሁሉም ነገር ይዘጋጃል » የሚል መልስ አገኘ።



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDF

«ሰላማዊ ትግል ብላችሁ አታስጨርሱን የሚል የአባላት ጥያቄ ከየአቅጣጫው ፕሮፌሰርን አስጨንቋቸው ስለነበር የአንዱ ዓለምን ጥያቄ አልጠሉትም። እንዲያውም እንደሰማሁት ከሆነ ወደመጨረሻ አካባቢ ይቀርብላቸው ለነበረው ጥያቄ ሁሉ የሚሰጡት መልስ « ላስጥላችሁ ስለማልችል ምርጫችሁን ከማክበር ውጭ አማራጭ የለኝም» ወደማለት ማመዘናቸውን ነበር። በዚህ ሁኔታ ሁሉም እራሱን የመከላከል ሥራ እንዲሰራ ቢስማሙም የድርጅቱን ዓላማና አመራሩን በማይጎዳ መልኩ ለማንቀሳቀስ ማንኛውም አካል የቻሉትን ያህል ለመርዳት ቃል ይገቡና ዘመቻው ቁርጥ ይሆናል። እኔ እደምገምተው ከሆነ በዚህ ወቅት ይመስለኛል ፕሮፌሰርና አስስማረ ዳኜ የተገናኙት። ይህንን ልገምት ያቻልኩትም ያለምክንያት አይደለም። አርባ ጉጉና በደኖ አካባቢ በደረሰው የሰው ህይወት ጥፋት እንጀታቸው ከፋኛ ተኮማትሮ እንደነበርና በመጨረሻም አንድ ያልታወቀ ሰው በወሰደው የበቀል እርምጃ መልሶ «ቸሰስ» ማለቱን እራሳቸው በአንደበታቸው ሲናገሩ እሰማ ስለነበር ነው።ይህንን ያደረገው አስማረ መሆኑ ግልፅ ነው። ሰውን ወዳድ እንደነበሩ የዛንም ያህል ሲበዛ እልኸኛና ቁጡ እንደነበሩ አምናለሁ። እንዲህ አይነቱን ጀግና አፈላልገዉ እንዳስጠጉትም ማመን ይቻላል።

እልሃቸው ከኢትዮጵያዊነት ባህሪያቸው የሚመነጭ እንጂ ከክፋት የወረሱት ነበር ለማለት አይቻልም። ጀግንነቱ ከዘር ሩህሩህነቱ ደግሞ ከራሳቸው ስብዕና የሚመነጭ ከሆነ ደግሞ የሚወዱት አማራ እንደዚህ እየተሰቃየ እያለና የድርጅታቸው አባላትና ልጆቻቸው እየሞቱ ቁርቶ በሊላም ቢሆን ከታሪክ አመጣጣቸው ስናይ መሳሪያን የሚጠሉ ሰው አይደለም። በሳቸው አነሳሽነት በሰው ህይወት ላይ ጥይት እንዲተኮስ ግን ስብዕናቸው የተገነባበት ህሊና ይፈቀድ ነበር ለማለት እና ለመደምደም ይከብደኛል። ጦርነት ምርጫቸው ነበር ብዬም አላስብም።

በርግጥ ዙሪያቸውን የከበባቸው ችግር እንደዚህ ያለውን ውሳኔ እንዲወስኑ አስገድዷቸው ሊሆን ይችላል።አንዱዓለም ይህንን የጦርነት አሳብ እንደልዩ አማራጭ ቢያቀርብላቸውም የሰሜን ሸዋ አርበኞች ምስረታ ግን የሳቸው ውሳኔ ስለመሆኑ ከእርግጠኝነት በላይ እርግጠኛ ሆኜ ለመናገር እችላለሁ። ከሳቸው



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ጋር እየተገናኘሁ መመሪያ ተቀብያለሁ:: በወቅቱ እምነታቸውን እንደተረዳሁት ከሆነ የአርበኞች ግንባር ንቅናቄን የአማራው ህዝብ የህይወት ዋስትና ነው ብለው ያምኑ ነበር:: የአርበኞች ግንባር የተመሰረተበትን ዝርዝር ፕላንም ከራሳቸው እጅ ተቀብያለሁ:: በመጨረሻም በወህኒ አብሬያቻው ታስሬ ስቃያቸውን በአይኔ አይቻለሁ:: ለህልፈተ ሞት ያበቃቸውንም ምክንያት በአንደበታቸው ከመነሻው እስከ መድረሻው ነግረውኛል እና ለኔ ሁሉም ነገር አዲስ አይደለም አልነበረም::ወደመነሻዬ ስመለስ ግን አንዱዓለም መላኩ ከፕሮፌሰር አሥራት ጋር መክሮ እንደጨረሰ ለዚህ ሥራ ተሰማሚ የሆኑትን ሰዎች ማፈላለግ ይጀምራል:: በዚህ ጊዜ የመጀመሪያው ሰው ሻለቃ መስፍን ታደሰ ነበር:: አንዱዓለም መላኩ ነፃነት ተገኝ ከሚባል ሰው ጋር በመሆን ከሻለቃ መስፍንና ከሌሎችም የፖርቲው አባላትና የተለያዩ የአካባቢው ተወላጅ ከሆኑት የጦር መኰንኖች ጋር ስለሽምቅ ውጊያው በሥፋት ይሞክራሉ:: የመከሩበት ወደ ዝርዝር ፕላን ከተቀየረ በኋ ለፕሮፌሰሩ ይስጥና አይተው ወደ ተግባር እንዲለወጥ ይነግሯቸዋል::

ኢህአድግ «ብሶት የወሰደኝ ነፃ አውጭ ነኝ» እንደሚለው ሁሉንም ሳይሆን ጥቂቶች የመአህድ አባላትንምብሶት ወለዳቸውና ባዶ እጃችንን ለጠላት ሰይፍ አንገታችንን ከምንሰጥ እኛም «ጠራኝ ዱሩ ጠራኝ ጫካው» ብለን እንግዲህ መጥተናል በማለት የተጣሩት የጦር ጥሪ እኔንም ተስማኝና ተቀላቀልሁ:: በሁለት ቦይ ጕን ለጕን ስንጓዝ የነበርን ሰዎች ሁላችንም በሥውር የአንድ ድርጅት አባል ሆነን ሊፈጀን የመጣውን ጠላት በጋራ ልንፋለም ቃል ተግባብተን የብዙ ሺህ የትግል ኪሎ ሜትር መንገድ አንድ ተብሎ በእኛ እርምጃ የተጀመረዉ ከዚህ በሁዋላ ነበር::ሄላችንም የተለያየ መንገድ ይዘን ስንጉዋዝ ያገናኘን መአህድ ነበር።

የትግሉ ሥልት በጠየቀው መስዋዕትነት ኢህአድግ ላይ ተጽዕኖ በማሣደር አማራውን ከጥፋት ማዳን ብቻ ሳይሆን በሀገር ላይ ያንዣበበውን የመነጣጠል ሥጋት ማስለወጥ እንደሚቻል የልባችን እምነት ነበር:: እናም ከፊቶ ለፊታችን እየመጣ ያለውን ጥቁር ሞት ለመቀበል ዝግጁ ስንሆን በሌላ በኩልም የህይወት ተስፋ ስንቅ አድርገን የነበረው የፕሮፌሰሩን የእምነት ቃል ነበር::



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

የመአህድ መሪ የእምነት ቃል የማይታጠፍ አቋም መሆኑን የተገነዘብን ሰዎች የተጣለብንን የአደራ ቃል እስከመጨረሻዋ ሰዓት ድረስ በትጋት ሠርተናል ብዬ አምናለሁ።

ይህ አሁን በሕይወት ያሉት አንዳንድ መአህድን የፈጠርን እኛ ነን የሚሉ ሰዎችን በጭራሽ የሚመለከት አይደለም። እነኚህ ግለሰቦች በዚህ መልኩ ታሪኩ እንዲነሳባቸውም አይፈልጉም። ይህ ታሪክ እንዲነሣባቸው የማይፈልጉበት ምክንያት ምናልባትም ምስጢሩ አልገባቸውም አለዚያም ደግሞ ሆንተብሎ የተደበቃቸው ስለሆነ አያውቁትም።ትክክለኛዉ እዉነታግን እንዱዓለም መላኩ ከሌሎች አባላት ጋር በመሆን በምንጃር ወደ ደራ ወረዳ አጥሬ ቆላ ውስጥ በመዉረድ ዋና ምሽጋቸውን ያደርጋሉ። እዛ ድረስ የሄዱበት ምክንያት ንቅናቄውን ከመላው አማራ ህዝብ ድርጅት የተለየ ሀይል ለማስመሰል ታስቦ ነበርየሚል እምነት ነበራቸዉ።

የመላው ኢትዮጵያ አርበኞች ንቅናቄ በሰሜን ሸዋ የሰሜንክንፍ አርበኞች ንቅናቄ የሚል መጠሪያ የተሰየመለት ቢሆንምበቀጥታ ይታዘዝ የነበረው ግን በፕሮፌሰር አስራት ነበር። ቤሌላ በኩልም በምዕራብ ሸዋ የሚንቀሳቀስ ሌላ ቡድንእንደነበረም አውቃለሁ። አጠቃይ እቅዱ ግን የአማራውን ክልል ያጠቃለለ ሲሆን በጐንደርና በጐጃም በነጀነራል ኃይሌ መለስ መአከልነት የሚመራውን ሃይል የሚያቅፍ ነበር።የሰሜን ሸዋ የመአህድ ተጠሪ የነበረው እንዱ ዓለም መላኩ እና የወታደራዊ ዘርፍ ኃላፊ የነበረው ሻለቃ መስፍን ታደሰ እንዲሁም የፖለቲካ ዘርፍ ሃላፊ የነበረው መኮንን ሁሉይፈር እኔም ሻምበል ሚካኤል በሰጠ አስተዳደርና ፋይናንስ ኃላፊ በመሆን ስራውን ስንጀምር ዋናው እቅድና መመሪያው ይወጣ የነበረው ግን ከመአህድ ቢሮ ነበር።ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት በኔ በኩል የነበረው ዋናው ሥራዬ የጐሬላ ሀይሉን የማደራጀት እና የመገናኘት መስመሩን ማመቻቸት ሳይሆን መረጃ ስራ ነበር። ለዚህ ስራ እኔ የተመረጥኩበት ምክንያት ደብብረብርሃን ከተማ ቀን በቀን ለመዘዋወር አንፃራዊ ነፀነት ስለነበረኝ ነው። በነበረኝ የረጅም ዓመት ልምድ የዘመቻ ዕቅዶችን ማዘጋጀትም ሆነ የድርጅቱን



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

መዋቅርና የሥራ ክፍፍሉን ማውጣት ለኔ በጣም ቀላል ነበር።

በጐሬላ ውጊያ ወቅት ቤንች ሳልሆን ግምባር ቀደም ተዋጊ (ተሰላፊ ነበርኩ) ካለፉት ድምሮቻችን በመማር ይህን ሃይል በተቻለ መጠን በዕቅድ የሚመራና ጠንካራ ድርጅታዊ መዋቅር እንዲኖረው ለማድረግ የመጀመሪያ ተግባራችን አድርገን ለመንቀሳቀስ ሁኔታን አንቆ ይዞን ብዙ ብንቸገርም ያለውን ጠባብ ሁኔታና ጊዜው የፈቀደውን ሥልት ሁሉ ለመጠቀም መወሰን የግድ ነበር:: ስለሆነም በጠንካራ ሞራልና መንፈስ ሥራውን በመጀመር የተሻለና አንፃራዊ ጠቀሜታ ያለውን የምንሻርና ወደራ ወረዳን በተለይም ተጉለትን የመጀመሪያ ምርጫችን አደረግን::

ድርጅታችን በዚህ ሁኔታ ከተዋቀረ በኋላ አካባቢውን በደንብ ጠንቅቆ የሚያውቅ አንድ በዛብህ የተባለ ሰው ስላገኘን እሱን እደምንም አግባብቱን ወደኛ እንዲገባ አደረግነው:: ይህ ሰው በዚያ አካባቢ ለነበረው እትስቃሴ ያበረከተልን አስተዋጽኦ ቀላል የሚባል አልነበረም::ለወታደራዊ እንቅስቃሴ ምቹ በሆኑ የተለያዩ ወረዳዎች ላይ ከ27-30 ታጣቂ ሀይል የተሰለፈ ሲሆን በአንድ ሰው እዝ ሥር እየሆንና የራሱን መንገድ ተከትሎ የመንቀሳቀስ ነፃነት ያለው ቡድን ነበር::

በይፋት አውራጃ ሌላ ሃይል የተሟሰረተ ሲሆን ይሄኛዉበወጣት ንጉሤ የሚመራ ነበር:: የግንኙነት መስመሩን በማስፋትም በምዕራብ እስከ መንዝ እና ግሽ በምስራቅ በኩልም ሰሜን ወሎ ድረስ እየሄደ ከኦሮሞዎችና ከአፍሮች ጋር ጥምር ግንኙነት እንዲፈጥር ተደረገ:: በዚህ መልኩ የተዘረጋው መዋቅራችን አጣይዬን ኢፍራትና ግድምን በማጠቃለል ወደ ወሎ ዘልቆ እዲገባ የግንኙነት መስመር ተዘረጋ:: ቀደም ሲል አቋርጠን በመጣናቸው ወረዳዎችም ጅሩና መረሀቤቴን የሚያንቀሳቅሱ ሃይሎች የተመደቡ ሲሆን የቀጥታ ግንኙነቱን በተመለከተ ግን አዲስ አበባ ከሚገኘው ማዕከል ትእዛዝ እንዲደርሰውና እንዲገናኝ ተደረገ:: እሱ ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ክልሎች ማንኛውም ትእዛዝ የሚደርሳቸው በዚሁ አዝ በኩል እንዲሆን ተደረገ::ተጉለትን በተመለከተም ዩሴፍ በተባለ የቀድሞ የአየር ወለድ ባልደረባ የሚመራ ጠንካራ ሀይል



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFC

ተደራጅቶ እሱም ተመሳሳይ እንቅስቃሴ ጀመረ:: ከሰሜን ሸዋ አማራ ክልል በኛ አደረጃጀት ውስጥ ያልተጠቃለለው እና የሰው ሃይል ያልተደራጀበት አንኮበር ወረዳ ጊናገርና በጥቅሉ ቡልጋ አካባቢ ብቻ ሲሆን ወደዚህ ቦታ መግባት ያልቻልንበት ዋንኛው ምክንያት እነዚህ ወረዳዎች በአስማረ ስር ስለነበሩ ነው::የሆነው ሆኖ በየቦታው እንዚህ አስኳሎች ይጣሉ እንጂ በመሣሪያና በገንዘብ ረገድ ሲታዩ እራሳቸውን ችለው ለመንቀሳቀስ ምንም አቅም አልነበራቸውም ለማለት ይቻል ነበር::

እነዚህ መጠነኛ ችግሮች እንዳሉ ሆነዉ የመአህድ ዋና መሪ ደግሞ የሰጡት የማያወላውል ትእዛዝ «ቅድሚያ ተግባር» የሚለው ስለነበር ሁሉንም ችግር ችለን አቅም የፈቀደውን መሞከር ነበረብን:: ስለሆነም ያለውን የሰው ሀይልና መጠን እንዲሁም ሊታጠቅ የሚገባውን የመሣሪያ ዓይነትና የግንኙነት መሣሪያ ቀልቡንና ተዛማጅ ወጭዎችን አጥንተን ሲፈጅ የሚችለው ጠቅላላ ጠቅላላ ወጪ ከግማሽ ሚሊዩን ብር የሚበልጥ ስለነበር በፍፁም የማይቀመስ አሳብ ነበር:: የማይቀር ሆነና አንዱዓለም ይህንን የወጭ ዝዝር አዲስ አበባ ወስዶ ለፕሮፌሰሩ እንዲያቀርብ ተወሰነ:: በወቅቱ አንዱዓለምን የጫነው መኪና ደብረብርሃን ሳያቆም በፍጥነት አቋርጦ እንደያልፍ ተደረገ:: አንዱአለም ያለምንም ችግር አዲስ አበባ ገብቶ መልእክቱን ያቀረበ ቢሆንም የተሰጠን መልስ ከጠበቅነው ውጭ በመሆኑም ሌላ አስደንጋጭም ነበር:: ከፕሮፌሰሩ የተሰጠን ትእዛዝ ቃል በቃል እንዲህ ይላል::

«ከሁሉ በፊት ሲያውቁት የሚገባው ይኸ ንቅናቄ እራሱን አሣውቆ በራሱ ጥረት ማደግ ያለበት መሆኑን ነው:: ስለዚህ እራሱን በራሱ ማሳደግ አለበት እንጂ አሁን ባለበት ደረጃ እንደ ድርጅት ታውቆና በጅት ተመድቦለት የሚንቀሳቀስ አይደለም:: እኛ ለመነሻ የሚሆናችሁን ለጊዜው ያለንን ሰጥተን ልከናል:: በዚህ ተጠቅማችሁ አንድ ነገር ማሳየት አለባችሁ:: እናንተ ከምታሳዩት እንቅስቃሴ ተነስተን ነው በሀገር ውስም ሆነ ለውጪ ወዳጆቻችን እና አጋሮቻችን አሳውቀን ከነሡ በምናገኘው ድጋፍ ንቅናቄውን የበለጠ ልናጠናክረውና ልናሳድገው



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

የምንችለው፡፡በዚህ ዕቅዳችሁ መሠረት ይህንን ገንዘብ ለመስጠት ብንወስን እንኳን ገንዘቡን ማኔጅ በማድረግ በተገቢው መንገድ ተጠቅማችሁ በሥራ ላይ ይውላል የሚል በቂ እምነት የለኝም፡፡ ይልቅስ አንድ ብልጭታ አሣዩ፡፡ የእስራኤል የጦር ጀነራሎች እኮ ጦራቸውን ከፊት ቀድመው እያዋጉ ነው በትንሽ መስዋዕትነት«ዘጠና ደቂቃ በኢቴቪ» የተባለውን እና ዓለም ሁል ግዜ የሚተርከውን ታሪክ የሰሩት፡፡ እናንተም እንዲህ መሆን አለባችሁ» የሚል ነበር፡፡ በመጣልን መመሪያ ላይ ብዙ ከተወያየንበት በኋላ አንዳንዶቹ ማድረግ አለብን ሲሉ እኔና ሻለቃ መስፍን ግን ሙሉ በሙሉ ሃሳቡን ተቃውመን፡፡ በተለይ ሻለቃ መስፍን እንደቅሬታ አንስቶት የነበረው ነጥብ በብዙ መንገድ ዋሽታችሁኛል፡፡ እኔን ወደዘዚህ ስታመጡኝ የተደራጀ ጦር አለን እሱን ምራልን ብላችሁ ነግራችሁኝ ነበር፡፡ በተግባር ሲታይ ግን እኔ ከምጠብቀው በታች ሆኖ ነው ያገኘሁት የሚል ነበር፡፡

በሁሉም መንገድ የተደራጀና የተሟላ ትጥቅና ስንቅ ያለው በቂ ጦር አለን ናና ምራልን ብላችሁ ካመጣችሁኝ በኋላ ግን ቃላችሁን የጠበቀ ነገር አላየሁም፡፡ አሁን ያለውን ሃይልም ቢሆን እናንተ አዘጋጅታችሁ የጠበቃችሁኝ ሳይሆን እኔ ከመጣሁ በኋላ ያደራጀሁት ነው፡፡ አሁን ደግሞ የአዲስ አበባው ቢሮ ቀጭን የጦርነት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡እንደዚህ ያለው ትእዛዝ በእኔ በኩል ተቀባይነት የለውም፡፡ይደረግ ከተባለ ግን ከጥቅሙ ይልቅ አደጋው የከፋ ነው የሚሆነው፡፡ በቂ ድርጅታዊ መዋቅር ሳይኖረን በቂ የግንኙነት መስመርና የዕዝ ሰንሰለት ሳንዘረጋ ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሶ ለማደራጀት በተዘጋጀ የሄድ ኳርተር ብቻ ተጠቅሞ ውጊያ እንጀምር ማለት ከወታደራዊ እሳቤ ውጪ ነው፡፡

ከዚህ በፊት አስማረ ዳኜ ዘንድ ሆኜ የገጠመኝን ዓይነት የመበተን አደጋ ልደግመው እንደማልፈልግ ልትገነዘቡልኝ ይገባል ፡፡ በሌላ በኩልም ቢሆን በአሁኑ ሰዓት ኢህአድግ ከአንድ ክ/ጦር በላይ ወታደራዊ ሀይል በሰሜን ሸዋ አከማችቷል፡፡ ይህ ሀይል ከማንም ላይ ከመተኰስ ወደ በኋላ እንደማይል መታወቅ አለበት፡፡ አስቀድመን ጦርነቱን መተንኰስ የተርብ እንጀራ እንደመንካት ይቆጠራል፡፡ መልሱ የከፋ መሆኑን ስለምረዳ በኔ በኩል



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

አላደርገውም። ለማድርሰው ጥፋትም በሆን ተጠያቂ መሆን እንደማፈልግ እንድትረዱልኝ እፈልጋለሁ» የሚል መልስ ሰጠ። እኔም ይህንኑ ሀሳብ አስፍቼ በማስረዳት በምንም ዓይነት መልኩ ወደ ወታደራዊ ትንኮሣ መግባት እደንደማይኖርብንና ያን ከአደረግን ግን ጋሪውን ከፈረሱ ማስቀደም እነደሆነ ለማሳሰብ ሞከርኩ። በዚህ መካከል ያሳዘነኝ አንዱአለም ነበር። ፊቱን ትኩር ብዬ ስመለከተው ሀዘን አይሎበታል። በሁለት ምጣድ መሀከል ሆኖ እሳት እንደሚነድበት ዳቦ እየተቃጠለ እደነበር ከፊቱ ላይ ያለው ረመጥ ይመሰክራል። ሲያደርገው የሚችለው አቅም ስላልነበረው አንዳንድ የገንዘብ ማግኛ ሀሳቦችን እያነሳ ለመጠቋቆም ሞከረ። ጭንቀቱ ስለገባኝ የሚለውን ሁሉ በጥሞና እደምጠው ጀመር። በርግጥም አንዱአለም መጨነቅ ነበረበት። ቤትና ንብረቱን ዳግም ላይመለስበት ተሰናብቶ ወጥቷል። እሱ የቱንም ያህል ቢደክምም ደስተኛ ስላልነበርን የቀረበውን ሃሳብ ሳንቀበለው ያለምንም መስማማት ለጊዜው ሁሉም ሃሳብ በእንጥልጥል እንዳለ ስብሰባችን ተበተነ። በማግስቱ ጠዋት ከመስፍን ጋር ተገናኝተን ፕሮፌሰር ላኩት ስለተባለው የጦርነት ትዛዝ ብዙ ተነጋገርንበት። እንደእውነቱ ከሆነ ትዛዙ ራሱ የፕሮፌሰሩ ስለመሆኑም እርግጠኞች አልነበርንም። ስለሆነም እንደገና ተሰብስበን ጉዳዩን ለማየት ተገደድን። ሃሰቡ ከእሳቸው የመጣ ቢሆንም እንኳን በእሩቅ አሻግሮ የሚያይ ሳይሆን ለፈተና የቀረበ ሊሆን ይችላል የሚል ድምዳሜ ላይ አደረሰን። ከዛም ይህንን ነገር ደጋግመን ካሰብንበት በኋላ « እንዳልከው የኛን አቅም ለመፈተን የመጣ ይመስለኛል » ሲል መለሰልኝ መስፍን።

ሃሳቡ በድጋሚ ለወይይት እንዲቀርብ ተደረገና ሁሉም አባላት ተሰባሰቡ። በድጋሚ በተደረገው ስብሰባ ላይም ቢሆን አንዱዓለም ከበፊቱ የተለየ አሳብ ይዞ ባለመቅረቡ « ወደዚህ ከመግባታችን በፊት ደጋግመህ እንድታስብበት እመክርሃለሁ » ሲል ሻለቃ መስፍን አስጠነቀቀው። ከሁለት ቀን ውይይት በኋላ ሁላችንም የተስማማንበት መሆኑን ሲረዳ የአንዱዓለም ፊት በደስታ ሲበራ ስመለከት እጅግ አድርጎ ነበር የገረመኝ። በወቅቱ በነበረን የመሳሪያ አቅም ላይ ውይይት ከተደረገ በኋላ በአለን መጠቀም እንደምንችል ከውሳኔ ላይ ተደረሰ። አንዱዓለም መላኩ እና መስፍን ታደሰ፣ መኮንን ሁሉይፈር ፣ እኔም ሚካኤል



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

በስጠና በባሰና ወቂና ወረዳ በወቅቱ የወረዳዉ ሊቀመንበር የነበረው ዳንኤል እነዚህ ሁሉ ሆነን የገንዘብ እና የመሣሪያ ማግኛ ታርጌቶችን ማጥናት እንዳለብን ተስማማን:: ይገኝበታል ተብሎ ለጥናት ከቀረበው ቦታ በሰላ ድንጋይ ከተማ የሚገኘው የወረዳ አስተዳደሩ የመሳሪያ ግምጃ ቤት ሲሆን ይህ ስፍራ በፖለቲካም ሆነ በመሳሪያ ትጥቁ በኩል ከቦታ አቀማመጡ ሲታይ የተሻለ ስለነበር የመጀመሪያ ምርጫችንን አደረግነው:: የመስሪያ ቤቶቹን አቀማመጥ በተመለከተም በአስተዳደሩ ግቢ ውስጥ የሚገኙት ፖሊስ ጣቢያው እና የመሳሪያ ግምጃ ቤቱ ሲሆኑ ራቅ ብሎ ደግሞ ወህኒ ቤቱና የገንዘብ ሚኒስቴሩ ይገኛል::

የገንዘብ ካዝናና ሌሎችም ምስጢራዊ ሠነዶች የሚቀመጡት በዚሁ ግቢ ውስጥ እንደሆነ በነበረን መረጃ ተረጋገጠ::ከምንም በላይ ደግሞ የወረዳ አስተዳዳሪው እና የፖሊስ አዛዡ ሁለቱ ግለሰቦች የአካባቢውን ህዝብ በማስቃየት የታወቁ ስለነበሩ ከዝርዝር ጥናቱ ውስጥ በመጀመሪያው ምዕራፍ የተያዘው እነሱን ማስወገድ ነበር:: እነዚህን ሰዎች አስወግደን በነዋሪው ዘንድ የኛን አለኝታነት በማረጋገጥ በህዝቡ በኩል ሙሉ ድጋፍን ሊያስገኝልን ይችላል ብለን አሰብን። ምክንያቱም ከመፈራት ይልቅ ተከብረን በነፃነት እንንቀሳቀሳለን የሚል ሙሉ ተስፋ ጫረብን:: በመንግስት ፖለቲካ በኩል ያለውን ተፅኖ በተመለከተም የወረዳ ዋና ከተማ በጉራላ ውጊያ ወረራ ተደርጎበት ከፍተኛ ጉዳትና ጥፋት ተፈፀመበት መባል ትልቅ ሽንፈት መሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ ነበር:: ታጥቆና ተደራጅቶ በህቡዕ የተደራጀ ሃይል መኖሩ በራሱ የወደቀውን የአማራውን ሞራል መልሶ ማንሳት እንደሚሆንም በዝርዝር ጥናቱ ላይ ተሰምሮበት ነበር::

ዝርዝር ጥናቱ በሙሉ ድጋፍ ከፀደቀ በኋላ የወታደራዊ መሰናዶ ሥራው የመስፍን ታደሰን አመራር ብልሃትና ብቃት የሚጠይቅ ሥራ ሆኖ ሙሉ ኃላፊነት ለሱ ተሰጠው::በሰላ ድንጋይ በዐደረግነው ወታደራዊ ጥናት የጠላት ተዋጊ ሀይልና የመከላከል ብቃትን፣የመረዳት ቻሎታውንና የመንቀሳቀስ አቅሙን



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ከምንም በላይ የሀይል መጠኑን፣ በአካባቢው ምን ያህል የሰፈረ ሰራዊት እንዳለ ትንትን አድርጐ ካስጠና በኋላ ዝርዝር የውጊያ ዕቅድን በተወሰኑ ቀናት ውስጥ አቀረበ:: የቀረበውን ዕቅድ በስፋት አይተን ከጨረስን በኋላ ያለምንም ተቃውሞ ሁሉንም እንዳለ አፀደቅነው:: ቀጥሎ ያለው የኛ የተዋጊ ሃይል መጠኑና ጥንካሬን መመርመር ሲሆን በወቅቱ እንዳየነው ከሆነ ብዙ ድክምት አልነበረም::

የሰው ሃይል ክፍተት ለመሙላት ሲባል ብቻ ከይፋት በኩል በወጣት ንጉሴና በሻለቃ ገዛኸኝ የሚመራው ጦር መጥቶ እንዲቀላቀለን ተደረገ:: ከመጡት በስም የማስታውሳቸው ዘገየ ሀ/ወልድንና ምህረት ዓለም የሚባሉትን ሲሆን አብዛኛዎቹ በጣም ትንንሽ ልጆች ነበሩ::ያም ሆኖ ግን ጠንካሮችና ልበ ሙሉ እንደነበሩ አስታውሳለሁ::እነዚህ ልጆች ከኔ ጋር እስከመጨረሻው ድረስ አብረው የታገሉ ሲሆን ሃይላችን ተደምስሶ በቁጥጥር ስር ከዋልን በኋላ የእስር ጊዜያችን አብረን አሳልፈን የወጣን ነበርን:: በተለያየ ቦታ የነበረው ጦራችን እንዲሰባሰብ ከተደረገ በኋላ የዘመቻ መጀመርያው ቀንና ሰዓት ዕቅድ ተይዞ ጦሩ በተጠንቀቅ እንዲጠባበቅ ተነገረው::



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

# ምዕራፍ ስምንት

## የሰላ ድንጋዩ ጦርነት

መጋቢት 12 ለ13 አጥቢያ 1986 ዓ.ም ከጉዶ በረት አካባቢ ከምሽቱ ሁለት ሰአት ተነስተን የመጀመሪያ እንቅስቃሴ በማድረግ ጠዋት 11 ሰዓት ሲሆን ከሰላ ድንጋይ ከተማ ከ2-3 ኪ.ሜ ርቀት ላይ በሚገኘውና በጣም ቆላማ በሆነው አካባቢ ከአንድ ገበሬ ቤት እንድናርፍ ተደረገ::

ቀኑን በዚያ ተኝተን ውለን ከምሽቱ አንድ ሰዓት አካባቢ ሲሆን ለጦራችን የዝግጅትና የጥንቃቄ መመሪያዎችን መስጠት ጀመርን:: በዚህ መልኩ እስከምሽቱ ሁለት ሰዓት ቆይተን ጦራችን የሰውነት እንቅስቂሴን እንዲያደርግ ረፍት ሰጠነው:: ከምሽቱ አራት ሰዓት ላይ በሻለቃ መስፍን አጠቃላይ የውጊያ ትዕዛዝ ማብራሪያ ተደርጎ ስለመሬት አቀማመጥና ስለጠላት ቦታ አያያዝ ሰፋ ያለ ግንዛቤ እንዲኖረው ለጦሩ አጥር ያለ ትምህርት ተሰጠው:: ቀጥሎም ያለውን የሰው ሃይል በሦስቱ ታርጌቶች ላይ በሚካተለው መልኩ ተከፋፍሎ እንዲመደብ የተደረገ ስሆን በወረዳው አስተዳዳሪ መኖርያ ቤት ላይ ጥቃት የሚሠነዝረው የሰው ሀይል ብዛት በቁጥር ሶስት ሲሆን ይመራ የነበረው በመኮንን ሁሉ ይፈር ነበር::

ሁለተኛው ምድብ በወረዳው የበአዴን ኃላፊን ቤት የሚያጠቃው ሲሆን በቁጥር ተመሳሳይ የሰው ሃይል አለው:: በወረዳው አስተዳደር ጽ/ቤት እና መሣሪያ ግምጃ ቤት እንዲሁም በእስር ቤቱ ላይ የተመደበው የሰው ሀይል በቁጥሩም በትጥቁም የተሻለ ሆኖ እስከ አስራ አምስት የሚደርስ በከባድ መሳሪያ የተደገፈ ሀይል ነበረው::አሰላለፉን በተመለከተም እንደቦታው አቀማመጥና እንደመግቢያና መውጫው ዝርዝር ጥናት መሰረት የመውጫና የመግቢያ መንገዶችን ሊዘጋ የሚችል በቁጥር ከሁለት ያልበለጠ ሃይል የደፈጣ ቦታውን እንዲረከብ ተደረገ::ወደውስጥ ዘልቆ የሚየጠቃውን የሰው ሃይል አሰላለፍ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

በተመለከተም እራሱ ሻለቃ መስፍን ታደሰ እና እኔም ሻምበል ሚካኤል በለጠ ፊት ለፊት ዋና የመግቢያ በሩንና በስተጀርባ ደግሞ በመ/አ ወንዳፍራሽ የሚመራ በሶስት የሰው ሃይል የተጠናከረ ሃይል ነበር::ከመሃል ከተማ ተነስቶ ወደ አስተዳደሩ ቢሮ ለመከላከል የሚመጣ ሃይል በድንገት የሚከሰት ቢሆን እሱን በአስበት እንዲቆም ለማድረግ በሻለቃ ገዛኸኝ የሚመራ አንድ ምድብ ተዘጋጀና የኋላ ደጀን በመሆን እንዲጠባበቅና እየተከላከለ እንዲያጠቃ ትእዛዝ የተሰጠው ከዚህ በተጨማሪም የተጣለበት አላፊነት ከግዳጅ በኋላ የማምለጫ ወይም የማፈግፈጊያ አቅጣጫን እንዳይዘጋ እንዲከላከልና በር እንዲያስከፍትነበር:: ሁሉም ነገር ከተጠናቀቀ በኋላ ለማረጋገጥ ሲባል የመጨረሻ ስም ጥሪ ተደርጎ ተዋጊ ሃይሉ በቦታው መኖሩ ተረጋገጠ::

የመነሻና የመደረሻ ጊዜና የውጊያ መክፈቻ ሰዓትና የግንኙነት ምልክቶችን፡ ከግዳጅ በኋላ የመሰብሰቢያ ወይንም የመገናኛ ቦታውን በተመለከተም በየትኛው አቅጣጫ ቢሆን እንደሚሻል ምርጫ ከተደረገ በኋላ የመገናኛ ምልክቶቹ ተነገሩቸው::ሁሉም የገባው መሆኑን በድምፅ ከአረጋገጠ በኋላ ምናልባትም ስጋት ናቸው ብለው የሚያምኑባቸው ነገሮች ካሉ ጥያቄ እንዲያነሡ ተጋብዘው የመሰላቸውን አሳተያት በማቅረብ ውይይትከተደረገበት በኋላ ለመንቀሳቀስ የመጨረሻው ትእዛዝ እስከሚሰጠው ድረስ የቀረችዉን የመጨረሻ ደቂቃጠሩ እየጠበቀ እንዲቆይ ተነገረው::



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

# ምዕራፍ ዘጠኝ

## የወረራው እቅድ ጥናት

መጋቢት 13 ለ14 አጥቢያ 1986 ዓ.ም ከምሽቱ ሶስት ሰዓት ሲሆን ቦታውን በዓይን ማየት በምንችልበት ሁኔታ ላይ ለመድረስ የወሰደብን የእግር ጉዞ ሰላሳ ደቂቃ ብቻ ነበር። የከተማዋ መግቢያ በር ላይ ስንደርስ ሁሉም ግዳጁን አውቆ እንዲንቀሳቀስ ለማድረግ ያህል ትውውቅ ተደረገና በመጀመሪያ ወደ አስተዳዳሪው ቤትና ቀጥሎም የብአዴን ተጠሪው ቤት ላይ አደጋ የሚጥለው ምድብ ቅድሚያ ተሰጠው። ይህ የተደረገበት ምክንያት ከነበርንበት ቦታ ተነስተ እዛ ለመድረስ የአስራ አምስት ደቂቃ ጉዞ ስለሚፈጅ ነበር።፡

ከዚያ ቀጥሎ አጋጅ ወይንም ዘጊው ምድብ ቦታ ቦታውን እንዳይዝ ተደገረ።በአስተዳደሩ መስሪያ ቤት ላይጨበጣ ሠንዛሪው ምድብ ከቦታው የተንቀሳቀሰው ከአስራ አምስት ደቂቃ በኋላ ሲሆን እንደደረሰም በሁለት ተከፈለና አንዱ በጀርባ ሌላው በፊለፊት በር ወደውስጥ ተጠጋ። ይህንን ምድብ እየመራን ያለነው እኔና ሻለቃ መስፍን ስንሆን በዋናው በር በኩል ወደ ውስጥ በመጠጋት ላይ እንዳለን ከውስጥ በኩል «ቁም!» የሚል ጩኸት ተሰማ።

ሻለቃ መስፍን « እጅህን ስጥ ተከበሀል »የሚል ትእዛዝ ቢሰጠውም ፖሊሱ ተኩስ ተኩስ በመክፈቱ ውጊያው ተጀመረ። ወደጠቅላላ ጦርነት በመግባታችንም በእኛ በኩል የነበረንን ከመትረየስ እስከ የእጅ ቦንብ እና ላውንቸር ተጠቅመን በፖሊሶቹ ላይ ከባድ ውጊያ ስለከፈትንባቸው ሃይላችንን ሊቋቋሙ አልቻሉም። የተከፈተው ተኩስ የተፋጠነ ስለነበር ፖሊሶቹ የተደመሰሱት በአጭር ሰአት ውጊያ ሲሆን አንዱ ፖሊስ ብቻ እየተታኮሰ ቆይቶ በመጨረሻ ላይ እሱም በቦምብ ተመታና ተኩሱ ሙሉ በሙሉ ፀጥ አለ። የጠዳደቁትን ሬሳዎች ተራምደን ወደ አስተዳደሩ ጽ/ቤት ዘልቀን በመግባት ዶክሜንቶችን በሙሉ አውጥተን ከበረበርናቸው በኋላ በእሳት ለኩሰን እንዲቃጠሉ አደረግናቸው።



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCom

ቀጥለን የገባነው ወደ መሣሪያ ግምጃ ቤቱ ሲሆን በመጋዘኑ ውስጥ ያሰብነውን ያህል መሳሪያ አላገኘንም ነበር። ገንዘብ ቤቱን በተመለከተ ግን ድካማችን ሁሉ ከህልም እንጀራ የተለየ አልነበረም። ለምን ቢባል ብሩ የነበረበት ካዝና መድፍ እንኳን ሊደፍረው የማይችል እጅግ ግዙፍ ከብረት የተሰራ በመሆኑ አይደለም ለመክፈት ለማንቀሳቀስም እንኳን የማይሞከር ነበር። ይሄንን ከአልሙኒየም የተሰራ ግዙፍ ካዝና ለትንሽ ግዜ ከተመለከትነው በኋላ ምንም እንደማይጠቅም ጥቁር አለት ድንጋይ የጎንዮሽ እያየን አልፈነው ግቢውን ለቅቀን ለመውጣት ተገደድን።

ስለ ብሩ አቀማመጥ የነበረን መረጃ በካዝና ውስጥ እንደ ሚቀመጥ ሳይሆን ከእንጨት ከተሰራ ሳጥን ውስጥ የሚጠራቀም መሆኑን ነበር።ምንም ይሁን ምን በመጨረሻ ላይ የወሰድነው ውሳኔ ትተን መሄድ ስለነበር ጥለን ወጣን።የግዳጁን መጠናቀቅ የሚያበስረው ፊሽካ በመስፍን ተሰማና የማፈግፈግ ስልት አደረግን።በሌላውም ምድብ የነበረው ጦር ወደተያዘለት የመሰብሰቢያ ወረዳ ቀድሞ የደረሰ ቢሆንም በአስተዳዳሪው እና በበአዴን ተጠሪው ቤት ላይ ጥቃት እንድፈፅም የታዘዘው ሃይል ገና ከፍተኛ የተኩስ ውርጅብኝ እያወረደ ስለነበር የቦንብ ፍንዳታ አላቆመም ነበር። ስለሆነም እነዚህ ሁለት ምድቦች የመጨረሻ ጥረታቸውን አድርገው እስኪመለሱ በአለንበተ ቦታ ተቀመጥን።

የወረዳው አስተዳደር ጽ/ቤት ላይ ለግዳጅ የተሠማራው ሀይል ግዳጁን ፈጽሞ ሙሉ ሀይሉን ይዞ ወደ ቀጠሮው ቦታ የደረሰው ከተያዘለት ግዜ ትንሽ ዘግይቶ ከተማዋን ለቅቀን ከወጣ በኋላ ነበር ከኋላችን ከፍተኛ የተኩስ ድምፅ ትንሿን ከተማ እያናጋት ያለው እራስን ለመከላከል አለዚያም ደግሞ ለማጥቃት የተከፈተ ሳይሆን ሁሉም በየደጁ ሆኖ ወደሰማይ የሚያጮኸው እንደነበር ወደ መጨረሻው ለመረዳት ችያለሁ፡ በዚህ መልኩ ለተወሰደው ግዳጅ ጦራችን የወሰደበት ጊዜ ሙሉ የአንድ ሰዓት ውጊያ ብቻ ነበር። የሞተ እና የቆሰለ ሀይል ለማጣራት በተደረገ ቁጥጥር በበአዴን ተጠሪው የመኖሪያ ቤት ላይ ጥቃት እንዲፈጽም ከተላከው ሀይል ውስጥ በተደረገ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

የተኩስ ልውውጥ አንድ ሰው በቦንብ ፍንጣሪ አንገቱ አካባቢ ቆስሎ ከመገኘቱ በቀር ሌላ የደረሰ ጉዳት ያለመኖሩ ተረጋገጠና የሁሉም ሰው የመጀመሪያው እፎይታ ተሰማ:: ከአራት ሰዓት የእግር ጉዞ በኋላ ከሰሲቱ አስር ሰአት ጉዶ በረት ከሚባል ስፍራ ደርሰን ከተዘጋጀልን የአንድ ገበሬ ቤት እንድናርፍ ተደረገ:: ለሁለት ሰዓት ያህል እረፍት አድርገን ከጠዋቱ አስራ ሁለት ሰዓት ሲሆን የግዳጅ አፈፃፀሙን ግምገማ ለ ማድረግ ስብሰባ ተቀመጥን:: ሁሉም ነገር ጥሩ ተብሎ ሊታሰፍ የሚችል የተሳካ ሚሽን እንደነበር ሁላችንም የተስማማንበት ውጤት ነበር ያገኘነዉ::

ለሰላሳደቂቃ ያህል በአደረግነው ውይይት የተገነዘብነውነገር ቢኖር እንደ መጀመሪያ ግዳጅ ሲታይ አጠቃላይ ውጤቱ በአሰላለፍ እንቅ ስቃሴው ክፋ የሚባል አልነበረም:: በፖለቲካ ጠቀሜታውም ቢሆን በጣም ከፍተኛ መሆኑ በወቅቱ የታመነበት ጉዳይ ነበር ለማለት ይቻላል:: በሌላ በኩል በወረዳ አስተዳዳሪው እና በብአዲኑ ተጠሪ ላይ የነበረው የማስወገድ ስራ የተሳካ ባይሆንም ሁለቱም ግለሰቦች ተመትተው ቆስለዋል ቤታቸውም በተደረገው የተኩስ ልውውጥ በቦንብ በመመታቱ ሙሉ በሙሉ ፈራርሶ ከጥቅም ውጪ ሆኗል:: የተወሰኑ ሰዎች የቆሰሉ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ አንደኛዋ የወረዳ አስተዳዳሪው ባለቤት ነበረች::

ይህቺ ሴት በተደረገው የተኩስ ልውውጥ በቦንብ ፍንጣሪ በመቁሰሏ አንድ ዓይኗ ሊጠፋ ችሏል:: አሳዛኝ ታሪኳ ይህ ብቻ ሳይሆን በወቅቱም የደረሰች ነፍሰጡር ነበረች:: ሴትየዋ እኛ በእስር ላይ እንዳለን ለምስክርነት በቀረበችበት ወቅት የአይኗን መጥፋት ለማየት ችያለሁ:: ያም ሆኖ በወቅቱ ስለነበረው ሁኔታ አቃቢ ህግ እንድታብራራ እና የምስክርነት ቃሏን እንድትሰጥ ሲጠይቃት የሰጠችው ቃል በሚከተለዉ ሁኔታ ነበር።

«ከነዚህ ሰዎች መሀከል እገሌ ነበር ብዬ ለማውጣት የአይን ብርሃን የለኝምና በሙሉ አላወቃቸውም» የሚል ነበር:: እንደዚህ ብላ ትመስክር እንጂ እሷ ግን ብዙ ታውቅ ነበር:: ይኸንን ያደረገችም ከፊት ለፊቷ በክብ ሳጥን ውስጥ ቆመው እየተመለከተቻቸው ነች:: ያለፈው አልፏልና ዳግም ላይመለስ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ከሌላ ጥላቻ ውስጥ እራሴን /አልከትም በማለት/ ይሁን ወይንም ደግሞ ተስፋ በመቁረጧ ሁሉንም ነገር ሆድ ይፍጀው ብላ ማንንም እንደማታውቅ የእምነት ቃሏን ስተሰጥ በጆሮዬ ሰምቼ በአይኔ ተመልክቻለሁ።

ያሰበችውን አስባ የምስክርነት ቃሏን በዚህ መልኩ ሰጥታ ስትወጣ ስመለከት ሀሊናዬ ክፉኛ ነበረ የተጎዳው። በዚህ የተበሳጨው አቃቤ ህጉ የለበሰውን ጥቁር ካባ እያወናጨፈ «ክቡር ፍርድ ቤት ህዝቡ ለመመስከር ፍላጎት የለውም። ተበዳዮቹ በበደሏቸው ሰዎች ላይ የእምነት ቃላቸውን የማይሰጡ ከሆነ እኔ ምን ላደርግ እችላለሁ?» የሚል ሀይለቃል ለፍ/ቤቱ በወቅቱ ከስነስርአት መናገሩን አስታውሳለሁ።የሰላ ድንጋይ ወረራችን በዚህ ትራጄዲና ኮሜዲ በሆነ አፈፃፀም ተጀመረና የፖለቲካው ጣጣ ባመጣው የመቢቃቀል አፀፋ ሰሜን ሸዋን ያምሰው ጀመር።

የግዳጅ አፈፃፀምና ውጤታችንን ገምግመን በውጤቱ በጣም የተደሰትን ብንሆንም የሚቀረው ቀጣይ ሂደት ለአዲስ አበባው ማዕከል ሪፖርት ማድረግ ስለነበር እሱን በተመለከተ አንድ ፅሁፍ አዘጋጅንና ላክን። ቀጥለንም በህዝብ ውስጥ የተፈጠረውን ስሜት ምን እንደሚመስል ለማጥናት ስንል የከተማ ዉስጥ ሪፖርት የማሰባሰብ ሥራ ጀመርን።

በወቅቱ እንደተረዳነው ተጓምር የወረደ ያህል አጀብ እየተባለና ወሬው በፍጥነት እየተናፈሰ የፖለቲካው አየር በጣም መሟሟቁን ሲሆን በቀርብ ቀናት ውስጥም ሰሜን ሸዋ ከኢህአዲግ ነፃ ትወጣለች የሚል ትንቢያ ቢጤ መወራትም ጀመረ ይህ ዜናም በመላውአገሪቱ መሰራጨቱን መረጃችን ቀልድ በታከለበት መልኩ ሲነግረን ለጊዜው ተሳስቀንም እንደነበር አስታውሳለሁ በሌላ በኩል ለአዲስ አበባዎቹ አለቆቻችን ሪፖርት ይዞ የሄደው መልእክተኛ «እኛ የምንለውም ሆነ የምንፈልገውም ይኸ ስለሆነ ቀጥሉበት»የሚል መልስ ይዞልን መጣ።በበጀት በኩል የነበረዉ አስተሳሰባቸዉ ግን ከበፊቱ የተለወጠ አልነበረም።



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

# ምዕራፍ አስር

## ሰላሳ ደቂቃ በደብረብርሃን

ለጦራችን የተወሰነ ጊዜ እረፍት ከሰጠን በኋላ ሌላ አዲስ የግዳጅ እቅድ ዝርዝር ነድፈን:: አዲሱ የወረራ እቅዳችን ያነጣጠረው በደብረብርሃን ከተማ ላይ ሲሆን ሁለት ወር ባልፈጀ ጊዜ ውስጥ የእቅዱ ፕላን ተጠናቀቀ:: የገንዘብ ጥያቄን በተመለከተ ከዋናው ቢሮ ያገኘነው መልስ አሁንም ቢሆን አጥጋቢ አልነበረም::

ወደኋላ የመመለሻ መስመራችን ከመጥበብ አልፎ የተዘጋም እንደሆን ጠንቀቀን ስላወቅን በገንዘብ ችግር ምክንያት የጀመርነውን ጥቃት ላለማቆም ቆርጠናል:: ያም ሆኖ እያለ ተስፋ ሙሉ በሙሉ ሊያስቆርጥ በማይችል መልኩ አጥጋቢ ባይባልም የተወሰነ የሚያስኬደን ገንዘብ ከዋናዉ ቢሮ በስንት ጥያቄ ተላከልን:: በተገኘው መጠነኛ ገንዘብ ምን እንደምንሰራበት ከተወያየን በኋላ ለአንዳንድ የመረጃ ስራ አውለን ደብረብርሃን ላይ የጀመርነውን ማሽን በተሳካ ሁኔታ ለመፈፀም ከስምምነት ላይ ደረስን::

የደብረብርሃን እስር ቤት የመጀመሪያው ሆኖ የተመረጠበት ዋናው ምክንያትም እንደነ ሻለቃ ወሰኔ አየለ ዝቁና ሌሎችም እኛ የምንፈልጋቸው ሰዎች በዚያ እስር ቤት ስለሚገኙ ነበር::ይህ ግዙፍ ወህኒ ቤት ከፖለቲካ ጠቀሜታው አንፃር ሲታይም ወደር የማይገኝለት ስምና ዝናን እንደሚያስጥ የተረጋገጠ ነበር::

የአንድ ክ/ጦር የዕዝ ሄድ ኳርተር በዚሁ ስለሚገኝ ይህንን ሃይል ለመድፈር በጥልቀት ከተመለከትን በኋላ የማይቻልበት ምክንያት የለም በማለት ከውሳኔ ላይ ደረስን:: የኢላማ /ታርጌት/ ሙሉ ጥናትና የመረጃ ሥራን በተመለከተም በኔ በሻምበል ሚካኤል በለጠ ላይ ተጣለ:: ይህ የተደረገበት ምክንያት ቀደም ሲል እንደገለጽኩት በደብረብርሃን ወህኒ ቤት ለ33ቀናት ታስሬ ስለነበር አጠቃላይ የወህኒ ቤቱ፣ኢቶማመኖ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ብቻ ሳይሆን ውስጠ ምስጢሩን እና የጥበቃ ዘዴውን ሳይቀር በትክክል አውቅ ስለነበር ነው።በሁሉም በኩል ሲታይ ይህንን እስር ቤት ለማጥናት ከእኔ የተሻለ መውጪያ መግቢያውን የሚያውቅ ሰው አልነበረም። እንደልብ መንቀሳቀስን በተመለከተም ወደ ደብረብርሃን ከተማ ገብቶ ሁኔታዎችን ለማጥናት ከማንም በላይ አንፀራዊ ነፃነት ያለኝ ነበርሁ ለማለት እችላለሁ። በመረጃ ስራውም ቢሆን ቀደም ሲል የጦር መኮንን በነበርኩበት ሰዓት በዘመቻ መኮንንነት የሠራሁ በመሆኑ ጥናቱን በትክክል መስራት እደምችል እራሴን ለራሴ እርግጠኛ ነበርሁ። እኔ ብቻ ሳልሆን አባሉም ቢሆን ሙሉ እምነቱን ጥሎብኝ ነበር።

ስለ ከተማው እውቀትና ከሰዎች ጋር ያለኝ ግንኙነት በጣም መልካም ስለነበረ ለዚህ ሥራ ተመራጭ ነበርኩ ለማለት እችላለሁ። የተሰጠኝን ከባድ ኃላፊነት በደስታ በመቀበል ለተገቢው ጥናት ወደ ደብረብርሃን ከተማ የተንዝኩት በሙሉ ፈቃደኝነት ነበር። በእቅዱ ፕላን ውስጥ ከተጠቃለሉት ዋና ዋና ነጥቦች የጠላት ሀይልና የውጊያ ብቃት የአፈጻጸም ችሎታ፣ የተነቃናቂነት መጠን እና ከምንም በላይ ደግሞ የመረጃ ችሎታውን የግንኙነት ድሩን ፣የውጊያ ሞራሉን የመሬት አቀማመጡን ሲሆን እነዚህን ሃሳቦች በመጀመሪያ በወረቀት ነደፍኩና ማጥናት ጀመሩሁ። እንቅስቃሴውን በተመለከተ በተገቢው ቁጥር ለራሴ ብቻ በሚገባኝ መልኩ ለሌሎች እንዳይገባ ውስብስብ ባለሁኔታ ዘረጋሁት።

በዚህ ዝብርቅርቅ ንድፍ ውስጥ ከተዋቀረው ሀይል ውስጥ በሁለት የተከፈለ መስመር ሲኖረው የመጀመሪያው መስመር የኢህዲግ ሰራዊትን አሰፋፈር በአንደኛ ደረጃ የፖሊስና የወታደራዊ ሀይል በሶስተኛ ደረጃ የተቀመጠው የከተከማ ታጣቂ ሀይል ሲሆን እነዚህ ሁሉ በምን አይነት መልኩ በቅንጅት እንደሚሰሩ በትክክል ማወቅና መረዳትነበረብኝ።ይኸንን በአምስት መልክ የተከፋፈለ እና በተለያየ ደረጃ የተቀመጠ ሀይል እንዴትና በማን ማስጠናት እንደአለብኝ ማሰብ ጀመርኩ። ከዚህያም በከተማ ውስጥ ያለው የቅድሚያ ጥናት እንደሚያስፈልገው ተረዳሀ ። ያም ቢሆን በዚህ በኩል የነበረው የጥናት መስመር የተወሰ ስለነበር በአንድ ሳምንት ውስጥ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ተጠናቀቀ:: ከመጠነኛ ጥናት እንደተረዳሁት በከተማው እንደልብ ተንቀሳቀስን ለመስራት ችግር እንደማገጥመን የሚጠቁም ፍንጭ መስጠቱን ነበር:: መረጃዎችን በመስራት ይረዱኛል በማለት ከመሃል ከተማ መ/አ ተስፋዬ ሀይሉንና መ/አ አሸናፊ በቀለየተባሉ ሁለት ሰዎችን መደብሁ:: ከነሱ በተጨማሪም ሁለት ሻለቆችን ተጨማሪ አድርጌ አዘጋጀሁ::

ከመለመልኳቸው ሰዎችጋር ሰፋ ያለ ውይይት ከአደረግንበት በኋላ ከጥር ወር 1984 ጀምሮ ወደጠቅላላ ስራችን ገብተን ሁኔታው ሲሞቅና ሲቀዘቅዝ እኛም እንደወቅቱ ሁኔታ እራሳችንን እየለዋወጥን በማንኛውም ህገወጥ ተግባር ላይ ሳንገኝ እርስ በራሳችን በመመካከር የተወሰኑ ጠራቶችን አሳለፍን:: በመንግስት የፀጥታ ሰራተኞች ክትትል ስር ስለነበርንም ራሳችንን ከሁሉም ነገር ቆጥበን መንቀሳቀስ እንደሚኖርብን ተረድተናል::

ለስራው መንቀሳቀሻ የሚደርግላቸውን ማንኛውንም ወጪ በዝርዝር ማቅረብ ያለባቸው ለኔ ብቻ እንደሚሆን ነገርኳቸው:: ስራቸውን በተመለከተ ግን የሚያጠኑትን የጠላት ሀይልና አጠቃላይ ሁኔታ ማወቅ እና ሪፖርት ማድረግ ሲሆን የሁሉም የስራ ክፍፍል መሆኑን በትክክል ተረድተው መስራት እንደሚኖረባቸው በትምህርት የተደገፈና ጠንከር ያለ መመሪያ የሰጠኋቸው ሲሆን 16ኛ እና 19ኛ ሻለቃን የማጥናቱን ስራ አጠቃይ ሁኔታዉን በተመለከተ በጥንቃቄ መስራት እንዳለባቸው መመሪያ ሰጥቼ ሳበቃ መ/አ ተስፋዬ ሀይሉና መ/አ አሸናፊ በቀለ የወህኒ ፖሊስን መጠንና ሃይል በሚከተለው መልክ እንዲያጠኑ ዝርዝር ፕላን ሰጠኋቸው::

በዝርዝር ሲተነተንም የወህኒ ቤቱን የጥበቃ ኃይሉን መጠንና የቦታ አያያዝ በከተማው ውስጥ ያለውን የፖሊስ ብዛትና በተለይም ደግሞ በከተማው ውስጥ በአሉት አራት ጣቢያዎች በእያንዳንዱ ጣቢያ ያለውን የሰው ሀይል መጠን በቁጥር እንዲገልፀ አደረግሁ::ኃይለ መስቀል ኬላ ቤት በመባል ከሚታወቀው አካባቢ ያለው የክፍለ ጦር ዋና መምሪያ በውስጡ ምን ያህል የሰው ሀይል መጠንና እንቅስቃሴ እንዳለው በትክክለኛ ቁጥር አጥንተው



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

እንዲያቀርቡልኝ ሙሉ ግዳጅ ባልኩባቸው:: የደብረብርን ወህኒ ቤትን በማጥናት በኩል ያንን ያህል የጎላ ችግር አልነበረም:: ለምን ቢባል እኔና መቶ አለቃ ተስፋዬ ሃይሉ ለብዙ ግዜ በውስጡ ታስረን ቆይተንበት ስለለነበር ማንኛውንም ምስጢር እንደራሳችን ጓዳ አጠቃላይ ይዘቱን እናውቀው ስለነበር ነው::

ከላይ በዝርዝር እደተቀመጠው ይህንን የመረጃ ሥራ እንዲሰሩ የተሰጣቸው የአንድ ሳምንት ጊዜ ብቻ ነበር:: በየእለቱ የሚገኘውን ከእኔ ጋር እየተገናኙ ሪፖርት እንዲያቀርቡ አደረግሁ::ሌሎችቴክኒኮችን በተመለከተ ግን የሁሉንም እንቅስቃሴ በቅርብ እየተከታተልሁ ክሮስ ቼክ ማድረግ የኔ ድርሻ ሲሆን በጠባሴ የሚገኙትን ሁለቱን የጦር ካንቦች ለማጥናት ሀላፊነት የተጣለባቸው መኮንኖች በቀጥታ የጦር ካምፕ ውስጥ ገብተው ያለውን የሰው ሀይልና የመሳሪያ አይነት አጥንተው ለማጠናቀቅ የተሰጣቸው ጊዜ ከነኚህኞቹ ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ከአንድ ሳምንት ባልበለጠ ቀናት ውስጥ አጠቃላይ ሪፖርት እንዲየቀርቡ አደረግሁ:: በከተማዉ ውስጥ በሆቴሎችና በመሸታ ቤቶች ሳይቀር መረጃ መሰብሰብ የሚችሉ ተጨማሪ ሰዎች የተዘጋጁ ሲሆን እነዚህ ግለሰቦች እንደማንኛውም ጠጪ እየሰከሩና እየረበሹ የሚፈልጉትን የመረጃ አይነት መሰብሰብ እንዳለባቸው በጥንቃቄ ተረድተዋል:: በአንደኛ ሻለቃ የነበረዉ የጥናት መስመር እንዲቀየር የተደረገ ሲሆን ጠቅላላ አሰራሩን ለመቀየር ያስፈለገበት ምክንያት አጠቃላይ ውስጡን የሚያውቅ ሰው ስላገኘን ነበር:: የተገኘው ሰው የመሳሪያ ጥገና እና የቀለብ ግምጃ ቤት አስተዳደርና ሂሳብ ሰራተኛ ሲሆን በእሱ አማካኝነት ጠቅላላ ሀይሉ ተለይቶና ተጣርቶ ዝርዝር ሪፖርቱ በትንሽ ሳምንታት ውስጥ ቀረበልን:: የጥናት ሪፖርቱ እንደሚጠቁመው የነዚህ ክፍሎች የውግያ ቴክኒካቸው ሳይቀር ከነስራ ባህሪያቸው በትክክል ተጠንቶና ቁልጭ ብሎ ነበር የመጣው::

የእዝ መዋቅሩን በተመለከተም በሰው ሃይል በኩል በየእለቱ ተለዋዋጭ በመሆኑ ሲያንስ ስንት እነደሚሆንና ሲበዛ ደግሞ ምን ያህል እንደሚጨምር በጥንቃቄ እንደገና ጥናት አድርጎ በአዲስ መልክ እንዲያቀርብ ለሰውየው ድጋሚ ትእዛዝ ተሰጠው:: ይህንን



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ያደረግኩበት ምክንያት ሥፍራው እንደጦር ማስተናገጃም ስለሚያገለግል በየእለቱ ከሰሜን ሸዋ የተለያዩ ወረዳዎች የተሰማራው የመንግስት ሀይል ከሁኔታዎች መለዋወጥ አንፃር የግዳጅ አፈፃፀሙ በትክክል መታወቅ ስለነበረነት ነበር:: ለሁለተኛ ጊዜ የመጣው ጥናትም ያመለከት የነበረው ከመጀመሪያው ጋር የተቀራረበ ሲሆን ለግዳጅ አፈፃፀም ከአንድ ቦታ ወደሌላ ቦታ ሲንቀሳቀስ ማረፊያው ይሄ ቦታ ነው ተብሎ ለመግለፅ አስቸጋሪ መሆኑን ነበር::

በየሀይል መጠን መለዋወጥ ስለሚያደርግም ያለውን ሀይል እርግጠኛ ሆኖ መናገር የማይቻል መሆኑ ተረጋገጠ:: እንዲህ አይነቱ የመረጃ ስራ ሲገጥም ከሁኔታዎች ጋር በየእለቱ የሚለዋወጥ ጥናት መስራት አስፈላጊ መሆኑን ስለተረዳሁ ተመሳሳይ ስራ ለመስራት ወደ አዲስ ለመቀየር ተገደድኩ::ጠባሴ 16ኛ ሻለቃ ተብሎ በሚጠራው ስፍራ ላይ ያለውን የጦር የአሰላለፍ ሁኔታ በተመለከተም የደረሰኝ መረጃ በሶስት የተከፈለ ሲሆን እሱም በመድፈኛነት ስልጥኖ የተቀመጠ አንድ በትረ ሻንበል ሀይል በታንከኛነት ስልጥኖ የተቀመጠ እና ሌላም ተጠባባቂ ሃይል እንደሚገኝበት የሚጠቁም ሲሆን መጠነኛ ቃኚዎች እና አሰልጣኞችም እንደሚገኙበት በቁጥር ጭምር ጥሬት ተብሎ ተሰርቶ የመጨረሻው የጥናት ሪፖርት ከእጄ ላይ ሊደርስ ቻለ::

የቀረበው መረጃ ሙሉ በሙሉ ትክክል ነው ተብሎ እምነት ባይጣልበትም እንደ መጀመሪያ ሪፖርት ሲታይ ግን ጥሩ ነበር ተብሎ ሊወስድ የሚችል ነበር:: ሪፖርቱ እንደሚጠቁመው አጠቃላይ የውጊያ ዝግጅትና የመንቀሳቀስ ችሎታው፣የእዝ አቀባበሉ የግንኙነት፣የውጊያ ዲሲፕሊንና የግል ዲሲፕሊን ሣይቀር ተጠንቶ የተጠናቀቀነበር የደረሰኝ:: በእነዚህ ሁለት ካንቦች ውስጥ ያለው ሀይል ተወርዋሪ ሆኖ ሌላውን ለማዳን ቀርቶ በራሱም ላይ ጥርት ቢፈፅም እራሱን የመከላከል የውጊያ ብቃት አልነበረውም:: አልፎ ተርፎም በአንድ ቦታ ላይ ረግቶ የመቀመጥ ሁኔታ አልነበረውም:: ጥናቱ ይህንን ያመለከት ስለነበር በጠንከረ የውጊያ ዲሲፕሊንና ግንኙነት ድር ተጠቀም በቀጭን



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ትእዛዝ የሚንቀሳቀስ ወታደራዊ ዝግጁነት ሥር ያልሆነ መሆኑን በትክል ለመገንዘብ ቻልኩ፡፡ የነበረውን ጠቅላላ ብቃት በተመለከተም በዚህ መልኩ ስለተረጋገጠ ስጋቱ በጣም ዝቅተኛ መሆኑ ለጊዜውም ቢሆን የታመነበት ጉዳይ ነበር፡፡ የተገኘው የመረጃ ጥንቅር እንደሚያሳየው በደብረብርሃን ከተማ ውስጥ ያለው የክፍለ ጦር ማዘገር ጣቢያ የመረጃ እና የዘመቻ መምሪያ ሲሆን በስ ስር ያሉ የግንኙነት ሰራተኛ መሆናቸው በትክክል ታወቀ፡፡ ቁጥራቸውን በተመለከተም ተጠንቶ የታወቀ ሲሆን ይህ ሀይል በብዛት ይሰራ የነበረውም በቢሮ ውስጥ ነበር፡፡

ስለሆነም ወታደራዊ ማዘገር ጣቢያውን ለቅቆ በመውጣት ሌላውን ለመርዳት መንቀሳቀስ የሚችል ሀይል እንዳልነበር ሪፖርቱ በትክክል ያሳይ ነበር፡፡በከተማው ውስጥ የነበሩት ሁለት ፖሊስ ጣቢያዎችን በተመለከተም የነበረው የሀይል መጠንና የከተማው ፖሊስ መጠን በዘጠኙም ቀበሌ ውስጥ ያለው የዘብ / የታጣቂ / በቁጥር ተጠንቶ መጣ፡፡ ከዚህ ውጪ የቀረው የፈረቃ ለአት መቀያየርና የመሳሪያ አይነት እንዲሁም የግንኙነት ዘዴ እና በወህኒ ቤቱ ውስጥ የሚገኘውን ጠቅላላ ገንዘብና መሳሪያ በተጨማሪም የሰነድ አቀማመጡን ጭምር ምን እንደሚመስል የሚገልፀው ሪፖርት በመጨረሻም ወህኒቤቶቹ የሚጠበቁበት የማማዎቹ ብዛትና አሰራር ወታደሮቹ የሚጠቀሙበት መሳሪያ አይነትና አቅም ሳይቀር የመጨረሻ ጥናት ተደርጎ ጠቅላላ ሪፖርቱ በእጄ ላይ ገባ፡፡

በየማማዎቹ ውስጥ የሚያድረው የሰው ሃይል ብዛትና በሌላ በኩልም የትኛው ማማ ሰው አልባ ሆኖ እንደሚያድር ጭምር የቀረበው ሪፖርት በዝርዝር ቁልጭ አድርጎ ያስረዳ ነበር፡፡ የቀረው ነገር ቢኖር ይህ ሁሉ ሀይል በምን አይነት ጥምረትና በምን ያህል የሰው ሀይል በየትኛው የቦታ አቀማመጥ በምን ዓይነት ሲስተም እየተጠቀመ ከተማዋን ይጠብቃል የሚለው ጥናት ነበር፡፡ እሱም እንደሶስተኛ ዙር ጥናት ሆኖ እንዲጠና ወስኜ እንደገና አዲስ ዝርዝር አወጣሁ፡፡ በዚህ በኩል የደረሰኝ ሪፖርት እደሚከተለው ሲሆን የማቃለያውንና ከኔ አለቃዎች ጋር ውሳኔ የሰጠንበት ነበር፡በከተማው የመኪናና የግረኞች መግቢያ በሮችበተለያዩ አምስት ቦታውች ላይ ያደፈጠ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ሀይል የሚያድር ሲሆን በሰው ሀይል ከ 3-5 ይደርስ ነበር። የዚህ ደፈጣ ሀይል ዋና እንቅስቃሴ ዋና ተግባሩ በድንገት የሚከሰቱ ችግሮችን ቀድሞ ለመረዳትና ከተማ ውስጥ የሚከሰተውን ድንገተኛ አደጋ ለመከላከል በከተማ ውስጥ ካለው ፖሊስጋር በጥምር ሆኖ የሚሰራ ነበር። ይንቀሳቀስ የነበረውም በሁለት ላንድ ክሩዘር ፒካፕ መኪናዎች መትረየስ እና ዙ ሃያ ሶስት ጠምዶ ሲሆን አንዱ ከፖሊስ አንዱ ከታጣቂዎች እንደየሁኔታው አንድም ሁለትም ሰዎች የያዘ የፓትሮል / ሮንድ/ የሚያደርግ ሀይል ነዉ።

19ኛ ሻለቃን በተመለከተ የቀረበው ሪፖርት እንደሚስረዳው፣ እስከ አስመራ በር ድረስ በመንቀሳቀስ ከተማዋን የሚሸፈን ሀይል እንዳለውና ሁሉም የጦር ክፍልና የፖሊስ ጣቢያዎችን ሳይቀር ከራሳቸው የጥበቃ ሰራተኞች ጋር በመሆን እርዳታ እንደሚሰጣቸው በዝርዝር ጥናቱ በትክክል ይታያል። ስለሆነም የደፈጣው የሰው ሀይል በአብዛኛው በየሰራዊቱ የሚከናወን ሲሆን በሰው ሀይል ረገድ ከ3 ወታደሮች የማይበልጡ መሆኑም በትክክል ታወቀ።

ከተጠኑት የደፈጣ ቦታዎች ለኛ አደገኛ የነበረው ሆንላስ ማርያም ቤተክርስቲያን በምትገኝበት በስተደቡብ ገብታ ሰፍራ ላይ ይመሽጋል የተባለው ሃይል ነበር፡ ይህ በደቡብ ጠርዝ አካባቢ ያደራል የተባለው የደፈጣ ሀይል ትኩረቱን የበለጠ እየሳበው የመጣ ሲሆን ዋናዉ ምክንያትም ሃይሉ እየሰፈረ ያድርበታል የተባለው ቦታ ወደ ወህኒ ቤቱ ለመጠጋት የሚያስችለን አጭርና ( ምቹ መቃረቢያ መንገድ) እሱ መሆኑን ቀደም ብሎ ስላጠናነው ነበር። ከጥናቱ እንደተረዳነው ሌሎች የመግቢያ መንገዶችን ብንጠቀም ግጭት ውስጥ ሊከተን እንደሚችል እርግጠኞች ነበርን።እሱን በተመለከተ አዲስ አቅድ አውጥቼ የጥናት ዝርዝር መስጠት እደሚኖርበረኝ ተረዳሁና ፕላን አውጥቼ ሰጠሁ። በአዲስ የተጀመረው ጥናት ሙሉ በሙሉ ተጠናቅቆ የደረሰኝ በጥቂት ቀናት ውስጥ ስሆን በዚህ ጥናት ውስጥም በሆንላስ ማርያም ኮረብታ ላይ መሽጎ ያድራል የተባለው ሃይል መጠን በትክክል ታወቀና ወደ ወህኒ ቤቱ ለመጠጋት በሆንላስ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ማርያም በኩል አቋርጠን ማለፍ እንደምንችል አረጋገጥኝ ሆንን:: ደፈጣው በየቀኑ አዚያ ላይ ወጥቶ ያድራል ወይ የሚለውን ለማረጋገጥ ሲባልም ቀለል ያለ የቅኝት ጥናት ለማድረግ ሲሳ ዝርዝር ጥናት ለመስራትም እኔ ራሴ ደፈጣ ያድርበታል ወደተባለው ቦታ በመሄድ ከዚያው ላይ አድሬ ለማረጋገጥ ወሰንኩ:: ሁኔታውን ለመ/አ ተስፋዬ ሀይሉ ነገርኩትና በተባለው ቦታ ሁለታችን አድረን የጥበቃ ሃይሉን በትክክል ማወቅ እንዳለብን ተስማማን::

መ/አ ተስፋዬ ሀይሉ አንድ ኦ.ዚ. ጠመንጃ እኔ ሽጉጥ በተጨማሪም ሁለታችንም ሁለት ሁለት ቦምብ ይዘን ለተከታታይ አምስት ቀን ከምሽቱ ሁለት ሰአት እስከ ሰባት ሰዓት ድረስ የቆየን ብንጠብቅም ቦታ ይዞ የሚያመሽ ሳይሆን ለተወሰኑ ሰአታት እየተዘዋወረ የቅኝት እንቅስቃሴ ከአደረገ በኋላ ተመልሶ የሚሄድ የተወሰነ ሃይል ነበር:: የቀረው ነገር ቢኖር የተገኘው መረጃ ከወታደራዊ ውጊያ አንፃር እንደ አማራጭ የውጊያ ዕቅድ አድርጎ ማቅረብ ነበር:: በደብረብርሃን ያለው የኢሕዲግ ሰራዊት እንደ አንድ ድርጅት ጥበቃ በክፍለ ጦር ዋና ዋና መምሪያዎች ውስጥ ያለ ሲሆን የጥገና፣የቅኝትና፣የከባድ መሳሪያ ምድብተኛ ኃይል የነበረ ነው:: ይህ ሀይል በተለያየ የሥራ ክፍፍል ላይ የተሰማራና ወጥ በሆነ አንድ ተዋጊ ሀይል ሥር ተደራጅቶ የሚታዘዝ ባለመሆኑ በድንገት የተፈጠረን ግጭት ፈጥኖ በመንቀሳቀስ ለማቆም የተዘጋጀ ነው ለማለት አይቻልም:: ሃይሉ በየንኡሳን ክፍል በተበጣጠሰ ሁኔታ በብዙ አለቆች የሚታዘዝ በመሆኑ ወጥ ትእዛዝ ከማንም አንተ ከሚባል ሀይል የሚቀበል አልነበረም::

ካለው የስራ ፀባይ አንፃር ሲታይ ቀን በቢሮ ውስጥ ሲሰራ ውሎ ማታ ሲመሽ ለመዝናናት ነፃነት ያለው በመሆኑ በካምፕ ውስጥ ብቻ ተወጥሮ ይቀመጣል የሚባልለት አይደለም:: ይህ ከሆነ ደግሞ በለሊት ውጊያ ቢፈጠር አንድ ላይ ተሰባስቦ ወደ ወታደራዊ ግዳጅ ከመሰማራት ይልቅ ባለበት ተደብቆ እራሱን ማዳን ያስቀድማል የሚል ንድፍ አሰፈርሁ:: በካምፕ ውስጥ የሚያድረውን ሀይል በተመለከተም ድንገት ጦርነት ቢቀሰቀስ በቢሮ ጥበቃና የራሱን የዕዝ ቦታ በመከላከል ላይ ያተኩራል እንጂ ፈጥኖ እርዳታ ለመስጠት ወደ ውጭ ይወጣል ተብሎ የማይታሰብ ነበር::



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

16ኛ ሻለቃ ውስጥ ያለው መድፍኛ ባትሪና ታንከኛ በተመለከተም ኪነታዊ ክፍል በመሆኑ ወደ እግረኛ ውጊያ ውስጥ ለማስገባት የተወሰነ ግዜ የሚወስድ ነበር:: ይሆናል ተብሎ ቢታሰብም እንኳን ከራሱ የካምፕ ጥበቃ አልፎ ለተወርዋሪነት ተግባር ለማሰማራት አጋጣሚ ካልሆነ በቀር ባአለው የአቅም ውስንነት እንደዚህ ለአለው ከባድ ግዳጅ ፈጥኖ ለመታዘዝ በፍፁም ዝግጁ አይደለም::ከአደረገም መሳሪያ ከምኛ ቤት አውጥቶ ታጥቆ አንድም በእግር አሊያም በመኪና ለመጓዝ ረጅም ሰዓት ይፈጅበታል ማለት ነው::ደብረብርሃን ከተማ የክ/ጦሩ ማዘገር ውስጥ ያለው ኃይል በተመለከተም በቁጥር የሚበዙት የቢሮ ሰራተኞችና ፀሀፊዎች በመሆናቸው የታጠቁት ሃይሎች ጥቂት ብቻ ናቸው::

ስለሆነም በውስጥ ያለው ትንሽ የታጠቀ ሃይል የራሱን የዕዝ ጣቢያ ከመጠበቅ ያለፈ ፋይዳ እንደማየኖረው የተረጋገጠ ነበር:: በከተማ ውስጥ ያለው የፖሊስ ሃይል እራሱን ከመጠበቅ ያለፈ ፋይዳ ይኖርል ወይ ተብሎ የሚታይ ነበር:: መልሱ አለው ተብሎ ከግምት የሚገባ አልነበረም:: በከተማ የሚንቀሳቀሰውን ታጣቂ ሃይል በተመለከተም ከጥናቱ እንደተረዳነው የነበረን ግምት ምናልባት ባለበት የግል ቤቱ ሆኖ ወደ ሰማይ ይተኩስ እንደሆነ እንጂ መደበኛ ሰራዊትን ተክቶ የመዋጋት ተልዕኮም ሆነ ወታደራዊ ልምዱ ስለሌለው ከግምት የሚገባ ትኩረት የሚሰጠው አይደለም ተብሎታለፈ::

በወህኒ ጥበቃ የተሰማራውን ፖሊስ በተመለከተም በሰላ ድንጋይ ከተማ ከደረሰው ጉዳት አንፃር ስንመለከተው ከመሸሽ ያለፈ ጠንክሮ የመዋጋት ሞራልም ሆነ ወኔው ሊኖረው ይችላል ተብሎ ስጋት የሚጥል አለመሆኑን አስምረንበት ነበር ያለፍነው:: ለመንቀሳቀስ አለዛም ደግሞ ለመከላከል ቢሞክር በቀላሉ አሸብሮ በቁጥጥር ስር ማዋል ስለሚቻል ውጊያው በጣም ቀላል በሆነ መንገድ ያለ ምንም ጉዳት እንደሚጠናቀቅና ከፍተኛ ድል እንደሚገኝም በዝርዝር ጥናቱ ዘጠና በመቶ የተረጋገጠ ሆነ::16ኛ እና 19ኛ ብርጌድ ውስጥ ያለው ሰራዊት ወደ ተወርዋሪ ሀይልነት ቢቀየር በምን ያህል የተነቃናቂነት ፍጥነት ተንቀሳቅሶ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

በየትኛው የመጠጊያ መንገድ ተጠቅሞ ወደ ኢላማው ይቃረባል የሚለውን ለማየት የቦታውን ርቀት በድጋሚ ለማይት አዲስ ፕላን ነደፍሁ:: የተገኘው ውጤት ሃይሉ በተከታታይ ዕዝ ሥር እንደመሆኑ ማስተባበርሩ ከተሳካለት ያለውን ሃይል በሁለት አቅጣጫ ከፍሎ ወደኛ መጠጋት ይችላል የሚል መጠነኛ ስጋት ያሳደረብኝ ሲሆን እንቅስቃሴውን በተመለከተም በሁለት አይነት ጉዞ የተከፈለ ነበር። አንድም በመኪና አልያም በእግር ይመጣል ለሚለው መልስ በእግር ከሆነ በደብረብርሃን ሱፍ ፋብሪካ በኩል አድርጎ በሬሳን ወንዝ አቋርጦ ወደ ወህኒ ቤቱ በሚያደርገው ረጅም መንገድ ከአንድ እስከ አንድ ተኩል ሰዓት ይወስድበታል:: በመኪና ከሆነ ደግሞ እስከ ሰላሳ ደቂቃ ሊፈጅ ይችላል:: ከ19ኛ ሻለቃ የሚነሳውን ሀይል በተመለከተም በመኪና እስከ 45 ደቂቃ በእግር ከሆነ ደግሞ ሁለት ሰአት ከ30 ደቂቃ ያህል ይወስድበታል የሚል ወታደራዊ ግመታ በንድፉ ላይ አሰፈርሁ::

የውጊያውን እቅድ በወረቀት ላይ በጥንቃቄ ነድፌ ከጨረስኩ በኋላ ከግምት ውስጥ መግባት ያለበትን ለይቼ ማውጣት ስለነበረብኝ እሱንም ለየሁ::ቀጥሎ የቀረው ትክክለኛ የሆነ የውጊያ ሰዓትን ለይቶ ማውጣት ሲሆን ከአካባቢው እንቅስቃሴ ጋር በማዛመድ ጥልቀት በተመላበት መልኩ ማጥናት ጀመርሁ::የዚህኛውን ጥናት በጥንቃቄ መመልከት ያስፈለገበት ዋንኛው ምክንያት የሲቪል ህብረተሰብ ህይወት እንዳያልፍ የሰራተኛ ከሥራ መውጪያና መግቢያ እንዲሁም የመዝናኛ ሰዓትን በትክል ማወቅና መረዳት ስለሚያስፈልግ ነበር::ጥናቱ ያሳየዉ የሰው እንቅስቃሴ የሚቆምበትና ሁሉም ነገር ፀጥና ረጭ የሚልበት ሰዓት ከምሽቱ አራት ሰዓት በኋላ መሆኑን ነበር::

የሱፍ ፋብሪካ ሰራተኛ የሥራ መለዋወጫ ወይንም የሽፍት መቀያየሪያ ሰዓትን በተመለከተ ባደረግነው መጠነኛ ጥናት በተገኘዉ ፍንጭ ከምሽቱ አራት ሰዓት ላይ መቀያየር እንደሚያበቃ ተረዳሁ:: የቀረው የመጨረሻው የኛ የውጊያ መጀመሪያ ሰዓት ነበር::እሱን በተመለከተም ኦፕሬሽኑ ለአምስት ሩብ ጉዳይ መጀመር እንዳለበት አረጋገጥሁ::



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ውጊያውን በታቀደለት የጊዜ ሰሌዳ ወይንም ሰዓት ለመጀመር ከክፍለጦት ስፍራ እስከ ግዳጁ ቦታ ያለውን እርቀት በጥንቃቄ ተመልክቶ ምን ያህል ሰዓት እንደሚፈጅ ተለይቶ መቀመጥ ነበረበት:: እኛ ካለንበት ከጊዜያዊ ማረፊያ ቦታችን እስከ ኢላማው የሚወስደውን ግዜ ገመትኩ:: ውጊያውን ለአምስት እሩብ ጉዳይ ለማስጀመር ከስፍራችን መነቃነቅ የነበረብን ለሶስት እሩብ ጉዳይ መሆን ነበረበት::

በየመግቢያ ቦታዎች ላይ ዘጊ ሀይል ብናስቀምጥ ጠላት እንዳይረዳ ለማድረግ ይቻላል የሚለውን ጥናት መልሼ ማየት ስለነበረብኝ እንደገና ንድፌን አየሁ:: ከዚያም በምን አይነት የውጊያ ዘዴ ብንጠቀም ነው የወህኒ ቤት ጥበቃውን ከውጊያ ውጭ አድርጎ እስረኞቹን ማስለቀቅ የሚቻለው? የሚለውን መልስ ለማግኘት የእቅድ ፕላኔን እንደገና በጥንቃቄ ተመለከትሁ:: ከዚያ በኋላ ነበር የወህኒ ቤቱን አጠቃላይ አቀማመጥ የሚያመለክት ቻርት መንደፍ እንደነበረብኝ የተረዳሁት::

ዉጊያዉ በተጀመረ ከሰላሳ እስከ አርባ ደቂቃ መጠናቀቅ ነበረበት::የመጠጊያ፣የማፈግፈጊያ፣ የመገናኛወይንም የመሰብሰቢያ ወረዳ የሚል ስም ሰጥቼ ለሁሉም ቦታ መረጥኩኝ:: አጠቃላይ ንድፌ ሃሳቡን በዚህ መልኩ ከከፋፈልሁ በኋላ የሰው ሀይል ፍላጎታችንን ለማሟላት ከየትኞቹ አስኳሎቻችን የተሸለ ተዋጊ ሃይል ማምጣት እንዳለብን እቅድ ያዝኩ:: እሱን ከጨረስኩ በኋላ እንደገና ወደኋላ ተመልሼ በየጦር ካምፕ ያለውን ሀይል ምን ዓይነት የውጊያ ዘዴ ብንጠቀም ድል ልናደርግ እንችላለን የሚል ሌላ አዲስ ጥናት ከውስጡ ወስጄ የሚከተለውን እቅድ አወጣሁ::በመጀመሪያ በወህኒ ቤቱ ላይ ጥቃት ለመሰንዘር አንድ የመቶ ጦር መትረየስ እና ላውንቸር ወይንም ባዙቃ መሳሪያ ያስፈልገዋል ከሚል ድምዳሜ ላይ ደረስሁ::በሌላ በኩልም የበሬሳ ወንዝን እቁርጦ የሚመጣውን ሃይል ለማስቆም አምስት ሰዎች መደብሁ::

በመኪና የሚመጣውን ሃይል ለማስቆምም አስፋልቱን በመትረየሥ እና በላውንቸር ለመምታት የተጠናከረ ሃይል መመደብ እንዳለበት አረጋገጥሁ::በምስራቅ በኩል ያለውን የእግር



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

መንገድ በተመለከተም ቀላል መሳሪያ የታጠቀ ሀይል በቂው መሆኑን በሚገባ አረጋገጥሁ። ከዚህ በተጨማሪ በደብረብርሃን ከተማ ውስጥ በአማካኝ ቦታ ላይ ያለው ተጠባባቂ ሃይላችን ጠባሴ የጦር ካምፕ ላይና ደብረብርሃን ፖሊስ ዋና መስሪያ ቤት ላይ የማስመሰስ ተኩስ እንዲከፈትና ለእርዳታ የሚመጣንማንኛውንም ሃይል በአለበት እንዲዘገይ እንዲያደርግ አስመረከብት። ይህ ሃይል በከባድ መሳሪያ ያለማቋረጥ ከተደበደበ ለእርዳታ መምጣቱ ይቀርና እራሱን ለመከላከል ይገደዳል።ከዚህ ጥቅል መንፈስ በመነሳት የሚበቃንን ሃይል እንዴት እናሰባስብ የሚለውን ጥያቄ እራሴ መመለስ ነበረብኝ።

ይህንን እያወጣሁና እያወረድሁ እያለሁ ነበር ዱሴፍ ጎሽ የተባለ አንድ ባዶ ቆላ ውስጥ የነበረ ሃይል ያስታወስኩት። በዘጠኝ የሰው ብዛት የተዋቀረና ሁለት ላውንቸርና ሁለት መትረየስ የታጠቀ በኔ አዝስርየነበረ ነበር። እሱ ከነሙሉ ትጥቁ እንዲመጣ ትእዛዝ እዲሰጠው አደረግሁ።በሌላ በኩል ደግሞ በንጉሴና ሻንበል ገዛኸኝ የሚመራውና ጠንካራ ነው ተብሎ የሚታመነው ሃይል ከሸዋ ሮቢት አካባቢ ያለዉሲሆንበአስቸኳይ ተንቀሳቅሶ ወደ ደብረብርሃን እንዲመጣ ተደረገ።መ/አ ብስራዬ ሃይሉና መ/አ አሸናፊ በቀለን በተመለከተም የራሳቸውን ጦር ይዘው ከአሉበት ስፍራ በአስቸኳይ እንዲመጡ ትዕዛዝ የተላለፈላቸው ሲሆን ከሰሜን ክንፍ የአርበኞች ንቅናቄ ዋና ማዕከል እስከ 30 የሚደርስ ከክላሽ እስከ ከባድ መሳሪያ ከተሟላ ጥይት ጋር ታጥቆ በተመደበለት ጊዜና ሰዓት መድረስ እንዳለበት ትዛዝ ተሰጠው። የዚህ ምድብ ዋንኛ ተግባሩ የወህኒ ቤቱን በሃይል ሰብሮ በመግባት እስረኞችን ነፃ ማውጣት ነበር። አመዳደቡን በተመለከተም ወህኒ ቤቱን ከደቡብ ወደ ሰሜን የሚያጠቃ አንድ ሃይል ከምእራብ ወደ ምስራቅ በዋናው በር የሚመጣውን ሃይል የሚመታና መንገዱን ካፀዳ በኋላ እስረኞቹን የሚያሳልፍ በላውንቸር የተጠናከረ ነው። በሰሜን በኩል ያለው የመላቀቂያ መንገዶችን የማያፀዳና የፀዱትንም እንዳይያዙ የሚጠብቅ ነበር።ከዋናው ክ/ጦር ማዘገየ ለድጋፍ የሚመጣውን ሀይል መቃረቢያ መንገዱ ላይ ሆኖ እንዲጠባበቅና የከባድ መሳሪያ አደጋ እንዲጥል የተመደበው ሃይል በመ/አ ምህረት አለም የሚመራ ሲሆን በሱፍ ፋብሪካ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ውስጥ አቋርጦ ከጠባሴ ለእርዳታ የሚመጣውን ጦር የሚያግድ አጋዥ ወይንም አዘግይ ሃይል ተብሎ የተቀመጠ ነው።በእግር ወይንም በመኪና ሆኖ የበሬሳን ወንዝ ተሻግሮ የሚመጣውን ሀይል የማመታ በመ/አ ተስፋዬ ሀይሉና በበዛብህ ዱሴፍ የተገነባ አንድ ጓድ T.TI በር ከፍ ብሎ ከሚገኘው መሬት በመትረየስና ላውንቸር ተጠናክሮ እንዲጠብቅ ተደረገ።በጠባሴ ጦር ሰፈር የማስመሰል ተኩስ የሚከፍተው ሌላው ምድብ የማስመሰል ተኩሱን የመክፈቻ ሰዓት የተነገረው ሲሆን አማራጭ ዕቅዱ በዝርዝር ታይቶ ለፍጻሜ ቀርቦ ያለምንም ተቃውሞና ማሻሻያ ወደ ተግባር ተላለፈ።የውጊያ አፈፃፀምና ከግዳጅ በኋላም የማፈግፈግን ስልት የሚመለከት ቻርት ሰርቼ ከወህኒ ቤቱ ፕላን ጋር በማያያዝ ሻለቃ መስፍን አስተላለፍኩለትና ከተመለከተ በኋላ ያለምንም ማሻሻያ ጥቅል ዕቅዱን አምኖበት ለአመራሮቹ እንዲያፀድቁት ለስብሰባ አቀረበ።እንዲዓለም መላኩ እቅዱን ከተመለከተ በኃላ ከእኛ ወታደራዊ አቅምና ችሎታ በላይ ስለነበር አይሳካም በሚል ጥርጣሬ ይመስላል ፍራቻ አድሮበት እንደነበር አስታውሳለሁ። የቀረበ ው ዝርዝር ጥናት ተቀባይነት አግኝቶ ፀደቀና ሻለቃ መስፍን ወደ ዝርዝር የውጊያ ትዕዛዝ እንዲለውጠው ተደረገ። በመጨረሻም የሰው አመዳደቡን አጥንቶ እንዲያሳውቅ ሀላፊነት ተሰጥቶት ዝርዝር ጥናቱን በሚያነብበት ሰዓት እንዱዓለም መላኩ ወደኔ እየተመለከተ

«ሚካኤል ሁላችንንም ወደዚህ ከባድ ግዳጅ ውስጥ ያመጣኸን አንተነህ። ይህ ዘመቻ ቢሳካ ተመስጋኝ ውድቀት ቢመጣም ተወቃሽና የታሪክ ተጠያቂም አንተ ትሆናለህ» አለኝ። ትኩር ብዬ ከተመለከትኩት በኋላ «ያለምንም ጥርጥር ይሳካል አትስጋ»አልኩና መለስኩለት። በርግጥም የተሳካ እንደሚሆን ምንም አልተጠራጠረም ነበር። በጠጣው ንድፈፕላን መሰረት በጥንቃቄ ከተሰራ ድል እንምናደርግ እርግጠኛ ነበርሁ። ትንሽ ስህተት ከተፈጠረ ግን ከፍተኛ ጉዳት ሊደርስ የማይችልበት አጋጣሚ ይኖራል ብዬ የማስብ አጉል ጀብደኛ አልነበርኩም።ስሆነም ነገሩ ዝግንን ስላለኝ «ይህንንስ የሰይጣን ጆሮ አይስማው»አልኩኚ። እያንዳንዱ ሰው ታሪክ ሰርቶ ለመሞት የነበረውን ወኔና



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ዝግጁነት ስመለከት ግን ድሉ የኛ እንደሚሆን እርግጠኛ ለመሆን ተቃርቤ ነበር:: እናም ሁሉም ነገር ጀሃነብ አልኩ በልቤ::በቀጣዩ ስብሰባ ሻለቃ መስፍን ታደሰ የውጊያ ዝርዝሩን አዘጋጅቶ ይዞ መጥቶ ለስብሰባው ያቀረበ ሲሆን የሰውን ሃይል አመዳደብ ዝርዝር በተመለከተ ያቀረበው ሃሳብ ያለንን የሰው ሀይል በግልፅ እንዲታወቅ ያደረገ ሲሆን በዚህ መሰረትም የውጊያው አፈፃፀም ስልትና የግንኙነት ዘዴ የማፈግፈጊያ ሰአትና የመገናኛ ቦታ ወይም ከግዳጁ በኋላ የመሰብሰቢያ ወረዳ እኔ ከነደፍኩት የተለወጠ አንድም አሳብ አልነበረም::

የውጊያ ትዕዛዝን በተመለከተም እኔ በሰራሁት over lay እየታገዘ ገለፃ ተደረገ::በዚህ መልኩ ወደተግባር የተቀየረው የውጊያው ክንውን በምንና እንዴት እንደሚጠናቀቅ ምን እንደሚመስል የግዳጅ አፈፃፀሙ ስልትና ቁርጠኝነት በትክክል ተመርምሮ ለጦራችን አጠር ያለ የማብራሪያ ትምህርት ተሰጠው:: እያንዳንዱ ሰው የተረዳው መሆኑ ከታወቀ በኋላም የምድቡ አባላት የሥም ዝርዝር ይፋ ሆኖ የተነገራቸው ሲሆን ምድብ አንድ በዋናው የማረሚያ ቤቱ በር ላይ ጨበጣ ተዋጊ ፣ ምድብ ሁለት ወህኒ ቤቱን ከደቡብ ወደ ሰሜን አጥቅቶ በአጭር ፍጥነት የወህኒ ቤቱን አጥር እየዘለለ በመግባት የወህኒ ቤቶቹን የእስረኛ ማዳራጃዎች በር በተዘጋጀው ዲጂኖና ብረት ሰባብሮ እስረኞቹን የማውጣት ስራ እንዲሰራ ተነገረው::

ምድብ አንድ የተከፈተው ዋናው የውጊያ አቅጣጫ በመሆኑ መስፍን ታደሰና እኔ ሚካኤል በለጠ አብረን ስንሆን ባዙቃን ወይንም ላውንቸር / RBGT / ከባድ መሳሪያ ታጣቂና ማማውንአፍራሽ ተብሎ ከነሙሉ መሳሪያዎቹ ተመደቡ:: በሁለተኛ ምድብ ጨበጣ ተዋጊ በመ/አ መኮንን ሁሉ ይፈርና በዳዊት ተገኝ የሚመራ ሲሆን እነኚህ ሰዎች የወህኒ ቤቱን ውስጠ ምስጢር ሳይቀር እንደ እጃቸው መዳፍ የሚያውቁና የሚያነቡ ደፋርና ጠንካራ ሰዎችም ነበሩ:: ሶስተኛው ምድብ በአንዱአለም መላኩናጠንካራው ተብሎ በሚጠራው ዳንኤል የተዋቀረ ሲሆን ከወህኒ ቤቱ በስተሰሜን አቅጣጫ በ150 ሜትር ርዕቀት ደፍጦ የጠላትን መምጫና መውጫ የሚከታተልና



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

የሚየጠቃ ነበር፡፡የበሬሳን ወንዝ በእግር አቋርጦ በሱፍ ፋብሪካ በኩል የሚመጣውን አጋዥ ሃይል የሚመታው ምድብ በመ/አ ምህረት ዓለም የሚመራ ሲሆን በስሩ አምስት ሰዎች የተመደበለት ነበር፡፡ ይህ ሃይል ከጠባሴ 19ኛ እና 16 ሻለቃ በመኪናም ሆነ በእግር ቢመጣ በሬሳ ድልድይ ላይ ዘግቶ የሚያቆም ነዉ። ከጎሹ ባዶ የመጣውን ሃይል በተመለከተም በመ/አ ተስፋዬ ኃይሉ የሚመራ ሃይል ሲሆን ከክፍለ ጦሩ መምሪያ ሊወረወር ይችላል ተብሎ የተገመተውን ሃይል በአለበት እንዲቆም ከማድረግ በተጨማሪ ከወህኒው ወደ ዋናው አስፋልት የሚሻገረውን መንገድ እንዲዘጋ ተደረገ፡፡ ትጥቅን በተመለከተም እያንዳንዱ ተዋጊ ሃይል በላውንቸርና በክላሽ ከነሙሉ ጥይቱ የተጠናከረ እንዲሆን ብዙ ተለፋበት፡፡

የ16ኛ ሻለቃ ጦር ካምፕና ደብረብርሃን ፖሊስ ዋና መምሪያ ላይ የማስመሰል ተኩስ የሚከፍት ጥቂት ሃይል ብቻ የተዘጋጀ ሆኖ የዚህ ሃይል ዋና ተግባሩ ፊት ለፊት ጦርነት መግጠም ሳይሆን ዋና ከተማዋን በተኩስ ማናወጥ እእደነበር ቀደም ሲል ጠቅሻለሁ፡፡ በመ/አ አሸናፊ በቀለ (አቡሽ) የሚመራው ሌላው ሃይል ሀንሳስ ማርያም ጉብታ ላይ ሆኖ የሱፍ ፋብሪካውን ወደ ምዕራብ በመተው በአርቶ ማሳያ መነፅር እየተጠቀመ የጠላት ሀይልን ተቆጣጥሮ በላውንቸር እንዲደበድብ ተመደበ፡፡ ይህ ሁሉ ከተጠናቀቀ በኋላ ሁሉም ግዳጁን በዝርዝር እንዲያውቅ ተነገረው፡፡

ሁሉም ነገር በዚህ መልኩ ተጠናቀቀና ሰያበቃ የመንገድ መሪነቱ ሃላፊነት በእኔ ላይ የተጣለ ስለነበር ጦሩን ሀንሳስማርያም ከአደረስሁ በኋላ እዚየ ጊዜያዊ የመሰብሰቢያ ወረዳ ሆኖ ከመሰብሰቢያ ወረዳው ሁሉም ወደየ ተመደበለት የማጥቂያ አቅጣጫ እንዲበታተን ከአደረግሁ በኋላ ከሁሉም ቀድሜ ታርጌቱ ቦታ በመድረስ ማማውን በላውንቸር መትቼ ድራሹን በማጥፋት ጦርነቱን ማስጀመር የኔ የስራ ድርሻ ነበር። ስለሆነም በትከሻዬ ላውንቸር መሸከም ነበረብኝ፡፡እነዚያን ማማዎች



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ለማጥፋት ምን አይነት ኢላማ መጠቀም እንደሚኖርብኝ በቅድሚያ ማሰላሰልና ማሰብ ጀመርሁ፡ይህ ብቻአይደለም። ውጊያውን ለማስጀመርም የላውንቸር ጥይት በከተማዋ እምብርት ሰማይና ጠባሴ የጦር ካምፕ አናት ማፈንዳትና ማሸበር እንዳለብኝ አውቃለሁ።

«ውጊያው አብቅቶ ግዳጅ ተፈፅሟል » የሚል ምልክት ለመስጠት የመጨረሻው የላውንቸር ጥይት ድምፅ ይሰማና ሁሉም ወደ ቀጠሮ ቦታ ወይም መሰብሰቢያ ወረዳ እንዲያፈግግ ይደረጋል።ይህም የኔ የመጨረሻ ግዳጅ ነበር።

ሁላችንም ግዳጆቻችንን በዚህመልክ የተቀበለን መሆናችንን ያረጋገጥን ሲሆን የወህኒ ቤቱን የእስረኛ በር ቁልፎች ለመስበር የሚያስችል ዲጂኖ ፣ሌባ ጎማ ፣መጥረቢያና ሌሎችም መሰል ቁሳቁሶችን የተሸከመ በቁጥር ሰባት ሰው ተመደበና መሳሪያዎቹ ተሰጡት።ተዋጊው ሀይል ወደ ደብረብርሃን ተጠግቶ ለሚሰፍርበት ሰወር ያለ ቦታ ጥናት የተሰጠው ለዳንኤል ስለነበር በተጣለበት ሃላፊነት አቶ ለማ ከሚባሉ ሰው ቤት ግዚያዊ መቆያ እንዲዘጋጅ ያመቻችሲሆን የአቶ ለማ ቤት የሚገኝበት ስፍራ ምከደብረብርሃን ከተማ ወደ አንኮበር በሚወስደው የመኪና መንገድ በቀኝ በኩል ወጣ ብሎ ከሚገኝ ገጠር መንደር ውስጥ ስለነበር ለጦራችን ጊዜያዊ ማረፊያነት ተስማሚ ነበር። የቀረው አዲስ አበባ ለሚገኘ ው ዋናው የእዝ ቢሮ ማስታወቅና የሚሰጠውን መልስ መጠባበቅ ነበር። አዲስ አበባ የተላከው የእቅድ ዝርዝር በውስጡ ማስጠንቀቂያ አይነት ሃሳብ ይዞ የመጣ። ሃሳቡ ቃል በቃል እንዲህ የሚል ነበር።

«በእስር ቤቱ ውስጥ ያሉትንም ሆነ በከተማው ኗሪ ሰላማዊ ህዝብ ላይ ምንም አይነት ጉዳት በማያስከትል መልኩ ተጀምሮ መጠናቀቅ አለበት። ያ ሳይሆን ቢቀርና ሰላማዊ ሰው ቢጎዳ የታሪክ ተጠያቂነት ሃላፊነቱን እንደምትወስዱ አውቃችሁ ደጋግማችሁ አስቡበት»



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

# ምዕራፍ አስራ አንድ

## ወህኒ ቤቱ ተሰበረ

ሚያዚያ 25 ቀን ለ 26 አጥቢያ ጀምበር ስታዘቀዝቅ ከነበረበት ጉዶ በረት አካባቢ ከምሽቱ ለሶስት እሩብ ጉዳይ ተንቀሳቀስን፡ ከብዙ ድካም በኋላ ከጠዋቱ 11:30 ሲሆን ከተዘጋጀልን ጊዜያዊ ማረፊያ ቦታ ለመግባት ቻልንና ቀኑን ተኝቶ እንዲያሳልፍ ለጠሩ ተነግሮት አዳራሹ ውስጥ አንዱ በአንዱ ላይ ተፋፍጎና ተደራርቦ እንዲተኛ ተደረገ።።ሚያዚያ 27 አጥቢያ ለሊት የውጊያው ቀን እንዲሆን ተወስኖ ስለነበር በእለቱ ለውጥ ሊኖር ይችላል በሚል ስጋት ሁለት ሰዎች ወደደብረብርሃን ገብተው የቅኝት ስለላ እንዲያደርጉ ብንልክም የተለወጠ አንድም ነገር እንዳልነበር ለማረጋገጥ ቻልን።።

ሚያዚያ 26 ለ 27 አጥቢያ ምሽት 4:40 የደብረብርሃን ወህኒ ቤትን ሰብረን እስረኞች የምናወጣበት ቁርጥ የፍልሚያ ቀን ሆኖ ከፊት ለፊታችን እየቀረበ መጥቶ ትንሽ ሽርፍራፊ ሰአቶች ብቻ ቀሩትና በሁላችንም ገፅ ላይ የለተለየ ስሜት መነበብ ጀመረ።። ከምሽቱ 3 ሰአት ሲሆን ካረፍንበት ቤት ወጥተን ወደ ደብረብርሃን መሃል ከተማ ተጠጋን።። ከሰባት ጥይት ጋር ላውንቸር ተሸክሚያለሁ።። ገዞው የተመጠነለት ሰዓት ስለነበር ከምሽቱ 4 ሰአት ሲሆን ሀንሳስ ማሪያም ሥር ደረስን።። ጥቂት ደቂቃ ቀደም በማለት የበሬሳን ወንዝ የሚዘጋውን ሀይልና በሱፍ ፋብሪካ በኩል የሚመደበውን አጋዥ ሀይል ቦታ አስይዘን ከጨረስን በኋላ ሌሎች ምድቦችንም ቦታ ቦታቸውን ለማስያዝ ጥድፊያ ጀመርን።። ከ15 ደቂቃ ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ሁላችንም የተመደበልንን ቦታ በትክክል መያዛችንን አረጋገጥን።።የከተማው የመሃል ዋና መንገድ አቋርጠን ወደ ወሀኒ ቤቱ አጥር ስር መጠጋታችንን እንዳረጋገጥሁ ለሻለቃ መስፍን የእስረኞች መጠበቂያ ማማውን ለመጠቆም ትክሻውን በእጁ ነካ አደረግኩና በአገልጩ በጨለማ ውስጥ ለብቻው ቀጥ ብሎ ሾሎ ወደሚታየው ሁለት ማማ አመለከትኩት።። በማማውና በኛ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

መካከል የነበረው ርቀት ከ30 እስከ 40 ሜትር ይሆን እንደነበር እገምታለሁ::ማማውን በላውንቸር መትቼ ለማፍረስ ዝግጁ ነኝ:: የውጊያው መጀመሪያ ነው::በጨለማው ውስጥ ወደ ሻለቃ መስፍን ዘወር አልኩ እና ተመለከትኩት::መስፍን ቆፍጠን ባለ ሁኔታ ትከሻዬን በያዛት ቀጭን ብትር ነካ አድርጎ

«ቀጥል ቶሎማማውን አፍርሰህ አሳየኝ»ሲል በጆሮዬ ላይበድንገት አንባረቀብኝ::እዎ የመጨረሻው ደቂቃ ሽርፍራፊ ያልቀረው:: ጥይት የጎረሰውን ላውንቸር በትከሻዬ ካደረግኩ በኋላ የውጊያ ማስጀመሪያ ፊሽካ ሲነፋ መውጊያውን ወደ ታች ረግጬ አቆምኩትና መልሼ ለቀቅኩት:ፍንዳታው ከፍተኛ ድምፅ እሰምቶ እየተምዘገዘገ ሄደና ማማውን ወገቡ ላይ በመምታት ለሁለት ገምሶ ሲጥለው ሌላ ከፍተኛ ፍንዳታ አሰማና ከተማዋን የብርሃን ርችት ረጭቶባት አለፈ::

ላውንቸሩ ከፈጠረው ከባድ ፍንዳታ የተነሳ የኤሌክትሪክ መስመርም አብሮ ተቆረጠና የፍዳታው ብርሃን መጥፋቱን ተከትሎ ከተማዋን ጥቁር ጨለማ ዋጣት:: ደብረብርሃን ፀጥታዋ ተናጋና በየቦታው የጥይትና የዉሾች ድምፅ ያምሳት ጀመር:: ከጥይት ጩኸት በስተቀር በሌላ ምድብ ምን እየተሰራ እንደነበር የምሰማውም ሆነ የማውቀው ነገር አልነበረም:: የማውቀው ነገር ቢኖር የስራ ድርሻዬን እየተወጣሁ መሆኔን ብቻ ነው:: አሁን ትእዛዝ ሰጭ ሳልሆን ትእዛዝ ተግባሪ ነኝ::

ማማው ውስጥ የነበረው አንድ የጥበቃ ፖሊስ በላውንቸሩ ወላፈን ከማማው ላይ ተወርውሮ መሬት እንደወደቀ በጨለማ ውስጥ በግምት ይታየኝ ነበር:: በየአቅጣጫው የነበሩ ፖሊሶች የተወሰነ የተኩስ ድምፅ ያሰሙ ቢሆንም ብዙ ባለመግፋታቸው እና በመጨረሻ ላይ የኛ ሃይል እያየለባቸው ስለመጣ ሮጠው ለማምለጥ ወዲህና ወዲያ በመሯሯጥ ላይ እንዳለ አንድ ፖሊስ ብቻ ዋናውን በር ከፍቶ ወደኛ መገስገስ ጀመረ::ፖሊሱን ለማስቆምና እጁን እንዲሰጥ ለማድረግ መስፍን ደጋግሞ «ቁም!» የሚል ትዕዛዝ ቢሰጠውም እምቢ ብሎ በመጠጋቱ ብዙም



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ሳይርቅ በጥይት ተመትቶ ወደቀ:: ወደ ውስጥ ዘልቀን ለመግባት የሚቋቋመን ሀይል አልነበረም:: ወህኒ ቤቱን ከደቡብ ወደ ሰሜን የሚያጠቃው ሀይል አጥሩን ዘሎ ለመግባት ሲታገል ከሌላ ማማ ላይ ተኩስ ስለተከፈተበት ሁለተኛውን የላውንቸር ጥይት በዚህ ማማ ላይ ስደግመው እሱም ወዲያው ከማማው ወረደ:: የማማጠዉም ድራሽ ጠፋ

በቦንብና በቀላል መሳሪያ እየታገዝን ወደ ውስጥ ዘልቀን በመግባት የወህኒ ቤቱን ግቢ ሙሉ በሙሉ በቁጥጥራችን ስር አደረግን:: ወደኋላ የቀረው በሩን ለመስበር የተዘጋጀው ጅሌ ሃይል ሲሆን ግቢው ከውጊያ ነፃ መሆኑን ሲረጋገጥ የመስበሪያ መሳሪያዎችን በትከሻው እንደተሸከመ ወደ ውስጥ ገባ::ከዚያ በኋላ ትዝ የሚለኝ ነገር ቢኖር እነዚያን ትላልቅ የወህኒ ቤቱን የችንካር ቁልፎች ፈልቅቆ ለመስበር በሩን እንደንብ መንጋ የወረወረው አፍራሽ ሃይል በተገርሞ አለዛም ደግሞ በመደነቅ መመልከቴን ብቻ ነበር:: የመጀመሪያው በር ዙሪያውን ክብ ሆኖ በውስጡ 11 መኖሪያ ክፍሎች ያሉት ነው:: ይህ ሰማይ ጠቀስ ግንብ በከፍተኛ ጥንቃቄና ጥንካሬ የተሰራ ሲሆን የተቆለፈበት የዋናው በር ቁልፎችም እጅግ ከባድ ከሆነ ብረት የተሰሩ ነበሩ::

ከተወሰኑ ደቂቃዎች በኋላ የዋናው መግቢያ በር ሙሉ በሙሉ ተሰባብሮ ወለል ብሎ ሲከፈት በደብረብርሃን መሃል ከተማ ሰማይ ላይ ሁለት ተጨማሪ የላውንቸር ጥይት ደገምሁ:: ከሌላ ወገን የሚተኮስ የመሳሪያ ድምፅ አልነበረም:: ወደ ወህኒ ቤቱ አስተዳደር ፅህፈት ቤትና ግምጃ ቤት ገብተው እያንዳንዱን ቢሮ በመፈተሽ የተለያዩ ሰነዶችን እንዲያወጡ ሻለቃ መስፍን ትዛዝ ሲሰጣቸው እየተጣደፉ በየቢሮው በመግባት ይበረብሩ ጀመር:: የእስረኞቹ በር ወለል ብሎ ሲከፈት እስረኞቹ ግር እያሉ በኛ ላይ ከፊት ለፊታችን መጡ::ከማደሪያቸው እንደተለቀቁ የዶሮ ጫጩቶች ተርመሰመሱ:: እስረኞቹን ስመለከት የደስታ ሲቃ ሲተናነቀኝ ተሰማኝ::እስረኞቹ በበኩላቸው «ነፃ ወጣን ማለት ነው » እያሉ በመጮህ በሩጫ በየአቅጣጫው ሲባረሩ እና አንዱ ከአንዱ ሲጠራሩ እንደሀልም ይሰማኝ ነበር:: ከዚያ ጥቁር ሞት ተብሎ ከተሰየመውና ከአዔው



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

መንግስት ጀምሮ የእስረኞች ማሰቃያ ከነበረው ጠሀኒ ቤት ነፃ የወጡት እስረኞች ከ650 በላይ ቁጥር ያላቸው ሲሆኑ በወቅቱ የነበረውን የእስረኞቹ ጩኸትና ትርምስ ሲታይ በአንድ ጠሀኒ ቤት የነበረ እስረኛ ብቻ ሳይሆን የደብረ ብርሃን ከተማ ህዝብ በሙሉ በመሸሽ ላይ ያለ ይመስል ነበር:: ደብረብርሃን ለተወሰነ ደቂቃ ያህል በዚህ ምስቅልቅል ውስጥ ጸጥታዋ ደፍርሶባት ቆየች::

በሌላ በኩል ግንየመንግስት ሰራዊት ወደከተማዋ ለእርዳታ የመጣ ቢሆንም ደፍጦ በነበረው ሃይላችን በተከፈተበት ተኩስ አንድ ሰው ሲሞት የተቀረው ደግሞ አቅጣጫውን ቀይሮ ለመሸሽ ተገደደ:: በግርግሩ ውስጥ ለምን እንደመጣ የማይታወቅ የቀይ መስቀል መኪና ሹፌር ተመቶ እንደቆሰለመጨረሻላይስንሰማ በሌላ በኩልም ከጠባሴ ወታደራዊ ካምፕ የመጣ አንድ ቀራጭ ፎቶ ለማንሳት ሲሞክሩ ከፍተኛ ጉዳት የደረሰበት መሆኑን ወደ መጨረሻው ሰምቻሁ::ከዚያ ውጭ ምንም አይነት ወታደራዊ ሀይል ለእገዛ የደረሰ አልነበረም :እስረኞቹከተማውን ለቅቀው መውጣታቸውን እንዳረጋገጥሁ ለማፈግፈጊያ ምልክት የተዘጋጀውን የላውንቸር ጥይት ለሁሉም በሚታይ መልኩ በአየር ላይ መተኮስ ነበረብኝ:: የመጨረሻው የግዳጅ ማብሰሪያ የላውንቸር ጥይት በደብረብርሃን ጥቁር ሰማይ ላይ ሽቅብ ተምዘገዘገ::

«አበቃ ደብረብርሃን ከእንደግዲህ በኋላ ወደሰላምሽ ተመለሺና አንቀላፊ:: ከአሁን በኋላ የምንመጣብሽ ለሽብር ሳይሆን ለመዝናናት ብቻ ነው » በጨለማ ውስጥ ደብረብርሃንን በሁሉም አቅጣጫ እየተመለከትሁ አፅናናኋት . . .. . . ::

እኔና ሻለቃ መስፍን ምድባችንን ይዘን ወደ ቀጠሮ ቦታ ስንደርስ ሁሉም በፍጥነት ተንቀሳቅሶ ቀጠሮ ቦታ እየጠበቅን ነበር::ከእያንዳንዱ ሰው ፊት ላይ የሚነበበው የደስታ ስሜት ቃላት አይገልፀውም ነበር:: ከዛሬ በኋላ ብሞትም አይቆጨኝም በማለት መሬት ላይ ይንከባለል የነበረ ሰውም አይቻለሁ:: አንዳንዱም አንገት ለአንገት ተቃቅፎ ይላቀሳል::



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

የሞተ የቆሰለ ሰው ቁጥጥር ተደርጎ በኛ በኩል እንኳንስ ለ እንጨት የሚረው አልነበረም፡፡ በ30 ደቂቃ ግዜ ውስጥ የደብረብርሃን ወህኒ ቤት ተሰብሮ ያለምንም ጉዳት 656 እስረኛ ነፃ የመውጣታቸው ተስፋ እውን ሆነ፡፡ የምንፈልገውን የተወሰነ ሀይል ከውስጡ መርጠን ይዘን ወደ ማረፊያ ቦታችን እንቅስቃሴ ስናደርግ ከሌሊቱ 7 ሰአት አካባቢ ሆኖ ነበር፡፡ያለምንም ችግር ማረፊያ ቤታችን ደረስንና ለሊቱን በዚያው አረፍት አደረግን፡፡ አለኝና ሻምበል ሚካኤል በለጠ አይኖቹን አጥምበቦ እሩቅ ሲያስብ ቆይቶ

«ሰማህ ዓለም ስገድ የደብረብርሃን ወህኒ ቤት እስረኞችን የማስለቀቁ እቅስቃሴና አተቃላይ ውጤት ይህንን ይመስል ነበር፡፡እስከ አሁን በሰማኸው የፕሮፌሰሩትእዛዝ ሰላሳ ደቂቃ በደብረብርሃን ኦፕሬሽን በዚህ መልክተጠናቀቀ፡፡ ዘጠና ደቂቃ በኢቲቪን አንብበኸዋል » አለና ጠየቀኝ በአዋንታ እራሱን ከፍና ዝቅ አደረግሁና « አዎ ጥሩ ታሪክ ነው » ስል እንዳነበብኩት አረጋገጥኩለት፡፡ ከዚያም በነገረኝ ሁሉ ተገርሜ ትኩር ብዬ እየተመለከትኩ«ከአነበብኳቸው የእስራኤል የሰለለ ሂደቶች ሁሉ እጅግ የመሰጠኝ ታሪክ ነበር፡፡ አሁን ደግሞ ሰላሳ ደቂቃ በደብረብርሃን የበለጠ አስደንቆኛል »ስለው ከተከቀመጠበት ተነስቶ በዝግታ እርምጃ እየተንጎራደደ፡፡

«ልክ ነህ፡፡ በአገራችን የመቀሌ እስር ቤትን ወያኔ ሲሰብር የነበረውን ሂደት ለመግለፅ በተደረገው ልዩ እንጠልጣይ ትረካ ተራራውን በአንቀጠቀጠው ትውልድ መፅሐፍ ውስጥ «አጅብ» ተብሎለታል፡፡ ዘጠና ደቂቃ በኢቲቪ የእስረኞች ማስለቀቅ ኦፕሬሽን የተከናወነው በአለማችን በሚታወቀው እና ከአንድ የጭድ ክምር ውስጥ በጨለማ መርፌ ፈልፍሎ ማውጣት ይቻላል የሚል አንፃራዊ ስም በተሰጠው የስለላ ድርጅ በሞሳድ ነው፡፡ የመቀሌው እስር ቤትም ቢሆን የረጅም ወራት እቅድን የወሰደ ነበር፡፡ ከዚያም በላይ ከአንድ ብርጌድ የበለጠ የሰለጠነ ጦር የተካፈለበት ነው፡ሰላሳ ደቂቃ በደብረብርሃን ግን ከአርባ ባልበለጡ ታጣቂዎች በሰላሳ ደቂቃ የተከናወነ እውነተኛ ታሪክ ነበር፡፡ብታምንም ባታምንም እኔ ከነገርኩህ በላይ ሂደቱ እጅግ ፈታኝ እንደነበር ላረጋግጥልህ እችላለሁ» አለኝና መንጎራደዱን ቀጠለ፡፡



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

# ምዕራፍ አስራ ሁለት

## የናዝሬቱ ሽማግሌ

በሳምንቱ መጨረሻ አርብ ከሰአት በፊት የምስራቅ ሸዋ ዋና ከተማ ወደ ሆነችው የአሁኗ አዳማ የጥንቷ ናዝሬት ከተማ ሄድሁ።።ናዝሬት የገባሁት ከጠዋቱ አራት ሰዓት አካባቢ ሲሆን በተ ሰጠኝ አድራሻ መሰረት በቀጥታ የሄድኩት ወደ ቀድሞው የመፀሀፎ ጽፈት/ ቤት ነበር። ከፅፈት ቤቱ እንደደረስኩ ያገኘሁት አንድ በሩን የሚጠብቅ ባላገር መሳይ ዘበኛ ነው። ዘበኛው አጭር ቆመጡን እያወዛወዘ ወደእኔመጥቶ ከበሩ ላይ አስቆመኝና ምን እንደምፈልግ ጠየቀኝ።

ከአዲስ አበባ የመጣሁ መሆኔን ገልጨለት ዋና ሊቀንበሩን ለማነጋገር እንደምፈልግ ለማስረዳወት ስጀምር ለምን ጉዳይ እንደምፈልጋቸው በቅድሚያ ለሱ መንገር እንዳለብኝ ገለፀልኝ። ያኒህ ግዜ ነበር ራሴን ለሱ በቅድሚያ ማስታወቅ እደነበረብኝ የተረዳሁት።።በግል ፕሬስ ውስጥ የምሰራ ጋዜጠኛ መሆኔን ነግሬው ዋና ሊቀመንበሩን ማግኘት እንዳለብኝ አስረዳሁት። ከቆምኩበት ትቶኝ ወደ አላፊው ቢሮ ገባ። ብዙም ሳይቆይ ተመልሶ መጣና እንድገባ የተፈቀደልኝ መሆኑን ነግሮኝ የመግቢያውን በር በአገጩ አመለከተኝ።

ከውስጥ የጠበቁኝ ረጅምና ቀጭን ሰው ብዙ የእድሜ ክልልን ያለፉና እርጅና ጥላውን የጣለባቸው ነበሩ። ያም ሆኖ ግንእርጅናዉ የልባቸውን ወኔ ገና ሙሉ በሙሉ በቅጥጥር ሥር አላዋለውም ብሎ ለመናገር እንደሚቻል በውይይታችን ወቅት ለመረዳት ችያለሁ። እኔ ከውጭ ስገባ ከተቀመጡበት ተነስተው ከጨበጡኝ በኋላ እንድቀመጥ ጋበዘውኝ እሳቸውም ተመልሰው ደረቋ የእንጨት ወንበር ላይ የመውደቅ ያህል ሲያርፉበት እቡቷታዋን አሰማች። የክፍሉን ጣሪያና በክፍሉ ያሉትን ቁሳቁሶች በአንክሮ ከታዘብኩ በኋላ ሽግሌውን አላፊም ደጋግሜ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

አስተዋልኳቸው።ቁመታቸው ከመርዘሙ ይመስለኛል ሰፊ ትከሻቸው እንደ ንስር አሞራ ክንፍ ቁልቁል ተመልሷል። ረጃጅም የእጆቻቸው ጣቶች በእርጅና ብዛት የፌንጣ እግር መስለዋል። በራቸው የራስ ቅላቸውን መሃል ለመሃል ስለገመሰው ወንዝ የከፈለው መሬት መስሏል። ትልቅ አፍናጫቸው ከወደ ጫፉ ሲታይ ወደ አንድ ጎን እንደ ደጋን ዞሮ ተጣምሟል። በአጠቃላይ እርጅና ሙሉ በሙሉ ጓዙን ጠቅልሎ ተሳፍሯቸዋል ማለት ይቻላል።የጠፋባቸውን ነገር እንደሚፈልጉ ሁሉ ከአጠገባቸው ያለውን ወረቀት እያገላበጡ ያለምንም ንግግር ብዙ ደቂቃዎች በዝምታ አሳለፍን።ከብዙ ዝምታ በኋላ «ለመሆኑ በደህና ልትጠይቀኝ መጣህ?» ካሉኝ በኋላ ነበር ስለመጣሁበት ጉዳይ በአጭሩ ማስረዳት የጀመርኩት።

«በሰላም ነው ጌታዬ » አልኩና ወደምፈልገው ዝርዝር ነጥብ ገብቼ ስጠቃቅስላቸው ትኩር ብለው እየተመለከቱኝ ለብዙ ደቂቃ ቆየን። ከዚያም እኔን ከአሁን በፊት በስም የሚያውቁኝ መሆናቸውን ጭምር አስረድተውኝ አንድ ቀን ብንገናኝ ብለው ይመኙት እንደነበር ከነገሩኝበኋላ ለቃለመጠይቅ መስማማታቸውን ስለተረዳሁ መቅረፀ ድምፄን አስተካክዬ ከጠረጴዛው ላይ በማድረግ

«በመአህድ ውስጥ የመጀመሪያው መስራች ነበሩ?» የሚል ጥያቄ ሰነዘርኩላቸው።

ሽማግሌው ለጥያቄዬ መልስ ከመስጠታቸው በፊት ትኩር ብለው በድጋሚ ተመልክተውኝ እንደገና አይኖቻቸውን ከእኔ ላይ በመንቀል በጠባቧ መስኮት እሩቅ አሻግረው ውጭ ይመለከቱ ጀመር። እንደ እውነቱ ከሆነ ይመለከቱ የነበረው በዚያ አካባቢ ያሉትን እንቅስቀሴዎች ሳይሆን አልፈው የመጡባቸውን ረጅምና የተወሳሰቡ መንገዶችን እንደነበር እርግጠኛ ሆኜ መናገር እችላለሁ።

«የመአህድ የመጀመሪያው መስራች ከሆኑት ሰዎች አንዱ ነኝ ብዙ ችግሮችንም ቀምሻለሁ» አሉኝ ከዝምታ መልስ።

«መአህድን ለመመስረት የፈለጋችሁበትን ምክንያት



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ሊገልፁልኝ ይችላሉ? ከሆነስ ዋና መነሻችሁና መሰረታችሁስ መአህድ ነበር? ወይስ ከጀርባ ሌላ ምክንያት ነበረው» ስላቸው:: በትናንሽ አይኖቻቸው ትኩር ብለው ከተመለከቱኝ በኋላ

«ለመአህድ ቅድሚያ መመስረት ሌላ የተደበቀ አጀንዳ አልነበረንም:: ለማአህድ መመስረት ዋናው መነሻ አርባ ጉጉና በደኖን በመሳሰሉት አካባቢዎች የደረሰው የአማራው ህዝብ ጭፍጨፋ ነበር:: ይህ ድርጊት ከጊዜ ወደ ግዜ እየሰፋ ስለመጣና በወቅቱ በሽግግር መንግስቱ በኩል ጉዳዩ ትኩረት ስለተነፈገው እና ሁኔታውም እየተባባሰ በመቀጠሉ ነበር የአማራ ድርጅት መመስረት እንደሚያስፈልግ የተገነዘብነው:: በተለይም ደግሞ ድርጊቱ ይቀነባበር የነበረው በየክልሉ ይገኙ በነበሩት የወቅቱ ባለሥልጣኖች ግፊትና ትዕዛዝ ስለነበር ይህንን ሁኔታ ለማርገብ ሲባል ነበር የተወሰንን ሰዎች በድብቅ መመካከር የጀመርነውና ስለአማራው ሊከራከር የሚችል አንድ አካል ለማቋቋም የወሰነው:: ከዚያ በፊት ግን ጥያቄህ ብዙ መንገድን ወደኋላ ተመልሶየሚቃኝ ስለመሰለኝ እኔም ወደኋላ ተመልሼ አንዳንድ ነገር ላብራራልህ መሰለኝ::

አማራው ቀደም ሲል በነበረው የመሪነት ደረጃው የአገሩን ዳርድንበርና አንድነት ከጠላት ለመከላከል በነጭ ለባሽነት ሲያገለግል በየጠረፉ ነበር የኖረው:: በመላ አገሪቱ በአሉት የጠረፍ ግዛቶች ተሰራጭቶ የኖረውም በደመወዝ ተቀጥሮ ሳይሆን በሚያስተዳድረው አካባቢ መሬት እንደደሞዝ እየተሰጠው እንደነበር ታሪክ ያስታውሳል:: እሱም ቢሆን ለራሱ ባርኔጣ እና ለእግሩ ጫማ ሳይኖረው ጠላት መጣ በተባለበት ሁሉ እየተንቀሳቀሰ አጥንትና ደሙን ለአገሩ ሲገብር ኖሯል::

በአሁን ወቅት የምንመለከተው ሃቅ ግን ከዚህ የተለየ ሆኖ አማራው የታሪክና የሀገር ጠላት እንደሆነ ተቆጥሮ ከደርግ መግባት ጀምሮ የመወገዝና የመግደል አጀንዳ ተከፍቶበታል:: ቀደም ሲል በነበረው የአስተዳደር ስርአት የነበረውን ይዞታ በተመለከተ እንደመቀስቀሻ መሳሪያ ተወስዶ ህዝብን በሃይል ቀምቷል ተብሎ ይዞታው ስለተወሰደ አሁን በየትኛውም ክልል



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ቢሆን እንደማንኛውም ነዋሪ በላቡ እየለፋ ነው:: ስለሆነም አሁን ያለው አማራ በሚኖርበት ክልል ሁሉ እየኖረ ያለው እንደ ማንኛ ውም የክልሉ ነዋሪ በመዛመድና በመደባለቅ በዘርም ሆነ በባህል ከምንም በላይ በእምነቱ ተመሳስሎና ተደባልቆ በሚኖርበትና በሰፈረበት ክልል ሁሉ እየተጋባና እየተዋለደ ዘሩ ከሌላው ዘር ተቀላቅሎአል::

በዘሩ ብቻ ሳይሆን ከሌላው ዘር ጭምር በማንኛውም ነገር ተመሳስሏል:: እየሰራ ተመሳስሎ በላቡ ወጤት ኖረ እንጂ እንደሚባለው በኃይል አስገድዶ እየዘረፈና እየቀማ የኖረ ጨካኝና እምነት አልባ ህዝብ አልነበረም አይደለም:: ሃቁ ይህ ሆኖ እያለ ነው እንደሽፍታ ተቆጥሮ ሰይፍ የተመዘዘበትና እንደ እንስሳ እንዲታረድ የተፈረደበት:: እኔ እነደማምንበት ከሆነ ከአያት ከቅድመ አያቶቻችን የወረስነው ባህልና እምነት እነሱ በሚሉት መንገድ እንደፈለግን እንድንኖር እና እድንሰራ የሚፈቅድልን ሳይሆን ፈርሃ እግዚአብሔርን የተከተለ ነው::

ለዚህም ይመስለኛል የዛኑም ያህል ቢበደል አገሩንና እምነቱን የሙጥኝ ብሎ በደሉን የቻለው:: አማራው በብሔር ደረጃ አማራ ተብሎ ከመጠራቱ በቀር በአማራነቱ ያገኘው የተለየ ጥቅም አልነበረውም:: በተለይ በአሁን ሰዓት ያሉት አማርኛ ተናጋሪዎች « አማራ » ናቸው ከመባላቸውም በቀር ከየትኛው የአማራ ክልል እንደመጡም እንኳን አያውቁትም:: አያትና ቅድመ አያቶቻቸው ከየትኛው የአማራ ክልል እንደመጡ ቢጠይቁም በትክክ አውቀው አይመልሱም:: እነሱ ወገኔ ብለው የሚጠሩት ሕዝብ የኖሩበት አካባቢ ሕዝብ ብቻ ነው:: በዚህ ሁኔታም ብዙ ዘመናትን አስቆጥረዋል::

በዚህ ሁኔታ የኖረን ህዝብ በድንገት « አገርሽ ለቀቀህ ውጣ» ተብሎ የአስቸኳይ መርዶ ሲሰጠው እና ከግንባሩ ላይ የጠመንጃ አፈሙዝ ከደረቱ ጦር ከአንገቱ ካራ ከጭንቅላቱ፣ መጥረቢያ ከሆዱ ሳንጃና ጦር ተደቅኖበት እንዲህ አይነት ትዕዛዝ ተሰጥቶት እንዴት ወዴት ብሎ ምክር ለመጠየቅም እንኳን ግዜ በማይሰጥ ሁኔታ ነበር እርምጃ እየተወሰደበት የነበረው::እነኚህ ሁኔታዎች



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ደግሞ በክልሉ መንግስት በኩል ድጋፍና ማበረታታት ይሰጣቸው ስለነበር ችግሩን የበለጠ እንዲወሳሰብና ግራ እንዲገባው ስለአደረጉት እራሱን እንኳን መከላከል ተስኖት በጅምላ እንደእንስሳ ታረደ:: ለአገራቸው ብዙ ነገር ሰርተው ያለፉት ጥንታዊ መሪዎችና አባቶችም የሰሩት ሁሉ ተዘንግቶና ተረስቶ ሳይሆን በምቀኝነት ብቻ በመነሳሳት የሰሩት መልካም ስራ ግብስብስና ቆሻሻ ተጭኖበት ውለታቸው ስድብ ሆነ:: ዘራቸውም እነሱ ፈፀሙት በተባለው ተጠያቂ ነው ተብሎ ስር ነቀል ዘሩን የማጥፋት ሰፊ ዘመቻ ተካሄደበት::

በተለይም የአማራው ተወካይ ነው ተብሎ በአማራው ስም ይንቀሳቀስ የነበረው ድርጅት ዋና ሊቀመንበር የነበረው ታምራት ላይኔ የበግ ለምድ ለብሳ በበጎች መካከል እንደገባችው የተኩላ ባህታዊ በአማራው ህዝብ ስም በአዲን የተባለውን ጭንብል አጠልቆ አማራውን ከምድር ዳርቻ ለማፅዳት ያለመታከት በየክልሎች እየዞረ የእልቂት ነጋሪቱን አስጎስሟል:: መጥቀስ ካስፈለገም በሱማሌ ክልል ተገኝቶ ነፍጠው « ምንትስ ሶማሌ » ሲልህ የኖረ ስለሆነ የመበቀያህ ወቅትህ አሁን ነው » በማለት የለየለት እብደቱን አስመስክሮ እንደነበር የታሪክ ምስክርነት የሚሰጠው እራሱ የሱማሌው ህዝብ ነው::

በወቅቱም በመንግስት የመገናኛ ብዙሃን የዚህን አይነት ፀረ አማራ እንቅስቃሴዎች በስፋት ሽፋን ተሰጥቶበት ቅስቀሳ ይደረግ ስለነበር በየክልሉ ያሉ በአሰስተሳሰብ ደረጃ ወደኋላ የቀሩና ሰውን መግደል እንደትልቅ ጀብደኝነት የሚቆጥሩ ወገኖችን በመወስወስና በማነሳሳት በአማራው ላይ ያደረሱት ጥፋት እንደዋዛ በቀላሉ የሚነገር አልነበረም:: አሁንም አይደለም::

በርግጥ በወቅቱ በመንግስት በኩል የነበረው ፕሮፓጋንዳ ከሁለት ዓመት ህፃን ያልተሻለ አመለካከት ነበረው ለማለት እችላለሁ:: አንድ በማስተዳደር ላይ ያለ አካል የሚመራውን ህዝብ እነደራሱ ቤተሰብ መቁጠር እና ጥበቃ ማድረግ ሲገባው ያንንአላደረገም:: እንዲያውም የራሱን ህዝብ ሁለት ቦታ በመከፋፈል «እገሌ ሲበድልህ ኖሯልና አሁን ግዜ ስለገጠመህ መበቀል አለብህ » የሚል መመሪያ መስጠት የለየለት እብደት



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ነው ባይባልም እንኳን ጀማሪ ወፊፌነት ነበር ለማለት ግን እችላለሁ::በነዚህ ምክንያቶች በየክልሉ በነበሩት አንዳንድ ግለሰቦች ምክንያት ብዙ ስህተት ብቻ ሳይሆን ብዙ እብደት ተፈለፅሟል::በዚህ እብደት መካከልም ብዙ የአማራ ብሔር ተወላጆች ከነህይወታቸው በጅምላ ወደ ጥልቅ ገደል ተወርውረዋል፣ ከነህይወታቸው ቤት ተዘግቶባቸው በእሳት ተቃጥለዋል፣ በስለት እየተተለተሉ ታርደዋል::በጥቅሉ ለመጪው ትውልድ ጥሩ ያልሆነ የታሪክ ስህተቶች ፈፅመው አልፈዋል:: የተሰሩት ስህተቶች በጣም አስቀያሚና በመጪው ትውልድ ህሊና ውስጥ ደስ የማይል በተለይም ለእኛ ለኢትዮጵያኖች ባህል እና እምነት የማይስማማ ነበር:: ባለቤቷ ከፊት ለፊት እያያት በእንስሳዊ ባህሪ ሚስት ወሲብ ተፈፅሞባታል:: ለአቅመ ሄዋን ያልደረሱ ሴት ልጆች በእናትና በአባታቸው ፊት ክብረ ንፅህናቸውን ተደፍረዋል::

ይህ ለእኛ ለኢትዮጵያኖች አይደለም እምነትና ባህል ለሌላቸውም አገራት ህዝቦች እንኳን የማይስማማ ጥቁር ጠባሳ ነው:: ያ ዘመን ለእኛ ጥሩ አልነበረም:: አሁን አለፈ ብለን እንደታሪክ ለማውራትም እንኳን ቁስሉ ገና ባለመጥገጉ ምንም ማረጋገጫ የለንም:: ለምን ብትለኝ ትውልዱ ብዙ ቂምና ብዙ ጠባሳ በሆዱ አምቆ እንደያዘ ነው::

የምነግርህ ተረት ሳይሆን ይህ ድርጊት ይፈፀም የነበረው በዚሁ በናዝሬት ወረዳ በሚገኘው አካባቢ ስለነበር ሁሉን ነገር በታዛቢነት አይቻለሁ ሰምቻለሁ:: ከዚህ በኋላ ነበር ሁለትና ሶስት ሰዎች እየሆንን መመካከርና ስልሁኔታው ምን ማድረግ እንዳለብንም መወያየት የጀመርነው:: ከብዙ ውይይት በኋላም የፖለቲካ ድርጅት በአማራው ስም ለመመስረት ተስማማን:: በርግጥ ከስላማዊ የፖለቲካ ትግል ውጭ የሆነ እራስን የመከላከል እና ሀይልን በሃይል የመመከት አሳብም ከብዙዎች በጥያቄ መልክ ይቀርብ እንደነበር አስታውሳለሁ:: በዚህ መንገድ አማራው ልሂድ ቢል የኢትዮጵያ የወደፊት ሁኔታ ትንቢት ሳያስፈልገው ምን



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ጥፋት እንደሚደርስ የታወቀ ስለነበር ይሄኛውን መንገድ እንደምርጫ አድርገን አልወሰድንም ነበር።በሰላማዊ መንገድ መንቀሳቀሱን ከተስማማንበት በኋላ የመጀመሪያውን ስብሰባ ያደረግነው በጥቅምት ወር ላይ በ1984 ዓ.ም ከጠዋቱ ሶስት ሰዓት በማርያምቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ ከቤተልሔሙ ጀርባ በናዝሬት ከተማ ነበር። ስብሰባችንን ናዝሬት ከተማ ያደረግንበት ዋናው ምክንያት እሁድና ቅዳሜ ከቅዳሴ በኋላ ምእመናን እየተሰበሰበ መወያየት ስለሚችሉና በቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ በረከት ያለ ሰው ተሰብስቦ ቢታይም ሌላ አላማ ይኖረዋል ተብሎ ትኩረት ስለማይሰጥበት እንደሚስጥር ጠባቂ ለመጠቀም አስበን ነበር። በርግጥም ልክ ነበርን። ማንም ምን ትሰራላችሁ ብሎ የጠየቀንም ሆነ ያየን አልነበረም።

ቅዳሜና እሁድ በቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ግቢ ከቅዳሴ በኋላ እየተገናኘን ለበርካታ ሳምንታት ተወያይተን በመጨረሻ አንድ ሀሳብ ላይ ለመድረስ ቻልን።እንደመነሻ ሃሳብ ይዘን የነበረው በቅድሚያ «ህዝብን ማነቃቃት »የሚል ሲሆን ለምስራቅ ሸዋ ቅርብ በሆነው አካባቢ ያለውን ገበሬ በመቀስቀስ እራሱንም ከጥቃት እየተከላከለ ሌላውን በተለይም በአርሲና በባሌ ክልል ውስጥ ያለውን ወገኑን ከሞት ማትረፍ እንዳለበት ለማስረዳት የምንችልበትን ንድፈ አሳብ ይዘን ቀርበን። በቀረበው ሃሳብ ላይ ትኩረት ሰጥተን ከተወያየንበት በኋላ ከውሳኔ ላይ ደርሰን ተለያየን።

እስከሚቀጥለው ቀጠሮ ማንኛውም ነገር በምሲጢር እንዲያዝ አድርገን ቆይተን ህዳር ስድስት ቀን 1984 ዓ.ም አረርቲ ወረዳ የመጀመሪያውን ስብሰባችንን በአደረግንበት ወቅት ከምንጃር ፣ከሸንኮራ ከቡልጋና ከተለያዩ የገጠር ወረዳዎች ብዙ ህዝቦች መጥተው እንደነበር አስታውሳለሁ። ከየወረዳው ለመጡት የገበሬው ተወካዮችም ስለጉዳዩ በጥቅል አነጋገርናቸው ለህዳር 14 ቀን 1984 ዓ.ም ቀጠሮ ይዘን የተለያየን ሲሆን ከዚያ በፊት ግን ማንኛውንም ነገር በድብቅ ተይዞ ውስጥ ለውስጥ ከመነጋገር



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

በዘለለ ከማንም ጋር ይፋ ውይይት እንዳይደርግ ስብሰባውን ከመበተናችን በፊት ከሁሉም ወረዳዎች ለመጡት ወገኖችአስጠንቅቀናቸው የሚቀጥለው ስብሰባችንም የሚደረገው በዚያው በአረርቲ ከተማ ሊሆን እንደሚችል ነግረናቸው ወደ ናዝሬት ተመልሰን መጣን::

ህዳር 19 ቀን 1984 ዓ.ም በነበረን ቀጠሮ አርርቲ ከተማስንደርስ ቦታዉን በህዝብ ተጨናንቆ ያገኘነው ሲሆን ከተለያዩ የገጠር ወረዳዎች የመጣው ሰው ቀላል የሚባል አልነበረም:: አብ ዛኛው ገበሬ ከነመሳሪያው ስለነበር ለጦርነት የተዘጋጀ እንጂ ለስብሰባ የተጠራ አይመስልም ነበር::

የተለያየ የጦር መሳሪያ የታጠቀውን ወገኔን ስመለከት ልቤን በጣም እየሞቀኝ በደስታ ተውጬ «አሁን የአንተ ወገን ነው ምንም ከለላ እንደሌለው ሰው በጅምላ የሚታረደው? » በማለት እየደጋገምሁ በስብሰባው መሃል ራሴን እጠይቅ ነበር:: በእለቱ ደግሞ የእንግሊዝ መንግስት በጎ አድራጊ ድርጅት ለአረርቲ ከተማ መብራት ለማስገባት አረርቲ መጥቶ ስለነበር ከአዲስ አበባ የመጡ የአካባቢው ተወላጆችም አብረው ነበሩ::

እኛም አጋጣሚውን በመጠቀም ከአዲሰ አበባ የመጡትን የአካባቢውን ተወላጆች የስብሰባችን ተካፋዬች እንዲሆኑ አድርገን ስለጉዳዩ በስፋት ለመነጋገር አጋጣሚውንአግኝተን ስላማከርናቸው እነሱም ሃሳቡን እንደሚደግፉትና አብረውን እንደሚሰሩም በሙሉ ፈቃደኝበት ገልፀውልን ነበር:: በተለይም የጥብቅና ሞያ ያላቸው አቶ ግርማ ማን አገደውና ጌታመሳይ ደገፋ የተባሉት ሁለት ሰዎች ከስብሰባ በኋላ አዲስ አበባ የሚገኙበትን አድራሻ ሰጥተውን እንዴት አድርገን መገናኘት እንደምንችል ከተነጋገርን በኋላ የስብሰባችን ፍፃሜ ሆኖ እንሱም ወደመጡበት ተመለሱ:: እኛም የለቱን ስብሰባ በዚሁ ዘግተን ወደናዝሬት መጣን::በሚቀጥለው ቀጠሮአችን ወደ አዲስ አበባ ገ|| ያደረግነው ከእኔ ጋር ሰባት ሰዎች ስንሆን ቀኛዝማች ነቅአጥበብ በቀለ ፊታውራሪ ተዘራ ወልደጊዮርጊስ አቶ ፀጋዬ ገብረሚካኤል፣አቶ ከንፈ ክብረት እኔም እራሴ እና ሌሎችም ነበሩ::አዲስ አበባ እንደደረስን በቀጥታ የሄድነው የአቶ ግርማ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ማን አግደው ቢሮ የሚገኝበት አካባቢ ብሔራዊ ተብሎ ከሚጠራው ሰፈር ሲሆን ብዙም ሳንደክም ነበር የአቶ ግርማን ቢሮ ያገኘነው:: ወደ ውስጥ ስንገባ አቶ ግርማን ከቢሮአቸው ተቀምጠው እየጠበቁን ስላገኘናቸዉ ከሳቸው ጋር አንዳንድ ሁኔታዎችን ከተወያየን በኋላ ጉለሌ ከሚገኘው የወይዘሮ አልማዝ ኃይለማርያም ቤት በአቶ ግርማ መሪነት በራሳቸው በአቶ ግርማ መኪና ተሳፍረን ጉዞ ጀመርን:: ከወይዘሮ አልማዝ ቤት ስንደርስ አምስት ሰዎች እየጠበቁን አገኘናቸው:: ከሁሉም ጋር የተዋወቅን ስንሆን አንደኛው የወይዘሮ አልማዝ ባል ነበሩ::

ዶክተር ፀጋዬ ወርቅነህ እና ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስም በቦታው ነበሩ:: በዚህን እለት ነበር ለመጀመሪያ ጊዜ ከፕሮፌሰር አስራት ጋር በግንባር የተገናኘሁትና የተነጋገርኩት:: በአጠቃላይ ስብእናቸውንና ግርማ ሞገሳቸውን ያስተዋልኩት በጆሮዬ ከምሰማው በእጥፍ አብልጬ ነበር ለማለት እችላለሁ:: አለባበሳቸውም ሆነ አነጋገራቸው ኢትዮጵያዊ ቃና ያለው ነበር:: ቀኑ ብርዳማ ስለነበር ነጣ ያለ ሙሉ ሱፍ ለብሰው በላዩ ላይ ጥቁር ባለወርቀዘቦ ካፓ ደርበውበታል:: ሽበት ሙሉ በሙሉ ወርሮት ገብስማ የሆነው ፀጉራቸውን ክምክም አድርገው አበጥረውት ስመለከት « ከመከም ጎፈሬው » የተባለውን አባባል አስታወሰኝ እና ለመጀመሪያ ግዜ ውስጤን ሲሞቀኝ ስለተሰማኝ ፈገግ አልሁ::

ፕሮፌሰሩ ሁላችንንም በወንድማዊነት መንፈስ ከተዋወቁን በኋላ ወደተሰባሰብንበት ዋናው ገዳይ ገብተን ብዙ ነገርችን ተወያየን::ፕሮፌሰሩም በወቅቱ እንደነገሩን ከሆነ በጉዳይ ዙርያ ከተለያዩ ሰዎች ጋር እየመከሩበት እንደነበር ነው:: ነገር ግን ጉዳዩን ጀምረውት የነበረው በልማት ስም እንደነበረ ገልጸው ይህ የተደረገበት ዋናው ምክንያት ገና ከጅምሩ እንዳይቀጭ ለማድረግ እንደሸፋን ለመጠቀም ሲባል መሆኑን በወቀቱ እዛ ለነበርነው ሰዎች አብራርተውልን ነበር::አሁንም መመስረት ያለበት ድርጅት በልማት ስም ሆኖ መላውን አማራ የሚወክል መጠርያም እንደሚሰጠው አስታውቀውን ለታህሳስ ሁለት ቀን 1984 ዓ.ም



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ቀጠሮ ይዘን የእለቱን ስብሰባችንን በመዝጋት ተለያየን::በወ/ሮ አልማዝ ኃይለማርያም መኖርያ ቤት ለሁለተኛ ግዜ ስንገናኝ ተገናኘን:: በእለቱ የነበሩት ሰዎች ከተለያዩ ቦታዎች የመጡና ቁጥራቸውም እጅግ የበረከተ ነበር:: ሁሉንም ከዚያን ቀን በፊት የማላውቃቸው ነበሩ:: በዚያን ቀን ድርጅቱ ተመሰረተና የመተዳደሪያ ሕግና ደንብ ከተነበበልን በኋላ የድርጅቱ የመጣሪያ ስምም የመላው አማራ ሕዝብ ድርጅት መዐሕድ እንደሚባል ተነገረን:: በድርጅቱ ህግና ደንብም ሆነ በስም ስያሜው የተቃወመባለመኖሩ ምርጫ መደረግ አለበት የሚል ሃሳብ ቀርቦ ፕሮፌሰር አስራት ሊቀመንበር አቶ አበበ ወንድሜነህ ምክትል ሊቀመንበር፣ ቀኛዝማች ነቀአ ጥበብ ተቀደሚ ሊቀመንበር::ዶ/ር ፀጋዬ ወርቅነህ ዋና ጸሐፊ ፣ አበበ ወልደ ሚካኤል የታሪክ ክፍል ፣ቀኛዝማች ይልማ በድሉ ገንዘብ ያዥ፣ ፕሮፌሰር ነብያት ተፈራ አስተባባሪ ፣ፊውታራሪ ማሞ በሼ አበበ ተዘራ ወልደጊዮርጊስ አባል ፣ዶ/ር ወርቅነህ ብስራት እና እኔም እራሴ ታዬ ተሰማ አባል ፣ግርማ መናግደው አባል፣ ጌታቸው ሁሴን ፣ አባል ፀጋዬ ገ/ሚካኤል ፣አባል ሀይለ ማርያም ፣ አባል ኮሎኔል በቀለ ደምሴ ፣ አባል ክንፈ ክብረት ፣ አባል ሆነን ከተመረጥን በኋላ ስብሰባው ተጠናቆ ከቀኑ አስራ አንድ ሰዓት ሲሆን ተለያየን::

የመዐሕድ ቅድመ ምስረታ ይህንን በመስለ ሁኔታ የተጀመረ ቢሆንም እኔ በበኩሌ ይህችን ቀን የማስታውስበት በሁለት አብይ ቁም ነገር ነው ብለውኝ በጠባቧ መስኮት አይኖቻቸውን አሾልከው ውጭውን ይመለከቱ ጀመር:: ከዚያም ከኪሳቸው ተጨመታትረ የተቀመጠች መሃረብ አውጥተው ከጎደጎዱ አይኖቻቸው ተገፍተው ብቅ ያሉትን እንጥፍጣፊ የእምባ ዘለላዎች አደራረቁና ቀጠሉ::አንደኛው እና ዋናው ፍሬ ጉዳይ በአማራው ላይ የታወጀው የጥፋት ዘመቻ እንዲቆም የመጀመሪያው ግድብ የተሰራበት መሆኑ ሲሆን ሁለተኛውና አሁንምድረስ ህሊናዬን እንደቆጠቆጠኝ ያለው ነገር ደግሞ ምትክ የሌለቸው ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስን ያጣነው በዚህች እለት መሆኑን ስለማምን ነው:: ያን ቀን እሳቸው ሳይፈለጉ በእኛ ግፊት ብቻ ወደ ፖለቲካ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

አዘቅት የከተትንበት እለት ስለነበር ሁልጊዜ አዝናለሁ፡፡ ለአማራው የህይወት ዋስትና ሲባል ብዙ ሰዎች ምትክ የሌላትን ውድ ህይወታቸውን ቤዛ አድርገው የሰጡበት የደም እና የአጥንት ታሪክ ማህተብ የታተመበት ያን እለት ነበር ለማለት እችላለሁ፡፡ ይህ ታሪክ ለማንኛውም ትውልድ የሚሸጋገርበት የቀጣይ ዘራችን ማስታወሻ እንደሚሆንምሙሉ አምነት አለኝ፡፡ መግፍም ያለበት ታሪክ እንደሆነ ስለማምንበት ነው ከመነሻ የጀመርኩልህ፡፡ አንተም ብትሆን ማንንም ሳታከስስና ስታወድስም እውነተኛውን ቁም ነገር እንደምታስቀምጥ እተማመናለሁ፡፡

በተለይም በዚህ ታሪክ ጉልህ ስፍራ ሊኖራቸው የሚገባ አንድ የሴት ጀግና አሉ፡፡ እኝህ ሴት በመግቢያዬ እንደጠቀስኩልህ ቤታቸውን ለመአህድ መመስረቻ ከመፍቀድ አንስቶ ለድርጅቱ መቋቋምያ የሚሆን ሰላሳ ሺህ ብርም እንደሰጡ አስታውሳለሁ፡፡ ስለወይዘሮ አልማዝ በአሰብኩ ቁጥር የማስታውሰው የአድዋ ጀግናዋን ጣይቱ ብጥልን ነው፡፡

በዚያ አስቸጋሪ ወቅት ቤታቸውን ለእኛ መሰብሰቢያነት ፈቅደው እኛ ስብሰባውን ስናካሂድ እሳቸው ውጭ በር ከአንዲት ደረቅ ወንበር ላይ ተቀምጠው ጥጥ የፈተሉ በመምሰል እንዝርት በእጃቸው ጨብጠው አካባቢውን በጥንቃቄ ሲጠብቁ እኛ ስብሰባችንን ጨርሰን እንለያይ ነበር፡፡ከምንም በላይ የማልረሳት ደግሞ ከአጠገባቸው የማትለያቸውን አጭር ዱላ ነው፡፡ እኛ ሴት ከሳቸው ፈቃድ ውጪ ወደ ግቢ በሃይል ልግባ ብሎ የሚሞክር ቢኖር ያለምንም ማመንታት በዚያች ቆመጣቸው መሃል አናቱን ፈንክተው እንደሚጥሉት እርግጠኛ ነበርሁ፡፡

ስብሰባ መጨረሳችንን ሲያረጋግጡ ወደቤት ገብተው ሻይ ቡና ከጋበዙን በኋላ ያሰናብቱናል፡፡ እና ይሄውልህ የመዐሕድ ፅንሰትና ውልደት በኋላም ጉልምስና ይህንን የመሰለ ሲሆን መአህድ በይፋ እንደተመሰረተ የመጀመሪያው ስብሰባ በናዝሬት ከተማ እንዲሆን ተወሰነ፡፡ፕሮፌሰር አስራት ስብሰባው በናዝሬት እንዲደረግ የፈለጉበትን ምክንያት ሲናገሩም « እናንተ ከናዝሬት



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

የመጣችሁት ሰዎች ለመአህድ መመስረት ምክንያት ስለሆናችሁ የመጀመሪያ ስብሰባችንም የሚደረገው በናዝሬት ይሆናል:: ሁለተኛው ስብሰባችን ደግሞ :: በብዛት ችግር በተፈጠረበትና አማራው በስፋት የጥቃት ሰለባ በሆነበት ክልል በአርሲ ግዛት በአሰላ ከተማ ይደረጋል »ያሉን ሲሆን ቃላቸውንም አክብረዋል::በእለቱ የአሰላውን ስብሰባ የመሩት ሁለቱ ምክትል ፕሬዳንቶች አቶ አበበ ወንድሜነህና ቀኝ አዝማች ነቅአ ጥበብ ነበሩ:: ይህ ሁሉ ሲሆን የመዐሕድ የውስጥ አላማና እንቅስቃሴ ሁሉን አቀፍ ፓርቲ መመስረት ስለነበር ከተለያዩ ብሔረሰቦች ጋርም በተለያዩ ቦታዎች የየድርጅቱ አላፊዎች እየተገናኙ ይመካከሩ ነበር::ሶስተኛው ስብሰባ የተካሄደው ደግሞ በአዲስ አበባ ከተማ በመስቀል አደባባይ ሲሆን በዚህ እለትም እጅግ ቁጥሩ የበዛና የተለያዩ ብሔረሰቦች ተወካዮችና የአገር ሽማግሌዎች ተማሪዎችና ወጣቶችም የተሰፋፉበት ነበር::

ቅርንጫፍ መስሪያቤቶችን በተመለከተም በአርባ ጉጉ ወረዳ የመዐሕድ ፅህፈት ቤት ተከፍቶ ስራውን የጀመሩ ሲሆን በሁሉም የአርሲ ወረዳዎች ጽህፈት ቤት ያስከፈትኩት እኔ ነበርሁ:: በምስራቅ ሸዋ በአሉት ወረዳዎች በመትሃራ፣ በምንጃር፣አረርቲ፣ በሸንኮራ ባልጩ ከተማ በበረከት ወረዳ ጽህፈት ቤቶች ተከፍተው በአውራጃ ደረጃ በደብረዘይት ከተማ ዋናው ጽፈት ቤት ተደርጎ እነኚህ ሁሉ ተጠቃለው ስራ ጀምረውም ነበር::

ሽማግሌው ያለፈውን ጊዜ በአዝነልቡናቸው ተመልሰው ይመለከቱ እንደነበር በውይይታችን ወቅት ስሜታቸውን በደንብ ተመልክቻለሁ:: ከፕሮፌሰሩ ጋር ከስብሰባ ውጭ እየተገናኙ ተነጋግረው ያውቁ እንደሆን ጠይቄያቸውም ነበር:: ብዙ ጊዜ አዲስ አበባ ከተማ ቸርችል ጎዳና ከማገኘው ዋናው የመአህድ ጽህፈት ቤት ለብዙ ቀናት ተገናኝተው ተወያይተው እንደነበር ገልፀውልኛል:: ምትክ የሌላቸውን መልካም ሰው አገራችን አጥታለች የሚል እምነት አላቸው::ፕሮፌሰር አስራት በእሳቸው እይታ ምን አይነት ሰው እንደነበሩ ሲተርኩልኝ ፊታቸው በደንገት መጫወቻውን እንደቀሙት ህፃን ይከፋና ወደዚያው



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

አይኖቻቸው በእንባ ጭጋግ ይሸፈኑ ነበር:: ከኪሳቸው ያችን የተጣጠፈች አሮጌ መሃረብ አውጥተው እንባቸውን ይጠራረጉና ትረካቸውን ይጀምሩልኛል::

ፕሮፌሰር እጅግ ሲበዛ ትሁትና ሰውን አክባሪ መሆናቸውን በተገናኘንባቸው ቀናት ሁሉ ለመታዘብ ችያለሁ:: በውይይት ሰዓት ሰውን ያለማበላለጥ ያደምጣሉ ያ ብቻ ሳይሆን የተናገርከውን በሙሉ አድምጠውህ ለሁሉም ሀሳቦች በቃል መልስ ይሰጣሉ እስከ አልገባው ድረስ ተናጋሪው መጠየቅና መረዳት አለበት የሚል እምነት አላቸው፡«መሰሎኝ ነው » አለዚያም ደግሞ « ሊሆን ይችላል » የሚል ግምታዊ አረፍተነገር በፕሮፌሰር ዘንድ አይሰራም:: ሁሉም ሰው እውነትነቱን ሳያረጋግጥ በይመስልና በይሆናል መናገር አይቻልም::

ለአቶ ታዬ ፕሮፌሰሩ የዚህ አይነት አመለካከት እያላቸው ለምን በዘር ፖለቲካ ገቡ የሚል ጥያቄ አቅርቤላቸው ነበር:: የእሳቸው መልስ እኛ ነን ያለ ፍላጎታቸው ያስገባናቸው ለዛም ነው ከላይ እንደጠቀስኩልህ እሳቸውን ያጣንበት ቀን ነው ብዬ ለማስቀመጥ የሞከርኩት እሳቸው እኮ እምቢ ብለው ነበር እኛ ነን እርስዎ ካልመሩን ብለን ከወይዘሮ አልማዝ ቤት ድንጋይ ተሸክመን የለመንናቸው:: ያለፍላጎራቸው በማስገባታችንም ለህይወታቸው መጥፋትም ተጠያቂዎች ነን ባይ ናቸው::

ቀጥዬ ያነሳሁባቸው ጥያቄ ፕሮፌሰር በጦር ማነሳሳትና ህዝብን ለአመፅ በመቀሰስቀስ ወንጀል መከሰሳቸውን በመጥቀስ ሲሆን በተለይም በደብረብሃን ከተማ ያደረጉትን ንግግርና በራሳቸው ቢሮ ከጎጃም ከመጡ ገበሬዎች ጋር የሽግግር መንስቱን በሃይል ለመጣል ዶልተዋል ስለተባለው የመንግስት ውንጀላ በመጠቃቀስ ነበር:: በሰሜን ሸዋ በቡልጋና በይፋት የተደራጀና በቀድሞ መንግስት ጦር መኮንኖች የተዋቀረ ተዋጊ ሃይል ነበራቸው ከመባሉም በላይ በቡልጋ የነበረው ጦር ይመራ የነበረውም የጊናገር ወረዳ አስተዳደሳሪ በሆነው አስማረ ዳኜ በተባለ ግለሰብ እንደነበርና ይህ ሰው በድብቅ አዲስ አበባ እየመጣ ጉምሩክ አካባቢ በሚገኘው የፕሮፌሰሩ የግል መኖሪያ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ቤታቸው ይሰነብት እንደነበር ስለሚወራው ወሬ የሚያውቁት እንዳለ በሚል ጠየቅኳቸው።ይህንን የመሳሰለውን ወሬ ሲወራ ይሰሙ እንደነበርና በዚሁ ከፕሮፌሰሩ ጋር አብረው የተከሰሱ የደርግ የጦር መኮንንኖችም እንደነበሩ የነገሩኝ ሲሆን በእሳቸው ግምት ግን ነው ብሎ በእርግጠኝነት ለመናገር እንደሚከብድ አስረድተውኛል። በሌላ በኩል ግን ፕሮፌሰር በጣም አድርገው ይበሳጩ ስለነበር አጋጣሚውን ካገኙት ወደ ሀይል ሚዛን ለመሸጋገር እንደማይመለሱ በእርግጠኝነት ለመናገር ይቻላል ይላሉ ሽማግሌው።

አያይዘውም « አስማረ ዳኜ ስለአልከኝ ሰው ግን በአካል ባላውቀውም ልቤ የሚያደንቀው ጀግና ነበር። አገሩንና ወገኑን የሚያኮራና የሚያስከብር ስራም ሰርቶ ለወገኑ ሲል በጀግንነት ወድቋል። ሌሎቹ ግን ለጥቃቅን ጥቅማቸው ሲሉ የወገናቸውንና የአገራቸውን ጥቅም ለሆዳቸው በመሸጥ በባንዳነት ከነበረበት ቦታ ድረስ በመሄድ ጠቁመው አስገድለውታል። በአካል ባለውቀውም በመንፈስ ግን ጀግንነቱን አሁንም ወደፊትም ሳደንቀው እኖራለሁ» ነበር ያሉኝ ሽማግሌው።

በፕሮፌሰር አስራት እና ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል መካከል ነበር ስለሚባለው ያለመግባባት ጠይቄያቸውም ፕሮፌሰር አስራትና ኃይሉ ሻውል የከረረ ጠብ እንደነበራቸው በግልጽ የሚያውቁት ባይኖርም ኢንጂነሩ ከመጀመሪያው ጀምሮ ለፕሮፌሰር አስራት እንቅፋት እንደነበሩ በመጨረሻም ኢንጅነሩን ከነበራቸው የኃላፊነት ስልጣናቸው አንስተው እንዳባረሯቸው እንደሚያውቁ ነግረውኛል። አያይዘውም ከድርጅቱ ከተባረረም በኋላ በውጭ አገር እሆኖ አገር ቤት ከነበሩት የራሱ ደጋፊዎች ጋር በማበር የድርጅቱን ብቻ ሳይሆን የአማራው ጣውንት ከነበሩት ኦነግን ከመሳሰሉት ተቃራኒ ሃይላት ጋር እየተገናኘ የፕሮፌሰሩን ስም በማጥፋት ተግባር ተሰማርቶ ነበር ይላሉ አቶ ታዬ። ትረካቸውን በመቀጠልም ጊዜውን ጠብቆ ጠላትነቱን ለማረጋገጥ ሲል የሞቱለትን እና ለአማራው ጥላ ይሆናል ተብሎ የሚታመንበትን የብዙ ሰዎቸ ህይወትና ደም የተከፈለለትን ድርጅት ህልፈተ ሞታቸውን በመጠበቅ ከውጭ ተሽቀዳድሞ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

በመምጣት በድርጅቱ ዉስጥ በነበሩት ረዳቶቹ አማካኝነት አፈረሰው::በዚህ ድርጊቱም የእሳቸውን መታሰቢያነት ብቻ ሳይሆን አማራውንም ያለታዛቢ አስቀርቶታል:: በድርጅቱ ውስጥ በነበሩት የእሱ ቁልፍ ሰዎች አማካኝነት የመአህድ ሁለተኛው ፕሬዘዳንት ተብሎ እንዲመረጥ ተደረገ:: ወንበሩን ከያዘ በኃላም ያለፈ ቂሙን ለመወጣት ሲል በወሰደው እርምጃ ድጅቱን አፈረሰ:: ይህ የሚያሳየውም ቂም ያለው ከፕሮፌሰሩ ጋር ብቻ ሳይሆን በራሱ በአማራው ብሔር ላይም መሆኑን ያመለክታል በማለት ምክንያቱን ሲዘረዝሩልኝም አማራው አይዞህ የሚለውና የሚጠለልበት ምንም ድርጅት ሳይኖረው እና በተለይም በዚህ ድርጅት ስም የብዙ ሰዎች ህይወት ጠፍቶበት እያለ አማራውን ያለታዛቢ ከሜዳ ላይ ለመጣል የተሼረበ ሴራ ነው ይላሉ አቶ ታዬ::

ለሽማግው ቀጥሎ ያቀረብኩላቸው ጥያቄ ሻለቃ አድማሱ መላኩ ስለተባለ ግሰብ ነበር:: ሻለቃ አድማሱ ፕሮፌሰሩ በእስር ላይ እንዳለ ከመአህድ ፅህፈት ቤት አንድ ጥራዝ ሰነድ አውጥቶ ለኢአዲግ አስረክቧል የሚል ሃሜት ሲኖር በዚህ ሰነድ ውስጥ የሰሜን ሸዋ አርበኞች ንቅናቄ ግንባር አመራሮችን ጠቅላላ ሊስት በውስጡ የያዘ እንደበር አንዳንድ ሰዎች ይናገራሉ:: ሰነዱን በተመለከተ ፕሮፌሰሩ እስር ቤት እያሉ ሻለቃው ወደ ቤቱ ይዞ ሲሄድከመንገድላይበደህንነቶችመቀማቱንለፕሮፌሰሩይነግራቸዋል፡በ ዚህን ግዜ ፕሮፌሰሩ በጣም ይናደዱና ሃዘን በተሞላበት ስሜት እየተመለከቱት«ስም ዝርዝራቸውን አውጥተህ ሰጥተህ አስፈጀሃቸው?» በማለት ምርር ብለው ሻለቃ አድማሱን ይጠይቁታል::

እንደሚባለው ከሆነ ሻለቃ አድማሱ ሰነዱን አውጥቶ ያስረከበው በፍቃዱ ሳይሆን ወይም ሞት ወይም ደግሞ ሰነዱን አውጥተህ ማስረከብ የሚል ማስጠንቀቂያ ከአንዲት ኤርትራዊ ከሆነች ወዳጁ ቀርቦለት ነዉ ይላሉ:: ሻለቃ አድማሱ ሁለተኛውን ምርጫ ተቀበለና ሰነዱን አውጥቶ አስረከበ:: እውነት ይሁን አይሁን በውል ባይረጋገጥም ወሬው በስፋት መወራቱ ግን አልቀረም:: እኔም ይህ ሁኔታ ይከነክነኝ ስለነበር ለአቶ ታዬ ስለተባለው ሰነድ የሚያውቁት



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ነገር አለ? ከሆነስ ደግሞ በዚህ ሰነድ ውስጥ የሽምቅ ተዋጊዎች ስም ዝርዝር ሊቀመጥ ይችላል ብለው ያምናሉ? የሚል ጥያቄም ለሰቶ ታዬ አቅርቤላቸው:: ነበር::

አቶ ታዬ ሲመልሱ የሰሜን ሸዋ የአርበኞች ማህበር የጦር አባሎች ስም ዝርዝር ነበረበት የሚል የህዝብ ሃሜት አለ:: በርግጥ ፕሮፌሰሩ ሻለቃ አድማሱን አምነውት ይህንን ያህል ከባድ ምስጢር የያዘ ሰነድ ያሳዩታል ብሎ መገመት ይከብዳል:: በፍፁም አያምኑትም:: ያም ሆኖ ግን የብዙ ሰዎች እምነት የነበረው ሻለቃው በቀረበለት ግዳጅ ሊስቱን አውጥቶ አያስረክብም ብሎ ለመገመት አይቻልም ካሉኝ በኋላ አያይዘውም «ስለሻለቃ አድማሱ በአጭሩ ይህንን ያህል ከነገርኩህ ይበቀል » ወደ አቶ ሃይሉ ልመለስና የብዙ ሰዎች ህይወት የተሰዋለትና ለብዙ ሚሊዮኖች የህይወት አክሊል ይሆናል ተብሎ ተስፋ የተጣለበትን የአማራውን ድርጅት የእሳቸውን ህልፈት ጠብቆ ለማፍረስ የበቃበት ምክንያት አማራውን ያለ አስታዋሽ ከሜዳ ላይ እንዲወድቅ ለማድረግ ብቻ ሳይሆን የምቀኝነትም ይመስለኛል:: በኔ በኩል ግን ፕሮፌሰር አስራትየተሰውበትን ድርጅት በህይወት እያለሁ ላለመተው ስል ያለምንም ድጋፍ ሻማዋ እንዳትጠፋ በማለት ይህችን ባንዲራና የእሳቸውን የቃልኪዳን ቀንበሮች ለመጠበቅ ለአንድ ፀሐፊና ለአንድ ዘበኛ ደሞዝ እየከፈልሁ ነኝ::

በህይወት እያለሁም የመአህድን ፅህፈት ቤት አልዘጋውም አለኝ:: ::እስከመቼ የሚል ጥያቄም አቅርቤላቸው የሰጡኝ ቁርጥ ያለ መልስ

«አማራውን የሚወክል አማራ እስከሚመጣ ድረስ» የሚል ነበር:: ከእሳቸው ጋር የነበረኝን የናዝሬት ቆይታ በዚህ መልኩ አጠናቅቂ ምሽት ላይ ወደ አዲስ አበባ ተመልስሁ:አዲስ አበባ እንደተመለስሁ ማታዉኑ የፕሮፌሰሩ ነገረፈጅ ለነበሩ አንድ ጠበቃ ስልክ ደዉዬ ላነጋግራቸዉ እንደመፈልግና በፕሮፌሰሩ ዙርያ ልጠይቃቸዉ እንደምፈልግ ነገርኩዋቸዉ።በማግስቱ ክስራ ሰአት በሁዋላ ቀጥረዉኝ ስልኩን ዘጋሁ።



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

# ምዕራፍ አስራ ሦስት

## የፕሮፌሰሩ ንግግር

ለጠበቃው ቅድሚያ ያቀረብኩላቸው ጥያቄ ፕሮፌሰሩ ህዝብን ለጦርነትና ለዓመፅ አነሳስተዋል ከጎጃም ከመጡ ገበሬዎች ጋር መንግስትን በኃይል ለመጣል ዶልተዋል ተብለው ስለተከሰሱበት ጉዳይ ሲሆን ምን እንደሚመስል እንዲያስረዱኝ ነበር።

ጠበቃው ለነዚህና ለሌሎችም ጥያቄዎች ከመመለሳቸው በፊት ሕዝብን ለአመፅ አነሳስተዋል ተብለው የተከሰሱበትን የንግግራቸውን ሙሉ ጽሑፍ ከአንድ ፋይል ውስጥ ነጥለው በማውጣት በቅድሚያ እንዳነበው ሰጥተውኝ አንብቤ ስጨርስ ምልክት እንድሰጣቸው ከነገሩኝ በኋላ ከሳሎኑ ፊት ለፊት ያለውን በር ከፈተው ወደ ውስጥ ገቡ። ባለ አስራ አምስት ገፅ ያለውየፕሮፌሰሩ ንግግር እንዲህ ሲል ይጀምራል።

ከሁሉ በፊት በእናንተ ውድ ወደገኖቼ መካከል በዚህ አደባባይ ላይ ተገኝቼ ስለሀገራችን ስለ ኢትዮጵያ ህልውና እንዲሁም በየቦታው በግፍ በመጨፍጨፍ ላይ ስለሚገኘው ወገናችን ስለ አማራው ሕዝብ የወደፊት መኖር ወይም አለመኖር ጉዳይ ለመወያየት ላበቃኝ ሁሉን ማድረግ ለሚቻለው አንድ አምላክ ምስጋና አቀርባለሁ።

የሽግግሩ መንግሥት ከተቋቋመ ጀምሮ ብሔር ብሔረሰቦች እንዲደራጁ ሲደረግ ስለጋራ ጉዳያችን የምንወያይበት ይህን ስብሰባ እንድናዘጋጅ ስለተባበረን በመላው አማራ ሕዝብ ድርጅት ስም ምስጋናዬን አቀርባለሁ።ዛሬ ለሁለተኛ ጊዜ የሰሜን ሸዋ አቀፍ ስብሰባ በዚሁ በደብረ ብርሃን አደባባይ ላይ ለማድረግ የተቻለው በሕዝብ ጥያቄና ግፊት ሲሆን ይህም ስብሰባ መዐህድን እንደፈረሰ አድርገው አሉባልታ የሚነዙትን የአማርውን ቀንደኛ ጠላቶች እና የወኪሎቻቸውን ከንቱ ሙከራ እንደ በጋ ጉም እንዲበን የሚያደርግና ስለወደፊቱም ትግላችን የጋራ ግንዛቤ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

የምናገኝበት እንደሚሆን አምናለሁ:: ከዚህ በቀር ይህ በህዝብ ሙሉ ቃል እና ፍላጎት ላይ የተቀናጀው ስብሰባችን የሰሜን ሸዋ መዐሕድ እንቅስቃሴን በመገምገምና ሕዝቡ ከመላው አማራ ሕዝብ ድርጅት ጋር ያለውን ግንኙነት በሚመለከት ያለውን የጠራ አቋም የምንዳስስበት ለወደፊትም እንቅስቃሴያችን የጋራ ዕውቀትና ትምህርት እንድንተነነብይበት ታስቦ የተዘጋጀ ነው::ይህ የአለንበት ዘመን አገራችን ኢትዮጵያ እና የኢትዮጵያ ሕዝብ በከፍተኛ ችግር ላይ የወደቀበትና ፈታኝ ከሆነ የጥፋት ማዕበል ውስጥ የገቡበት ወቅት መሆኑ ይታወቃል::በተለይም የኢትዮጵያ የታሪክ ጠላቶች ኢትዮጵያን ለማጥፋትና ለማዳከም ሲያውጠነጥኑ የኖሩበት ዕቅድና ስልት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ መሆን የጀመረበት ወቅት ስለሆነ በኢትዮጵያዊነታችን ለምናምን ሁሉ አሳሳቢ ብቻ ሣይሆን እጅግ ፈታኝ የሆነ ወቅት ላይ እንገኛለን::

ይህ ሀገራችንንና ሕዝቦቻችንን ከጥፋት ውስጥ ያስገባ ችግርና ወጥመድ በኢትዮጵያዊያኖች የተጠነሰሰና የተፈጠረ ሳይሆን በውጭ ጠላቶቻችን የረቀቀና ለተግባራዊነቱም ገንዘብ ዕውቀትና ቁሳቁስ ተመድቦለት በከፍተኛ ደረጃ ክትትል የሚደረግበት ከመሆኑም በላይ ዓለም በአንድ ኃይል መዳፍ እጅ የመግባቷን ሁኔታ ሲያበስር የኢትዮጵያ ጉዳይ ደግሞ ከራሷ ሕዝብ በቀር ሌላ ዳኛና ተቆርቋሪ የሌላት መሆኑን መገንዘብ ይኖብናል::

የኢትዮጳያ ጠላቶች ኢትዮጵያን ለማጥፋት ሲያቅዱና ሲዘምቱ ለረጅም ጊዜያት የኖሩ ቢሆንም እደዛሬው ኢትዮጵያን ባዶዋን ያገኙበት ጊዜ በታሪክ አልታየም:: ይህ የሀገራችን ባዶነት ሊከሰት የቻለውም ከረጅም ጊዜ የጠለቶቻችን የውስጥ ቡርቦራ በኋላ ህዝቡ እንዲከፋፈል እና በራሱ ልጆች ላይ ዕምነት እንዲያጣ ሞራሉንም ታሪኩንም ሃይማኖቱንም በአጠቃላይ ሁለንተናውን ሁሉ እንደምሰጥ ውሰጥ ውስጡን ሲበሉት የቆዩ ቦመሆናቸው ነው::ከዚህ በቀር በአሁኑ ወቅት በዓለም ላይ የተከሰተው የፖለቲካ ሁኔታ ለኢትዮጳያ ሕዝብ ችግር ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያደረገ መሆኑ ይታያል::ከዚህ የተነሳ የዓለም ሕዝብ የጋራ ሕልውናና የታናናሽ አገሮችን



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ደህንነት በማስጠበቅ ረገድ ከፍተኛ ሐላፊነት የሚጠበቅበት የተባበሩት መንግስታት ድርጅትም የዓለም ታላላቅ ኃይሎች ሚዛን ባልታሰበ ሁኔታ በድንገት ስለተዛባ በአንድ ኃይል አመራር ሥር ወድቆ ለዳግመኛ የታሪክ ትዝብት ተጋልጦ ይገኛል:የራሱን ሚዛን በመለዋወጥ ላይ የሚገኘውን የዓለም ሁኔታ በብቸኛ ኃያልነት የሚመሩት ወገኖች በየትኛውም አካባቢ ያለውን ፍላጎታቸውን ለማርካትና ጥቅማቸውን ለማመቻቸት የሚችሉ ቡድኖች በሥላጣን ላይ እንዲቆናጠጡ ከማድረግ ባሻገር የሀገሩን ሕዝብ ጩኸት የሚሰሙበት ጆሮአቸውን ይሁነኝ ብለው ደፍነውታል::

ስለሆነም በማንኛውም አገር ውስጥ ምንም ዓይነት ችግርና በሕዝብ ላይ የሚፈፀም ዕልቂት ቢከሰት ከእነሱ ስልትና ጥቅም አንፃር የሚያሳስባቸው ሆኖ እስካላዩት ድረስ ስሜት የሚሰጣቸውና የዕልቂቱም ሰቆቃ የሚቀሰቅሳቸው አይደለም::ይህ የውጭ ሀይሎች ስልት ይህችን የምንኖርባትን ክፍል ዓለም ማለትም የአፍሪካን ቀንድና እንዲሁም ባውሮፓና በዮጎዝላቢያም ምድር ሕዝብን እርስ በርሱ በማፋጀት የሚፈፅሙበት ደባ በገሀድ እየታየ ነው:: ጠባብ አመለካከትና ቡድናዊ ስሜት ያላቸውን ኃይሎች በማስታጠቅና የነሱ ደጋፊ ትከሻ በመሆን በሌላ በኩል ደግሞ የመሳሪያ ፋብሪካቸው ገበያ እንዲያገኝ የጦር መሳሪያዎች በገፍ በማቅረብ ሕዝቡን እርስ በርሱ በማፋጀት ረገድ ወኪሎቻቸው የነሱን ዓላማ ለማራመድ የሚችሉበትን በረቀቀ ጥናት የተደገፈ ተክህኖ ይሰጧቸዋል::

እርስ በርስ የማፋጀት ስልታቸውም ትኩረት የሚደርገው በረጋው ማህበረሰብ ውስጥ ጎሳን ቋንቋንና ሃይማኖትን ለሕዝቡ አጉልቶ በማሳየትና በዚህ አንፃር በመከፋፈል ነው::በኢትዮጵያ ላይ የውጩ ኃይል ትኩረት ማድርግ ከጀመረ ብዙ ምዕተ ዓመታት ያለፈ ቢሆንም በይበልጥ ስሏተዊ ዕቅዱን ይፋ ያደረገዉ በዳግማዊ ምኒልክ መሪነት ኢትዮጵያ በአድዋ ላይ ካስመዘገበችው ድል በኋላ ነበር::በነጮች ዕውቀት የተገነባውን ያንን የወቅቱን ኃይል ሀገር ጦር በአፍሪካ ምድር የሚቋቋመው ኃይል የለም በሚባሉት በዚያ ጨለማ ዘመን ኢትዮጵያ ያስመዘገበችው የጦር



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ሜዳ ድል ወደ አፍሪካ ያነጣጠረውን የውጭ ኃይል እንደገና እንዲያሰላስልና እንዲያስብ ስላደረገው ሕዝብን ማሸነፍና መያዝ የሚቻለው በጦርነት ብቻ ሳይሆን እራሱን በራሱ እንዲጎዳና እነደዲከፋፈል በማድረግ የሕዝቡን ኃይል በቀላሉ ሊፈራርስ የሚችልበትን ስልት በመቀየስ ጭምር መሆኑን እንዲያምኑበት አድርጓቸዋል::ስለሆነም ኢጣሊያ በአድዋ ላይ የደረሰባትን አሳፋሪ ሽንፈት መነሻ በማድረግ 40 ዓመት ሙሉ ሲጠናበት እና ሲታቀድ ቆይቶ ከሞላ ጎደል ከሰሜኑ ኢትዮጵያ በተወሰደው የኢትዮጳያ አካል የሆነውን የኤርትራን መሬት መቆናጠጫ በማድረግ የኢትዮጵያን ሕዝብ እርስ በርሱ የማባላቱ ተግባር በግንባር ቀደምትነት ተጀምሮ ነበር::

ኢጣሊያ ይህን ዓላማዋን ለማራመድ እንዲያስችላት የኢትዮጳያ አካል በሆነው የኤርትራ መሬት ላይ ከተቆናጠጠች በኋላ ወደ ደጋማው የኢትዮጳያ መሬት ከመንቀሳቀሷ በፊት ከምእራባውያን ኃያላን መንግስታት ጋር ምስጢራዊ ስምምነት ማድረጓንም ከታሪክ እንረዳለን::

በወቅቱ በነበረው የኃያላን መንግስታት አሰላለፍ እስትራቴጂ መሰረት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን መያዟ በነርሱ መካከል የቅርጫ ድርሻዋ መሆኑን በማሳመን ጭምር ሲሆን ቀደም ብሎ በይዞታ ሥር ከነበረው የኢጣሊያ ሶማሊያ ይልቅ የኤርትራን ምድር የተደላደለ የጦር ሰፈር በማድረግ የወረራ እንቅስቃሴዋን ባፋፋመች ጊዜ ሕዝቡን ለማሰልጠንና ሀገሩን ለማልማት የተደረገ በጎ እንቅስቃሴ እንደሆነ ተደርጎ እንዲታይ በሃገር ውስጥም ሆነ በውጭው አገር ፕሮፓጋንዳ ለመንዛት ተሞክሯል::

ይህ ፕሮፓጋንዳ ዛሬም ቢሆን መልኩንና ቅርፁን ለውጦ ኢትዮጵያ ኤርትራን በቅኝ ገዥነት እንደያዘችና ኢጣሊያን ደግሞ አገር አልሚ እንደነበች ተድጎ እየተነገረ ነው::ኢጣሊያኖች በዚህ ሁኔታ የኢትዮጵያ አካል በሆነው በባህር ምድር ማለትም የዛሬው ኤርትራ መሬት ላይ ከተቆናጠጠች በኋላ የክፍለ ሀገሩን ሕዝብ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

በከፍተኛ ቁጥር በመመልመልና በጦር ግንባር በማሰለፍ በዓለም በተከለከለ የመርዝ ጢስና በከባድ መሳሪያ በመታገዝ በቀረው የኢትዮጲያ ሕዝብ ላይ ወረራ በማካሄድ 5 ዓመት የቆየውን ጭፍጨፋ በኢትዮጲያ ሕዝብ ላይ ለማካሄድ በቅታለች።

የኢጣሊያ ወረራ ዋና ዓላማ የነበረውም ቁጥሩ የበረከተውን የሀገሯን ሥራ አጥ ሕዝብ በሰፊው የኢትዮጲያ ለም መሬት ላይ በማስፈር የሀገራችንን ጥሬ ሀብት ለመበዝነዝ እና የትዮጵያን ህልውና በረቀቀ መንገድ በማጥፋት ቋሚ ገዥነቷን ለማረጋገጥ እንደነበር ይታወሳል። የኢጣሊያን ወረራ በኢትዮጵያ ሥር እንዲሰድና የኢትዮጲያን ህልውና እንዳልነበር አድርጎ ቀኝ ገዥነቷን እንዲያረጋግጥ ለማድረግ የታመነበት በኢጣሊያ ዕቅድ መሰረት የሚከተሉት ከኢትዮጵያ ምድር ሲጠፉ ነው በማለት ሲሆን እነሱም 1ኛ ዘውድ 2ኛ የኦርቶዶክስ ሀይማኖት 3ኛ የአማራው ሕዝብ ነበሩ።

ዘውድ የኢትዮጵያን ሕዝብ በአንድነቱ የሚያተሳስር ምልክት ነው በመባሉ አፄ ሀይለ ሥላሴ እንግሊዝ ሀገር በስደት ላይ በነበሩበት ግዜ እንኳን ሳይቀር ሞሶለኒና የሮማው ካቶሊክ ጳጳስ ከፍተኛ ገንዘብ በማበርከት ንጉሰ ነገስትነታቸውን እንዲሰረዙና በዚህም ድርጊታአው ብዙ ገንዘብ አግኝተው ከችግራቸው ተላቀው በተድላና በደስታ እንዲኑ ተማልደዋቸው እንደነበር ይታወሳል።አጼ ኃይለ ስላሴ ለዚህ ባለመበገራቸውና የኢትዬጵያን ክብር አዋርደው እጃቸውን ባለመሰጠታቸው የኢትዮጵያ መንግስት ህልውና ህጋዊ መሰረቱ ፀንቶ በዓለም ሕዝብ ዘንድ እንደታወቀ በመቆየቱ ኢትዮጵያ በኢጣልያን ተወረረች እንጂ የቅኝ ተገዢ እናዳልሆነችና እንዳልተንበረከከች ተረጋግጦ የአርበኞችም ትግል በኢትዮጵያ መንግስት እየተመራ ለድል እንዲበቃ ተደርጓል።2ኛ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሀይማኖትም በውጭ ኃይል ስለማትታዘዝና ስለማትገዛ በጥንታዊነቷ በፍልስፍናዋ በትምህርቷ በዓለም የሚወዳደሯት በጣም ጥቂቶች ስለነበሩ በአቋሟና በዕምነት ፅናቷ ታስቀናና ትፈራ ስለነበር ነው።



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

እንዲሁም ለሀራችን የትምህርትና የሥነ ፅሁፍ የባህልና የአስተዳደር መሠረት ስለነበረችና ከሁሉም በላይ ደግሞ ለኢትዮጵያ ህልውና ስለነፃነትና ስለሰው ልጅ ክብር የምታስተምር በግንባር ቀደምትነት የምትቀሰቀስና የምትመራ ስለሆነች ነው።።

የዛሬውን አያድርገውና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስስ ሃይማኖት አባቶች ለሀገራቸው ለሃይማኖታቸውና ለሕዝባቸው ነፃነት ክብር በግንባር ቀደምትነት ተሰልፈው በዓርአያነት ሕዝቡን የሚመሩ እንደ እነ አቡነ ጴጥሮስና እነ አቡነ አብርሃም የመሳሰሉት የሃይማኖት አባቶችም በኢጣሊያ መትረየስ ፊት ቆመው ሕዝቡ ለነፃነት እንዲነሳሳና እንዲዋጋ አስተምረው በመስዋዕትነት ያለፉ መሆኑን በመረዳት ነበሩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን እንድትጠፋ ተፈረደባት።።

በ3ኛ ደረጃ እንዲጠፋ የተወሰነበት የአማራው ሕዝብ እንደ ኢትዮጵያ ጠላቶች አባባል በራሱና በታሩኩ የሚተማመን አትንኩኝ ባይ ለነፃነቱ እና ለህልውናው ከምንም በላይ ለሃይማኖቱና ለሀገሩ ዳር ድንበር መከበር የሚሞት በመሆኑ ነበር።። ይህም ሕዝብ በታሪክ ውስጥ በገሐድ እንዲታየው በማናቸውም ጊዜ ቢሆን ለውጭ ሃይልና ለውጭ ጠላት ለሀገሩ መዋረድና መደፈር መሣሪያ ሆኖ የማያውቅና የማይደለል ከመሆኑም በላይ በሀገሩና በሃይማኖቱ ጉዳይ አማራው አክራሪ ነው በመባሉ ነው።።አማራን ለማጥፋትም ለየት ያለና ራሱን የቻለ ስልት የተቀየሰ ሲሆን አማራው በጠላቱ ፊት ተባብሮ እንዳይቆም ለማድረግ በስም ከፋፍለው በተለይ የሸዋ አማራ በቅድሚያ ከምድረ ገፅ እንዲጠፋ ካልተደረገ በቀር የኢጣሊያ ወረራ ጊዜያዊ ድል ከመሆኑ ባሻገር ሀገሪቱን በቅኝ ግዛትነት ለመያዝ አንችልም የሚል መደምደሚያ ላይ ደርሰው በዚሁ ዕቅድ ለመግፋት እንደወሰኑ በታሪክ የተረጋገጠ ነው።።በዚህ መሠረት ሙሶሊኒ በቀጥታ ለጦር አዛዦቹና ኢትዮጵያ ላሉት አገረ ገዥዎቹ ያስተላለፈው የቴሌግራም ትዕዛዝ አማራውን ከሌሎች የኢትዮጵያ ሕዝቦች ጨርሶ ለማጥፋት የሚያስችል እርምጃ እንዲወሰድ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

የሚያዝ ስለነበር በዚህ ትዕዛዝ መሠረት ዕልቂቱና ጭፍጨፋው በዐማሪውና በካህናቱ ላይ በገሐድና ያለማቋረጥም እንዲፈፀም መደረጉን የቅርብ ጊዜ ታሪኮችን ይመሰክራል።በኢጣሊያን ስልት የአማራውን ሕዝብ የማጥፋቱን ዘመቻ በራሱ በአማራው ከሌሎች የተጀመረ ሲሆን በሌሎች የኢትዮጵያ ግዛቶችም ትኩረት ተሰጥቶት አማራውን የማጥፋቱ ዘመቻ በሌሎች ኢትዮጵያውያን ጎሣዎች እንዲደገፍና እንዲያውም አማራን የማጥፋቱ ተግባር በሌሎች የኢትዮጵያውያን ጎሣ ሕዝብ በግንባር ቀደምነት እንዲፈፅም ከቅስቀሳ ጀምሮ እስከ መሳሪያ ድጋፍ ድረስ ተሰጥቷል።በዚህ ሁኔታ በአንድ ፊት አማራውና የኦርቶዶክስ ሃይማኖትን የማጥፋቱ ዘመቻ ሲከናወን በሌላ ወገን ደግሞ የእስልምና ሀይማኖትን የማስፈፋፋቱ ተግባር ቀጥሎ ነበር። በኢትዮጳያ ምድር እስልምናን የማስፋፋቱ ተግባር በኢጣሊያ የተደገፈው ለኢትዮጵያ እስላሞች ጥቅም በማሰብ ሳይሆን በወቅቱ የኢጣሊያ መንግስት ከሊቢያ ቅኝ ግዛቷ ሕዝብና ከዓረቡም ዓለም ድጋፍ ለማግኘት ሲባል ብቻ ነበር።በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ በዚህ ሁኔታ የተቀናጀ ዕልቂትና ጭፍጨፋ እየተካሄደ በሌላ በኩል ደግሞ ሀገራችንን በአምስት የጎሣ ቋንቋዎች ከፋፍሎ የማስተዳደሩ ሥራም ተጀምሮ ነበር።

ኢትዮጵያን በጎሣና በቋንቋ የመከፋፈሉም ስልት የአጭር ጊዜ ጥቅሙ አማራውን ከሌሎች የኢትዮጵያ ክልሎች ለማስወገድ እንዲቻልና በአንድ ቦታ ተወስኖ እንዲኖር በማድረግ በኢትዮጵያ ምድር እንደሰደደ እሳት እየተቀጣጠለና እየጋመ የነበረውን የአርበኞች ትግል ለማዳከም ነበር።የረጅም ጊዜ ጥቅሙ ደግሞ « ኢትዮጵያ » የሚለውን ቃል ከዓለም ካርታ ላይ ለማጥፋትና ኢትዮጵያ ውስጥ ከኢትዮጵያዊነት ስሜት ይልቅ የጎሳ ስሜትና መንፈስ ገንኖ ኢትዮጵያዊነትን ለዘለዓለሚ በማጥፋት በአፍሪካ ቀንድ ወሳኝ ሥፍራ ያላትን ሀገራችንን የቅኝ ገዥዎች መፈንጫ ለማድረግ ሕዝቧም ለጎሣና ለቋንቋ ስሜት ተገዥሆኖ የኢትዮጵያዊነት ክብሩንና ኩራቱን አጥቶ «የአድዋንድል» እንዳያስብና ለዘላዓለማዊ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ተገኘርነቱ የተመቻቸ ለማድረግ ነው።የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ለዚህ የጠላቶቻችን ተንኮል አልተንበረከከም። በእርጥም ከስንዴ መካከል እንክርዳድ እንደማይታጣ ሁሉ በኢጣሊያ ጦር ሥር ሆነው የጠላታችንን ዓላማ አንግበው በወንድማቸው ቀዬ እያደፈጡ ለሀገራቸውና ለነፃነታቸው የቆሙትን የሚሰልሉ ታጥቀው በባንዳነት የተዋጉ ኢትዮጵያዊያኖች ቢኖሩም ጀግናው የኢትዮጵያ ሕዝብ የራሱን መሪ በየጎሣው እየመረጠ ለለነፃነቱ ተዋግቷል። በተለይም የአማራው ሕርብ በአማራ አገር በባንዳነት መሰለፍን የሞት ሞት እንደሆነ ቆጥሮ እምቢ ለነፃነቴ! እያለ ቤቱን እየዘጋ ልጆቹንና ሚስቱን እየተወ የሰባት ዓመት ልጅ ሳይቀር በአርበኝነት በጦር ግንባር ተሰልፎ ለአፍሪካ ምድር የነፃነት ዓርማ የሆነ ሙያ በመፈፀም የሀገሩን ክብር አስመስክሯል።

የኢትዮጵያዊያን መስዋዕትነት በእግዚአብሄር ፊት ዋጋ አግኝቶ የኢትዮጵያም ነፃነት ተመልሶ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ርዕሰ ብሄርነት የኢትዮጵያን መንግስትን ለማቋቋም በተጀመረበት ወቅት ኢትዮጵያን በሞግዚትነት ለመግዛት እንግሊዝ ከነበራት የዕቅድ እንቅስቃሴ ጋር ለ3 ዓመት ያህል ከፍተኛ ሠላማዊ ትግል ከተካሄደ በኋላ የኢትዮጵያ መንግስት በዘመናዊና በአስተማማኝ መልኩ የማቋቋሙ ተግባር ሊሰምር በቅቷል።ከዚህ በኋላ ከኢጣሊያ ጭፍጨፋ በተረፈው ጥቂት የተማረ የሰው ሃይልና በብድር የተጀመረው የሀገር ግንባታ ያተኮረው በአንድ በኩል የኢትዮጵያ አካል የሆነችውን ኤርትራን ከእናትአገሯ ከኢትዮጵያ ጋር ለማቀላቀልና ከአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ይዞታ እንዲኖራቸው ከሚጥሩ ኃያላን መንግስታት ጋር የሚደረግ ትግል ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያን አስተዳደር እርምጃን ከዓለም የሥልጣኔ ዕርምጃ ጋር ለማያያዝ የሚያስችለውን ዘመናዊ አሰተዳደር በመጀመር መሰረት የመጣል ትግል ማካሄድ ነበር።በተለይ የኢጣሊያ ጦር ከኤርትራ ምድር ከወጣ በኋላ እንግሊዝ በኢጣሊያ ተተክቶ በዚያ ምድር ለመቆየት ይፈፅም የነበረውን ምስጢራዊ ደባ በስልት ከመታገል ጀምሮ ኤርትራ ወደ እናት አገሯ እንደትዋሀድ ለማድረግ በኤርትራ ጀግኖች የተደረገውም ትግል ቀላል መስዋዕትነት የተከፈለበት አልነበርም።ይህ ሁሉ ትግል ከረጅም ጊዞ በኋላ ውጤት አግኝቶ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ኢትዮጵያን በኢኮኖሚና በፖለቲካ መልክ ራሷን ችላ የአፍሪካ የነፃነት አርማ በመሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚደነቅ ተሰሚነት እንድታገኝ ተደርጓል::ይህ ሁሉ ሲሆን በሌላው አንፃር በሀገር ውስጥ ያልተፈቱ ችግሮች እንደነበሩና ከሁሉም ጎሣ ተውጣጥተው በኢትዮጵያ መንግስት ውስጥ ሥልጣን የያዙ ግለሰቦች በሥልጣን ባልገው እንደነበርም የማይታበል ሃቅ ነው::

አጼ ኃይለስላሴ ከእናት አገራቸው ተለይተው የኖሩትን ኤርትራዊያን በመንከባከብ ላይ ትኩረት ሰጥተው ሁሉን ነገር ወደዚያ ሆኖ በእናት ጥቅም እንዲረኩ ለማድግ ሲሞክር ሌሎች ኢትዮጵያኖች ተረስተው እንደነበርም ግልፅ ነው::የኢትዮጵያ ጠላቶች በዚህ ትግል ውስጥ በተከፈለው መስዋዕተነት ምክንያት እንደ ግንባር ቀደም ጠላት አድርገው የአማራውን ሕዝብ « ገዥ መደብ ነው» እያሉ ሲያጥላሉት በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል ደግሞ ለአማራው ሕዝብ ምንም ዓይነት የዕድገት በር ሣይከፈትለት ደበሎውን እንደለበሰ ተረስቶ እንዲቀር በሞራልና በትምህርት ብቻ ሣይሆን በአካልም በድህነት ሥር እንዲኖር የተፈረደበት እዳ ከፋይ ሆኖ ቆይቷል ሁሉም ነገር በማንኛውም ተመልካች ዓይን ጎልቶ የሚታይ የማይካድ ሐቅ ሆኖ እያለ ከአብራኩ የወጡት ልጆቹ ሳይቀሩ በትምህርት ቤት ውስጥ በሚነዛው አሳሳች ዘገባ እየተመረዙ አማራውን ሲገዘግዙትና ሲያዳክሙት በባህሉ በታሪኩና በእሱነቱ እንዳይተማመን ሲያዋርዱት ኖረዋል::

በአጼ ኃይሥስላሴ ዘመነ መንግስት ማክተሚያ አካባቢ የተማሪዎችና የምሁራኖች ንቅናቄ በዚህ በተሳሳተ አቅጣጫ ተመርዞ በኢትዮጵያ ጠላቶች የውስጥ ሴራ እየተራመደ የገዛ ሀገሩን በሚገዘግዝበት ወቅት « ኢትዮጵያ እንዳትደፈር» በሚል የመቆርቆር ስሜት የተነሳሳ መስሎ የኢትዮጵያ መለዮ ለባሽ « ኢትዮጵያ ትቅደም» የሚል አስመሳይ መፈክር በማስቀደም ሕጋዊውን የኢትዮጵያ መንግስት በአፈሙዝ ኃይል ሲገለብጥና በተረጋጋ ሁኔታ የኢትዮጵያን አመራር ሲጨብጥ የቻለው ሀገራችንና ሕዝቡ በዚህ ውዥንብር ውስጥ በነበሩበት ወቅት እንደነበር እናስታውሳለን::ከዚህም በኋላ ቢሆን በደርግ ዙሪያ የተሰባሰቡት የጦር መኮንኖች በኢትዮጵያ ታሪክም ሆነ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

በፖለቲካው ስልት መሐይም ከመሆናቸው የተነሳ እነሱን በቅረቡ አወቅን ባይ ሠርጎ ገብ ምሁራን ዕቅድ አውጪነት የመለዮ ለባሹ ኃይል የኢትዮጵያን አንድነትና ዳር ድንበር ከመጠበቅ ይልቅ ለኢትዮጵያ ሕዝብ እልቂት እና ጥፋት ምክንያት መሣሪያ ሊሆን በቅቷል።የአማራው ህዝብ የዚህ ዕልቂትና ጠፋት ግንባር ቀደም ኢላማ ሆኖ እንደተጨፈጨፈና በተለይም ይህ የሕዝብ ዕልቂት በሰሜን ሸዋ ላይ ትኩረት ተሰጥቶት በመንዝ በመርሐድ ብሩና በመስፍን ብሩ መሪነት በመርሐቤቴ አውራጃም በአርሶ አደሩ ግንባር ቀደምትነት የተንቀሳቀሰው አማራ ደርግን በመጀመሪያ የተጋፈጠ ሕዝባዊ ኃይል እንደነበርና በዚህም የተነሳ ያለማቋረጥ ለሰባት ዓመት በፈጀው የደርግ የዓየር ጭፍጨፋ ያለቀው የሰሜን ሸዋ ሰላማዊ ሕዝብ በደብረ ብርሃን እና በሌሎች የሰሜን ሸዋ ከተሞች ውስጥም በቀይ ሽብር የተጨፈጨፉት የአማራው ልጆች እና ምሁራን ታሪካዊ ተጋድሎ ሲታወስ የሚኖር ነው።

በተመሳሳይ ሁኔታም በወሎ በጎንደርና በጎጃም የዐማራው ሕዝብ ልጆች ለይ ጭፍጭፋ ተንዟዷል።በሌላ በኩልም ቢሆን በደቡብና በምሥራቅ ኢትዮጵያ በአህዳዊ አባሎችና አስተዳዳሪዎች መሪነት አማራው ትጥቁን እንዲፈታ እየተደረገ አድሐሪና ነፍጠኛ የሚል ቅፅል ስም እየተሰጠው እጅና እግሩ እየታሰረ በቤት ውስጥ እንዲቃጠል የተደረገውን ስናስታውስ በየግዜው የሚነሱት ገዥዎች አማራው ላይ የሚያተኩሩበት ምክንያት ለመብቱና ከሁሉም በላይ ደግሞለሃይማኖቱና ለሀገሩ አንድነት ቀና በመሆኑ ብቻ እንደሆነ መገንዘብይገባናል።

በአማራው ላይ የደረሰው ግፍ ከደርግ የአመራር ደካማነት ጋር ተዳምሮ በደርግ ላይ የተፈጠረው ጥላቻ እጅግ መራራ ከመሆኑ የተነሣ በደርግ ምትክ ዱያቢሎስም ቢመጣ በዐማራው ክልል ውስጥ ተቀባይነት እንደሚኖረው በወቅቱ የታወቀ ሐቅ ነበር ለለማለት ይቻል ነበር።በደርግ ላይ የሰፈነው ጥላቻ የኢሕአዲግን ጦር በአማራው ክልል እንዲታቀፍና እንቅስቃሴውም እንዲደገፍ ያደረገው ሲሆን ህዝቡ ኢትዮጵያዊነት ባህሉንና ሃይማኖቱን በኢሕዲግ ይጠብልኛል የሚለውን



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

የአማራውን ዕምነትና ምኞት ተላብሶ ስለነበር በአማራው ልጆች የሕይወት መስዋዕትነት ዳብሮና አድጎ በደርግ ላይ ድልን እያገኘ ኢሕአዴግ በአማራው ትከሻ ላይ ሆኖ አድካሚ ባልሆነ አቋራጭ መንገድ አዲስ አበባ ሊገባ በቅቷል፡ባጭሩ የታሪኩችን ሂደት ይህን የመሰለና ሐቁም ይህ ሆኖ እያለ በኢጣሊያ ወረራ ጊዜ እንደተፈፀመው ዛሬ ደግሞ በኢሕአዴግ አገዛዝ ዘመን በአማራው ላይ የተመዘዘ ሰይፍ አማራው ምን ጥፋት ተገኝቶበት ነው? የሚል ጥያቄ የሚያቀርቡ ወገኖች ካሉ የኢትዮጵያ ጠላቶች ምስጢራዊ እርምጃን ካለመረዳትና ኢትዮጵያ በሚለው ስም ዓይናቸው በመሸፈኑና በየዋህነት የሚያነሱት ጥያቄ ካልሆነ በቀር «ዲሞክራሲ» ራሱ በተለይ የአማራው ጠላት ሆኖ የተወለደ እዳይመስላቸው በአፋጣኝ እንዲነቁና ወደታሪካቸው እንዲያተኩሩ እጋብዛቸዋለሁ።

እንዴት እንዲህ ይሆናል የሚሉ የዋሆች አሁንም ካሉ እስቲ ከኢሕአዲግ ሥልጣን መያዝ ጀምሮ አማራው ላይ የተከናወኑትን ባጭሩ እንመልከት፡-ኢህአዲግ በአማራው ግንባር ቀደም መስዋዕትነት በተገኘው ድል ታጅቦ አዲስ አበባ ከገባና ሥልጣኑን በመላ ኢትዮጵያ ካረጋገጠ በኋላ የሽግግር መንግሥቱን ለመመሥረት ብሔር-ብሔረሰቦችን ሲያሰባስብና ከጉባኤው ላይ ተወካዮቻቸው እንዲኙ በክብር ሲጋብዝ ከኢትዮጵያ ሕዝብ 45 ከመቶ የሚሆነው የአማራው ሕዝብ ተወካዮቹን እንዲልክ ወይንም ራሱ እንዲያደራጅ አልተደረገም እንዲደረግም ፍላጎት አልነበረውም።በሽግግር መንግስቱ ምሥረታ ላይ አማራው ለምን እንዳልተካፈለ በወቅቱ ለሽግግር መንግስትቱ ፕሬዘዳንት ለክቡር አቶ መለስ ዜናዊ ከጋዜጠኞች ጥያቄ ቀርቦ በሰጡት መልስ የአማራ ሕዝብ ተወካይ እንደሌለው ገልፀው « አህአዴግ » በአማራው አገር ውስጥ አልፎ የመጣ ስለሆነ የአማራውን በደልና ስሜቱን የተገነዘቡለትመሆኑን አረጋግጠውለታል። በዚያ እውነተኛ መልሳቸው ውስጥ አማራው ስላልተደራጀ የኢሕአዲግ አንዱ አካል የሆነው ኢሕዴንን ለአማራው ሞግዚት እንዲሆን የወሰኑ መሆኑን ግን እንዳልገለጹልን አስታውሳለሁ።ከሽግግሩ መንግሥት ምስረታና በኢትዮጵያ ምድር ዲሞክራሲ መስፈኑን



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

የሚያረጋግጠው የሽግግሩ ቻርተር ከፀደቀ በኋላ በአማራው ላይ የወረደውን መአት በዓይናችሁ የምታዩት እና በጆሮአችሁ የምትሰሙት ስለሆነ መዘርዘሩ ለኢትዮጵዊነት ክብራችን ውርደት ስለሆነ አልፈዋለሁ::ባጭሩ ግን አማራው ለጥቃት እንዲጋለጥ ለማድረግ ዛሬም እንደ ኢጣሊያው ወረራ ጊዜ በሶስት መከፋፈሉንና « ወራሪ ነፍጠኛ ጨቋኝና ተጨቋኝ » የሚል ሶስት መደብ እንደተሰጠው ለውይይታችን እንዲያመች ያህል ላስታውሳችሁ እገደዳለሁ:: ክፍፍሉም በራሱ አማራው አገር ያለው አማራ ጨቋኝና ተጨቋኝ ተብሎ እርስ በርሱ እንዲጨፋጨፍ ሲደረግ በሌላው የኢትዮጵያ ክፍል የሚገኘው የአማራው ደም ያለበት እንዲያውም ሃይማኖቱ ክርስቲያን የሆነ ሁሉ

«ወራሪ ነፍጠኛ » ተብሎ ለታጠቁትና ለተደራጁት የጦር ጓደኞች ለጎሣ ቡድኖችና ለአክራሪ እስላም ኃይል ጉርሻ ተሰጥቶ ባለቤት እንደሌለው እንስሳ በየቀዬው እንዲጨፈጨፍ ሲደረግ ከርሟል::በፕሮፓጋንዳው መስክም ቢሆን የሞራል ማዳከሙ ተግባር ተቀይሶ አማራው ብቻውን ኢትዮጵያን እንደበደለና ብቻውንም ኢትዮጵያን በመግዛት ሲጠቀም እንደቆየ በኤርትራ መሬት እስከ ዛሬ ድረስ የተካሄደውም ጦርነት አማራው በቅኝ ገዥነት ያቀጣጠለውና ያካሄደው እንደሆነ ተደርጎ መካሄዱም እንዲታመን ለማድረግ በአማራ ስም ይቅርታ የሚጠይቅ ቡድን ወደ ኤርትራ እንዲላክ መደረጉና በዚህም አናፃር ከፍተኛ የቅስቀሳ ስልት በአማራው ላይ እንዲካሄድ ተደርጓል::

ይህ ሁሉ እየተደረገ ኢትዮጵያ በጎሣና ፣በሃይማኖት የምትፈራርስበት ዕቅድ በሥራ ላይ ውሎ አገራችን ስትመሰቃቀል አማራ በገዛ አገሩ ታዛቢ ሆኖ ከመታየት በቀር በሀገሩ ላይ ምንም ዓይነት ሚና እንደሌለው ተደርጎ እና እንደውጭ ባዕድ ተቆጥሮ አገሬ ብሎ ከኖረበት የኢትዮጵያ መሬት እንዲወጣ የማድረጉ ዘመቻም በሌሎች የጎሣ ኃይሎች ሕጋዊነት ያለው እርምጃ እንደሆነ ተገመተ::በራሱ በአማራው ክልልም ቢሆን ስለሀገሩ የሚቆረቆረው ወገን ልዩ የወንጀለኛነት ስም እየተሰጠው አርበኞችም ተጋድሏቸው ዋጋ አጥቶ አገር መካሪ ሽማግሌዎችም



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

የተለየ ስም ተሰጥቷቸው መዘለፍ ብቻ ሣይሆን ከሕዝብ ጋር እንዳይገናኙ እንዳይመክሩና እንዳይመካከሩ በአጠቃላይ አገር አውል መሆን ኃጢአትና ወንጀል እየሆነ ዳኝነትና ይግባኝ በሌለባቸው ፈራጆች ያስቀጣና ያስጨፈጭፍ ጀመር።በደርግም ሆነ ባለፈው አንድ ዓመት ይህ ሁሉ ውርጅብኝ ለምንድነው በአማራው ላይ የተፈረደው? ወይም የሚደርሰው? ብሎ ለሚጠይቅ ሰው ምክንያቱ ግልፅ ነው። ዝንተ ዓለም የኢትዮጵያ ጠላት መጣ በተባለ ቁጥር ስንቁን ሰንቆ ቤት ንብረቱን ትቶ ነፍጡን ይዞ በረሃብና በእርዛት እየኖረ የሀገሩን ጠላት እየተዋጋ ህልውናና ዳር ድንበሯን ስላስጠበቀ ብቻ ነው።

ሌሎች ጎሣዎችም እንዲደራጁ ተደርጎ የየጎሣቸውን ጥቅምና ደህንነት እንዲያስጠብቁ ሲደረግና ይህም ሁሉ ጭፍጨፋ እየተፈፀመበት አማራው በኢትዮጵያዊነቱ ብቻ ተማምኖ የተለመደ ትእግስቱን ብቻ መሣሪያ አድርጎ ሣይደራጅ እስከጥር ወር 1984 ዓ.ም ድረስ 8 ወር ሙሉ ሊቆይ ችሏል።አማራ ከኢትዮጵያ ምድረ ገጽ እንዲጠፋ የተወሰነበት ከመሆኑ የተነሳ በየቦታው ያለገደብ የሚፈፀምበት ጭፍጨፋ እና መሰደድ የሕጋዊነት ገጽታ እየተሰጠው ስለሄደ የአማራውን ሰብዓዊ መብቱን ለማስከበር ስንል የሚፈፀምበትንም ጭፍጨፋ ለምንግሥትና ለዓለም ሕዝብ ለማሳወቅና ለኢትዮጵያ አንድነት ከሚታገሉ የጎሳ ድርጅቶች ጎን አማራው በአንድነት ቆሞ የበኩሉን አስተጽኦ ለሀገሩ እንዲያደርግ ለማስተባበር በታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ አማራው በጎሣ በማደራጀት «የመላው አማራ ሕዝብ ድርጅት » እንዲቋቋም አደረግን።

የመላው አማራ ሕዝብ ድርጅት የአማራውን ሰብዊ መብትና ጥቅም እንዲጠበቅ በግንባር ቀደምትነት ከመቆምና የኢትዮጵያን አንድነት ከማስከበር ባሻገር ሌላ ምንም ዓይነት ዓላማ እንደሌለው ለሁላችንም ግልፅ መሆን አለበት።የኢትዮጵያ ሕዝብ በጎሣ በቋንቋና በሃይማኖት ሳይከፋፈል የጎጠኛነት ድንበር ፈጦሮ የጎሪጥ ሣይተያይ የጋራ የሆነችውን ውድ ሀገሩን ኢትዮጵያን እንዲያለማ ክብሯንና ነፃነቷን በጋራ እንዲያስከብር ኢትዮጵያ ሀገራችን በጎሣና በቋንቋ ድንበር ሳትከለል ሕዝቡ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

በኢትዮጵያ ምድር በማንኛውም ክልል ተከውኖ በጉልበቱና በዕውቀቱ እየሠራ ሀገሩንም እየገነባ በእኩልነት ላይ በተመሰረተ አንድነት አብሮ እንዲኖር ለማድረግ የመላው አማራ ሕዝብ የበኩሉን አስተዋጽኦ ከማድረግ በቀር ሌላ ዓለማ አይኖረውም።

ከዚህ መሰረታዊ አገር አቀፍ አላማ በመነሳት በሽግግሩ ቻርተር መሰረት መዐህድ በመላ ኢትዮጵያ ምድር በሕዝብ መካከል ለመንቀሳቀስ ጥረት አድርጓል። የሕዝብንም ልባዊ ድጋፍ አትርፏል።ሆኖም በቻርተሩ እንደተረጋገጠው ሣይሆን የመዐሕድ እንቅስቃሴ ብዙ ችግሮችና ወጥመዶች ያሉበት በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ እንኳን በቻርተሩ የተፈቀደው ሰብዐዊ መብቱ የታፈነበትና ለሌላው የጎሣ ድርጅት የሚሰጠው እድል የተነፈገው ሌላው ቀርቶ በጋዜጣና ራዲዮ በአጠቃላይ በመንግሥት የመገናኛ መሣሪያዎች ላይ ሀሳቡን ለማቅረብ ቀርቶ የስብሰባ ጥሪ እንኳን እንዳይተላለፍለት የታፈነ ስሙን በሃሰት ለማጥፋት ካልሆነ በቀር ለመዐሕድ መናገርና መጻፍ በመገናኛ መስክ የተከለከለ ሆኗል።

በአንዳንድ ሥፍራ የመዐሕድ አባል ሣይሆን የመዐሕድ ፕሮግራም ይዞ መገኘት እንኳን እንደከፍተኛ ወንጀል ተቆጥሮ ፕሮግራማችንን የያዙ ሰዎች ታስረው ማስጠንቀቂያና ማስፈራሪያ እንዲሰጣቸው እየተደረገ ነው።በሰሜን ሸዋ የሽግግር መንግስት ተወካይ መልካም ፈቃድ በየወረዳው የመዐህድን ቅርንጫፎች ለማቋቋም ከፍተኛ ሙከራ ብናደርግም እንኳን በመዐህድ ደጋፊነቱ የተነሣ በሕዝብ ላይ ከፍተኛ ችግሮችና መሰናክሎችም እየተደቀነበትና በግልጽም ወታደራዊ ዘመቻ እየተካሄደበት ይገኛል።በዚህ ዘመቻ በመዐሕድ አባልነታቸው የታሠሩ የተገረፉ የተገደሉና ከአካባቢያቸው የተፈናቀሉ እንዳሉ ሕዝብ ማወቅ አለበት። እነሱንም በምሳሌ ለመጥቀስ በይፋት አውራጃ ውስጥ የመዐሕድ አመራር አባለት ግንባር ግንባራቸውን በጥይት እንደሚባሉ የኢህዲግ ካድሬዎች በሕዝብ ፊት የዛቱ መሆኑን ገልፀን ይህ ከቻርተሩ ውጭ የሆነ አሠራር እልባት እንዲሰጠው ለሰሜን ሸዋ መስተዳድር ያመልከትን ሲሆን እስካሁን መልስ አላገኘንም። አሁን በቅርቡ በዚሁ የሰሜን ሸዋ ክልል ኩታገጠም



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

በሆነው በአብቹና ፐኦ ወረዳ ውስጥ አንድ የሽግግሩ መንግስት የቀበሌ ባለሥልጣን ከጥቅሙ አንፃር ባካሄደው ዘመቻ ከ20 የበለጠ አማሮች ሲገደሉ ቁጥራቸው ገና በውል ያልታወቁ ሰዎች ከመኖሪያቸው ተፈናቅለዋል ንብረታቸውም ተዘርፏል።

በሰሜን ሸዋ ክልል መስተዳድር በባሶና ወራና ወረዳ ውስጥ አሁን በቅርቡ በሕዝብ ላይ በተካሄደው ወታደራዊ ዘመቻ የደረሰውን እጅግ አሰቃቂ ጭፍጨፋ እናንተው ራሳችሁ ምስክሮች ናችሁ።በዚህ በደብረብርሃን አካባቢ « አባትህ ጠመንጃ የቀበረበትን ቦታ አሳይ » ተብሎ አንድ ህፃን ሆዱ በስለት እየተሸነተረ በስቃይ እንዲናገር የተገደደበት ሁኔታ እንዳለ ታውቃላችሁ።

በምስራቅ ሸዋ በምንጃርና ሸንኮራ በበረከት ወረዳዎችም ተመሳሳይ ሆኑታዎች ተፈጽመዋል አሁንም እየተፈጸመ ነው። በጎንደር በጎጃምና በወሎም ይሄው ጭፍጨፋ በስፋትና በጥልቀት እየተፈፀመ ይገኛል።በሌላው አካባቢም በተለይም በክልል አራት መስተዳደር ውስጥ የሚገኘው በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠረው የዐማራ ሕዝብ በቻርተሩ የተረጋገጠለት ሰብአዊ መብቱ ተገፎ ልጆቹ እንኳን በአማርኛ ቋንቋ እንዳይማሩ ተከልክለው አማራው በገዛ ሀገሩ የሁለተኛ ደረጃ ዜግነት መብት እንኳን አጥቶ እንደባይተዋር እየታየ የእንስሳት ሕይወቱን እየገፋ ይገኛል።

በአርሲ አካባቢ በተለይም በአርባ ጉጉ አውራጃና በምሥራቅ ኢትዮጵያ በአማራነቱ እና በክርስቲያንነት መነሻ ወገኖቻችን እየተጨፈጨፉ ናቸው።ላረጋግጥላችሁ የምፈልገው ይህ ጭፍጨፌ የአማራውን ትግል ያጋግለዋል እንጂ እንገቱን ሊያስደፋው እንደማይችል ነው። በአማራው ላይ የሚደርሰው ጭፍጨፋ እንዲቆምና ሕጋዊ መብቱ እንዲጠበቅለት ስናሳስብ መዐህድ ትምክህተኛ እና ነፍጠኛ እየተባልን ያለፈውን ሥርአት እንዲመለስ የምናሟርት ተደርጎ ገደብ በሌለወ የመንግሥት የፕሮፓጋንዳ መሣሪያ ሲታወጅብን በቻርተሩ ለብሔርብሔረሰብ የተሰጠውየሰብአዊ መብትም=የምናሳውቅበት ዕድል አላገኘንም።



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

መዐሕድ በሽግግሩ ዘመን ለምን እንደ ጠላት ተቆጠረ እንደሌሎቹ ህብረተሰቦች የመንቀሳቀስ የማስተማርና የማደራጀት መብቱ ለምን « አይከበርም?» የሚል ጥያቄ ታቀርቡ ይሆናል:: የዚህ መልሱ «አማራው ለምን ይጨፈጨፋል?» ለሚለው ጥያቄ የተሰጠው መልስ ጉዳዩን የሚያብራራ ይሆናል::የመዐሕድ መታፈን በዚህ ሁኔታ በልዩ ልዩ ስልት እየተካሄደ በሌላ መልኩ ደግሞ በአርሶ አደሩ መካከል ስለ መዐህድ የሚካሄደውን ቅስቀሳ «መዐሕድ ነፃ መሬትና የታጠቀ ሰራዊት ስለሌለው ከምንም ነገር አያድናችሁም» የሚል ነው:: እንዲያውም ይህንኑ ለማብሰር አባላት ሲደበደቡና ሲታሠሩ «እስቲ የእናንተ መዐህድ መጥቶ ያስጥላችሁ» እየተባለ እንደሚነገርና በዲሞክረሲ ስም እጅግ አስቃቂ የሆነ ኢ ዲሞክራሲያዊ ድርጊቶች በአማራው ላይ እየተፈፀመ ነው::

እርግጥ ነው እስከአሁን ድረስ መዐሕድ ነፃ መሬት ወይም የታጠቀ ሰራዊት የለውም::ሆኖም የመዐሕድ ነፃ መሬት የእያንዳንዱ አማራና የመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃ ልብ መሆኑን እድትገነነዘቡልኝ እየጠየቅሁ በሌላበኩልም::ለኛ የመዐህድ የታጠቀ ሠራዊት መላው የኢትዮጵያ ሕዝብመሆኑን ልናረጋግጥላቸው እንገደዳለን::በሌላ በኩልም አንድን ሕዝብ በመሣርያ ኃይል አስገድዶ ማሳመን መቻል በጊዜያዊ ድል ሊያኩራራ ይችል እንደሆነ እንጂ የሕዝብን ልብ እስካላገኙ ድረስ በመሣሪያ አፈና በተገኘ ድል መኩራራት እና በሠራዊት ኃይል መመካት ለደርግምዕንዳልበጀ አረጋግጠናልና ስለነፃ መሬትና ስለሰራዊት ብዛት ብዙ መናገር የሚያዋጣ እንዳልሆነ ከልባችን ምክራችንን ልንለግስና ልናስረዳ እንወዳለን::ለምን ቢባል እኛ በሕዝብ ኃያልነትና ወሳኝነት አናምናለን::ስለሆነም ይህ ሕዝብ ዳግመኛ ወደጠቅላጦርነትእንዳይገባአጥብቀንእንጠነቀቃለን::ለምንቢባልየጦር ነትን ጎጅነት ከማንም የበለጠ አማራው ስለሚያውቅና በጦርነት የሚገኝ ድልም ቂም በቀልና የታሪክ ጠባሳን እንደሚያስከትል ስለምንረዳ ብቻ ነው::ስለሆነም ለጦርነት በፍፁም አንቾኩልም የተለዩ ዝግጅትም



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

አናደርግም፡፡ለምን ቢባል በሕዝብ ኃያልነትና ውሣኔ የሚያምን እንደ መዐሕድ ያለ የሕዝብ አካል የሆነ ድርጅት ወደ ዋሻ በመግባት ተራ ሽፍትነትን በማራመድ ለሥልጣን መራወጥን እንደስልት አይጠቀምበትም፡፡ በሌላ በኩል ለማስገንዘብ ካስፈለገም ሕዝባዊ ትግል መነሻው ጫካና ዋሻ ወይም የጠረፍ ተራራ ሣይሆን ራሱ ሕዝብ ስለሆነ ነው፡፡ ስለሆነም በጠመንጃና በሠራዊት ብዛት የሚመኩ ወገኖች ከዚህ የተሳሳተ ዓላማቸው ተመልሰው ጀብደኝነቱ እንዲያከትምና ከዚህ ፀረ ሕዝብ ተግባር መለስ ብለው በጥሞና መንፈስ ስለጋራ ሀገራችን እንድናስብና ስለዘለቄታው እንድንዋያይ ስንወተውት የቆየንባቸውን ጊዜዎችን በገንቢ መልኩ ቢጠቀሙባቸው ለሁላችንም ቢሆን የሚበጅ ይሆናል፡፡በዚህመልኩየምናራምደዉንትእግስተኛነት ባይጠቀሙበት ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ ትዕግስተኛና ቦርነትም የሠለቸው ቢሆንም እንደምርኮኛ እጁን ወደላይ ሰቅሎ ኡጉል ሞትን እንደማይጠበቅ ደግሞመታወቅ አለበት፡፡ በኛ በኩል በበቂ ተጨባጭ ማስረጃ እንዳረጋገጥነውና የዓለም ሕዝብም በታዛቢነት እንደተረዳው አማራውን ጦርኛና ትምክህተኛ ለማድረግ የተሞከረውን ያህል በራሱ ቀዬ በአሰቃቂ ሁኔታ እየተገደለ ሀብት ንብረቱ እየተደፈረና እየተዘረፈ ትዕግስተኛና ለሕግ ተገዠ መሆኑን አስመስክሯል፡፡ ይህንን ትዕግስተኛነትና የሕግ ተገዠነት የሽግግሩ ባለሥልጣኖች በአንክሮት እዲመለከቱናዋጋ እንዲሰጡት ደግመን ደጋግመን እንጠይቃለን፡፡

በሌላ በኩልም አማራው አሁንም ከመሣሪያና ከጦርነት በመለስ ስለመብቱ እየተናገረየተለመደትዕግስቱንም እንዲቀጥልበት የምንጠይቀው እርስ በርስ መጨፋጨፉ የሚያስገኘውን ውጤት ከጠቅላላው የሀገራችን ጥቅምጋር በማያያዝና በማገናዘብ ጭምር ነው፡፡ለግንዛቤያችንም እንዲረዳ የኢትዮጵያን ሁኔታ ባጭር ባጭሩ ማየት ያስፈልጋል፡፡ በአሁኑ ጊዜ የሀገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ ስንመለከት በጣም በሚያሳዝን ደረጃ ላይ እንደሆነች እንገነዘባለን፡፡ ኢትዮጵያ በጠላቶቿ ፊት በጣም የደከመችና ለቅርጫ ሲያመቻቿት የኖሩት ጠላቶቿ ይህን ወቅት ሊጠቀሙ እየተሯሯጡ እንደሆነ እያየን ነው፡፡ ስለሆነም ከደርግ የሥልጣን



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

መነሻ ዘመን ጀምሮ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሞራሉም በሃብቱም በዕምነቱም ተመናምኗል።በተለይምየአማራውሕዝብና የኦርቶዶክስ በተክርስቲያንበከፍተየውድቀትማጥውስጥእንዲገቡተደርጓል።ባህላችን እና ሃማኖታችን ከምንም በላይ ሞራላችን እንዲደበዝዝ ቅርሳችን እንዲዘረፍና እንዲባክን መጪው ትውልድ የሚነሳበት የታሪክ ቅርስ እንዳይኖረው ተደርጓል አሁንም እየተደረገ ነው የሀገራችን አዋቂዎችና ሊቃውንቶችም ባላቸው የዕውቀትና የመንፈስ ጥንካሬ ለድህነታቸውሣይንበረከኩ ለሀገራቸው ከልብ ተቆርቁረው እንዳያስተምሩ በአፈሙዝ አስገዳጅነትና በቤተክህነት ደካማ አመራር ተከልክለው ኢትዮጵያ ለባህሏናለሃይማኖቷ ጠበቃ እንዳይኖራት የሚናገርላትም እንዳይኖር ተደርጓል።በተለይም በቤተክህነት አመራር ላይ የወጡት ብዙ መሪዎች ሊቅ የሆኑትን የሀገሪቱን አዋቂዎች በማፈንና ከውጭ ኃይሎች ጋር በመመሳጠር ቤተክርስቲያናትን ባዶ ለማድረግና ዕምነትን ለማጥፋት ከፍተኛ ሚና እየተጫዋቱ ነው። ይህም በመሆኑ ስንት ቤተክርስቲያናትና ካህናት ከነህይወታቸው ሲቃጠሉና በስለት እየተሰነጠቁ ሲገደሉ ሊቆረቆሩ ቀርቶ ይሕ መፈፀሙን እንኳን አያውቁም ሊያውቁትም አይፈልጉም። ቢያውቁም ግድ የላቸውም። በአጠቃይ የሃይማኖት አባቶቻችንንማንነታቸውንበተግባራቸውምበኑሮአቸውምእያየናቸውና እያወቅናቸው ነው።

በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ በሁሉም መልክና አቅጣጫ በአደጋ ላይ ትገኛለች። ስለሆነም በዚህ አደጋ ባንዣበበት ወቅት አማራው የቆየ ልምዱንና ትዕግስቱን ተጠቅሞ ለዘለቄታው የኢትዮጵያ ዕድልና ጥቅም በረጅሙ እንዲያስብ ስንጠይቅ ሌሎቹ ደግሞ በገዛ ዱራችን ዋሻዎችና መሬታችን እንዴት እንደምንሸፍትና እንዴት እንደምንዋጋ ሊያስተምሩንና በአጭሩ እንድናስብ ሊገፋፉን ይፈልጋሉ።እኛ ግን ስለጦርነት ለአማራው መናገርና መገፋፋት ልጅ ለእናቷ ምጥ አስተማረቻት እንደማለት ነው እንላቸዋለን። ምክንያቱም አማራ መሣሪያውን ለምንና እንዴት እንደሚጠቀምበት፣መቼ እደሚያነሳውና በማን ላይ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

እንደሚሰነዝር ጠንቅቆ ያውቃልና ነው።ስለዚህ በኢትዮጵያነታችን የምንኩራ አማሮች ማንኛውንም ነገር በጥሞናና በትክክለኛነት በመገንዘብ በአሉባልታና ከዘመኑ የውሸትፋብሪካምንጭ በሚነዛው የወሬ ውዥንብር ሣንታለልና ሣንፈታ በሁኔታውም ጨርሰን ተስፋ ሳንቆርጥየአትንኩንወኔያችንንምጨርሰንሳንተው የሌላውንም መብት ሣንነካ አርቀን በመመልከት በመጀመሪያ እንደማንኛውም የኢትዮጵያ ሕዝብ ሕጋዊመብታችንእንዲከበርበጥሞና እንታገላለን እናሳስባለን።

በሌላ በኩል ደግሞ ትዕግስት በተላበሰ ወኔና እርምጃ ስለጠቅላላው የኢትዮጵያ ደህንነትና ህልውና መከበር በሚደረገው ትግል ውስጥ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እናደርጋለን።ነገር ግን ይህንን የሚጸረሩና በዚህ ሁኔታ የምናራመድውን ትዕግስት ለመከተል የማያስችሉ እና አማራው በክልሉ እንኳንበሰላምናበፍትህ ለመኖር መብት ያጣበት ድርጊቶች በጉልህ እየተፈፀሙ መሆናቸው እያሳሰበን መንገዳችንን ሊያስለቅቁን እየሞከሩ መሆኑን ለዐማራው ሕዝብ ማሳሰብግዴታዬይሆናል።እንዲያውምስለአማራው ትዕግስት መላበስ ደጋግሜ ሳነሳና ስጠይቅ በአሁኑ ግዜ የአማራው ክልል ከሆነው ከጎጃም፣ ከጎንደር፣ ከሰሜን ወሎና ከሰሜን ሸዋ ክልሎች እየተወለደ ለሌላ ክልል ሲሰጥና አማራውም ያለባህሉና ያለልማዱ በሌላ ክልል ውስጥ በተደራቢነት እንዲተዳደር እየተደረገና በያለበት ያለገደብ እየተጨፈጨፈ አማራው ትዕግስት እንዲኖረው መምከር እንዴት ይቻላል? ትሉኝ ይሆናል።

አባባሉ ትክክል ሲሆን እንደዚህ ያለውን ሕዝብን ከሕዝብ መንግሥትን ከሕዝብ የሚጋጭ ድርጊት እንዲያቆምና በቻርተሩ መሰረት እስከ 1966 ዓ.ም ድረስ ፀንቶ የቆየው ክልል እንዲከበር አሠራሩም እንዲስተካከልየሽግግሩመንግስትንከመጠየቅና ከማሳሰብ አንቆጠብም። በቅርቡም ከአማራው ክልል ለሌላክልል ስለተሰጡት በርካታ ስፍራዎች ለሽግግሩ መንግስት ግልፅአቤቱታ ለማቅረብ እየተዘጋጀን ሲሆን በአቤቱታችንም «ሕዝብ» የሚለውንየህዝብ ስሜትና ዕምነት መሆኑን ለመንግስት ለማስረዳት እንጥራለን።



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ከዚህ በኋላ የማስተካከሉና የማረሙ ጉዳይ የሽግግር መንግሥቱ ፋንታ ሲሆን ይህ ሳይደረግ በመቅረቱ ደግሞሕዝቡየራሱን ውሣኔ መውሰድ እንደሚገደድ ከታሪክ ሀቅ መረዳር እንችላለን::የወገንና የሀገር ጉዳይ በመሆኑ ብዙ በመናገር ጊዜያችሁን እንዳባከንኩ ይሰማኛል:: ሆኖም የአባቶቻችንን የሚያኮራ ታሪክ በማስደፈርም ሆነ ባለማስደፈር በውርደትም ሆነ በኩራት ለመጪው ትውልድ ለማስረከብ ባለብን የዜግነት ግዴታ አንፃር በአሁኑ ጊዜ ከታሪክ ፊት ተጋልጠን የምንገኝ መሆኑን እንደገና ላስታውሳችሁ እገደዳለሁ::ለምን ቢባል በጠላት ወረራ ጊዜ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሶስት ተከፍሎ እንደነበር የምናስታውስ ሲሆን አንደኛው ወገን ውርደትን በመጥላት ለነፃነቱና ለክብሩ ሲል ቤት ንብረቱን ትቶ ወደ አርበኝነቱ በመግባት የዱር ገደሉን ኑሮ በመጀመር ታሪክ ሰርቶ ያለፈና የኖረ ነው:: ሁለተኛው ደግሞአገር ሲረጋ እመለሳለሁ ብሎ ሕይወቱን ለማዳል ሲል የተሰደደ ነበር:: ሶስተኛ ውና የመጨረሻው ለሆዱ አድሮ የጠላት መሣሪያ በመሆን ወገኑን ከሚጨፈጭፈው የኢጣሊያን ጦር ጋር ያበረ ነበር::

በዚህ ሁኔታ ሆዱን ለመሙላትና የማይቀረውን ሞት ለጊዜው ለማዘግየት ሲል የውርደትን መንገድ የመረጠው ከንቱ በትዝብት ውስጥ ወደቀ ዕንጂየኢትዮጵያአርበኖችድል አድራጊነት አልቀረም::ወገኑን የከዳውና ለሆዱ ያደረው ባንዳም ከውርደት በቀር ትርፍ ሕይወትና ትርፍ ኑሮ አልኖረም ነበር:: ዛሬም ቢሆንም እንደዚህ ያሉ ለማንኛውም ወገን የማይጠቅሙ የህዝብ ጠላቶች የሀገርና የወገንን ጉዳይ ለጥቃቅን ጥቅማቸው የሚሸጡ የትውልድ አተላ ስለሆኑ እግዚአብሄር በቸርነቱና በሀይሉ ቀናውን አስተሳሰብ እንዲሰጣቸው እየተመኘሁ ይህን ከመሰለው የትውልድና የታሪክ አተላነት የሚላቀቁበትን ልብ ለማግኘት በቂ ጊዜ ስላላቸውማሰብና ደጋግመው ማሰላሰልከዚያም ስለአቋማቸው መወሰን ይኖባቸዋ እላለሁ:: ለወገን ውድቀትና መጠቃት ለአገር መዋረድና መበታተን ለዲሞክራሲና ለሰብአዊ መብት መታፈን መሣሪያ የሚሆኑ ሆዳም አማሮች ካሉአጥብቀን እንመክራቸዋለን::



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

በተለይም ወጣቱ ክፍል የአባቶቹን ዓላማያለጥርጥር እንደሚያነሳ ሙሉ ዕምነት አለኝ::በሌላ በኩል ግን መዐሕድለዐማራው ሕዝብ ሕጋዊ መብት መጠበቅ እና ለኢትዮጵያ አንድነትናሉአላዊነት መከበርየሚያደርገውንትግልበቆራጥነትመቀጠሉንይገፋበታል:የቀቋ ቋመበት ዓላማው ስለሆነም በማንኛውም ቦታ የሚፈፀሙትን ኢዲሞክራሲያዊ እንቅስቃሴዎች መታገሉን በግንባር ቀደምትነት ማስተባበሩን ይቀጥላል::

በመጨረሻም ላሳስባችሁ የምፈልገው ዛሬ ዓለም በሥነ ጥበብ መጥቃ በመሄድ አገርን በማልማትና የህዝብን ማህበራዊ ፍላጎት በማርካት ከፍተኛ እርምጃ የሚካሄድበት ጊዜ መሆኑን ነው:: በዚህም መሰረት ሀገራቸው ምድረ በዳ የሆኑ አገሮችም እንኳን በሠላም በመስራታቸው ለሕዝባቸው ብዙ ጥቅም እያስገኙ ናቸው:: ኢትዮጵያ ሀገራችን በምድር ላይ ያለች ገነት መሆኗን ሙሶሎኒ ሳይቀር ሲመሰክር ለወታደሮቹ ባደረገው ንግግር «ይህችን የምድር ገነት ውረሱ» ነው ያላቸው:: ስለዚህ ሁላችንም ሕዝብም ሹማምንትም በሰላምና በእኩልነት ተፈቃቅሮ መሥራቱ ጥቅሙ የሁላችንም መሆኑን ተገንዝበን በመሃላችን ያለውን ልዩነት ከማስፋፋትይልቅበመሃላችንሊጎለብት የሚችለውን ስምምነታችንን እንዲጠናከር በማድረግ አርቀን እንድንመለከት ጥሪ አቀርባለሁ::

ኢትዮጵያ በልጆቿ መስዋእትነት አንድነቷና ነፃነቷ ተከብሮ ለዘላለም ይኖራል! አስራት ወልደየስ የመዐሕድ ፕሬዜዳንት::

ንባቤን እንደጨረስኩ ቀና ብዬ ስመለከት ጠበቃውን ከመስኮቱ አጠገብ ቆመው ወደኔ ሲመለከቱ አይን ለአይን ተገጣጠምን:: ከዚያም እረጋ ብለው እየተራመዱ መጡና ከሶፋው ላይ አረፍ በማለት «አነበብከው? » አሉኝ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

# ምዕራፍ አስራ አራት
## ጀግኖች ናቸዉ

ሚያዝያ 22-2001 ዓ.ም. ከቀኑ አስር ሰአት አካባቢ ላይ ከማላውቀው ሰው የስልክ ጥሪ ደረሰኝ:: ወፈር ብሎ ረጋ ያለውና ከስልኩ በወድያኛው ጫፍ እየመጣ ያለው ድምጽ ርጋታን የተላበሰ ከራስ የመተማመን መንፈስ የሚመነጭ እንደነበር በቅላጼው ያስታውቅ ነበር::

«ሄሎ ........ ፈልጌ ነበር::»

«አቤት......... ነኝ ማን ልበል?»

«ስሜ ሽማግሌው ይባላል:: ሽማግሌው እያልክ አናግረኝ»

«እሽ ሽማግሌው ምን ፈልገው ነው?»

« በአንድ ጉዳይ ዙሪያ ላነጋግረህ እፈልጋለሁ::» እንድንገናኝ ትፈቅድልኛለህ?» አለ ፍጹም የተረጋጋው ድምጽ::

«የተፈለግሁበትን ጉዳይ ልወቀውና መገናኘት እንችላለን?»

«ጉዳይ በስልክ ተነግሮ አያውቅም። በቅድሚያ በአካል መገናኘትና መተዋወቅ ይቀድማል::»

«በመጠኑም ቢሆን ስለማንነትዎ በስልክ መግለጽን የሚከለክል ህግ ያለ አይመስለኝም::»

«የቀድሞ የመአህድ አባልና መስራች ነበርሁ "አለ በሣቅ የታጀበ ድምጽ።

«እሽ አቶ ሽማግሌው ::" እንደነዚህ ያሉ ሰዎችን ማግኘ ትና ማናገር እፈልጋለሁ:: መቼ እንድንገናኝ ፈለጉ?»

«ነገ ይመችሃል? የአመቱ ጊዮርጊስ ስለሆነ ታቦት ከገባ በኋላ ፒያሳ ብንገናኝስ?»



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

«ጥሩ አቶ ሽማግሌው ፍቃደኛ ነኝ። የምንገናኝበትን ስፍራና የእርስዎን ምልክት ቢነግሩኝ::»

«እኔ ስለማውቅህ ምልክት መንገሩ አያስፈልግም። የምንገናኝበት ከቤተክርስቲያኑ በስተደቡብ በአሉት ህንፃዎች መዳዳውን ካፌዎች አሉ:: ከነሱ ደረጃውን እንደወጣህ ከፎቁ በረንዳ የመጀመሪያዉ ካፌ ከጃንጥላዎቹ በአንደኛው ስር ተቀምጠህ ጠብቀኝ::»

«እሽ ታቦት እንደገባ ወደዚያ እሄዳለሁ::»

«መቀመጫ እንዳይያዝ ቀደም በል::»

«እሽ አቶ ሽማግሌው:: እንደዝያ አደርጋለሁ::»ከወድያኛው ጫፍ ወፍራም ሳቅ እንዳጀበኝ ስልኩን ዘጋሁ::

በማግስቱ ጠዋት ለቅዳሴ ለመድረስ ማለድ ብዬ ነበር ተነሣሁት። ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ግቢ ስገባ ከማለዳው አስራ ሁለት ሰዓት ተኩል ቢሆንም ምድረ ግቢው ነጫጭ ለብሰው በሚያስቀድሱ ምእምናን ተጨናንቆ ለጠጠር መጣያ የሚሆን ቦታ ያለ አይመስልም:: ከውጭው በር እስከ ቤተመቅደሱ መግቢያ ድረስ ያለው መንገድ በአራት ሜትር ያህል ስፋት ክፍት ሆኖ ወደ ውስጥ የሚገቡና ከውስጥ ወደውጭ የሚወጡ በርካታ ሰዎች ያለመጨናነቅ እንደልብ በስርአት ሠልፋቸውን ይዘው ይተላለፋሉ::

ወደ ውስጥ እየገባ ያለውን ሰልፍ ተከትዬ ወደቤተ መቅደሱ አመራሁ:: የመጀመሪያውን በር ገብተን ከሁለተኛው ስንደርስ መጠነኛ መጨናነቅ ስለነበር ተራ ተጠባብቀን ተላለፍን። ሰአታት ቆመው ያደሩ ምእምናን ሳይሆኑ አይቀሩም በርካታ ሰው ወደውጭ ሲወጡ ከእነሱ በእጥፍ የሚበልጠው ደግሞ ወደ ቤተመቅደሱ ይጐርፋል::ከአድዋ ጦርነት መልስ በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግስት የተገነባው የአራዳው ጊዮርጊስ ቤተመቅደስ አንድ ምእተ አመት ያለፈው ቢሆንም አሁንም ላይ ሲታይ ዘመናዊነቱን እንደያዘ ነበር።



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ይኖራል ብሎ መናገር የሚቻል አይመስልም። ቤተመቅደሱ እዚህ ቀረህ የማይባል ውብና ድንቅ ነው።

ከበሩ ላይ ስደርስ ጫማዬን አወጣሁና ወደ መቅደሱ ገባሁ። ከዋናው በር እስከ ቅድስቱ መግቢያ ያለው ስፍራ ክፍት ነበር። ከዚያ ውጭ ያለው ስፍራ እንደሚዶ ችምችም ብሎ በቆመ ህዝብ ተሞልቶ ውስጡ ከሰዎቹ በሚወጣው ትንፋሽ በመጋሉ እንደሳተ ጉሞራ የሚጋረፍ ሙቀትተሰማኝ።የቅድስቱ ግድግዳዎች በተለያየ መንፈሳዊ ስእሎች ተሞልቷል!! ጊዮርጊስ በፈረስ ላይ ሆኖ ወደ አድዋ ሲዘምትና እዚያም ደርሶ የጣልያንን ጦር ድል ሲያደርግ የሚያስሳየው የስእል ታሪክ የነጭ አንገት ላይ ያረፈ ሰይፍ እንደጨበጠ በሌላ በኩልም ደራጐንን በጦር ሲወጋው ሌሎችም የተለያዩ የመልእክትና የጻድቃን ምስሎች እየሱስ ክርስቶስ በዮርዳኖስ ወንዝ በዮሐንስ ሲጠመቅ ሰባአሰገል ጌታ ወደተወለደበት ቤተልሄም በኮከብ እየተመሩ ሲመጡ እረኞች ህፃኑን ዙሪያውን ከበውት እንስሳት በትንፋሻቸው ሰያሞቁት ዮሴፍና እናቱ ማርያም የተወለደውን ህፃን በስስት ሲመለከቱት የሚያሳዩው ስዕል .......... ሁሉም ነገር ከመቅደሱ እስከ ቅድስቱ ዋልታ ያለው ግድግዳ እነዚህን በመሳሰሉትስእሎች ተሞልቷል።

ሰፊው መጋጃ ወለል ብሎ ተከፍቶ ስለነበር እስከ ቅዱሳን ቅዱሱ መንበር ድረስ ያለው ስፍራ ይታያል። በመቅደሱ በስተሰሜን አቅጣጫ በርካታ ካህናት በጽናጽንና በከበሮ ደስ የሚል ወረብ እየወረቡ ናቸው። ከበሮዉ አንድ ጊዜ ዘገም ሌላ ጊዜ ፈጠን ሲል ለሰውነት ብቻ ሳይሆን ለአእምሮም ደስ የሚል ፈጣን እንቅስቃሴ ያለው ስሜትን ይናኛል። ተራውን እየጠበቀ በሁለት የተከፈለ ቡድን በየተራ በግእዝ ቋንቋ ዝማሜን ሲያሸበሽብ ሰማየ ሰማያት እያደረሰ ይመልሷል። ዜማው አስደሳችና ልዩ ጣእም ያለው ነበር። በነጫጭ ልብስ የደመቁት ካህናት ዜማቸውን እያንቆረቆሩ ጽናጽል ከፍና ዝቅ በማድረግ መቋሚያቸውን በልዩ ኪነታዊ ጥንቃቄ ሲያነሱና ሲጥሉ ስመለከት ለተወሰነ ጊዜ መኖሪያዩ በዚያው ቢሆንልኝ እያስመኘኝ ነበር።



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

የእጣኑ ሽታ ልዩ ስሜት አለው፡፡ መቅደሱ በእጣን ጢስ ቢታፈንም ደስታን ይሰጣል እንጅ አይከረክርም። ከጠዋቱ ሶስት ሰዓት ሲሆን የቅዳሴው ስርዓት አበቃና ቀሳውስቱ ታቦተ ህጉን ወደውጭ ለማውጣት እንዲያመቻቸው ለማድረግ በመቅደሱ ያለነው ቦታ እየለቀቅን እንድንወጣ በድምጽ ማጉያው ተጠየቅን፡፡ ቤተመቅደሱን በአምሳ ሜትን ያህል እርቀት ክብ ሰርተን ቆመን ስንጠባበቅ ካህናቱ ታቦቱን እንዳጀቡ ከመቅደሱ ወጡና የቤተመቅደሱን በረንዳ አንድ ዙር ከዞሩ በኋላ የመጀመሪያዎቹን ደረጃዎች በመውረድ በስተሰሜን ወደሚገኘው ዋና በር በካህናት እንደታጀበ ወረደና ወደ ውጭ መንገድ ጀመረ፡፡

ታቦቱ ፈጠንና እረጋ እያለ ዋናውን የውጭ በር ከወጣ በኋላ በቀጥታ ያመራው የአፄ ምኒልክ ሃውልት ወደ አለበት አደባባይ ነበር፡ ለመቁጠር በማይቻል ህዝብ እንደታጀበ ሃውልቱን አንድ ጊዜ ከዞረ በኋላ ከሃውልቱ በስተደቡብ ከመዘጋጃውና ከቤተክርስቲያኑ መሃል ከሚገኘው ሰፊ አስፋልት ላይ ምንጣፍ ተነጥፎለት ሲቆም ካህናቱ ወረብ ጀመሩ። በካህናቱ ሲንቆረቆር የነበረው ወረብ አበቃና የጊዮርጊስ ገድል ተነበበ፡፡ *ከዚያም በአደዋ ላይ የሠራው ታምር ቀጠለ፡፡ እነኝህ ሁሉ እስከሚጠናቀቁ* ከቀኑ ዘጠኝ ሰአት ሆኖ ነበር፡፡ስነስርዓቱ አብቅቶ ታቦቱ ወደ ቤተመቅደሱ ሲመለስ እኔም ወደቀጠሮዬ ቦታበውጭ ተመለስሁ፡፡

ከካፌው በረንዳ በአንደኛው ጃንጥላ ስር ያልተያዙ ሁለት መቀመጫዎች በማግኘቴ ፈጣሪን እንደልዩ እድል አመስግኜ በአንድዋ ላይ ተቀመጥኩና አንደኛዋን ሰው እንደይቀመጥበት መከላከል ጀመርሁ፡፡ በስተደቡብ ያሉትን የአድማስ ርቀቶች በአይኔ እየተመለከትሁ ነበር አንድ እጅ ትከሻዬን ሲዳስሰኝ ተሰማኝና ከመቀመጫያዬ ለመነሳት ስሞክር በዚያዉ ጫን ብለው አስቀሩኝና እሳቸውም ተቀመጡ፡፡በድንገት ግስላ እስከሆኑበት ድረስ ፍጹም በተረጋጋ ስሜት ነበር እያዋሩኝ የቆዩት፡፡ ስለመጽሐፌጠየቁኝና መልስ ሳይጠብቁ በድንገት በእልህ እየተንቀጠቀጡ መናገር ጀመሩ፡፡ሁኔታዎችበድንገት በመቀየራቸው ተገርሜ ዝም ብዬ ከመመልከት በቀር አንዳችም



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

አይነት መልስ ሳልሰጣቸው አዳምጣቸው ጀመር:: ከትንሽ ደቂቃዎች በፊት ቅዱስ ሊያሰኛቸው የሚችል ትህትህና የነበራቸው የእድሜ ባለፀጋ በድንገት አራስ ነብር ሲሆኑ መመልከት አስደናቂ ነበር::

((በብእርህ ዋሽተኸል:: ሸምጥጥ አድርገህ ነው የዋሸኸው!! ስለ አንተ ኃይሉ ሻውል ብእርህ እውነትን አልተናገረም!! አንዲትም ቅንጣቢ እውነትን ያልያዘ ከንቱ ውዳሴ ያነበነበውን ብእርህን ሰባብረህ ጣለውና ላወደስከው ሰው በአሽከርነት ገብተህ መኪና ንዳለት!! አለዚያም ደግሞ ብእርህን እውነት አናግረውና የዋሸኸውን ሕዝብ እሱ ከሚጠይቅህ በፊት አንተ ይቅርታ የምትጠይቅበትን አጠር ያለጽሑፍጽፈህእውነትን ተናዘዝ::ሁለተኛም እንደዚህ ያለ የነውር ሥራ እንደማትደግመው ቃል ግባለት))::

ቀና ብዬ ተመለከትኳቸው!! ፍፁም ጤነኛ ሰው ነበሩ:: ትኩር ብለዉ እየተመለከቱኝ ስለነበር የተሳሳቱ መሰለኝ:: እኔን የመሰለ ሰው የሆነ ነገር ጽፎ በሬድዮ ሲተላለፍ ሰምተው መሆን አለበትም ስል አሰብሁ::

በደንብ አድርጌ ተመለትከትኳቸው:: አፍሮ የተበጠረው ሽበት ጸጉራቸውየተባዘተጥጥይመስላል!!ጠይምፊታቸው በነጭ ሪዝ ቢሸፈንም ወዘናቸው ይስባል:: ቀጭን እረጅም ናቸው:: ትናንሽ አይኖቻቸው ከጥልቅ ጉድጓድ ውስጥ እንደቀረ ጭላጭ ውሃ ቢርቁምየደከሙ አልነበሩም:: ምንም እንኳን በንዴት ሃይለ ቃል እየተናገሩኝ ቢሆኑም የአነጋገራቸው ቅላፄ አረጋዊ ደርዝን የለቀቀ አልነበረም::ከምንም በላይ የሳበኝ አለባበሳቸው ነበር:: ሙሉ ነጭ ሱፍ በሰማያዊ ሸሚዝ ባለ ቢራቢሮ ሮዝ ከራቫትና ጥቁር ቡኒ ጫማ ዝብርቅርቅ ያለ:: በላዩ ላይ ነጣ ያለ የሱፍ ካፖርት ከአንገታቸው ላይ ከሱፍ የተሰራ ነጭስካርቭ በጠቅላላው ሽክ ብለው ለብሰዋል::

«አባት የተሳሳቱ መሰለኝ)) አልኳቸው ለክብራቸው ስል ከተቀመጥሁበት እየተነሳሁ::



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

«አልተሳሳትኩም ልክ ነኝ። አሁንም ደግሜ እነግርሃለሁ የተሳሳትክ አንተ ነህ!! ታሪክ ይቅር የማይለው ሥራ ሰርተሃል።» ዙሪያዬን ተመለከትሁ። በመዝናኛው ሥፍራ የተቀመጡት በመሉ ሃሳባቸው ያለው በየግል ጉዳያቸው ላይ ስለነበር ማንም ወደኔና ወደ ሽማግሌው ያተኮረ አልነበረም።

«እረጋ ብለው ጥፋቴን ቢነግሩኝ ከመቀጫ ጋር ለመቀበል ሙሉ ፍቃደኛ ነኝ።» አልኳቸው።አንተየነገረኝምሰውአንደበተርቱእ መሆንክን ነበር። አንደበትህ የተሳለ ሰይፍን እደሚያደንዝ ነግሮኛ ል። አንደበተህና ትህትናህ ይስባል። በእርህ ግን የህልም እንኳሴ ጦር ነው። የወጋው አይድንም!! ሾተላይ ነው። ጥላ ወጊ ታውቃለህ? ብእርህ የጥላ ወጊ ነው።»

«እሽ ሁሉንም እቀበላለሁ።» አልኩና ላባብላቸዉ ሞከርሁ።

«የመጽሐፍህ ርእስም እንደ አንደበትህ ሁሉ ይስባል። እናም እርእሱ ሳበኝና ገዛሁት። በቀጥታ ያመራሁት ወደቤቴ ነበር። እቤት እንደገባሁ ንባብ ከፍሌ ለመግባት ጊዜው ያጠረብኝ ስለመሰለኝ ከሳሎን ተቀመጥሁ። እውነቱን ለመናገር ምሳ አልበላሁም። አስራ አምስተኛው ምእራፍ ላይ ስደርስ ነው ጦርህ የወጋኝ። ያን ጊዜ ወደፊት መቀጠል አልቻልኩም። ቃትቼ ፀጥ ብዬ ቀረሁ» አሉኝና ትኩር ብለው ተመለከቱኝ።ዝም ብዬ አዳምጣቸው ስለነበር እብድ እንዳልነበሩ ተረድቻለሁ። ትልልቅ ሰዎች ሲቆጡም ሆነ ሲያወድሱ ዝም ብሎ ሲያደምጧቸው ደስተኞች እንደሚሆኑ ጠንቅቄ አውቃለሁና ሃሳባቸውን እስከሚያጠቃልሉና እንድናገር እስከሚጋብዙኝ ድረስ መጠበቅ ነበረብኝ።

«መጸሐፍክን ምእራፍ በምእራፍ ተንትነህ ስለማንና ስለምን እንደ ጻፍህ እንደምታውቀው እገምታለሁ።» አሉኝ እረጋ ብለው። .

«ይመስለኛል)) አልኳቸው በትህትና።»



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

«አስራ አምስተኛው ምእራፍ ላይ የጠቀስከውን ባለታሪክ ግን በትክክል እንደማታውቀው እርግጠኛ ነኝ!! አለዚያም ደግሞ አድር ባይነት አሳይተሃል።»

ራሴን በዝግታ ወዘወዝኩና ((በኔ መንገድ እርግጠኛ ነበርሁ)) ስል መለስኩላቸው።

"እንደዚያ እየካብህ የቆለልከውን ሰው ከኔ በላይ የምታውቀው ከሆነ እኔ ማመዛዘን የማልችል ዱባ ራስ መሆን አለብኝ!! ልልህ የፈለግሁት ሰውን መገመት የማልችል ደካማ ልሆን እንደምችል ነው። የምገምት ከሆነ ግን እውነቱ በተቃራኒው መሆን አለበት)) አሉኝና ሳቅ በማለት ተመለከቱኝ። ተናንሽ ነጫጭ ጥርሶቻቸው ረጅም የእድሜ ጉዳና ተጉዘው የመጡ አይመስሉም!! እንደታጠበ ሲኒ ያብረቀርቃሉ።ትክ ብዬ እየተመለከትኳቸው በድጋሜ ራሴን አወዛወዝሁ።

«ሲበዛ ትሁት ነህ............» አሉኝና ትከሻዬን በፍቅር አይነት መታ አደረጉኝ!! አልተቀየምኩህም ለማለት እንደሆነ ገባኝ።

በአስራ አምስተኛው ምእራፍ ላይ ስለጠቀስኩት ባለታሪክ እሳቸው ብቻ ሳይሆኑ ብዙ ሰዎችም ተመሳሳይ ሃሳቦችን ስንዝረውብኛል። እንደሳቸው ግን በተግሣጽ የወረፉኝ አልነበረም። ምናልባትም እንደዚያ በሃይለ ቃል የሚናገሩት የእድሜአቸውን አጥር በድፍረት እንደማልዘል ገምተውኝ ይሆናል። የፈለጉትን ቢሉኝም ያንን ግዙፍ የእድሜ አጥር ለመነቅነቅ ልቤ አይፈቅደውም።የሸበትን የግዝፈት ሃይል በመረዳት ያደግሁበትን ማህበረሰብ ማመስገን እንደሚገባኝ አውቃለሁ!! የህጐች ህግ ሊባል የሚገባው ነገር ካለ እምነትና ባህል መሆን አለበት። በተለይም ባህል በየትኛውም አገር ባሉት ሕዝቦች ውስጥ እንደህግ ሆኖ ያስተዳድራል!! አገራችን ኢትዮጵያ ከሌሎች አገራት በባህልና በእምነት በኩል የታደለች ስለመሆኗ ሽንጥን ገትሮ መመስከር



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ይቻላል። ከሰሜኑም ሆነ ከደቡቡ ከምስራቅም ሆነ ከምእራብ የአገራችን ሕዝቦች ጋር ያለውን የባህልና የእምነት መስተጋብር በተለያዩ መንገዶች ለማወቅና ለመረዳት በአደረግሁት ጥረት በመጠኑም ቢሆን ልረዳ ችያለሁ።ከሽማግሌው ጋር ለረጅም ሰዓት ቆይታ ስናደርግ ብዙ ጉዳዮችን እያነሳን ከአለፈው ታሪክ እያጣቀሱ ይጠቅማል ያዘው እያሉኝ ስንማማር ቆይተናል።ሽማግሌው የእድሜ ብቻ ሳይሆን ጥሩ የቋንቋ ሊቅም ናቸው። ከአገር ውስጥ ቋንቋዎች ግእዝንና አማርኛን ኦሮምኛን ትግሪኛንና ሲዳምኛን አቀላጥፈው ይናገራሉ።

ስለቋንቋ ችሎታቸው አልተገረምኩም። የተወለዱት ባሌ ጠቅላይ ግዛት ዋና ከተማ ጐባ ስለሆነ አማርኛና ኦሮምኛ ሁለቱም የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ነበር!! በስራ ዘመናቸውም የሲዳሞ ጠቅላይ ግዛት ምክትል አገረ ገዥ በሁዋላም የኤርትራ ክፍለ ሃገር የከረን አውራጃ ገዥ ሆነው ለአስራ አምስት ዓመታት በዝያው ስለቆዩ ትግሪኛንም በደንብ አቀላጥፈው ይናገራሉ።

እንደሳቸው አጣርቼ እናገራለሁ ባልልም ሁሉንም ቋንቋዎች እሞክር ስለነበር በፊት የተናደዱብኝን ያህል ወደኋላ ላይ ሳይደሰቱብኝ የቀሩ አይመስለኝም። ብቻ ተግባብተናል። ያ ቁጣና እልሃቸው ጠፍቶ ከፊታቸው የማነበው ርህራሄና ትህትናን ነበር!! ብሔራቸውን ግን ለመጠየቅአልሞከርኩም። ሁለመናቸው ሁሉ ነገራቸው ሽታው ግምት አለኝአንድነት በመሆኑ ብሔር ብጠይቃቸው እርግጠኛ ነኝ በዚያችው ቅጽበት በተቀመጥኩበት ትተውኝ ይጠፋሉ።

ትናንሽ ጥልቅ አይኖቻቸውን ከአድማስ ጠርዝ ላይ የእሳት አለሎ መስላ በደመና ከተንጠለጠለችው የምሽት ፀሐይ ላይ እንደተከሉ ምንም ሳንነጋገር ብዙ ደቂቃ ቆየን።የአድማሱን ጠርዝ ይዞ የተጋገረው የደመና ባዘቶ ደም የተነከረ ሽማ መስሏል። የሽማግሌው አይታ ወደዚያዉ ሳበኝና እኔም በአድማሱ ጠርዝ ላይ ከአለው የተፈጥሮ ትእይንት ላይ ለብዙ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ደቂቃ አይኖቹ ተጣብቀው እንዳሉ ከየት መጣ ያልተባለው ጥቁር ደመና ቀስ በቀስ እየተሳበ ያንን የተፈጥሮ ትርኢት ወደ ጽልመት ሲለዉጠው ፀሐይም የመጨረሻ ስንብት አድርጋ በአድማሱ ተዋጠች፡፡ከተፈጥሮው ትርኢት አይኖቻችንን ስንመልስ

«አየኸው የተፈጥሮን ተለዋዋጭነት?» አሉኝ!!

«አዎን፡፡ተፈጥሮ በራሱ ሕግ ድንቅ ትርኢቶችን ይፈጥራል፡፡» አልኳቸው፡፡

«ልክ ነህ!! ግን አንድ ያልተረዳኸው ነገርም አለህ፡፡ ተፈጥሮ የምትለዋወጥ ከሆነ አንተ ታዲያ ከምን እምነት ተነስተህ ነው አንድ ግለሰብ ፍጹም አድርገህ ልታጭበረብረን የሞከርከው?» አሉኝ እየሳቁ፡፡

«ስለሰምክርዎ አመሰግንዎታለሁ!! ሁሉንም ነገር እንድገነዘብ አድርገውኛል፡፡» ስላቸው፡፡

«ጥሩ..........» አሉኝ ሳቅ ብለው «መልካም ነው፡፡ ግእዝ የሆነው ነገር ጸንቶ በማይቆምበት አለም ላይ አንተ ስለሰው ፍጹምነት ልትሰብከን ስትነሳ መናደድ ይነሰኝ ታድያ? አየህ ሁልጊዜ አንደኛው በአንደኛው ይዋጥና ይሸፈናል፡፡ ሁነቶች ሁሉ ይቀያየራሉ፡፡ ብርሃን በጨለማ ይዋጣል፡፡ ጨለማም በብርሃን ይገፈፋል፡፡አንደኛው ከአንደኛው አይበልጥም፡፡ አንደኛውም ከአንደኛው አያንስም፡፡ ሁሉም እኩል ስልጣን አላቸው፡፡ ጨለማውም ሆነ ብርሃኑ እኩል የሆነ ዋጋ አላቸው፡፡ጠዋት ሁሉም ወደየምላዱ ተሰማርቶ ነበር፡፡አሁን ደግሞ ወደቤቱ ለመግባት እየተጣደፈ ነው፡፡ለተረኛው ለመልቀቅ፡፡አሁን የኔና የአንተም መሰነባበቻ መድረሱ ነው)) ትንሽ እንደማሰብ ብለዉ

«ፕሮፌሽሩ ኃይሉ ሻውልን የመአህድ የውጭ ግንኙነት ሆኖ እንዲሰራላቸው አስጠግተውት ነበር፡፡እሱ ግን ምን ይሰራ እንደነበር ታውቃለህ አማራውን ከኢትዮጵያ ምድር ለማጽዳትና ነፃነት ለማወጅ ከሚንቀሳቀሱ ኃይሎች ጋር የምስጢር ግንኙነት



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

በማድረግና ኢህአዴግን በመጣል ኦሮሞን ወክሎ ኢትዮጵያን ለመምራት ከኦነግ መሪዎች ጋር ህብረት ፈጥሮም ነበር:: ይህንን ከሰሙ በኋላ ነው ኘሮፌሰሩ ከውጭ ግንኙነት ስራው አግደው ያባረሩት!! የሞቱለትን ድርጅት አፍርሶ በራሳቸው ቢሮ ውስጥ የራሱን ፓርቲ በመመስረት በቀሉን ተወጥቷል:: ይህንን ሰው ነው ከመልካምም ወደ ፍጹማዊ መልአክነት ልትለውጠው የሞከርከው!! ይቅርታ አድርግልኝና ስለሱ የፃፍከውን አንብቤ ስጨርስ ምን እንደተሰማኝ ታውቃለህ? ይህ ሰው ከደራሲነት ወደ አዝማሪነት ተቀየሯል የሚል ነበር::ስለሃይሉ ከሰጠኸው ትረካ በቀር ሌላው እንከን የማይወጣለት ፈጣንና ልብ አንጠልጣይ ትረካ በመሆኑ በመጨረሻዋ ሰዓት አመስግኜህ እንለያይ:: ከመቸት አመራረጥህ እስከ ታሪክ አወቃቀርና ገጸ ባህርይ አሳሳልህ ከድንቅ የቃላት አወቃቀር ጋር እንከን የለሽ ጥሩ ስራ መሆኑን ስነግርህ በኃየሉ የበደልከኝን በሌላው መጽሐፍህ እንደምትክሰኝ ተስፋ በማድረግ ነዉ አሉኝ·ሽማሌዉ::

«ወቀሳዎን በሙሉም ባይሆን በከፊል ለመቀበል የምገደድ ይመስለኛል:: ከምርጫ ዘጠና ሰባት በኋላ እርስዎ የተሰማዎትን አይነት ስሜት በኔም ውስጥ እንደተጫረ በእርግጠኝነት እነግርዎታለሁ:: ለዚህም ነው ወቀሳዎን በከፊል እቀበላለሁ ያልኩት!! እንዲረዱኝ የምፈልገው እውነታ አለኝ:: እኔ ጥብቅ ምስጢርን የጻፌኩት በሰማንያዎቹ መጨረሻ አለዚያም ደግሞ በዘጠናዎቹ መጀመሪያ ላይ ነበር::

እንጂነሩ ከውጭ ተጠርተው መአህድን እንዲመሩ በተመረጡበት ወቅትም ድርጅቱን አፍርሰው ህብረብሔር ፓርቲ አድርገው ሲመሰርቱ አብዛኛው የቀድሞ አባሎች ጥለው ወጥተው ስለነበርነበር በዚህ ዙሪያ በ96 መጨረሻ ላይ አነጋግሪያቸው እንደነበር አስታዉሳለሁ!! በዚህ ወቅት እኔን ለማሳመን ብዙ ምክንያቶችን ደርድረውልኝእንደነበርምአውቃለሁ::ይናገሩ የነበረው እራሳቸውን ምሳሌ አድርገው ከኦሮሞና ከአማራ የተወለዱ መሆናቸውን ሲሆን ምረጡ ቢባሉ ግን የመንታ እናት ማንን ከማን ለይታ ትመርጣለች የሚል ምሳሌ በማጣቀስ ስለነበር



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ማመን ብቻ አይደለም በሚነግሩኝ ምክንያት ለጊዜው ደስተኛም ነበርሁ:: እኔ ጸሐፊ እንጂ ነብይ አይደለሁም)) ስላቸው ሽማግሌው የምጽአት ሳቅ ስቀው «መጽሐፉ የታተመው ሃይሉ በእስር ላይ እያለ እንደነበር እየነገርከኝ ነው?»አሉኝ።

«ትክክል:: መጽሐፌ ታትሞ የወጣው ሀምሌ ሰባት ቀን 1999ዓ.ም. ነው:: እነሱ ጠፋተኝነታቸውን አምነውና መንግስትና ህዝብን ይቅርታ ጠይቀው የተለቀቁት ነሐሴ ይመስለኛል:: ወሩን እርግጠኛ ባልሆንም መጽሐፉ ሁለተኛው ህትመት እገበያ ላይ ሲውል እንደተፈቱ ግን በእርግጠኛነት እነግርዎታለሁ::»

«እንደዚያ እያሞካሸህ ያጋነንከው ኃይሉ በኢትዮጵያ ሕዝብ መካከል እራቁቱን ሲቆም ስትመለከት ምን ተሰማህ?»

«አዝኛለሁ: በተለይም በዶክተር ብርሃኑ ነጋና በኢንጂነሩ መካከል በነበረው የመዘላለፍ አተካሮ በትክክል ያልተረዱት አንዳንድ የጉራጌ ብሔረሰብ አባላት በቃላት እንደዘለፉኝም አስታውሳለሁ::»

«አልገባኝም? ጉራጌዎቹ ለብርሃኑ ተደርበው ነው:»

«እንደሚታወቀው አብዛኛው የመጽሃፍ ነጋዴ የጉራጌ ብሔር ተወላጅ ነው:: በመጽሐፉ ላይ የኢንጂነሩ ፎቶ ስለነበር አንዳንዶቹ ፎቶውን ላለማየት ሲሉ መጽሃፌን ተረክበው ለመሸጥ ፍቃደኛ አልነበሩም::»

«አየኸው አይደል ያንተን ንጉስ የስነልቦና ብቻ ሳይሆን የኢኮኖሚም ኪሳራ አድርሶብሃል:: ሃይሉ አንተን ብቻ ሳይሆን ሰባ ሚሊዮን ህዝብንም አክስሯል:: በወቅቱ ያልተሳሳተ አለ ብዬ ለመናገር ይከብደኛል:: እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ባያስባት ኖሮ ሃይሉ እንደተመኘው አስራ አምስት ሺህ ሰው አዲስ አበባ ላይ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ጭዳ አድርጐ የነሱን ደም በመረማመድ ወደ ስልጣን ቢወጣ አገራችን በአፍጋኒስታን በኢራቅና በሶማሌ ከታዩው በባሰ መለኩ የትርምስና የደም መሬት ከመሆን አትዘልም ነበር!! ይህችን አገር እግዚአብሔር ሲያስባት በመኢአድ ቢሮ ውስጥ እርስ በርስ ጠብ ጀመሩ!! በውስጥ የበነሩት አባሎች ሁለት ቦታ ተሰንጥቀው አንደኛው ግሩፕ አምባገነን ስለሆናችሁ ከእናንተ ጋር አልሰራም ሲል መግለጫ አውጥቶ ወጣ!! ሃይሉ በወቅቱ «እነኝህ ግለሰቦች የወያኔ ተላላኪዎች ሆነው ስላገኘናቸው አባረናቸዋል።»ብሎ መግለጫ ሲሰጥ በወቅቱ በነበረው ገናናነት እውነት አይደለም ብሎ የተከራከረ አይደለም ስለተገነጠሉት ሰዎች ያዳመጠም አልነበረም። እነሱ ግን ከልክም በላይ ልክ ነበሩ።»

«ከተገነጠሉት ውስጥ እርስዎም ነበሩበት ማለት ነው?»

«የለሁበትም!! እኔ ቀደም ብዬ ነው ከድርጅቱ በራሴ ፍቃድ የወጣሁት። መአህድ ከፈረሰ በኋላ የተወሰነ ጊዜ አይቻቸው ለቅቄ ወጣሁ። በዚህም እራሴን እንደ እድለኛ ነው የቆጠርኩት!! ከአውሮፓ እየተመጸወተ በሰበሰበው ብር ድንጋይ የሚወረውርና ጐማ የሚያቃጥል ቡድን አሰማርቶ የንጹሐንን ህይወት ጭዳ ከአደረገ በኋላ የምኒልክ ቤተመንግስት ምኞቱ ህልም መሆኑን ሲረዳ እንደነጠላ ያረጀች ህይወቱን ለማትረፍ ሲል የስድብ ግባስ ሲጥልበት በነበረው ኢህአዴግ ጫማ ላይ ተደፍቶ ምህረት ሲማጠን ሴቶቹ እንኳን አልቀደሙትም።

ኢህአዴጐች ጀግኖች ናቸውና በአላማቸው ባልወዳቸውም አከብራቸዋለሁ። የነሱ እናት ቀና ብላና በኩራት ትክሻዋን እሰበቀችና ሽንጧን እያውረገረገች ትራመድ። የጀግና እናት መኩራት የጥንት ልማድ ስለሆነ ትኩራ። ሚስትም ልቧ በሐሴት ይሙላና ጉሮዋሽበዬ አንተን አንተን ይልሃል ግዳይ እያለች እሷም እንደ አማቷ ከጀግና ባሏ ጀግና ልጅ ለመውለድ ትማልል። የአንተ አለቃ እናትና ሚስት ግን......... > አሉኝና ይስቁ ጀመር ሽማግሌው።እኔም በኔም አብሬአቸዉ እስኪበቃኝ ደረስ ሳቅሁ!!



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ከዚያም «የኔን ጥፋተኝነት ስረዙልኝ ማለት ነው?» ስል ጠየቅኋቸዉ!! «መጀመርያም እኮ ሙሉ በሙሉ መአቀብ አልጣልኩብህም:: ለመአቀብ የሚሆን ምን አቅም አለኝ:: የተናገርኩህ ለወቀሳ ያህል የተሰማኝን ለመግለጽ ብቻ ነው:: አሁን ግን ከምትለኝ አንጻር እሱንም ትቼልሃለሁ::»አሉኝ በእምባ የደፈረሱ ዓይኖቻቸዉን መሀረብ አዉጥተዉ እያደራረቁ!!

«የነገሩኝን በምጽፈው መጽሐፍ እንዳካትተው ይፈቅዱልኛ ል?»ስል ጠየቅሁዋቸዉ።

((ስሜን ካልጠቀስህ))አሉኝ።

«ስምዎ ቢጠቀስ ይደርስብኛል ብለው የሚሰጉበት ችግር አለ እንዴ?» ቀና በዬ ተመለከትሁዋቸዉ።

«ችግር ይደርስብኛል ብዬ አስቤም አላውቅም:: ስሜን ጠቅሰህ ብትጽፈው ኃይሉ በቂም በቀል ነው እያለ ስለኔ ምንም ሲያወራ መስማት ስለማልፈልግ ብቻ ነው::»

«እሽ አመሰግናለሁ!! ሽማግሌዉ እያልኩ ብጽፍስ ይፈቅዱልኛል?»

«ሽማግሌው? ጉረምሳው ብለህ ፃፍ!! ደግሞ ሞት ያጠላበት ሽማግሌ አድርገህ ስለህ በጣረሞት እንዳታስበረግገኝ» አሉኝ እየሳቁ::

«እንደዚያእንኳንአላደርግም»አልኳቸው እኔም አብሪያቸው እየሳቅሁ::በመጨረሻም ስለሻምበል ሚካኤል ያውቁት ከሆነ በማለት አንዳንድ ነገር ስጠይቃቸው በደንብ አድርገው እንደሚያውቁትና እሱ በታሰረበት ወቅት እሳቸውም ታስረው በሁለትዓመታቸውከእስርመለቀቃቸውንአጫወቱኝ::የመታሰራቸው ምክንያት ምን እንደነበረ እንዲገልጹልኝ ጠየቂያቸው መነሻው በሰሜንሸዋ ይንቀሳቀስ በነበረው አማፂ ሐይል ተጠርጥረው በመጨረሻ አቃቢ ህግ በሳቸው ላይ የተሟላ ማስረጃ ባለማቅረቡ ከስር መለቀቃቸውን ነገሩኝ::አማፂው ወይም የሰሜን ሸዋ አርበኞች ግንባር የተባለ ሃይል በትክክል ይመራ የነበረው በኘ ሮፌሰር አስራት ነበር ወይ የሚል ጥያቄም



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

አቅርቤላቸው ነበር። ቃል በቃል ነበር ብለው ባይነግሩኝም በተዘዋዋሪ መንገድ ግን « ጉዳይክን ለሚመለከተው ክፍል አቅርበህ ሰሚ ስታጣ ያዋጣኛል ያልከውን መንገድ ብትከተል ወንጀሉ ከምን ላይ ነው?» የሚል መልስ ሰጥተውኛል። ከዚህ መልሳቸው መረዳት የሚቻለው ፕሮፌሰሩ ንቅናቄውን መምራት ብቻ ሳይሆን ሃይልን እንደ አማራጭ መጠቀማቸውን ጭምር ያዉቁ አለዚያም ደግሞ ያምኑበት እንደነበር ነው።ሽማግሌው በመጀመርያ ጀማሪ ንክ ያልመሰሉኝን ያህል ወደመጨረሻ ላይ ጭዋታቸውእየሳበኝብዙአብረውብዙ እንዲቆዩ ፈለግሁ።አይዘዉም እንጂነሩን ቃለመጠይቅ በአደረግሁላቸው ወቅት የመለሱልኝን መልስ እንዳስረዳቸዉ ጠየቁኝ።

«በድምጽ ህዝብ ያሸነፈውን መንግስት እናንተ በአመጽ ለመጣል በአደረጋችሁት የስትራተጂ ስህተት የብዙ ሰዎች ህይወት ለማለፍ ችሏል። ይህም የሆነበት ዋናው ምክንያት እናንተ የአመጽ መንገድን እንደትግል አማራጭ በማድረጋችሁ እንደነበርየህዝብ እምነት ነው።»የሚል ጥያቄምአቅርቤላቸዉ ነበር።

«ስህተቱ እንደስህተት ሲታይ የህዝብ አስተያየት ትክክል ነው። እንደ ትግል ስልት ሲታይ ግን ያለመስዋእት የተገኘ ድል በአለማችን የታዬም ሆነ የተመዘገበ የለም»የሚል መለልስ ሰጥተዉኝ ነበር!!

«እነሱ የድሃውን ልጅ ቀስቅሰው ወደ ነደደ እሳት ሲከትቱት የነሱ ልጆች ግን ቀደም ሲል ወደተዘጋጀላቸው የሰለጠነው አለም ሄደዋል። ከዘህ በተጨማሪም ህዝቡን በርታ አለንልህ እያሉ ወደሞት እየገፉት ራሳቸውን በህንፃዎቻቸው ውስጥ ቀብረው ቆይተው በጨረሻም እስር ቤት ገብተዋል። ከእስር ከተፈቱም በሁዋላ ለበደሉት ህዝብ የሞራል ካሳ አልከፈሉትም!! የሚል አስተያየት አለ። ይህንን እንዴት ይቀበሉታል።»ብያቸዉም ነበር።

«አባባሉ ትክክል መሆኑን አምነዉ ከዚያ ውጭ በግለሳቸዉ ቤተሰቦቻቸው ለተገደሉባቸዉና ጉዳት ለደረሰባቸዉ ወገኖች ከስር እንደተፈቱ በጽህፈት ቤታቸዉ የመጽናኛ እርዳታ እንዳደረጉላቸጠ መልሰዉልኛል። ይህም



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ወደፊት የሚቀጥል ነው» ብለውኝ ነበር።

«ከደረሰው ጉዳት አንፃር ሲታይ ያደረጉትን እርዳታ በቂ ነው ብለው ያምናሉ?»በማለት ጠይቂያቸውም ነበር።

«አለም እኮ ከዚህ የከፋ ብዙ ችግሮችን እያስተናገደች ነው ከዚህ የደረሰችው፡፡ ስለዚህ የመጀመርያው ታወቃሽ ልንሆን አንችልም))አሉኝ በግዴለሽነት፡፡

«በምሁራኖች ትንትና መሰረት» ኢህአፓ የኢትዮጵያን የፖለቲካ ሂደት ለሰላሳ አመታት ወደኋላ ጉትቶታል፡፡ ቅንጅት ደግሞ ከነሁሉም ገድሎ አብሮት ወደመቃብር ወርደ» ብለዉ ይተቻሉ!! እርስዎ ለዚህ ምን ተጨባጭ መልስ ይኖርዎታል?»ስላቸዉም

«ይህ የደካማ ምሁራኖች የምናብ ስሌት ነው፡፡ ቅንጅት ያለው በህዝብ ልብ ውስጥ ስለሆነ አይሞትም፡፡»በማለት በኩራት መልሰዉልኛል።

«ቅንጅት በምርጫ ዘጠና ሰባት እንቅስቃሴ ወቅት ከፍተኛ የሆነ የገንዘብ እጥረት ደርሶበት ስለነበር አመራሮቹ ከውጭም በአገር ውስጥም ያሉ ሃብታሞችን እርዳታ ጠይቀው ሃብታሞቹ እርዳታውን ለመስጠት ፍቃደኛ ሆነው ብሩን በታማኝነት የሚረከባቸው አካል እንዲያቀርቡ እርዳታዉን ለጠየቁት አካላት መልስ ይሰጣሉ፡፡ የቅንጅት አመራሮችም በቅንጅት ስም ገቢ እንዲያደርጉላቸው ይነግሯቸዋል፡፡ እርዳታ ለጋሾቹ እምነት ባለማሳደሯቸው እርስዎ በግልዎ ካልተረከቡ በቀር እርዳታ እንደማያደርጉ ቁርጥ ያለ መልስ ይሰጣሉ፡ከዚያ በኋላ እርስዎ ቀርበው አስራ አምስት ሚሊዮን ብር ተረክበው በግል አካውንትዎ ገቢ እንዳደረጉና ይህ ገንዘብ የታሰበውም እናንተ መንግስት በምትመሰርቱበት ወቅት ወጭ እንዲደረግ ነበር፡፡ ከሁሉም በፊት እናንተ ቀድማችሁ እስር ቤት ገባችሁ፡፡ ከስር ስትፈቱ ፍቺ መሰርታችሁ ተለያይታችኋል፡፡ እንደ አስተያዬት ሰጭዎች እምነት ከሆነ ብሩ እስከ አሁንም ድረስ በእርስዎ የግል



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

አካውንት እንዳለ ነው የሚታመነው:: ይህ አባባል እውነት ነው ወይስውሸት?»የሚልጥያቄምአቅርቤላቸዉነበር።በወቅቱምየመለሱል ኝ«እንዲሁበወሬ ደረጃ እኔም እንዳንተ እሰማዋለሁ»አሉኝበአጭሩ!!

«እንጂነሩ ከእስር ከተፈቱ በኋላ ሁለት ቀን የፈጀ ቃለመጠይቅ አድርጌላቸው ነበር::»

«እና ምን የተጨበጠ ፍሬ አገኘህበት?» አሉኝ

«ለምጠይቃቸው ሁሉ አሁን እደሚያዩት ቀጥተኛ የሆነ መልስ ከመስጠት ይልቅ ያድበሰብሱታል::»

«ቃለመጠየቅ እንዳደረግህለት ሰምቻለሁ:: የጠየቅኸውም በአዲስ አበባ በስተምእራብ ከሚገኘው የግል መኖርያ ህንፃው ድረስ ሄደህ ነው አሁን አጥብቂ የፈለግሁህም ከመአህድ እስከ ቅንጅት ከዚያ መልስ መኢአድን እስከማቋቋም የሚል የታሪክ መጽሐፍ ለመጻፍ በድርጅቱ ስም ከኢንጅነሩ ጋር ውል መፈራረምክን ስለሰማሁ ስህተህትህን እንዳትደግመከዉ ለማስገንዘብ ነው))አሉኝ።ሽማግሌው ሁሉንም ትክክል ነበሩ!!

«አዎን ተዋውለን ነበር::»

« እና አሁን እየፃፍህ ነህ?»

«ሁሉም ነገር ባዶ ሆኖ አገኘሁት።በዛም ላይ ለመጻፍ የተመቻቸ መንገድ ስለሌለ አቁሜአለሁ::»

«እንደኔ ባትጽፍ ይመረጣል:: እንኳንስ በብእር በወርቅ ብትጽፈው የነሱ ታሪክ ታሪክ ሊሆን አይችልም!! በቃ ይኼው ነው )) አሉኝ ኮስተር በለዉ:: ከዚያም "በል ደህና ሁን ........» ብለዉኝ እጄን ጨብጠውኝ በተቀላጠፈ ፍጥነት መኪናቸውን አስነስተው ተፈተለኩና በአቡነ ጴጥሮስ ሃውልት ቁልቁል ተወንጭፈው ወደ ጉጃም በረንዳ ተሻገሩ::ከፊት ፊት የመዘጋጃ ግዙፍ ህንጻ በስተጀርባዬ የጊዮርጊስ ቤተክርስትያንን ተንተርሶ የተሰራውና በርካታ ካፌዎችን ያጠቃለለው ህንጻ እኔ ከመካከል የአስፓልቱን ጠርዝ እንደያዝሁ ቆሜ ነበር::



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

# ምዕራፍ አስራ አምስት
## ከጠበቃው ማስታወሻ

«አነበብከው?» አሉኝ ጠበቃው::

አንገቴን በአሉታ አነቃንቄ « አወን አነበብኩት» አልኳቸው:: ከዚያም «ብቻ አልፎ አልፎ ካልሆነ በቀር ንግግራቸው በሙሉ ህዝብን ለጦርነት ያነሳሳል የሚል እምነት አላሳደረብኝም:: ያም ሆኖ ንግግሩ ቀላል ተብሎ የሚታለፍ አይደለም:: ለማንኛውም እንደጦርነት መቀስቀሻ ከተወሰደ ሊሆን የማይችልበት ያለ አይመስለኝም » ስላቸው

«በደንብ እንደምትመለከተው ነው የኔም እምነት » አሉኝ አንገታቸውን ከፍና ዝቅ አድርገው በማነቃነቅ::

«በደንብ አድርጌ ነው የተመለከትኩት:: ቃሉ ልብን ስለሚያንጠለጥል ትረካው መስጦኛል::»

«ጥሩ ትንቢታዊ ንግግር ነበር ከንግግራቸው አብዛኛው ተፈጽሟል የሚል እምነት አለኝ::» አሉኝ እንደመሳቅ ብለው

«አንብቤ እንደተረዳሁት ከሆን የኔም እምነት እንደዝያው ይመስለኛል» ስል መለስኩላቸው::

«ጥሩ ተገንዝበሀዋል:: እና በዚህ ንግግር ነው ተከሰው ዘብጥያ የተወረወሩት:: ይህንን የፈፀሙት አካላት አሁን ላይ ሆነው ሲያስቡት ምን እንደተሰማቸው ባላውቅም እንደሚፀፀቱበት ግን ጥርጥር የለኝም»ቁጭትን በሚገልፅ የድምፅ ቅላጼ ተናገሩ ጠበቃው::

«የከሳቸዉ ዋና ምክንያት ይህ ንግግር ብቻ ነው ብለው ያምናሉ?» አልኩና ጠየቅኋቸው ጠበቃውን::

«ታዲያሌላምንምክንያትይኖራቸዋልብለህትገምታለህ?»ሲሉ መለሱልኝ::

«በርግጥ እኔ ይሆናል ብዬ የምጠረጥረው ነገር አለኝ:: ፕሮፌሰር በሰሜን ሸዋ የሚንቀሳቀስ እና አርበኞች ንቅናቄ ግንባር የተባለ ተዋጊ ሃይል



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

እንደነበራቸው ይወራል። መንግስት ንግግራቸውን እንደሸፋን ተጠቅሞ ምናልባትም በዚያ ቂም ሳያስራቸው አልቀረም የሚሉ ወገኖች ስላሉ ከነዚህም አብዛኛዎቹን አግኝቼ ጠይቂያቸዉ እንደመለሱልኝ ከሆነ ሰዎቹ የፕሮፌሰር እስር ዋና ምክንያቱ ጦርነቱ እንጂ ንግግራቸው አይደለም ብለው ያምናሉ »

ትኩር ብለው እየተመለከቱኝ « ያንተስ ግምት?» አሉኝ። «የመታሰራቸው ምክንያት በዚህ ንግግር ብቻ ከሆነ ያንን ያህል የተጋነነ አድርጌ ባልወሰደውም እርሶ ከላይ እንደጠቀሱት በመጠኑ መፀፀታቸው አይቀርም። ነገር ግን ምክንያቱ ይህ እንዳልሆነ በመረጃ የተረጋገጠ ማስረጃ በእጄ ላይ ይገኛ ነው የማነጋግርዎት »ስላቸው ደንገጥ ብለው እየተመለከቱኝ

«አልገባኝም » አሉኝ።

«የሽግግር መንግስቱን በጦር መሳሪያ በተደራጀ ኃይል ለማስወገድ መንቀሳቀሳቸው እውነት ከሆነ ማለቴ ነው» ስላቸው።

«ያም ቢሆን ልክ ነበሩ » አሉኝ በአጭሩ

«ለምን?» አልኳቸው በሁኔታው እየተገረምሁ።

ትንሽ ሲያስቡ ቆዩና « እነሱስ ስልጣን የያዙት በኃይል በጠመንጃ ያለውን ገዥ አስወግደው አይደለም እንዴ » እየሳቁ መለሱልኝ። ሁለታችንም ከተሳሳቅን በኋላ በአምንታ ራሴን አነቃንቼ ሌላ ጥያቄ አቀረብኩላቸው።

«ፕሮፌሰሩተከሰውጥብቅናከመቆምምበፊትያውቋቸውነበር።»

«አዎን » አውቃቸው ነበር » አሉኝ

«በእርሶ እይታ ምንአይነትሰውነበሩብለው የምናሉ?»።ሲበዛ ቁጥብና ዝምተኛ ነበሩ ለማለት እችላለሁ።ሲስቁም እንኳን ከትተከት ብለው ስቀው የሳቸውን ጥርስ አየሁ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ብሎ መናገር የሚችል ሰው አለ ብዬ አላምንም:: ፈገግታቸው ምጸአታዊ ነበር የሚመስለው » አሉኝ

«ከራስዎ ግምት እና ከነበራቸው መሰረታዊ በሀሪይ በመነሳት መንግስትን በጠመንጃ ለመገልበጥ ሞክረዋል የሚባለውን አባባል ይቀበሉታል? » ለዚህ ጥያቄ ፈጥነው መልስ አልሰጡኝም:: ብዙ ሲያስቡ ቆይተው

«በርግጥ ሌላ አማራጭ በይኖር ኖሮ ያደርጉት ይሆናል የሚል ግምት አለኝ:: እንደዚያም የምልህ የስላሙ በር የተዘጋ ቢሆንና በሰላመዊ መንገድ ለመታገል ባይችሉ ማለቴ ነው » አሉኝ

«በእርሶም እይታ መዐሕድ በሰላማዊ መንገድ ሲታገል ምንም የገጠመው እንቅፋት አልነበረም ለማለት ነው?::» እደመሳቅብለውከተመለከቱኝበኋላ«እንደዚለማለትአይደለም::ብዙእን ቅፋቶች እንደነበሩት አውቃለሁ:: ያም ያየሁትና የሰማሁትነበር:: ሆኖም ለዲሞክራሲ ስርአት ግንባታ ገና በጅምር ላይ ለሆነችው አገር እነዚህ እንቅፋቶች ሁሉንም ነገር አስጥለው ከጫካ ያስገባሉ የሚል እምነት ስለሌለኝ ነው:: ሆኖም ግን ብዙ ችግሮች እንደነበሩት እርግጥ ነው:: እያልኩኝ ያለሁት እንደሳቸው ክፉና ደጉን ለይተው የሚያውቁ ሃይልን እንደአማራጭ እንደማይጠቀሙበት እና ከምንም በላይ ደግሞ የአገራቸውን ችግር ከጊዜያዊ ግጭት አብልጠው ይመለከታሉ ብዬ ስለማምን ነው::»

እሳቸውም እኮ በንግግራቸው ላይ «የምናደርገው የሰላም እንስቃሴ መንገድ ከተዘጋና አማራጭ ካጣን» የሚል ማስጠንቀቂያ ነው የጠቀሱት» ስላቸው::

«በርግጥ እንደዚያ የሚል ማሰስጠንቀቂያ አስተላልፈዋል:: ነገር ግን የስላሙ በር በሙሉ ተዘግቶ ነበር ወይ? የሚለው ጥያቄ መነሳት ያለበት ይመስለኛል:: ፕሮፌሰር እንደሚሉት እኮ ድርጅታቸው ቢዘጋና አመራሮቹ አንዳንዶቹ ቢገደሉም የሰላሙ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ትግል አከተመለት ማለት አልነበረም። ይህ አይነት ሁኔታ

አማራጭን አሳጣን ተብሎ በተስፋ መቁረጥ በፍፁም ወደ ጫካ የሚያስኮበልልም አይደለም። ለዲሞክራሲ የታገሉ በርካታ አገራት እኮ ከዚህ በላይ ብዙ መስቃየት ደርሶባቸዋል» አሉኝ ጠበቃው።

«ፕሮፌሰር የጦር ትጥቅ እንደ አማራጭ ወሰደው ከሆነ ስህተት ነበር እያሉኝ ነው? » ስላቸው።

«ለጦርነት መዘጋጀታቸው እውነት ከሆነ ከህግ አንፃር ስንመለከተው ስህተት ብቻ ሳይሆን ወንጀልም ነበር ለማለት ይቻላል» አለኝ እሩቅ እየተመለከቱ

«ለጦርነት የተዘጋጀ ሃይል ያንቀሳቅሱ እደነበር ቢያውቁ ኖሮ ለጥብቅና አይቆሙም ነበር ማለት ነው ?» ስል ጠየቅኃቸው።

አሁንም ለተወሰኑ ደቂቃዎች በመካከላችን ፀጥታ ሰፍኖ ቆየና ከፀጥታ በኋላ

«ይመስለኛል። ለዚህ ደግሞ ሁለት ምክንያቶች ይኖሩኛል። እነሱም ህገወጥ እና ውጤት አለማምጣት ናቸው። ፕሮፌሰር ድርጊትን ፈፅመውት እያወቅሁ ነፃ ለማውጣት ብከራከር እንደማይሳካልኝ አውቃለሁ። በሌላ በኩልም በህገመንግስቱ ላይ እንደተቀመጠው አንድመንግስት በሃይል መገልበጥ እንደሚያስቀጣ አምናለሁ። እነኚህን ነገሮች ከፊት ለፊቴ አድርጌ ልሞክር ብል እንኳን መንግስት ምስጢሩን በትክክል ስለሚያውቅ ለውጤት በቅቼ ከእስራት ነፃ እንደማላዋጣቸው የሚታመን ሃቅ ነው። »

«በፕሮፌሰሩ የክስፋይል ውስጥ ከተከሰሱት መካከል የደርግ የጦር መኮንን የነበረ ሚካኤል በለጠ የተባለውን እስረኛ ያስታውሳሉ?» ስላቸው በአዎንታ እራሳቸውን ከአነቃነቁ በኋላ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

«አስታውሳለሁ። ከእስር ከተፈታም በኋላ አግኝቼው ነበር እኮ» አሉኝ ወደኔ ትኩር ብለው እየተመለከቱ።

«ወደ እርሶ እንድመጣ እና እንዳነጋግረዎት የጠቆመኝ እሱ ነበር። በዚህ ዙሪያ ሰፋ ያለ ቃለ መጠይቅ አድርጌለታለሁ። ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን ነው የሰጠኝ። እሱ ከሰጠኝ መረጃዎችም አንዳንዶቹ ይሆናሉ ብዬየማልገምታቸው ግን የተደረጉብዙታሪኮችን እንዳውቃቸው አረድቶኛል»ስላቸውበመስኮቱ አሻግረው ውጭውን እየተመለከቱ ቆዩና

«እና ታድያ ምን አለህ?» አሉኝ።

«እሱ እደነገረኝ ከሆነ እርስዎ ፕሮፌሰሩን በደንብ እንዳላወቋቸው ነው የገመትኩት። ለማንኛውም ስለነገረኝትክክለኛው ታሪክ ከመነሻው ጀምሬ ልጠቋቁመዎት። በሰሜን ሸዋ በአሉት ቆላማ አካባቢዎች በሽግግሩ ወቅት በትጥቅ የሚንቀሳቀሱ ሽምቅ ተዋጊዎች ነበሩ። ቦታውን ለማስታወስ ያህልም በይፋት ቅወትና ማፋድል ወረዳ በመርሃቢቴ እንዲሁም በተጉለት እና ቡልጋ ፣ከሰምና ሸንኮራ የተደራጀ ሃይል ከሽግግሮ መንግስቱ ጋር ይዋጋ እንደነበር ከዚሁ መኮንን ሰምቻለሁ። ይህንን ያወቁት ወይም የሰሙት ነገር ነበር እንዴ?» ስላቸው

«በወሬ ደረጃ ሰምቻለሁ። በርግጥ በመንግስት ለውጥ ወቅት በአገሪቱ በርካታ ክልሎች ችግሮች እንደነበሩ የምናውቀው ሃቅ ነው። የዚህ ዓይነት ግጭቶች በየትኛውም የአገሪቱ ክልሎች ስለነበሩ ያን ያህል አያስደንቅም» አሉኝ።

«ነገሩ በወሬ ደረጃ የተደመጠ ብቻ ሳይሆን እውነትና የተደረገም ነው። ቅድም ስሙን የጠቀስኩልዎት የጦር መኮንን ከነዚህ በአንደኛው ወረዳ ይንቀሳቀስ የነበረውን የሽምቅ ሃይል ተዋጊ መሪ እንደነበር እራሱ ነግኛል። የደብረብርሃን እስር ቤት የተሰበረውና ከሰባት መቶ የሚያንሱ የተለያዩ እስረኞች ነፃ የወጡትም በራሱ በዚህ የጦር መኮንን እቅድአዉጭነትና መሪነት እንደነበር



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

እራሱ በመረጃ አስደግፎ ነው ያጫወተኝ:: ከዚህ ውጪ በርካታ ኦፕሬሽኖች በዚሁ ሰው ተደርገው አብዛኞቹ የተሳኩ እንደነበረ በቃለ መጠይቃችን ወቅት በስፋት እየዘረዘረ አስፈድቶኛል» ሲላቸው ጠበቃው በሚሰሙት ሁሉ ተገርመው ዓይንና አፋቸውን በመክፈት ይመለከቱኝ ጀመር:: ከዚያም ቀጥል በሚል አኳኋን እያስተዋሉኝ

«እሺ?» በማለት በረጅሙ ተነፈሱ::

«እሱ እንደነገረኝ ከሆነ ይህ የሚንቀሳቀስ ኃይል በቀጥታ ይታዘዝ የነበረው በፕሮፌሰሩ እንደነበር ነው:: ምናልባት ስሙን ሲጠራ ሰምተው ከሆነ የጊናገር ወረዳ አስተዳዳሪ የነበረው በኋላም በሽምቅ ውጊያ የሸፈተው አስማረ ዳኜ የተባለው ግለሰብ ከፕሮፌሰሩ ጋር በቀጥታ ግንኙነት እንደነበረውና ወረዳ አስተዳዳሪነቱን በመተው ወደጫካ የገባው ከእሳቸው ጋር ከተገናኘ በኋላ መሆኑን የጠቀስኩሎት የጦር መኮንን በመረጃ እያስደገፉ አንድ በአንድ ነግሮኛል::

ስለዚህ ጉዳይ የድምፅ እና የፅሁፍ መረጃዎች ከሱ ወስጃለሁ:: የተቀበልኩት መረጃ እንደሚጠቁመኝ ከሆነ አስማረ የሸፈተው የወረዳ አስተዳዳሪነቱን ስልጣን በመተው ለኢህአዲግ አላገለግልም በማለት ሲሆን ለመሸፈት ያነሳሳው ዋናው ምክንያትም ከእሳቸው ጋር በመገናኘቱ ነበር:: ሲሸፍትም በወረዳው ግምጃ ቤት ውስጥ የነበረውን የጦር መሳሪያ ከነጥይቱ ይዞ እንደነበር ነው ይህ የምልዎት ሰው የነገረኝ:: በወቅቱም ብዙ ሰው ተከትሎት ወደ ጫካ መግባቱንና ለመንግስትም አስጊ ደረጃ ላይ ደርሶ እንደነበር በፅሁፍ ጭምር የሰጠኝ ሲሆን በምፅፈው መፅሐፍ ውስጥም አካትቼዋለሁ:: ሙሉ ታሪኩን መፅሐፉ ከታተመ በኋላ ሊያዩት ይችላሉ::»

በምነግራቸው ሁሉ መገረማቸውን በሚገልፅ መልክ ትኩር ብለው ከተመለከቱኝ ባኋላ እራሳቸውን በዝግታ አወዛወዙ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

«አስማረ ደኜ የተባለው ሽፍታ ቀላል እንዳልነበር በወቅቱ እሰማ ነበር:: ያልሰማሁትና አዲስ የሆነብኝ ታሪክ የፕሮፌሰሩ የተደበቀ ብቻ ሳይሆን የተለየው ባህሪያቸው ነው:: እኔም ሆንኩ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለፕሮፌሰሩ ካለን ግንዛቤ አኳያ አሁን የምትለውን አምነን ለመቀበል የምንቸገር ይመስለኛል » አሉኝ::«

«በርግጥ ይህንን የጦር መኮንን አግኝቼ እስከአነጋገርኩበት ጊዜ ድረስ በፕሮፌሰሩ ላይ የነበረኝ አስተሳሰብ ከእርሶዎ የተለየ አልነበረም::አምኜ የተቀበልኩት ግን እንደነገርኩዎት ሻምበሉ ትክክለኛው ታሪክ ይህ ነው ብሎ በፅሁፍና በድምፅ መረጃውን ከሰጠኝና በመፀሀፍም እንዳዘጋጀው ከፈቀደልኝ በኋላ ሌሎችም ስማቸውን እንዳልጠቅስ አስጠንቅቀውኝ ከሱ ጋር ተመሳሳይ የሆነ የቃልና የፅሁፍ ማስረጃ ከሰጡኝ በኋላ ነው:: እሱን ብቻ አምኜ ታሪኩን ለመፃፍ ባለመድፈሬ ከሱጋር ነበሩ ያለኝንና ተከሰው ታስረው የነበሩ ሌሎች መኮንኖችም አነጋግሬ የሰጡኝ መልስ ተመሳሳይ ስለሆነ እውነትነቱን አምኜበታለሁ:: ወደዱም ጠሉም እውነቱ ይሄ ነው» አልኳቸው ጠበቃውን::

«ጥሩ ታሪክ ነው » አሉኝ በረጅሙ ተንፍሰው ከዚያም

«እምትለኝ ሁሉ እውነት ከሆነ የእሳቸው ጠበቃዎች እንደከም የነበረው ዝም ብለን ነበር ማለት ነው » አሉኝ::

«ከዚህ አንፃር ከታዬ ትክክል ነዎት የሚል ግምት አለኝ:: ወደ ክስማመልከቻችሁ እንግባና ስለሱ ትነሽ እንድትገልፁልኝ እፈልጋለሁ:: የአቃቢ የክስ ማመልከቻ ምን የሚል ነበር:: እሱን ሊያስረዱኝይችላሉ?»በዚህ መካከል ሁለታችንም በርከት ያሉ ደቂቃዎችን ያለምን መነጋገር አሳልፈን ከብዙ ዝምታ በኋላ በዚህ መልኩ ይተርኩልኝጀመር::ዐቃቤ ሕግ በሁለቱም ክሶች ላይ የወ.መ. ሕግ ቁጥር 269/ሀ እና 252/1/ሀ አጣምሮ በመጥቀስ ካደረጉት ጠቅላላ ንግግር ውስጥ ቃላትን በመልቀምናከንግግሩ ጠቅላላ ይዘትና አላማ ውጭየራሱን ትርጉም በመስት ወንጀልን ለመፍጠር ከመሞከሩ በቀር ሕጉ በሚጠይቀው



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

መሰረት አልነበረም ክሱን የመሰረተው። ንግግሩ በወንጀለኝነት የሚቋቋም መሆኑን በጭራሽ የማያመለክት ነው።

በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 23 መሠረት ወንጀልን ከሚያቋቁሙት መሠረታዊ ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ የሀሳብ ክፍል መኖሩ መረጋገጥ ነበረበት።የአቃቤ ሕጉን የክስ ማመልከቻ ጠቅላላ ይዘት ስንገመግመው ግን ፕሮፌሰር ለህዝብ ያደረጉት ንግግር እንደ የዐቃቤ ሕግ ክስ አቀራረብ ሕዝብ በመንግስት ላይ ወይም ህዝብ በህዝብ ላይ የጦር መሣሪያ ይዞ እንዲነሳሳ ያደረገ መሆን አለመሆኑ የሚመዘነው ከንግግሩ ውስጥ አንዳንድ ዐረፍተ ነገሮችን ነጥሎ በማውጣት ከተናጋሪው አላማና ፍላጎት ውጭ የተዛባ ትርጉም በመስጠት ነበር።

በመሰረቱ አንድ ሰው አሳቡን በንግግር ሲገልጽ የንግግሩ አላማና ግብ ምን እንደሆነ ሊታወቅ የሚቻለው ከንግግር ውስጥ እንደንድ ቃሎችን ወይም ዐረፍተ ነገሮችን ነጥሎ በማውጣት ሳይሆን የንግግሩን ይዘት በሙሉ በማንበብና መደምደሚያውን በማየት እንጂ ከቀቃላቱ ሁሉ መጥፎ መንፈስ ያለውን ነጥሎ በማውጣት አይደለም።ፕሮፌሰር ለህዝብ ባደረጉት ንግግር ላይ ዐቃቤ ህግ ለክሱ በዋቤነት የጠቀሳቸውና የተዛባ ትርጉም የቸራቸው ዐረፍተ ነገሮች ብቻቸውን በምንም ዐይነት ተከሳሹን የወንጀል መስራት ሀሳብ አያመለክቱትም። የተከሳሹ ንግግር የተቋጨው በሚከተለው ዓረፍተ ነገር ሲሆን ሙሉ ቃሉም።«......
ስለዚህ ሁላችንም፣ ሕዝቡም ሹማምንትም፡፣ በሰላምና በእኩልነት ተፈቃቅሮ መስራቱ ጥቅሙ የሁላችን መሆኑን ተገንዘብን በመሀላችን ሊጎለብት የሚችለው ስምምነታችን እንዲጠናከር በማድረግአርቀንእንድንመለከትጥሪአቅርባለሁ»የሚልነው፡የፕሮፌሰ ርንግግር ከመጀመሪያው እስከመደምደሚያው ስንመለከተው በመንግስት ላይ ተነሱ ጦር



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ይዞችሁ አምጹና ተዋጉ ብሎ ሲቀሰቅስ አይታይም ::ፕሮፌሰሩ ንግግራቸውንየደመደሙት ከላይ በተጠቀሰው አስተያየት በመሆኑ እሳቸው ለሰላምና ለተባበረ የህዝብ ሕይዎት አድማጩ እንዲሰለፍ አጥብቆ የሚያሳስብ እንጂ ዐቃቤ ሕግ እንደሚለው ሕዝብ የጦር መሣሪ ይዞ እንዲነሳ የሚገፋፉ አልነበረም::ያደረጉት ንግግር የተደመደመው ዐቃቤ ሕግ እንደጠቀሰው በህዝብና በመንግስት ላይ መዓት ለማምጣት የጦር አውርድ ጥሪ ባለመሆኑ ከተከሳሹ ሀሳብና ፍላጎት ውጭ ተከሳሹ ስለሰላምና ስለ ህዝብ ትብብር ያደረጉት ንግግር በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 23 የተደነገገው ወንጀልን ሊያቋቁምየሚችል የሀሳብ ክፍል የሚያሟላነበር::

ዐቃቤ ሕግ በክስ ማመልከቻው ከፕሮፌሰር ንግግር ውስጥ እየሸራረፈ የደረደራቸው ከንግግሩ አጠቃላይ ይዘትና ዓላማ ውጭ ትርጉም ሊሰጡ የማይችሉ ዐረፍተ ነገሮች የተከሳሹን የወንጀል መሥራት ሀሳብ የማያሳዩ ከመሆኑም ሌላ እነዚህ ዐረፍተነገሮች ከታቀዱበት ዓላማ ውጭ በማመሳሰል ወንጀል ለመፍጠር የተሳሉ ለመሆናቸው ዐቃቤ ሕጉ ያቀረበው ክስ በወንጀለኛ መቅጫ ሕ-ቁጥር 2/1 የተፃፈውን ድንጋጌ የሚጻረር ነው:: አንድ ሰው በወንጀል ሕግ ተጠያቂ ሊሆን የሚችለው ፊዕሟል በተባለበት ድርጊት እና ተላለፈ በተባለው የሕግ ቁጥር መካከል በግለፅና በቀጠታ ግንኙነት ያለው መሆኑን ማሣየት ሲችል ሊታለፍ የማይችል በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 112 መሠረት በዐቃቤ ሕግ ላይ የተጣለ ግዴታ ነው::

ይህም ግዴታ የተጣለው በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ቁጥር 2/1 እንደተደነገገው በማስመሰል ወንጀል ፈጥሮ ክስ እንዳይቀርብ ለማገድ ታስቦ ነበር::ከዚህ አንጻር ሲታይ ዐቃቤ ሕግ በፕሮፌሰሩ ላይ ክስ ያቀረበው ከተከሳሹ ንግግር ውስጥ አንዳንድ ዐረፍተ ነገሮችን ነጥሎ በማውጣት ከንግግሩ ዓላማ ውጭ የራሱን ትርጉም በመስጠት ወንጀል እንደተፈፀመ በማስመሰል ስለሆነ ይህ ደግሞ በወንጀለኛ መቅጫ ህግ 2/1 መሠረት በትርጉም



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ወንጀል እንዳይፈጠር በግልጽ የተከለከለውን በመተላለፍ የቀረበ ክስ ስለሆነ መሠረዝ ነበረበት።በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁጥር 269 በአማርኛው ቅጂ መሠረት « ማንም ሰው ከዚህ በላይ በተመለከቱት ምዕራፎች ውስጥ የተጻፉት ሥራዎች እንዲፈፀሙ ለማድረግ በመርዳት ወይም በመደገፍ» ከ«ሀ» እስከ «መ» የተዘረዘሩትን አድራጎቶች የፈጸመ እንደሆነ ከአንድ ወር እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል እስራት እንደሚቀጣ ተደንግጐአል። ቁጥር 269 የሚገኘው በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ልዩ ክፍል በ3ኛው መፅሐፍ በአንቀፅ አንድ በምዕረፍ አንድ ሥር ነው።በቁጥር 269 «.... ከዚህ በላይ በተመለከተቱት ምዕራፎ.....»ተብሎ የተጠቀሰው ከዚህ ምዕራፍ ውጭ የሆኑትንና ከምዕራፉቀድመው የሚገኙትን ሌሎች ምዕራፎችን የሚመለከት ሲሆን።ከቁጥር 269 ጋርተጠቅሶ በተከሳሽ ላይ የተጠቀሰው ቁጥር269በሚገኘው ምዕራፍ ውስጥ ነው። ስለዚህ በቁጥር 269 «ከዚህ በላይ በተመለከቱት ምዐራፎች» የሚለው አነጋጋር ቁጥር 252ን የሚያጠቃልል ስለሆነ ቁጥር 269 ከቁጥር 252 ጋር ተጣምሮ በተከሳሹ ላይ የቀረበው ክስ ሕጋዊነት የለውም ማለት ነው።

የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ በመጀመሪያ በተቀረፀበት የፈረሳይኛ ቋንቋ ቅጂ እና የፈረንሳይኛው በተተረጎመበት የእንግሊዘኛ ቅጂ «ማናቸውም ሰው በዚህ ምዕራፍ ከዚህ በላይ ባለው ክፍል የተዘረዘሩትን ድርጊቶች ለመፈፀም ለመፍቀድ ወይም ለመደገፍ በማሰብ» ከ «ሀ» እስከ «መ» የተዘረዘሩትን አድራጎቶች የፈጸመ እንደሆነ ከአንድወር እስከ አምስት አመት ሊደርስ በሚችል እስራት እንደሚቀጣ ተደንግጓል። በሁለቱ ቅጂዎች «በዚህ ምዕራፍ የሚለው አነጋገር የሚመለከተው ቁጥር 248 እስከ 272 የያዘውን አራሱ ቁጥር 269 የሚገኘውን ምዕራፍ አንድ ነው። በምዕራፍ አንድ ውስጥ ሦስት ክፍሎች ያሉ ሲሆን ቁጥር 269 የሚገኘው በሦስተኛው ክፍል ውስጥ ነው። በቁጥር 296 «ከዚህ በላይ ባለው ክፍል» ተብሎ የተጠቀሰው የሚመለከተው ክፍል ሁለትን ነው።



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

በክፍል ሁለት ያሉት ቁጥሮች ደግሞ ከቁጥር 259 እስከ ቁጥር 266 ያሉት ናቸው:: ቁጥር 252 የሚገኘው በክፍል አንድ እንጂ በክፍል ሁለት አይደለም:: ከዚህ በላይ እንደተቀመጠው ቁጥር 269 ከቁጥር 252 ጋር ተጠቅሶ በምንም አይነት ክስ ሊቀርብ አይችልም:: ስለዚህ ቁጥር 269/ሀ ከቁጥር 252/1/ሀ ጋር ተጣምሮ ክስ የቀረበው ህጉ በግልፅ ከሚደነግገውና ከአላማ ውጭ ይመስላል::« በ1949 ዓ/ም ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 252 መሰረት በአንድ ሰው ላይ ክስ ሊቀርብ የሚችለው በንጉሠ ነገሥቱ ፣ በመንግሥፅቱ ወይም በሕገ መንግስቱ በተቋቋሙ ባለስልጣኖች ላይ እዝባዊ ሁከት ወይም ወታደራዊ አድማ ወይም በመሣሪያ የተደገፈ አመፅ ማስነሳቱ ወይም ለማስነሳት መሞከሩ ሲረጋገጥ ነው:: ተከሳሽ የቀረበባቸውን ክስ በንግግር ቅስቀሳ አድርገዋል የሚል ነው::

ተከሳሽ ታህሳስ 11 ቀን 1985 ዓ:ም በደብረብርሀን ከተማ ያደረጉት ንግግር የአገር አንድነት እንዲጠበቅ ሕዝብ በጎሳ ተከፋፍሎ እርስ በርሱ እንዳይጋጭ በአማራው እዝብ ላይ የሚፈጸመው ግፍና በደል እንዲቆም ሕዝቡ በሐይማኖት እንዳይከፋፈል የሚማጸን እንጂ ተከሳሹ እራሳቸው መሳሪያ አንግበው ሕዝብን በማሳደም ወይም ከወንበዴዎች ጋር አብረው በመንግስት ላይ ለውጊያ ለመነሳታቸው ወይም ለመነሳት መሞከራቸውን ዐቃቤ ሕግ በክስ ማመልከቻ የገለጸው ነገር የለም:: በርግጥ ፐሮፌሰር የተደራጀ ጦር እንደ ነበራቸውና ይህንንም በትክክል የሚያስራዳ የድምፅ እና የፅሁፍ ማስረጃ በመንግስት እጅ መኖር እውነት ከሆነ አቃቤ ህግ ለምን አልጠቀሰም ነበር::? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል::

ይህንን ቢያውቅምና መረጃው በእጁ ላይ ቢኖረውም በዚህ ወንጀል መክሰስ አይፈልግም:: ለምን ቢባል ጦርነቱ ተጀመረ ከተባለ የሚከሰሰው ጦርነቱን የጀመረው ወይንም እየተዋጋ ያለው ሃይል ብቻ ስለሚሆን አገር አቀፍ ክስ ለመመስረት አይቻልም:: አቃቢ ህግ ፕሮፌሰር በትጥቅ የተደራጀ ጦር እንዳላቸው እያወቀ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

በማነሳሳት የከሰሰበት ምክንያት ክሱ ሁሉን አቀፍ እንዲሆንለት አስቦ ያደረገው ነው።ወደጭብጡ ልመለስና በተራ ቁጥር አንድ እንደተመለከተው ሁሉ የተከሳሹ ንግግር ዋናው አላማ በአገሪቱ የሽግግር ወቅት ሂደት ውስጥ እንግዳ በሆነው የብሄር ብሄረሰቦች የራስን ድል የመወሰንና የመገንጠል መሰረታዊ መርሕ ላይ አልፎ አልፎ በሀገሪቱ አንዳንድ ክፍሎች የተፈጠረን የተዛባ በመንግስትና በህዝብ የታመነውን ችግር ሰላማዊ መፍትሄ እንዲያገኝ ለማስገንዘብ የታሰበና የታቀደ ለመሆኑ የንግግሩን ቃል በግርድፉ መውሰድና መመልከት ይቻላል። የንግግሩ ይዘት ይህ ሆኖ እያለ ከተከሳሹ ንግግር ውስጥ «ስለጦርነት ለአማራው መናገርና መገፋፋት ልጅ ለእናቷ ምጥ አስተማረች ነው……» የተባለው የአማራ ክፍል በሁኔታዎች ተገፋፍቶ ጦርነት እንዲነሳ የሚያስገነዝብ ነው ከተባለም በንግግራቸው መደምደሚያ ላይ ተከሳሹ ለህዝቡ ጥሪ ያደረጉት፣ በሚከተለው ዐረፍተነገር ሲሆን

«ስለዚህ ሁላችንም ህዝብም ሹማምንትም በሰላምና በእኩልነት ተፈቃቅሮ መሥራቱ ጥቅሙ የሁላችልም መሆኑን ተገንዝበን በመሀላችን ያለውን ልዩነት ከማስፋፋት ይልቅ በመሀላችን ሊጎለብት? የሚችለውን ስምምነታችንን እንዲጠናከር በማድረግ አርቀን እንድንመለከት ጥሪ አቅርባለሁ»በማለት ይደመድማል። ንግግሩ እንደገባኝ ከሆነ ፕሮፌሰሩ « በመፈቃቀድና በዕኩልነት» ከተመሰረተው የመንግስት መርሀ ውጭ ያልሆነ ሰላምን የማስፈን መንፈስ የያዘ እንጂ ጦርነትን የሚያውጅ ንግግር እንዳልሆነ በጉልህ የሚያስረዳነው።ፕሮፌሰሩ ክስ ሊቀርብባቸው የቻለው ለህዝቡ ንግግር አርገዋል ተብለው ከሆነ ደግሞ ሐሳብን በዕሁፍ መግለፅ የማንኛውም ዜጋ ተፈጥሮአዊና ሕጋዊ መብቱ መሆኑን ህገመንግስቱ ተቀብሎት ያለገደብ ያረጋግጣል። ይህም ነጻነት በብዙ አገሮች ሕጎችና በተባበሩት መንግስታት የዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች አዋጅ በግልፅ የተረጋገጠና ሕጋዊ ጥበቃም የሚደረግለት ነው። የኢትዮጵያ የሽግግር ወቅት ቻርተርም የተባበሩት መንግስታት



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ዓለም አቀፍ የሰአዊመብቶች አዋጅን ሙሉ በሙሉ እንደተቀበለ በቻርተሩ ላይ በግልፅ የተመለከተ ነው። ፕሮፌሰሩ በዚህ መብታቸው ተጠቅመው ለአገር አንድነትና ለሕዝብ ሕብረት ይበጃሉ ብለው ያመኑባቸውን ሀሳቦች ከማሰማት በስተቀር መሳሪያ አንግበው ሕዝብ በመንግስት ላይ ወይም ሕዝብ በሕዝብ ላይ እንዲነሳሳ የሚል ሃሳብ አላስፈሩም ።

ሀሳብን መግለፅ መሰረታዊ መብት ነው እስከተባለ ድረስ አንድ ሰው ሀሳቡን በመግለፅ ብቻ ወንጀለኛ ሊሆን አይችልም። ወንጀለኛ የሚያሰኝ የሕግ ቁጥርም ከተገኘ በቻርተሩ የተረጋገጠ ውን ሰብአዊ መብት የሚደፈር ስለሚሆን ቻርተሩን የሚፃረር ሕግ ሥራ ላይ እንዳይውል በቻርተሩ በግልፅ የተወሰነ በመሆኑ የዜጎች ሰበዓዊ መብት በሚከበርበትና በሚረጋገጥበት የፍትሕ አደባባይ ላይ ተቀባይነት ሊኖረው የሚገባ አልነበረም።

ፕሮፌሰሩ ከሀገሪቱ ዋና ዋና ከተሞች ጋር ሲነፃፀር አነስተኛ በሆነው በደብረብርሀን ከተማ ለተሰበሰበ የተወሰነ ህዝብ ያደረጉትን ንግግር በአገሪቱ ያለው የመንግስት መገናኛ ብዙኃን ይፋ አውጥተው ለኢትዮጵያ ህዝብ አሰምተውታል። የፕሮፌሰሩን ንግግር መንግስት ወንጀል አለመሆኑን ካላመነበት በቀር የኢትዮጵያ ህዝብ በሙሉ እንዲሰማው ሊያደረግም አይችልም ነበር። መንግስት እንደሚለው ወንጀል ከሆነም ደግሞ

እርሳቸው ሲያሰሙት ወንጀል የሚሆንበት መንግስት እርሳቸው ካስደመጡት በሚለዮን እጥፍ ለሚሆን ሕዝብ ሲያዳርሰው ወንጀል የማይሆንበት ምክንያት ሊኖር ስለሚችል ፕሮፌሰሩ ከተከሰሱ መንግስትም የማይከሰስበት ምክንያት አልነበረም። መንግስት ግን አልተከሰሰም። ለምን? እኔ እንደገባኝ ከሆነ ዐቃቤ ሕግ ከፕሮፌሰሩ ንግግር ውስጥ አንዳንድ ዐረፍተ ነገሮችን ከንግግሩ ጠቅላላ ዓላማ ውጭ ለይቶ በማውጣት ወንጀል ለመፍጠር ሞከረ እንጂ የፕሮፌሰሩ ንግግር በምንም



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ዓይነት መስፈርት በወንጀልነት የሚቋቋም አይደለም፡፡ አንድ ሰው ወንጀል ሳይፈፅም ደግሞ በወንጀል ሊከሰስ አይችልም፡፡

ስለዚህ የወ.መ.ሕግ ቁጥር 269/ሀ እና 252/1/ሀ-እና – ለ ተጠቅሶ በፕሮፌሰሩ ላይ የቀረበው ክስ በርግጥ በፕሮፌሰሩ ላይ የቀረበው ክስ በንግግሩ ሳይሆን በቀጥታ በጦርነት በመሰለፋቸው ሊሆን እንደሚችል አሁን እየገባኝ ነው፡፡ ይህንን ነገር አርቀን ስንመለከተው መንግስት ይፋ ሊያወጣውና በተዘዋዋሪም እሳቸውን በወንጀሉ ሊቀጣ ያሰበበት ምክንያት መሆን አለበት፡፡ ከዚህ በላይ በዝርዝር እንደተመለከተው ተፈፀመ የተባለው ድርጊት በየትኛውም መለኪያ ቢሆን ወንጀል ነው የሚባል አይደለም፡፡ ሊሆን ይችላል የሚባል ቢሆንም እንኳን በአንድ ቀንና በአንድ ስፍራ ለተወሰኑ ሰዎች የተደረገውን ንግግር ሁለት ቦታ ከፋፍሎ ፣ ሁለት ዓይነት ወንጀል አድርጎ ማቅረብን የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 60/1 እንደሚከለክል የተረጋገጠ ነው፡፡

በህግ በተጠበቀ በአንድ መብት ላይ የሚሰሩ አንድ ወይም የተቀላቀሉ የወንጀል አድራጎቶች በአንድ አሳብ ወይም ቸልተኝነት የተፈፀሙ ሲሆን ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ የቅጣት ድንጋጌዎች ሊወስንባቸው እንደማይቻል በዚህ የሕግ ቁጥር በግልፅ ተመልክቷል፡፡ ለሁለቱም ክሶች መነሻ የተደረገው አንድ ንግግር ነው፡፡ ፕሮፌሰሩ ፈፀሙ የተባለው አንድ ተግባርን ነው፡፡ ለዚህ ተግባር ተፈፃሚ የሚሆነው አንድ የሕግ አንቀጽ ብቻ ነው፡፡የሕጉ መንፈስም በአንድ ሀሳብ ውስጥ የተካተቱና የተለያዩ ትርጉሞች ሊያስከትሉ የሚችሉ ተግባሮች ሁሉ ዐቢይ ነው፡፡ በተባለው በዋናውወንጀል ውስጥ ተጠቃለው ይህን ወንጀል በሚሸፍነው የሕግ አንቀፅ ክስ እንዲመሰረት ለማድረግ ነው፡፡ ለምሳሌም ያህል ያለተፈቀደ መሳሪያ በመያዝ የሰው አጥር ሰብሮ በመግባት ባለቤቱን ከሰደበ በኋላ የግድያ ወንጀል የሚፈጽም ሰው ያልተፈቀደ መሳሪያ በመያዝ መኖሪያ ቤት



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

በመድፈር በስድብና በግድያ ተብሎ አራት ክሶች ሊመሰረቱበት እንደማይችሉ ያስረዳል::ፕሮፌሰሩ በተከሰሰበት ጉዳይ ዐቃቤ ሕግ አንድን ንግግር እየከፋፈለና እየቆነፀለ ለሁለት ሰንጥቆ ለዚያውም አንድ አንቀፅ ማለትም ቁጥር 269/ሀ በመጥቀስ ሁለት ክስ መመስረቱ ሕጉን መተላለፍ በመሆኑ ውድቅ ሊሆን የሚገባው ጉዳይ ነበር:: ፕሮፌሰሩ የማነሳሳት ወንጀልን የሚያቋቁም ሕገ ወጥ ድርጊት ፈፅመዋል ለማለት ቢያንስ እንዲፈፀም የተፈለገው ድርጊት የተሞከረ መሆኑን ዐቃቤ ሕግ በክስ ማመልከቻው የገለፀውን ማስረጃ ውድቅ የሚያደርገው አንቀፅ የትኛው ነበር? ወንጀል የሚባለው ምን ሲሆን ነው? ለሚለው ለማነሳሳት የሚደነግገው የወ.መ.ሕ ቁጥር 269 የማነሳሳት ወንጀል መሰረታዊ ሃሳቦችን ከሚያስቀምጠው ከ.ወ.መ.ሕ ቁጥር 35 ጋር አብሮ ሲታይ የቀረበው ክስ ሕጋዊ መሰረት ያለው አይመስለኝም::

በዚህ ሕግ መሰረት የወንጀል ስራን አነሳስቷል የተባለ ሰው የሚከሰሰውና የሚቀጣው በማነሳሳት ሊፈፀም የታቀደው ወንጀል በፕሮፌሰሩ ቢያንስ የተሞከረ እንደሆነ ነው:: በሁለቱም ክሶች ላይ ንግግር የተደረገለት ህዝብ የጦር መሳሪያ ይዞ እርስበርስ ለመበጣበጥ ወይም በመንግስት ላይ ለመነሳት ሙከራ ለማድረጉ በክሱ የተገለጠ ነገር የለም::

በሰሜን ሸዋ አሉ የተባሉት አማፅያንም በክሱ አልተጠቀሱም:: የጦር መሳሪያ ትጥቅ መጀመሩ እየታወቀ ለምን በማነሳሳት ክስ ተመሰረተ? ለሚለው ጥያቄ ቀደም ሲል ጠቅሼልሃለሁ:: ሕዝብ መሳሪያ ይዞ እንዲበጣበጥ ፣ ወይም በመንግስት ላይ እንዲነሳ የተደረገ ማነሳሳት መኖሩ ፣ብቻ ተጠቅሷል ለምን? ተነሳስቷል ወይም ተቀስቅሷል የተባለው ሕዝብ የተነሳሳበትን ተግባር መሞከርያ ፣ ወይም መፈፀሙ ሻምበሉ ከሰጠህ መረጃ አንፃር መነሳሳት ሳይሆን ጦርነት ተጀምሯል:: ስለዚህ ጉዳይ አቃቤ ሕግም መጥቀስ አይፈልግም:: ይህ ስለ መሆኑ የተገለፀ ነገር የለም ዐቃቤ ሕጉ ይህ ነገር



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

እንደማያዋጣው ስላወቀ ይሆን መሞከር አለበት የተባለውን ወንጀል የሙከራ ሙከራ ወይም የማነሳሳት ሙከራ እንዳለ በማስመሰል የወ.መ.ዝ.ቁጥር 27 ጠቅሶ ክስ የመሰረተው እነዚህ ሁሉ ለኔ የአሁን ጥያቄ ስለሆኑ ትርጉም አልባ ናቸው፡፡ዐቃቤ ሕግ በአንድ ስፍራ፣ ቀንና ሰዓት የተፈፀመውን ድርጊት አንዱ ውጤት ያገኘ ወንጀል ሌላውን ሙከራ በማለት ክስ ማቅረቡ ቀድሞውኑ ክሱ ከመሰረታዊው የማነሳሳትድርጊት የዘለለ መሆኑን ስለሚያመለክት ክሱ ዐቃቤ ሕግ የተከሳሽን ንግግር ወንጀል አስመስሎ ለማቅረብ ከጉዳዩ ጋር አግባብነት የሌለውና የማይሆን ነው የቀረበው ክስ ከሕግ ውጭ ስለሆነ ክሱ ሙሉ በሙሉ ሊነቀፍና ሊሰረዝ የሚገባው ነበር፡፡ ስለዚህ ነገሩን ለማጠቃለል ፕሮፌሰሩያደረጉት ንግግር የተደመደመው በተዋጊልኝ ወይም በእንዋጋ ጥሪ ሳይሆን ሰላማዊ ሁኔታ የሚፈጠርበት መንገድ በመግለፅና ለዚሁም ዓላማ ጥሪ በማድረግ ስለሆነ ተከሳሹ በምንም ዐይነት መመዘኛ ወንጀል የመስራት ሃሳብ አልነበራቸውም፡፡ የተፈፀመ ወንጀል ሳይኖር የቀረበው ክስ ሕገ ወጥ መሆኑ እየታመነበት ዐቃቤ ሕግ ተከሳሽ ያደረጉትን ንግግር በቁንፅል በመልቀም ለራሱ የክስ ግብ በሚያመቸው ዐይነት ያቀረበው የማመሳሰል ክስ ከወ.መ.ሕ.ቁ2 ውስጥ የቀረበ የአናሎጂ ክስ ነበር፡፡

የወ.መ.ሕግ ቁጥር 269 ከቁጥር 252 ጋር ተጣቅሶ በክስነት ሊቆም ስለማይችልና የወ.መ.ሕግ ቁጥር 269 እና 252 ዓላማም ሆነ ግብ የተለያዩ መብቶችን ስለሚጠብቅ ዓቃቤ ሕግ የማይዛመዱ የሕግ ቁጥሮችን አጣምሮ ክስ ያቀረበው አለአግባብ በመሆኑ ብቻ ሳይሆን
የሚያስጠይቀውም ነበር፡፡ እነኝህ ነጥቦች የሚታለፉበት ምክንያት የለም እንጂ ቢታለፉም እንኳ የተጠቀሱት ቁጥሮች በያዟቸው የሕግ ፅንስ ሀሳቦች እና ሕጉ እንዲሟሉ ከሚጠይቃቸው መስፈርቶች አኳያ ሲታይ ተከሳሽ ያደረጉት ንግግር ከሕጉ ጋር የማይጣጣም ስለሆነ ፣ በሽግግሩ ወቅት ቻርተር አንቀፅ 1 መሰረት የግለሰብ ሰባአዊ መብቶች ያላንዳች ገደብ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

እንደሚከበር በመረጋገጡና ተከሳሽም ንግግሩን ያደረጉት በቻርተሩ የተረጋገጠውን መብት መሰረት በማድረግ ሆኖ ሳለ ቻርተሩንየሚፃረርየሕግቁጥርተጠቅሶክስመቅረቡ አግባብነትየሌለው መሆኑን በግልፅ ይታያል።በወ.መ.ሕግ.ቁጥር 60 መሰረት በአንድ ወንጀል የመስራት ሃሳብ ስር ሊውል የሚችልን ድርጊት በታትኖና ደራርቦ ማቅረብ የተለየ ግብር ከመሻት ውጭ ሕጋዊ ነው ሊባልም የሚችል አይመስለኝምየማነሳሳት ወንጀል በሕግ ረገድ ሊያስጠይቅ የሚችለው ፕሮፌሰሩ እንዲፈፅም የተፈለገውን ተግባር ቢያንስ መሞከሩን ማረጋገጥ ሲቻል በመሆኑና እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ለመፈጠሩ ዐቃቤ ሕግ በክሱ ላይ ያልገለፀ ስለሆነ ክሱ ሙሉ በሙሉ ውድቅ ነው ባይነኝ ነኝ በማለት የጀመሩልኝን ሃሳብ ሙሉ በሙሉ ሲጨርሱ እኔም መቅረፀ ድምፄን ዘግቼ አመስግኛቸዉ ተሰናብቻቸው ወጣሁ።



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

# ምዕራፍ አስራ ስድስት
# የፕሮፕፌሰሩ እዉነተኛ ታሪክ

ቀኑ ከሰአት በኋላ ነው፡፡ ከወደ መገዘዝ በኩል እየነፈሰ ያለው ነፋስ ካፊያን የቀላቀለ ስለነበር ቅዝቃዜው አጥንት እየሰረሰረ ሲገባ ይታወቃል፡፡ በጊዜ እርዝመት ምክንያት ምርጊቱ ረግፎ እንጨቱ ተጣምሞና ተወላግዶ የሚታየው የደብረብርሃን ከተማ ባለቆርቆሮው ክዳን ቤት አብዛኛው ለመውደቅ ወደ አንድ ወገን አዘንብሏል፡፡ በአካባቢው ያሉት ቤቶች በሙሉ ያረጁና የተጎሳቆሉ ነበሩ፡፡

ረጅም ቁመታቸውን ጎበጥ አድርገው ከዘራቸውን በማስቀደም እየተመረኮዙ በዝግታ የሚራመዱ ሽማግሌ ከአሮጌው ቤት ከውስጥ ወደ ውጭ ብቅ አሉ፡፡ እኔን ይዞኝ የሄደው ሰው ቀደም ብሎኝ ወደውስጥ ገብቶ ስለነበር ወደ እኔ ይዞአቸው እየመጣ እንደሆነ ተረዳሁ፡፡ መንገድ መሪዬ ከጎናቸው ሆኖ እረጋ ብሎ እየተራመደ መጣና ከሽማግሌው ጋር አስተዋወቀኝ፡፡ ብዙ የእድሜ አጥር እየዘለሉ መጥተው እዛሬ ላይ የቆሙትን ሽማግሌ ትኩር ብዬ አስተዋልኳቸው፡፡ እርጅና ሙሉ በሙሉ ከነልጅ ልጆቹ ተሳፍሮባቸዋል፡፡ ከሽማግሌው ጋር ከተዋወቅን በኋላ ለምን እንደመጣሁ የስራ ድርሻዬን ጭምር ነገርኳቸው፡፡

በእርጅና ብዛት ወደ ውስጥ ጠልቀው ገብተው ጭልጭል በሚሉት አይኖቻቸው አትኩረው እየተመለከቱኝ እጅግ በሚማርክ ድምጽ « ከኔ የሚጠቅም ታሪክ የምታገኝ ይመስላልሃል » አሉኝ እንደመሳቅ ብለው፡፡ትኩር ብዬ በድጋሚ አስተዋልኳቸው፡፡ የእጅና የሰውነታቸው ቆዳ ተሸብሽቦ ተጣጥፏል፡፡ ሞራ የጋረዳቸው ትናንሽ አይኖቻቸው ከጥልቅ ጉድጓድ ውስጥ የቀረ ጭላጭ ውሃ ይመስላሉ፡፡ ዝም ብያቸው ስለቆየሁ ሳይሆን አይቀርም እሳቸውም ትኩር ብለው ይመለከቱኝ ነበር፡፡ በሽበታም ሪዛቸው ከተከበበው አፋቸው የሚወጣው ቃላቸው ይጥማል፡፡



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ያም ሆኖ ግን ብዙ የሚሰማ አልነበረም:: እንደተረዳሁት ከሆነሽማግሌው ጥርሶቻቸው በመርገፋቸው መሆን አለበት ሙሉ ድምጻቸው ወደውጪ የማይወጣው:: በእርግጠኝነት ለመናገር እድሜአቸው ከዘጠና አመት በለይ ሊደርስ ይችላል:: በሌላ በኩል ግን ከአነጋገራቸውና ከጠቅላላው አመለካከታቸው የተረዳሁት አስተዋይነታቸውን ብቻ ሳይሆን የኒንያ ማንነት ለማወቅና ለመረዳት ጥልቃዊ አመለካከት እንደነበራቸው ነው::

ለሽማግሌው እንደመንደርደሪያ ያቀረብኩላቸው ጥያቄ "ለፕሮፌሰር አስራት የቅርብ ዘመድ እንደሆኑ ሰምቻለሁ እርግጠኛ ነኝ?" የሚል ነበር::ከብዙ ዝምታ በኋላ «ትክክል ነህ:: አስራት የእክስቴ ልጅ ነው:: እናቱን በጣም እወዳት ነበር:: ያም ሆኖ ግን እሷ የሞተችው ገና ህፃን እንዳለሁ ነው:: አስራት እናቱን በደንብ ለይቶ የሚያውቃት አይመስለኝም» እንደዚህ እያሉ ሲነግሩኝ እሩቅ እያሰቡ እንደነበር ተርድቻቸው ነበር::

«ፕሮፌሰር የግል ህይወታቸውን በተመለከተ አንዳንድ ሰነዶችን ይይዙ እንደነበር የሚያውቁት ነገር አለ?»

በጭራሽ ስለዚህ ጉዳይ ምንም የማውቀው ነገር የለኝም:: አስራት በጣም ስለሚፈራኝና ስለሚያከብረኝ ሁሉም ነገር ለእኔ አውጥጦ አያሳየኝም ነበር» ሽማግሌው አይኖቻቸውን አጥብበው ሲያስቡ ቆዩና

« በዚህ ዙሪያ ሊረዳህ የሚችል አንድ ሰው አስታወስሁ:: ይህ ሰው ከአስራት ጋር የጠበቀ ወዳጅነት የነበረው ነው:: በጣም ምስጢራዊእንደነበሩምአውቃለሁ::ስሙሙላቱካሳዬይባላል::የሚኖረው አዲስ አበባ በቅሎ ቤት እየተባለ ከሚጠራው አካባቢ እንደነበርምትዝይለኛል::እሱንአግኝተህ ብታነጋግረው ምናልባትም ጥሩ ፍንጭ ሊሰጥህ ይችላል ብዬ እገምታለሁ»አሉኝ ሽማግሌው::

«አቶ ሙላቱ ካሳዬ አሉኝ?» ስላቸው እራሳቸውን ከፍና ዝቅ በማድረግ

« አዎን ሙላቱ ካሳዬ» አሉኝ::



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

«እሳቸውን ሰውዬ ከአሁን በፊት ላነጋግራቸው ፈልጌ ሁለትሶስት ጊዜ ቀጥረውኝ መጥፋታቸውን አስታውሳለሁ» በማለት መለስኩላቸው::

ሽማግሌው በጥልቅ ሀሳብ ውስጥ የገቡ መስለው ቆዩና

«ለምን ጉዳይ እንደፈለግኸው ገልጠሕለት ነበር» አሉኝ

«አዎን:: ስለፕሮፌሰር አስራት አንዳንድ ነገር ማወቅ እንደምፈልግና በዚህ ዙሪያ አንድ መፅሐፍ እያዘጋጀሁ ስለሆነ መረጃ በመስጠት እንዲረዱኝ በስልክ ጠቅሼላቸው ነበር::»

« እና ታዲያ ምን አለህ?» አሉኝ::

«በመጀመሪያ ለምጠይቃቸው ሁሉ ፈቃደኛ መስለውኝ ነበር:: በመጨረሻ ግን ሁለት ሶስት ግዜ እየቀጠሩኝ ጠፍተው በመጨረሻም ስልካቸውን ዘጉብኝ::»

ሽማግው አንገታቸውን በዝግታ ሲያነቃንቁ ቆይተው በረጅሙ ተነፈሱና «አዎ:: ልክ ነህ:: ሁሉንም ነገር በአደራ ከአስራት የተረከበው እሱ ስለሆነ ማንም ሰው እንዲያነጋግረው አይፈልግም:: ያስራት ሁለቱ ልጆችም ያሉት በውጭ አገር ነው:: ቤቱን አጠቃላይ የሚቆጣጠረው እሱ ነው:: ውድ የሆኑ በርካታ እቃዎች ቢኖሩም በምን ላይ እንደሚገኙ ልጆቹ እንኳን የሚያውቁ አይመስለኝም» አሉኝ::

«ቤቱን ማን ይጠብቀዋል::?»

«ሰራተኛዋ ከዚያው ነው የምትኖረው» ሲሉ መለሱልኝ::

«እቃዎቹን እርስዎ ሄደው ለማየት አልሞከሩም::?»

«በጭራሽ አስቤውም አላውቅም?» አሉኝ ባጭሩ::



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

«ታዲያ አቶ ሙላቱ ከሰው መገናኘት የማይፈልጉት ለምንድን ነው?» ስል ጠየቅኋቸው::

«እቃዎቹም ሆኑ በባንክ ያለው ገንዘብ በእሱ እጅ ነው የሚገኘው:: ይህንን ማንም ቀርቦ እንዲያውቅበት አይፈልግም:: በተለይ አንተን ማነጋገር ያልፈለገበት ምክንያት ፀሐፊ በመሆህ ይመስለኛል»አሉኝሽማግሌው« ፕሮፌሰርን እርስዎ ይበልጧቸዋል ማለት ነው?» ስላቸው

«ትክክ ነህ:: ብዙ እበልጠዋለሁ:: አስራት በኔ እድሜ ሲታይ ገና ልጅ ነው» አሉኝ ሳቅ ብለው::ቀጥለውም« አስራት የተወለደው ሰኔ 12 ቀን 1920 ዓ/ም በአዲስ አበባ ከተማ ነው:: በተወለደ በሶስተኛው ዓመት ከቤተሰቦቹ ጋር ወደድሬዳዋ ሄደ:: እዚያውድሬድዋእያለምየቤተክርስቲያንትምህርትበመከታተልበሰባ ትዓመትእድሜውዳዊትበመድገምተመርቋል::አስተማሪው አለቃ ለማ ወልደመስቀል የሚባሉ መሪ ጌታ ነበሩ:: እሳቸውም ቢሆኑ በትምህርት አቀባበሉ በጣም ይወዱት እንደነበር አስታውሳለሁ::

አስራት በጣም ጎበዝ ተማሪ ነበር:: ዓመት ሳይሞላው ወንጌልን ከነቁጥር ከፍካሬ እስከ ነቢያት በመድገሙ ዲቁናም ተቀብሏል:: በእድሜው ሳይሆን በትምህርት ባሳዩው ብልጫ የተማሪዎች አለቃም ነበር:: በዚያው በድሬደዋ ከተማ በሚገኘው ፈረንሳይ ት/ቤት ገብቶ ዘመናዊውን ትምህርት ለመከታተል በመሰናዳት ላይ እንዳለ አገራችንን ጣሊያን ትወራለች:: ያሰበውና ያለመው ተሰናከለ የቀለም ትምህርቱ ተቋረጠ:: አባቱ አቶ ወልደየስ አልታዬም የካቲት 12 ቀን 1929 ዓ/ም አዲስ አበባ ውስጥ በጠላት በአካፋና በዶማ በግፍ ከተጨፈጨፉት ብዙ ሺ የነፃነት ሰማእታት መካከል አንዱ ሆነው በግፍ ተገደሉ::

የእናቱ ወላጅ አባት የነበሩት አያቱ ቀኛዝማች ዕጌ ወረደወርቅም በግዞት ወደጣሊያን አገር ሮም ከተማ ተወሰዱ:: እናቱ ወ/ሮ በሰልፍ ይዋሉ ዕጌ በሕመም ቀደም ሲል ሞታለች::



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

በዚህ መካከል አስራት ገና በጨቅላ እድሜው የሃዘን ጥላ ድባቡን እያጠላበት መጣ::አያቱ ቀኛዝማች ዕጌ ወረደወርቅ ከሶስት ዓመት ተኩል ግዞት በኋላ ከጣሊያን ወደ አገራቸው ሲመለሱ አስራትን ከድሬዳዋ ወደ አዲስ አበባ ይዘውት መጡ:: ለአምስት ዓመት ያህል ከቤተሰብና ከአካባቢ ከሚገኘው ትምህርት በስተቀር መደበኛ ትምህርት ሳይማር እስከ ጣሊያን መወጣት ድረስ ቆይቶ ጣሊያን ከተባረረ በኋላም እስኪረጋጋ ድረስ በሚል ሰበብ ለዘጠኝ ወራት ያህል ትምህርት ቤት አልገባም ነበር:: በ1934 ዓ/ም በተፈሪ መኮንን ት/ቤት በመግባት ዘመናዊውን ትምህርት አንድ ብሎ የጀመረው በዚያን ግዜ ነበር::

አስራት አዲስ አበባ ከመጣ ጀምሮ ከአያቱ ከቀኝአዝማች ጵጌ ተለይቶ ውሎ አያድርም ነበር:: አያትና የልጅ ልጅ በማንኛውም-ጊዜና ቦታ ተያይዘው ነው የሚዘዋወሩት:: ዓስራት ከልጅነቱ ጀምሮ ብልህና ያስተማሩትን ወዲያውኑ የመቀበል የላቀ ተሰጥኦ ነበረው ለማለት ችላለሁ:: ጣሊያን ከተባረረ በኋላ ራዲዮ በየአደባባዩ ተተክሎ ህዝብ ማንኛውንም ወሬ ይከታተል የነበረው በዚያ ነበር:: አያቱ ራዲዮ የተናገረውን ወሬ አዳምጦ እንዲመጣ ሲልኩት የተባለውንና የተነገረውን ሁሉ እንደ ትልቅ ሰው በጥሞና ያዳምጥና የሰማውን በሙሉ ለአያቱ ልቅም አድርጎ ይነግራቸው ነበር:: ሽማግሌው ትረካቸውን እስከሚያቆሙ እየጠበቅኋቸው ነበር::

«ፕሮፌሰር ወደፖለቲካው ከገቡና ከዚያም የመላው አማራ ሕዝብ ዋና መሪ ከሆኑ በኋላ ተገናኝታችሁ ነበር? ከሆነስ የፖለካ ድርጅት መሪ ስለመሆናቸው ደግፈዋቸው ነበር ወይስ ደግሞ ተቃውመዋቸዋል?» የሚል ጥያቄ ሳቀርብላቸው ትንሽ ሲያስቡ ቆዩና እንደዚህ ሲሉ ጀመሩልኝ::የመላው አማራው ሕዝብ ፕሬዘዳንት ሆኖ በሚሰራበት ወቅት ከመታሰሩ በፊት መሆኑ ነው አዲስስ አበባ ድረስ ሄጄ በጉዳዩ ዙሪያ አነጋግሬው እንደነበር አስታውሳለሁ:: እንዲያውም



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ከሙያው አንፃር ነገሩን ትኩረት ሰጥቶበት እንዲተው አበክሬ ነግሬው እንደነበርም ትዝ ይለኛል። እሱ ግን በጎሳ ፖለቲካ የመደራጀት አላማ እንዳልነበረውና ሁኔታዎች እንዳስገደዱት ገልጾልኝ በአማራው ላይ የተመዘዘውን ሰይፍ ለማደነዝ እንጂ ለጎሳ ፖለቲካ እምነት ኖሮት እንዳልገባበት ነግሮኝ በጉዳዩ ዙሪያ ሊያሳምነኝ ሞክሮም ነበር።

በእርግጥም እኔም ብሆን በጉዳዩ ትኩረት ሰጥቼበት ፖለቲካውውስጥ ያስገባውን እጁን ሳይቆሽሽ መልሶ እደንዲያወጣ ለመምከር ሞክሬ ነበር። እየሰራ ያለው የፖለቲካ ስራ ሳይሆን የእሳት አደጋ ስራ ሆኑን ሲነግረኝ ባልቀበለውም ዝም ማለቱን መረጥሁ። እሱ የሚለው አገር ስትቀጣጠል በተገኘው ነገር ለማጥፋት መሞከር እንጂ እኔ የእሳት አደጋ ሰራተኛ አይደለሁም እና አይመለከተኝም ብሎ ዝም ለማለት አይቻልም ባይ ነው። ይህ አባባሉ በብዙ መልኩ ያስኬዳል።

ስለሆነም በነገረኝ ሁሉ አምኜበት ነበር። በወቅቱ የተሰማኝ ስሜት እሱያለው አይነት ስለነበር ከዚያ በኋላ አጥብቄ ልቃወመውአልደፈርኩም አሉኝ ሽማግሌው ቀጥዬ ያነሳሁላቸው ጥያቄ የጊና አገር ወረዳ አስተዳደሪ ስለነበረውና በመጨረሻ አካባቢ ስለሸፈተው አስማረ ዳኜ ስለ ተባው ሰው የሚያውቁት ነገር አለ ወይ የሚል ነበር።

«ጥያቄህ አልገባኝም። ምን ስለሆነ ነው የማውቀው ስለሽፍትነቱ ከሆነ የጠየቅከኝ ሰምቻለሁ» አሉኝና አተኩረው ተመለከቱኝ።

«ስለሽፍትነቱ ሳይሆን ከፕሮፌሰር ጋር ስለነበራቸው የጠበቀ ግንኙነት የሚያውቁት ካለ እንዲነግሩኝ ብዬ ነበር። አስማረ ማንኛውንም የገንዘብ ድጋፍ ያገኝ የነበረው ከፕሮፌሰሩ ነበር የሚል ወሬ አለ። ስለዚህ የሚያውቁት ወይም የሰሙት አለ?» ስላቸው



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

«በእውነቱ ከአስራት ጋር ይገናኝ አይገናኝ የማውቀውም ሆነ የሰማሁት ነገር የለም:: ብቻ አስራት በጦር የተደራጀ ሀይል በሰሜን ሸዋና በጎጃም እንዲሁም በጎንደር ያንቀሳቅሳል የሚል ተባናኝ ወሬ እሰማ ነበር:: በመጨረሻም በዚሁ ወንጀል ተከሰሰ እስር ቤት ተወረወረ» አሉኝና አሁንም እሩቅ ያስቡ ጀመር::

«ይህንን አባባል እርሶ አያምኑበትም» ስላቸው እራሳቸውን አወዛውዘው «በፍፁም ሊሆን የማይቻል ነገር ነው» አሉኝ::ቀጥለውም እንደዚህ አሉኝ።

«አስራት ከልጅነቱ ጀምሮ ለየት ያለ ባህሪ የነበረው ነው:: አስተሳሰቡ እንደ አዋቂ ስለነበር ትንሹን ከትልቁ ለይቶና አመዛዝኖ ነው የሚናገረው::በሁሉም ነገር ሸማግሌ ነበር ለማለት እችላለሁ::

በቤተሰብ መካከል አለመግባባትና ጥል ሲፈጠር ሁኔታውን ሰምቶና ተመልክቶ ዳኝነት እንዲሰጥ አያቱ ትእዛዝ ይሰጡታል:: አስራት ሁኔታውን ከተመለከተ በኋላ የመሰለውን ይፈርዳል:: አያቱ በዚህ ፍትህ አዋቂነቱ ብዙ ነገርንም ያማክሩት ነበር::የሚጠሩትም በክርስትና ስሙ መልአከ ብርሃን ብለው ነው::እንዲያውም አንዳንድ ግዜ ስምን መልአክ ያወጣዋል ብለው ይናገሩ እንደነበርም አስታውሳለሁ፡

አያቱ የቀለም አቀባበሉን ይመለከቱና ሀገራችን ጥበብ የሚያውቁ ልጆች ቢኖሯት እኮ ትልቅ ሀገር ነበረች የሚይናቅ ሕዝብና ባህል አላት:: አንተም ትልቅ ሁን እያሉ የሀገር እና የወገን ፍቅርን ከምንም በላይ የአንድነት መሰረትን ጥቅም በዚያን ግዜነበርያስተማሩት::

አስራት ስለሕዝብ ፍትህ ግንባቤ ማግኘትና ፅኑ የሀገር ፍቅር ያደረበት በዚያ በልጅነቱ እእምሮው ነው::እንደዚህ ባለ ስነምግባር ያደገና ለዚያውም በአለም የታወቀ ስም ያለው ሰው አስራት



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ይቅርና ሌላውም ቢሆን ይህንን ይሰራል ብዬ አላምንበትም:: አስራት አኮ በአገርና በወገን ፍቅር ስሜት ልቡ መንደድ የጀመረው አሁን ላይ ሆኖ አልነበረም::

ታዲያ በሚወደው ህዝብና አገር ላይ ጦርነት መፍትሔ ነው ብሎ ይሰናዳል የሚል እምነት ስለሌለኝ በዚህ ጉዳይ ግራ እጋባለሁ:: በተለይም ደግሞ በ1981 ዓ/ም ታትሞ በወጣው የካቲት መፅሔት ላይ አያቴ ስለሀገሬ የሚነግሩኝ ዛሬ ለኔ ለጓም ሆኖኛል ጫና ሆኖኛል:: ብሎ የሰጠውን አስተያየት አንብቤ ስለነበር ለአገሩና ለወገኑ ያለውን ፍቅር ለመረዳት ችዬአለሁ:: ምንም እንኳን በአማራው ላይ የደረሰው ጥፋት ከፍተኛ ቢሆንም ይደህንን ያደርጋል:: የሚል እምነት የለኝም አሉኝና አትኩረው ተመለከቱኝ::

ቀጥዬ የጠየቅኳቸው ፕሮፌሰሩ ስለነበራቸው የትምህርት ዘመን ሲሆን የሽማግሌው መልስ አስራት ቀደም ብሎ ንባቡንና ሌላውንም ተምሮት ስለነበር ሲፈተን ጥሩ ውጤት ስላገኘ በተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት 13ኛ ክፍል ገባ:: በዚሁ ዓመት ከተማሪዎች ሁሉ ልቆበመገኘቱ ወደ 1ኛ ክፍል ተዛውሮ በ1935 ዓ.ም ከትምህርት ቤቱተማሪዎች በሙሉ አንደኛ በመውጣቱ የካሜራሽልማትከንጉሱ እጅ ተቀብሎ እንደነበርም አስታውሳለሁ::

የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን ከአጠናቀቀ በኋላም የከፍተኛ ትምህርት እድል አግኝቶ ወደ ግብፅ አሌክሳንድሪያ በመሄድ በቪክቶሪያ ኮሌጅ ገባ:: በዚያ ቆይታው ወቅት የሀገር ናፍቶትና የባሕል አለመጣጣም ቢያስቸግረውም ትምህርቱን በሚያስደንቅ ሁኔታ በመከታተሉ መጀመሪያ ላይ ያስገቡት በዝቅተኛ ደረጃ በሚገኝ ክፍል ቢሆንም «በተርም» ባገኘው በጣም ጥሩ ውጤት ወደ ሁለተኛ ደረጃ ተሸጋገረ:: በትምህርት ቤቱ ደንብም ጎበዝ ተማሪ የመኝታ ክፍሎች ኃላፊ ይሆን ነበርና አስራትም



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ኃላፊ ሆነ። በዚያን ወቅት አብረውት ይማሩ የነበሩትን የዛሬ የዮርዳኖስ ንጉስ የሆኑትን ሁሴንንና ሌሎችንም ተማሪዎች እየኮረኮመና እየተቃለደ ያስጠናቸው እንደነበር የግብፅ አገር የትምህርት ቆይታውን ወደአገር ከተመለሰ በኋላ አጫውተኛል።

አስራት ትምህርት የመቀበል ችሎታው የላቀ ቢሆንም ቀደም ብሎ ያልተጤነውና በኋላ ላይ ጎልቶ የታየው ግን ለሃይማኖቱ እና ለአገሩ የነበረው ፅናትና አትንኩኝ ባይነቱ ነበር። በሰው ሀገር ያውም በአረብ ሀገር ግብፅ በፆም አልበላም በማለት የትምህርት ቤሃላፊዎቹን በማስቸገሩ በአንድ ወቅት ብላቴን ጌታ ሎሬንሶ ትእዛዝግብፅ ሄደው ሳለ ዓስራት በፆም አልበላም ብሎ አስቸገረ» ተብሎ ይነገራቸዋል። ሎሬንሶ አስራትን አቅርበው «እኛ እንኳ እንበላ የለምእንዴ ስለዚህ አንተም መብላት አለብህ» በማለት ሊመክሩትና ሊገስፁት ቢሞክሩ።

«እርስዎ ገደል ቢገቡ እኔ ገደል እገባለሁ ወይ» በማለት ቁርጥ ያለ መልስ በመስጠት እንዳሰናበታቸው አውቃለሁ። በግብፅ አምስት ዓመት ቆይታው ከፍተኛ የትምህርት ውጤት በማምጣቱ ወደ እንግሊዝ ሀገር ሄደና ስኮትላንድ በሚገኘው ኤደንብራ ዩኒቨርስቲ ሁለተኛ ድግሪውን ተከታትሏል። ከዚያም በከፍተኛ መአረግ ተመርቆ ወደ አገሩ ተመልሶ በመምጣት ወገኑን ለማገልገል በቅቷል።

በወቅቱ የተላከው የህግ ትመህርት እንዲከታተል ቢሆንም የፈቀደውና ፍልጎቱ የሕክምና ሙያ ማወቅ ስለነበር የሕክምና ትምህርት ነበር ያጠናው። ህክምና ለምን እንደመረጠ ጠይቂው የመለሠልኝ የፈረንጅ ቀበብ ማወቅ የሚለው የአያቱ ምክር በውስጡ ማደሩንና ከምንም በላይ ደግሞ የታመሙ አያቱ ሆስፒታል ገብተው ያለህክምና እርዳታ መሞታቸው ህክምናን እንዲያጠና እንዳስገደደው ነግሮኛል። የህክምና ትምህርቱን በጥሩ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ሁኔታ አጠቃልሎ በማዕረግ መመረቁ ብቻ ሳይሆን ኢንዶብራ ዩኒቨርስቲ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ የሕክምና ተማሪ መሆኑ የተለየ ያደርገዋል። ከጠላት ወረራ በኋላ ወደ ውጭ ሀገር ከተላኩት ኢትዮጵያውያን መካከል 42ኛው የውጭ አገር ተማሪ ነበር።ከውጭ አገር ትምህርቱን አጠናቅቆ እንደተመለሰም ለአንድ ዓመት ያህል በየሆስፒታሉ ልምምድ ሲያደርግ ቆይቶ በ1947 ዓ/ም መደበኛ ስራውን በልእልት ፀሐይ ሆስፒታል ጀመረ።

ጣሊያን ተባሮ ነፃነት ከተመለሰ በኋላ የጤና ጥበቃ ሚኒስትር ሆነው ተሾመው የነበሩት ደጃዝማች ፀሐይ እንቁስላሴ ነበሩ። ምኒስትሩ አስራት ከውጭ እንደተመለሰ የጤና ጥበቃ ስልጣኑን ለሱ ለማስረከብ ፈልገው ነበር። ስለሆነም አስራት ስልጣኑን እንዲረከብ «እኛ በአርበኝነት ይህችን ሀገር ከኢትዮጵያ ጠላቶች ስንጠብቃት ከረምን። አሁን የተማራችሁት ኢትዮጵያውያን ተገቢውን አመራርና ኃላፊነት ለመውሰድ ስለመጣችሁ በጣም ደስ ብሎኛል። ይህንንም ለግርማዊ ጃንሆይ አስረዳለሁ» በማለት ደጃዝማች ፀሐዩ የጤና ጥበቃ ኃላፊነቱን እንዲረከብ ለአስራት ቢያስረዱት ፈቃደኛ አልሆነም። እንደምክንያት የሰጠው ነገርም በበለጠ ለሀገርና ለወገን መስራት የሚያስችለው በቀጥታ በህክምናው ሙያ ተሰማርቶ መገኘቱ እንደሆነ ስለተረዳሁ የወንበሩን እርክክብ አልቀበልም የሚል ነበር። ስለሆነም ስልጣኑን ሳይቀበለው ቀረ። ከዚያም በቀጥታ በሙያው ውስጥ በመግባት ለአምስት ዓመታት ያህል በህክምና ሙያው ሲሰራ ቆየ።

የአምስት ዓመታት የሕክምና ሙያ አገልግሎት ከሰጠ በኋላ እንደገና ወደ ብሪታንያ ተመለሰና በእንድብራ ኢንግላንድ ውስጥ በሚገኘው ሮያል ኮሌጅ ኦፍ ሰርጀርስ የቀዶ ሕክምና ልዩ ትምህርት ያጠና ጀመር። የቀዶ ጥገና ትምህርቱን ተከታትሎ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

እንዳጠናቀቀ ወደ አገሩ ተመልሶ በልዕልት ፀሐይና በጥቁር አንበሳ ሆስፒታሎች በዋና ሰርጀሪነት ወይም ቀዶ ጥገና ሐኪምነት ከሰላሳ ዓመታት በላይ ሲያገለግል መቆየቱን አውቃለሁ:: በሀገራችን የህክምና አገልግሎቶችና ልዩ ልዩ ጥናቶች ውስጥ በኃላፊነት ደረጃም ይሰራ ነበር:: በቀደሞ ዓፄ ኃይለ ስላሴ ዩኒቨርሲቲ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ የሕክምና ፋኩሊቲ ዲንም ነበር:: የሕክምና ዳይሬክተር በነበረበትም ወቅት የልዕልት ፀኃይ ሆስፒታል ተስፋፍቶና ተጠናክሮ እንዲገኝ በብርቱ ይታገል እንደነበር አስታውሳለሁ:: በኢትዮጵያ ምድር እሱ ያልረገጠው የህክምና ተቋም አልነበረም ለማለት እችላለሁ:: በብዙ ስፍራዎች ሰርቷል::

አስራት ባሳለፈው በርካታ የሕክምና ዘመን ውስጥ የአያሌ ሕሙማንን ሕይወት ስለማትረፉና ከምንም በላይ ለሙያው ከፍተኛ ጽናት ያላው እንደነበር በቅርብ የሚያውቁት ምስክሮች ሊሆኑ ስለሚችሉ እነሱን በሙያው በኩል ያለውን ብታነጋግር እመርጣለሁ:: በኔ በኩል የማውቀውን ያህል ለመናገር በቀን እስከ አስራ ስምንት ሰዓት ድረስ የሰራባቸው ጊዜዓቶች በርካታ ነበሩ ነው የሚባለው:: በተለይም በልዕልት ፀሐይ ሆስፒታል በነበረበት ወቅት መኖሪያው በሆስፑታሉ ግቢ ስለነበረ የጠናበት በሽተኛ ከመጣ እሱ መጠራቱ የግድ ነበር::

እኔም በእንግድነት ከቤቱ ለማደር በሄድኩበት ወቅት ብዙ ግዜ ከተኛበት እየተጣራ ይሰራ እንደነበር ገጥሞኛል:: እንዲያውም አብራው ትሰራ የነበረችው ጓደኛው ነርስ ስለስራው ፀባይ ስትናገር «ከሳቸው ጋር ጸሀፊያቸው ሆኜ ለበርካታ አመታት ሰርቻለሁ:: ፕሮፌሰር ዘንድ የስራ ሰዓት ማክበር ብሎ ነገር የለም:: ሌት ከቀን ይሰራሉ:: የህክምናውንም ያስተዳደሩንም ስራ ሲሰሩ የጊዜ እጥረት ስለነበረ የምሳና ቁርስ ሰዓታችን አይከበርም:: የእሳቸውን ሁኔታ እያየሁ ሁሉንም ነገር እንድታገስ እና መስዕዋት



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

እንድከፍል እገደድ ነበር» በማለት ከሱ ቤትበእንግድነት መጥታ በድንገት ተገናኝተን ያጫወተኝ መሆኗን አስ ታውሳለሁ::ነርሷ አልማዝ የምትባል ስትሆን ከሱ ጋር ለብዙ አመታት ሰርታለች:: እንደአለቃ ብቻ ሳይሆን እንደ አባት ታከብረው እደነበር ነው በወቅቱ ያጫወተኝ:: እሷ እንደነገረችኝ «በታካሚዎቻቸውም ሆነ በስራ ባልደረቦቻቸው ዘንድ ፕሮፌሰር ከፍተኛ ከበሬታ አላቸው:: ከሁሉምበላይየሚደንቀኝ ደከመኝ የሚለውን ቃል አለማወቃቸውና ሰው ሲናገረው ከሰሙ መቆጣታቸው ነበር:: ከሳቸውጋር አብሬ በልዕልት ፀሐይና በጥቁር አንበሳ ሆስፒታሎች ለሰላሳ አመታት ያህል አገልግያለሁ::

ፕሮፌሰር አስራት ለሕመምተኞቻቸው ታላቅ አክብሮት ነበራቸው:: ሰውን አያበላልጡም:: ከስራው ዓለም ጀምሮ እስከ ተለየኃቸው ጊዜ ድረስ የማይሰለቹና የማይደከሙ የሙያ ሰው ናቸው:: ከባድ የሆነውን የልብ ኦፕራሲዎን ካደረጉም ወዲህ አልተለወጡም::የሙያልጆቻቸው በሁሉም ነገር እናከብራቸዋለን:: እሳቸው ለሙያቸው በሚሰጡት ፍቅር እኛም ሙያችንን እንድናከብር አድርገውን ነበር::በሽተኞችም በሳቸው ላይ ያላቸው እምነት በጣም የላቀ ነበር::

ከዚያም በላይ የማልረሳው አንድ ታሪክ ከአርባ ምንጭ የመጡ አንድ በሽተኛ «ዓስራት የሚባል ጠበል ፈልቋል ስላተባልኩኝነውወደዚህየመጣሁት»ያሉኝንእስታውሳለሁ::በእምነታ ቸውበኩል ከነበራቸው ፅናት የተነሳም ኦፕራሲዎን ከማድረጋቸው በፊት የመጀመሪያስራቸውን ለእግዚአብሄር አደራ ሳይሰጡ አይጀምሩም::ሙያቸው ሁለገብ ነው:: ሁሉንም የህክምና ዓይነት ይሰራሉ» እያለች ስትተርክልኝ እኔ የማውቀውን አስራትን አልመስልህ ብሎኝ በተመስጦ አደምጣት ነበር:: አሉኝና ትንሽ ካሰቡ በኋላ ዶክተር ስዩም ዮሴፍ የተባለ አንድ ሐኪም ስለሳቸው ብዙ እንደሚያውቅ ነግረውኛል:: አሰስራት ከሞተ በኋላ ተገናኝተን የሱ ተማሪም ነበርኩ አስራት ምንም እንከን



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

የማይወጣለት ባለሙያ ነበር አስተማሪም ሆኖ ተማሪው ማግኘት ያለበትን ዕውቀት አግኝቷል ብሎ ካላመነ ከክፍል ንቅንቅ አይልም::በሚሰራው ስራ ሁሉ አክብሮትና ፍቅር አለው:: በተለይም በሽተኞች ሲሰቃዩ አብሮ ይሰቃያል:: በሌላ በኩልም አስፈላጊውን የቅድመ ምርመራ ሳያካሂድ ኦፐራሲዮን አያደርግም:: አድርጎም ከሆነ በሽተኛው ቢድን እንኳን ክትትሉን አያቋርጥም::እሱጋር ሕይወት ከፍተኛ ዋጋ አላት:: በበሽተኛውም ሆነ በስራ ባልደረቦቹ ዘንድ አክብሮትንና አድናቆትን የተቸረው በዚህ ይመስለኛል:: ላመነበት ነገር ከቶውንም ወደኋላ የሚል አልነበረም:: እንደአስተማሪዬም በኋላም እንደስራ ባልደረባዬ አከብረው ነበር::

ከሱ የተማርኩትሙያን ብቻ ሳይሆን የታረመ ስነምግባርን ጭምር ነው::ይህ ብቻ ሳይሆን አገሬን እንድወድና የተቸገሩ ወገኖቼን እንድረዳ ጥሩ ስነምግባር እንደሰጠኝ እረዳለሁ:: በተለይም ሁልጊዜ የማስታውሰው በስራ ላይ እንዳለን አንድ የአስራ ስምንት ዓመት እድሜ ያለው ከግሪክ ሀገር የመጣ ወጣት ለሽርሽር ናዝሬት ሄዶ እያለ በጥይት ይመታል:: ቁስለኛውን ጥቁር አንበበሳ ሆስፒታል ሕክምና ያደረገለት አስራት ነበር::

አስራት ለወጣቱ ህክምና ከአደረገ በኂላ ወደ ውጭ ሀገር ሄዶ ስለነበር ይህን አጋጣሚ ያገኙት የግሪክ ኮሚኒቲ አባላት ካገራቸው ሀኪም ለማስመጣት አፄ ኃይለስላሴን ይጠይቃሉ:: ንጉሱ ይፈቀድላቸውና ግሪካዊው ሐኪም ይመጣልዕዕ ሐኪሙም የልጁን የህክምና ሁኔታ መርምሮ ከተረዳ በኃላ ለአጼ ኃይለ ስላሴ ሲናገር « እኔ ከመገረምና ከመደነቅ ውጭ የምጨምረው ነገር የለም:: ኢትዮጵያ ውስጥ እንደዚህ አይነት ሐኪም መኖሩ አስደንቆኛል» ብሎ እንደነበር አስታውሳለሁ::በሌላ በኩል አንዲት እንግሊዛዊት ወይዘሮ ማግደሊን ዋይን የሚባሉ ሴት ኢትዩጵያ ውስጥ እያሉ በድንገት ይታመማሉ:: ሕክምና ያደረገላቸው



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

አስራት ነበር:: በዚህ ህክምና የተደነቁት የብሪታንያ አምባሳደር ለአስራት ደበዳቤ ሲጽፉ «ተወዳጁ ሐኪም በቅድሚያ የዩኒክ ታይለር እህት በደረሰባቸው አሰቃቂ አደጋ ወቅት ለአሳዩት ደግነትዎና ወደር ለማይገኝለት ችሎታዎ ጥልቅ ምስጋናዬን በብሪትሽ ካውንስል ስም አቀርባለሁ::ለአደረጉትና ለፈጸሙት የላቀ ተግባር ከፍተኛ የሆነ አድናቆት አሳድሮብኛል::በሙያዎ ለፈጸሙት ጥሩ የሆነ ስነምግባር አስፈላጊ ሲሆን ማንኛንም የሚያስፈልጎትን ነገር እንዲገልጹልኝ በአክብሮት አስታውቃለሁ::

በአሁኑ ጊዜ ገንዘብ ምንም አይደለም:: ከዚህስ ይልቅ ለኛ ትለቁና አስፈላጊያችን ደግነትዎና ችሎታዎ ከምንም በላይ ደግሞ የችግራችንተካፋይነትዎነው::ስለሆነምበድጋሚ አመሰግንዎታለሁ» የሚል ደብዳቤ ከንግስቲቱ ተልኮለት ነበር::አስራት የሙያ ብቃቱ ብቻ ሳይሆን በማንኛውም ነገር ላይ ቁጥብና ቆፍጣና ነበር:: ከምንም በላይ የማ ያስደንቀው የማስታወስ ችሎታው ነበር::

ነገርን አይዘነጋም:: ማንኛውንም ነገር ቀድሞ ይተነብያል::ሁሉነገርቀድሞ ይገባዋል:: በተለይም በእድሜ እየገፋ ሲመጣ አረጋዊ ስብዕናው አክብሮት እንዲቸረው ያደረገው ይመስለኛል::ከመፍራት ይልቅ የመደመጥና የመከበር እድል አለው::በምንም ዓየነት ቢሆን የእግዚአብሄርን ሀያልነት ሳያደንቅ አያልፍም::ስለስራውእንኳንአስተያየትሲሰጠው«ብቻዬንአይደለሁም::

ከእግዚአብሄርና ከስራ ባልደረቦቼ ጋር ነው» ይላል እንጂ አንድ ቀንም ብቻውን ተመስግኖ አያውቅም » በማለት ዶክተር ስለአስራት ሲተርክልኝ እኔ የማውቀው ቢሆም በሌላ ሰው ሲመሰገን በመስማቴ በደንብ ከልቤ ሆኜ አዳምጨው ነበር:: አሉኝና አይኖቻቸው እምባ ሲያቀሩ ንግግራቸውን አቁመው በአሮጌው ጋቢያቸው ጫፍ አይንና አፍንጫቸውን መደባበስ ጀመሩ::ከዚህ በኋላ ልጠይቃቸው አልፈለኩም:: ብዙ ነገር



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ነግረውኛል።ከሽማግሌው ጋር የነበረኝን ውይይት በዚሁ ቋጩሁና ተሰናብቻቸው ልወጣ ከተቀመጥኩበት ስነሳ እጄን ያዝ አድርገው «ትሰማኛለህ የኔ ልጅ በምትፈፅመው ታሪክ ላይ መጠንቀቅ እንደሚኖርብህ አትዘንጋ።አሁን በምትሰኝ መንገድ የአስራትን ታሪክ ብትፅፍ ማንም እውነት ነው ብሎ ሊቀበልህ አይችልም። ብዙ ሰዎችን አነጋግረህ በመረጃ የተረጋገጠ ታሪክ ማውጣት ይኖርብሃል።አስራት የሃይል መንገድ መጀመሩ እውነት ከሆም ከጥንት አባቶቹ የተቀበለው የአጥንትና የደም የጀግንነት ውርስ ስለሆነ እኮራብታለሁ እንጂ በኔ በኩል አላፍርበትም። ምናልባትም ለአስራት ስም እና ዝና ሳይሆን የአስራትታሪክ ጎልቶ እንዳይወጣ ለማድረግ የሚቃወሙህ ግለሰቦች ሊኖሩ ይችላሉእነዚህ ሳይሞቱ ታሪካቸዉ የተቀበረባቸዉ ደካሞች የአስራት ስም ከነሱ ጎልቶ እንዲወጣ አይፈልጉም።እኔ ግን ጅምርክን እዳር እንድታደርሰው እፀልይልሃለሁ።በሌላ በከል ልብ እንድትለዉ የማስገነዝብህ ሀብቱን በተመለከተ ምንም እንዳታነሳ ነዉ"አሉኝ።

"አልገባኝ" ስላቸዉ

"እየህ የኔ ልጅ የአስራት ሀብት በየነዉ ተበትኖ የቀረዉ።የሃብቱንጉዳይበተመለከተልጆቹመከታተልይችላሉ።እንዲያ ዉም በዚህ ዙርያ ያግለሰቦች ስለምንም ነገር ባታነጋግራቸዉ እመርጣለሁአስራት ብልጭ ብሎ ብርሃን አሳይቶ መለሶ የጠፋ ነፀብራቅ ነው።ነፀብራቁም ወደ አማራው ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያም ላይ ወድቆ የነበረውን የመለያየ ጥቁር ጨለማ በትኖታል።አሉኝና እጄን ጥብ አድርገው በመጨበጥ ወደራሳቸው እቅርበውኝ መሃል አናቴን ከሳሙኝ በኋላ አሰናበቱኝ።



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

# ምዕራፍ አስራ ሰባት

# የጥቁር አንበሳው ዶክተር

መልኩ ጠይምና ሰውነቱ የወታደር አይነት ቅርፅ ያለው ግዙፍ ሊባል የሚችል ቀልጣፋ ሰው ነው:: በመጀመሪያ በስልክ ቀጠሮ የሰጠኝ ጦርሃይሎች አካባቢ ከሚሰራበት የግል ሆስፒታ ማክሰኞ ከሰዓት በኋላ እንድንገናኝ ነበር:: ማክሰኞ ስምንት ሰዓት ከሆስፒታሉ ደረስሁና በቀጥታ ወደ እንግዳ መቀበያው ክፍል አመራሁ::

ከፊት ለፊቱ ከባኮኔዉ ጀርባ ያለችዉን ቀይ ቀጭን መልከመልካም ልጅ እየተመለከትሁ «ዶክተር እ ለማግኘት እችላሁ እመቤት» ስል ጠየቅኳት::

ቀና ብላ እየተመለከተችኝ «ዶክተር እ አልገባም::አስር ሲአት ላይ ይመጣል ቁጭ በልና ጠብቅ» አለችኝ::

ለእንግዳ መቀመጫ በተዘጋጀው ባለ ጥቁር ቆዳ ሶፋ ላይ አረፍ አልሁ:: ከእንግዳ መቀበያው ሰፊ ክፍል ከአንድ ጥግ በኩል ከሳተላይት የሚተላለፍ የፊልም ፕሮግራም እየተሰራጨ ስለነበር ከፊልሙ ላይ አይኔን አሳርፌ ስለቀጣዩ ሁኔታ በልቤ አስብ ጀመር:: ብዙ ሰዓት የተቀመጥሁ መሰሎኝ ሰዓቴን ብመለከትም ለዘጠኝ አስር ጉዳት ይላል:: የሰዓቱ መንቀርፈፍ አናደደኝና ተነስቼ ወደ ውጭ ወጣሁ::

ምድረ ግቢው ደስ ይላል:: ሁሉም ነገር የተያዘው ጥንቃቄ በተመላበት ንፅህና ነው:: በግቢው ውስጥ እየተዘዋወርሁ ሁሉንም ገር በምጎበኝበት ሰዓት ተራቸውን የሚጠብቁ በርካታታካሚዎች ተመለከትሁ::አብዛኛዎቹ ታካሚዎች ለሽርሽር የመጡእንጂ ፍፁም የበሽተኛ ገፅ አይታይባቸውም::ከ'ዚህ ታካሚዎች የተረዳሁት ነገር ቢኖር ወደዚህ ሆስፒታል የሚመላለሱት በእስጊ ህመም ተይዘው ሳይሆን እራሳቸውን ቼክ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ለማድረግ እንደሆነ መገመትይቻላል::ሁሉም የቅንጦት ታካሚዎች እንጂ እውነተኛ ህመምተኛ አለመሆናቸውን በትክክል ለመረዳት ይቻላል::አስር ተኩል ሲሆን ዶክተሩ ወደ ቢሮው መግባቱን ልትነግረኝ እንግዳ ተቀባይዋ ወደእኔ መጣች::አመስግኛት ከእንግዳ መቀበያው ፊት ለፊት ወደ ሚገኘው ሰፊ ቢሮ ሳመራ ወለል ብሎ በተከፈተው በርከጠረጰዛው በስተጀባ የተቀመጠውን ጠይምበእስፓርት የተገነባ የሚመስል ግዙፍ ሰውነት ያለውን ሰው ተመለከትሁ::ከሱ ፊት ለፊት ሌሎች ሶስት ሰዎችም ተቀምጠዋል:: እየተወያዩ ስለነበር በስራ ጉዳይ ላይ እየተመካከሩ እንደነበር ገመትሁ:: እበሩ አጠገብ ስደርስ በእጁ ምልክት ሰጠኝና ወደኔ መጥቶ ይቅርታ ጠይቆኝ ለአምስት ደቂቃ ከውጭ እንድጠብቀው ነገረኝና ወደ እንግዳዎቹ ተመለሰ::

ለአስር ደቂቃ ያህል በግቢው ስዘዋወር ቆይቼ ከአስር ደቂቃ በኋላ እራሱ መጣና ወደ ቢሮው እንድገባ ጠራኝ:: ዶክተሩ ትህትናው ይስባል:: ተያይዘን ወደ ውስጥ ከገባን በኋላ እስክቀመጥ ድረስ ጠብቆኝ እሱም አረፍ አለ:: ከሱ የተረዳሁት ቢኖር መልካም ስብእናን የተላበሰና ምሁራዊ ትህትናን ጭምር እንደካፓ የደረበ መሁኑን ነበር::ከዚያ በፊት በአካል ተገናኝተን አናውቅም:: ምንም ሳንነጋገር የተወሰኑ ደቂቃዎች እየተከታተሉ ሄደው በመጨረሻም በሱ ጋባዥነት የውይይት ርዕስ ተከፈተና ለምን ጉዳይ እንደምፈልገው ጠየቀኝ:: እራሴን ለማስተዋወቅ ያህል ጥብቅ ምስጢር በሚል ርዕስ አሳትሜው የነበረውን እና የፕሮፌሰሩ ምስል ያለበትን መፅሐፍ ከቦርሳዬ አውጥቼ ሰጠሁት::

ይህ ደግሞ ማንነቴን በደንብ እንዲረዳ ያደረግኩት የመጀመሪያመግባቢያነበር::መፅሀፉንከተመለከተበኋላስለምፈልገው ጉዳይ አጠር አድርጌ እንዳስረዳው ነገረኝ:: ስለምፈልገው ጉዳይ አጠር አድርጌ ካስረዳሁት በኋላ ሌላ ጊዜ ቀጠሮ መያዝ እንዳለብን ነግሮኝ እራሴን እንድመርጥ ከሰኞ እስከ አርብ ያሉትን ቀኖች ደረደረልኝ:: ማክሰኞ እንደሚሻል ስለመረጥሁ ማክሰኞ ከሰዓት ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል እንድንገናኝ ቀጠሮ ይዞልኝ ተለያየን:: ዶክተሩን በቀጠሮአችንለት እንደጠበቅሁት አልነበረም



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ያገኘሁት:: ዶክተሩ በፍፁም መረጋጋት አይታይበትም:: ይህ ሁኔታ ደግሞ በልቤ ውስጥ አንድ ጥርጣሬ እንዲጭርብኝ አድርጎኛል:: ምናልባት ካቀረብኩለት ጥያቄ አንዱር ሳይጠራጠረኝ እንዳልቀረ እርግጠኛ ነበርሁ::ፕሮፌሰሩ በመሳሪያ የተደራጀ ኃይል ነበራቸው ስለሚባለው ታሪክ ጠቀስ አድርጌለት ነበር።በመጀመሪያ ስለዚህ ጉዳይ ቀድሜ ማንሳት እንዳልነበረብኝ የተረዳሁት ዘግይቼ ነበር:: ማንም ሰው ፕሮፌሰር አስራት የጦር መሳሪያ አንስተዋል ብሎ ቢናገር የሚቀበለው እንደማይኖር ሽማግሌው በአንክሮ አስረድተውኛል::ለዶክተሩ ይህንን ጥያቄ ሳነሳበት የመንግስት ሰላይ መስዬ እንደታየሁት አሁን ላይ ምንም አልተጠራጠርኩም:: የፈራሁት አልቀረም ዶክተሩ ምንም የሚያውቀው ነገር እንደሌለ ገልጾልኝ በዚህ ዙሪያ ሌሎችን ባነጋግር እንደሚሻል ከነገረኝ በኋላ በወቅቱ በእሳቸው ቤት ይኖር የነበረ አንድ ሰራተኛቸው በሆስፒታሉየቀንሰራተኛነት እየሰራ እንደሚገኝ ገለፀልኝእንደዚህ በማለት ነበርየገለጠልኝ::

«ይህ ሰው በዚህ ዙሪያ ያለውን ነገር ሊረዳህ ይችላል:: እንደ አትክልተኛም እንደ ዘበኛም በመሆን ከፕሮፌሰሩ ቤት ለብዙ ዓመታት አብሮአቸዉ ነበር:: እሳቸው ከሞቱ በኋላም ቤቱን እየተቆጣጠረ እስከአሁን ድረስ በዚያው ቆይቷል:: ስለሆነም ብዙ ምስጢር የሆኑ ነገሮችን ሊያውቅ እንደሚችል እገምታለሁ:: ከእሱ ስትገናኝ አንድ ነገር መጠንቀቅ ይኖርብሃል:: ከኢንጂነሩ ጋር መግባባታችሁን በፍፁም ማወቅ የለበትም::ይህንን ካወቀ መረጃመስጠትአይደለምአጠገብህእንኳንለመቆም አይፈልግም::ሰላይ ላኩብኝ ነው የሚለው» አለኝ ዶክተሩ እንደዚህ እያጋነነ ሲነግረኝ በሩ ተከፈተና አንድ የወዛደሮች ጋዎን ያጠለቀ ሰው ከውጭ ወደ ውስጥ ገባ:: ከገባው ሰው ጋር ለተወሰኑ ደቂቃዎች ተፋጥጠን ተያየን::ይህ ሰዉ በትክክል ያውቀኛል እኔም በደንብ አድርጌ አውቀዋለሁ::ዶክተሩ ደእያጋነነ የነገረኝ ስለዚህ ሰው ከሆነ ትክክል አልነበረም:: ሰውየው እኔን ሲመለከት አመድ እንደነፋበት ሁሉ ፊቱ ሲቦን ይታየኝ ነበር:: ዝናብ እንዳጣ የጤፍ ሰብል ሳስተው ጭንቅላቱን ያጋለጡት ብናኝ ፀጉሮቹ የነፈሰው ሁሉ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ያወዛውዛቸዋል፡፡ ፊቱን የከበበው ሪዙ የጫካ ባህታዊ አስመስሎታል፡፡ ቁመቱ መካከልኛ ሲሆን ለብዙ አመት ከጋሪጋር የታገለው ሰውነቱ የፈረጠመ ነው፡፡

«እየነገርኩህ የነበረው ሰው እሱ ነበር፡፡ ተዋውቀው ተስፋዬ፡፡ ስለፕሮፌሰር አንድ መፅሐፍ ለማዘጋጀት ይፈልጋል» አለ ዶክተሩ ወደወዛደሩእየተመለከተ እንደዘህ አለኝ፡፡

ተስፋዬ በቆመበት እንደደረቀ ነበር፡፡ ለዶክተሩ ዋሽቶታል ከነ አቶ ኂይሉ ግሩፕ እንደማይገናኝ ነግርታል፡፡ እኔ ግን ከዚህ ቢሮ በሄድኩባቸው ቀናቶች ሁሉ አገኘው ነበር፡፡ ከሂሳብ ሹምና ከገንዘብ ከፋዩ ጋርም የጠበቀ ትስስር እንደላቸው አውቃለሁ፡፡ ወደውጭ አገር ለሚሄዱ ሰዎች የሃሰት የአባልነት መታወቂያ ቅብብሎሽ እንደሚሰራም እንደማውቅ ተስፋዬ ጠንቅቆ ማወቅ ብቻ አይደለም ከኔ መሸሽ እንዳለበትም በነዚሁ ሰዎች ጥብቅ ትእዛዝ ተሰጥቶታል፡፡ ትክክል ነበሩ፡፡ በዚህ ዙሪያ ያለው የገብዘብ ቅብብሽ ሁሉንም ከተራ ድህነት ወደ ግል ባለንብረትነት አሸጋግሮአቸዋል፡፡ የዚህ አይነት ጥቁር ገበያ እንደኔ ካለ ፀሐፊ መደበቅ እንዳለበትም ተስፋዬ ስራው ነውና ጠንቅቆያውቃል፡፡

ቀና አልሁ ወደ ዶክተሩ «እሱንማ አውቀዋለሁ» ስል መለስኩለት፡፡ዶክተሩ ፈገግ ለማለት እየሞከረ አስተዋለኝ።

በዚህን ግዜ ነበር ተስፋዬ የበለጠ የደነገጠውና እጅና እግሩ ሲንቀጠቀጥ ያስተዋልኩት፡፡ እንደምንም ብሎ ወደኔ ተጠጋና እጄን ዘርግቶ ጨበጠኝ፡፡ በላብ የተጨመቀው ቆርፋዳ መዳፉ አዳለጠኝና ቶሎ ብዬ ለቀቅኩት፡፡ ጊዜ አላባከነም። በመጣበት አኳኋን ገርበብ ያለውን በር ታክኮ ተመልሶ ወጣ፡፡ ከዚያ በኋላ ስለነበረው ሁኔታ ባላውቅም ከኔ ጋር መገናኘት እንደሌለበት ዶክተሩን እንደሚያስጠነቅቀው እርግጠኛ ነበርሁ፡፡ ከዶክተሩ ጋር በጨረፍታ ተያየን፡፡ ግራ የመጋባት ስሜት አነበብኩበት፡፡ ባለመረጋጋት ስሜት እንደተዋጠ ከቢሮው ትቶኝ ወጣና በኩሪደሩ በስተምስራቅ በአለው አቅጣጫ እየተፋጠነ ሲራመድ የጫማው ኩቴ ተሰማኝ፡፡ ያለምንም ጥርጥር ተስፋዬን ፍለጋ ነበር የሄደው። ከተወሰነ ቆይታ በኋላ ያለሁበት በር



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ተከፈተና የዶክተሩ ግዙፍ ቁመና ወደክፍሉ ውስጥ ገባ። ቀና ብዬ ስመለከተው ፊቱን የጠመዘዘብኝ መሰለኝ:: ምንም ሳያናግረኝ በጀርባዬ በኩል አልፎ ከወንበሩ ላይ ተቀመጠ ።አጕንብሶ ወረቀት ማገላበጥ በመጀመሩ ፊት እየነሳኝ መሰለኝ:: ግምቴ ትክክል ነበር:: ዶክተሩ ከደከመህ ልትወጣ ትችላለህ በሚል አይነት ወረቀት ማገላበጡን ቀጥሏል:: ከሰው ቢሮ ውስጥ ተቀመጦ መዘጋጋት ህሊናን የሚደፈጥጠዉ ስሜት ከባድ መሆኑን የተገነዘብኩት በዚያች ሰአት ነበር:: ተነስቼ ልወጣ እያመነታሁ እያለሁ በድንገት ቀና ብሎ አየኝና "በጣም አዝናለሁ ። ወደ ሰርጂካል ክፍል ልገባ ስለሆነ ቀጠሮአችንን ወደሌላ ቀን እናሸጋግረው" አለኝ::

«ይቻላል» አልኩት:: በመገላገል አይነት ስሜት::

«አርብ እኔ እራሴ እደውልልሀለሁ::»

"ጊዜህን በመሻማቴ በጣም ይቅርታ አልኩት። ከተቀመጥኩበት በመገላገል ስሜት ፈጠን ብዬ እየተነሳሁ::

"ምንም አይደለም። ልረዳህ በቻልኩ በጣም ደስ ባለኝ ነበር:: ለሁሉም ይቅርታ መጠየቅ ያለብኝ እኔ እንጂ አንተ አይደለህም። የእኛ ስራ የተቆረሰ እንጀራ አያስጕርስም" አለኝ ከተቀመጠበት እየተነሳ።

"አመሰግናለሁ ዶክተር" የተናገርኩት ከልቤ ነበር። ተስፋዬ ከጥርጣሬ ውስጥ የሚከትት ነገር ለኮሰበት እንጂ ይህ መቀያየር ከዶክተሩ የመነጨ እንዳልሆነ ተረድቼዋለሁ:: ስለኔ ብዙ ማወቅ ስለፈለገ ይመስለኛል ቀጠሮአችንን ወደሌላ ጊዜ እንዲሸጋገር ያደረገው። ይህ ከሆነም ዶክተሩ ትክክል ነው:: በጥርጣሬ እንደተሞላ ማንነቱን ለማያውቀው ሰው ቃል ሰጥ ብሎ የሚያስገድደው የህሊናም ሆነ የህግ ዳኛ የለም። ተሰናብቼው ወጣሁ:: አርብ ጠዋት ዶክተሩ ሲደውልልኝ ሁኔታዎች



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

እንደተሻሻለ ገምቼ ነበር::አራት ሰዓት ላይ ቀጥሮኝ ስለኩን ሲዘጋ የራሴን ሰዓት አየሁ:: ለአራት ሩብ ጉዳይ ይላል:: የምንገናኝበትን ሰአት በማሳጠሩ ነገሩ የግብር ይዉጣ መሰለኝ። ቢሮ ስደርስ ለአምስት አስር ጉዳይ ሆኖ ነበር:: ወደ ቢሮው እንደገባሁ ያለፋታ እያነጋገረኝ ስለነበር አቀራረቡ ቀጥተኛ ስላልነበር ተግባብተን ቁም ነገር እንነጋገራለን የሚለው እስተሳሰቤ ከውስጤ እየተነነ ጠፋ። የቢሮውን በር ከፍቼ ወደ ውስጥ ስገባ የነበረዉ አመለካከት መልካም አልነበረም::ፕሮፌሰሩ በእስር ላይ እንዳለ እሱ በዉጭ አገር እንደነበር አስረዳኝ:: ለቃለመጠይቅ ያዘጋጀሁትን ፅሁፍ መልሶ ሰጠኝ። በቴፕ ለመቅረፅማ ፊፅሞ የማይታሰብ ጉዳይ ነበር::ሁኔታው እያስገረመኝ ተሰናብቼው ልወጣ ስዘጋጅ ከተቀመጠበት ተነሳ። ወደበሩ ስራመድ ተከተለኝና

«አንድ ነገር ልንገርህ?» አለኝ:: ለመስማት እየጓጓሁ እሺ ታዬን አንገቴን በማወዛወዝ ብቻ ገለፅኩለት::

«በእኔ እምነት ፕሮፌሰር የሞቱት በኢህዲግ ሳይሆን ከጎናቸው በከበቧቸው የራሳቸው ሰዎች ነዉ የግምት ነዉ ያለኝ:: ይህ ግምቴ ትክክል እንደነበረም የተረዳሁት የሞቱለትን ድርድት አፈርሰው መታሰቢያቸውን በማጥፋት እነሱ በፈለጉትና ሲመኙት በነበረው መንገድ በስማቸው ብቻ እየነገዱ ሳያቸው ነበር» አለኝና ከበሩ ላይ ስንደርስ እጄን ለስንብት ጨበጠኝ::

ይህንን ሁኔታ ግልጽ እንዲያደርግልኝ ብጠይቀውም እንደማይነግረኝአጋግጦልኝ በሩን ከፍቶልኝ እኔ እንድወጣሁከኋላዬ መልሶ ዘጋው:: ስለፕሮፌሰሩ የሰጠኝ አስተያየትበአእምሮዬ ውስጥ ብዙ ጥያቄ ያስነሳብኝ ስለነበር አያሌ ትዝታዎችን እያስላሰልሁ ግቢውን ለቅቄ ወጣሁናቁልቁለታማውን የጥቁር አንበሳ ሆስፒታል መንገድ በደመነፍስ እየተገፋሁ ወረድሁ:: ብሔራዊ ቴአትር ግቢ ከአለው የመዝናኛ ስፍራ ገብቼ ቡና አዘዝሁና እየጠጣሁ ብዙ ነገሮችን አወጣና አውርድ ጀመር:: የዶክተሩን አይነት አስተያየት የሰጡኝ እጅግ ብዙ ሰዎች ነበሩ:: በተለይ የድርጅቱ መስራች የነበሩናየሸዋ አማራዎች የመኢህድን መፍረስ የወሰዱት ሆን ተብሎ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

በአማራው ላይ የተፈፀመ ሴራ አድርገው ነው። ሌላው ብሔር ከሁለትናከስስት ያላነሱ እራሱን የሚጠልልበት የፖለቲካ ድርጅት እያለው ከአገሪቱ ህዝብ አርባ በመቶ የሚሸፍነውን አማራ ያለድርጅት ማስቀረት አማራዉን ለማጥፋት የተወጠነ የተንኮል ሴራ ነው ብለው ያመኑ ብዙ ሰዎች አሉ።

በተለይም እንደ ብሄረ አማራ ያለ በብዙ ችግሮች የተከበበ ብሔር አንድ መአህድ ቢኖረው እሱን እንዲፈርስ የተደረገበት ዋናው ምክንያት አማራውን ሆን ተብሎ ቢጠቃ የሚከራከርለት እንዳይኖር ለማድረግ ታስቦ እንጂ መአህድን ወደ መኢአድ እንደቀየሩት ሰዎች የአማራውን ህዝብ ይሁንታ ያገኘ ለውጥ አይደለም አልነበረም።

በመአህድ መፍረስ አብዛኛዎቹ የቀድሞነመስራችአባሎች ቅሬታ ማሰማት ብቻ ሳይሆን መአህድን ጥለው ተሰናብተዋል። በተለይም የሸዋ አማራ ነን የሚሉት ከመአህድ መፍረስ በተጨማሪ የፕሮፌሰር አስራት ምስል የድርጅቱ ልሳን ከሆነው እና ከፕሮፌሰሩ ጀምሮ ከሚታተመው አንድነት ጋዜጣ ላይ መነሳቱ ምክሩ እንደአበሳጫቸው ይናገራሉ።በማነጋግራቸው ወቅትም አብዛኞቹ ይህንን ገልፀውልኛል። የቀረበልኝን ቡና እየጠጣሁ ብዙ ነገሮችን ሳስብ ቆየሁና በመጨረሻም የገጠመኝን ሁሉ ለሻንበል ሚካኤል በለጠ ለመንገርና በጉዳዩ ላይ እንደገና እንድንወያይበት ለማድረግ አሰብሁ።

ማስታወሻዬን አውጥቼ ሳገላብጥ ቆይቼ በመጨረሻ ላይ ስልኩን ስለአገኘሁት ቁጥሮቹን ከሞባይሌ ላይ በመመዝገብ መደወያውን ተጭኜ ተጠባበቅሁ።ስልኩ ተነሳና ሻምበል ሚካኤ በለጠ ለምን እንደጠፋሁ ከጠየቀኝ በኋላ ተገናኝተን በገጠመኝ ነገር ሁሉ ብንወያይ እደሚሻል ነግሬዉ ተሰናበተኝ።ከሶስት ቀን በኋላ እነና ሻምበል ሚካኤል በለጠኤምፔሪያል ሆቴል ተገናኝተን ቡና እየጠጣን ስለስራ ስለኑሮ ትንሽ ከተጫዋወትን በኋላ ወደዋናው ቁም ነገር ገብቼ የገጠመኝን ሁሉ እየዘረዘርሁ ማስረዳቴን ቀጠልሁ።ናዝሬት ሄጄ አቶ ታዬ ከሰጡኝ አስተያዬት ጀምሬ ደብረብርሃን ከተማ ያገኘኋቸውን



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

የፕሮሰሩ አጎት ምን አይነት ትሁት ሽማግሌ እንደሆኑና ከሰጡኝ መረጃ ጋር አንድ በአንድ አጫወትኩት:: ዶክተር ደረጀ ስለሰጠኝ አስተያዬት እና ስለተስፋዬ ሁሉንም ነገር ነገርኩት::በተለይም ደብረብርሃን ከተማ ያሉትን የፕሮፌሰሩን አጎት አንስቼ ስለ ፕሮፌሰር የሰጡኝን አስተያየት በምነግረው ሰዓት እጅግ ተገርሞ ነበር ያዳመጠኝ::

«ሰመሆኑ እንዴት ልታገኛቸው ቻልክ? እኔ እኮ የቅርብ ዘመድ ያላቸው አይመስለኝም ነበር » አለኝ ሻምበል ሚካኤል

«የቅርብ ዘመዳቸዉ የሆኑ ሰው ደብረብርሃን እንደሚኖሩ የነገረኝ ሰሚኔን ገበያ አካባቢ የሚኖሩ አንዲት ሴት ናቸው » አልኩት።

«ከእሳቸው ብዙ ነገር እንደምታገኝ እገምታለሁ » ሲል መለሰልኝ ሻምበሉ።

«አግኝቻለሁ አስራትን ከውልደት እስከ አስተዳደጋቸው ያለውን ታሪክ ነግረውኛል::»

«ታሪኩ አንተ በምትፈልገው መንገድ እንደምትጽፈው ገልጸሁላቸዋል::?»

«ገልጬላቸዋለሁ:: በመረጃ የተደገፈ እና እውነትነትን የጨበጠ ከሆነ እንደሚደሰቱ ነው የነገሩኝ።»

«በፕሮፉሰሩ ላይ ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል::?»

«ይህንንእንኳንሰመገመትይከብደኛል:: እሳቸው ሊነግሩኝ የፈለጉት በእውነት ላይ ተመርኩዤ እንድፅፈው ብቻ ነው::በሌላ በኩል ስለ አስራት የሰጡኝ አስተያየት አስደንቆኛል::»

«ምን አሉህ ?» አለኝ ሻምበሉ::

«አስራት አንድ ጊዜ ብቻ ታይቶ የጠፉ ነፀብራቅ ነው:: በዚያው ቅፅበትም በአማራው ላይ የነበረውን መጥፎ አሰመለካከት ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያም ላይ አንዣብቦ የነበረውን የጥላቻ አደጋ ለውጦታ አሉኝ::ከዚህ በመነሳት እኔም የመፅሐፉን ርዕስ

«ነፀብራቅ ልለው ወስኛለሁ አንተስ ምን ይመስልሃል?» ስለው

«ጥሩ እርእስ ይመስለኛል»አለኝ ሻምበልሚካኤል:: ክፍል ሁለትን በቅርብ እጀምራለሁ:: ቃለመጠየቅ ሳደርግልህ ብዙ ቡና መጣጣት ያስፈልገኛል:: አንተ ቤት ብመጣ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

አታስፈ.ሳልኝም?» አልኩት እሳቀሁ።

«አንተ እንደሆንክ የትዳር ሽፍታ ሆንሃል» አለኝ እሱም ከትከት ብሎእየሳቀ።ከሻምበል ሚካኤል ጋር ያደረግነው ውይይት ረጅምና በአብዛው በመኢአድ ሰዎች የተደረገበትን የከፋ በደል የሚተርክ ነበር።በእስር ቤት ከደረሰበት የበለጠ ችግርና ስቃይ የተቀበለው በመኢአድ ሰዎች ነበር።በነበረው ቆይታ በነዚህ ሰዎች የማስገደል ሙከራም ደርሶበታል።እ እንደነገረኝ ድርጅቱ ለምርጫ ዘጠና ሰባት ውድድር አባላትን በሚያስባስብበትና የፖለቲካ ትምህርርት በሚሰጥበት ወቅት በተለያዩ የሃገሪቱ ክልሎች ብዙ የቅስቀሳ ስራ በመስራት ለመኢአድ ጥሩ መሰረት የጣለ ሰው ነበር።በወለጋ በጅማ፣ በጎጃም ፣በጎንደር እንዲሁም በደቡብ ክሎች በርካታ የማደራጀት ስራዎችን በመስራት ለቅንጅት ወደመጨረሻ ጠንክሮ መውጣት መሰረት የጣለ ሰው ነው።የዚህ አይነቱ ጥንካሬ በመኢአድ ሰዎች የሚደገፍና የሚበረታታ ባለመሆኑ ሰሜን ሸዋ አንኮበር ወረዳ በቅስቀሳ ስራ ላይ ሊያስገድት ሲሉ ለትንሽ እንደተረፈም በጭውውታችንወቅትነግሮኛል በሰሜን ሸዋ ቆላማው አካባቢ የቅስቀሳ ስራ እንዲሰራ በድርጅቱ በኩል ሲልኩት እሱን በዚያው የሚያስቀር ገዳይ ቡድን የተመደበለት መሁኑን አንድ ሰው ስልክ ደውሎ ጥንቃቄ እንዲያደርግ ይነግረዋል ወደሰሜን ሸዋ መሄዱን ባይሰርዝም ወደተመደበበት ቆላማ አካባቢ ከመውረዱ በፊት አንኮበር ወረዳ ውሎ ማደር ይመርጣል።

እሱንለመግደል የተመደበው ሰው እየተከታተለው ስለነበር አልጋ ሲከራይ ገዳዩም ከሱ ቀጥሎ አንድ ክፍል ይከራያል ከምሽቱ ሰባት ሰዓት አካባቢ በተከራየበት አልጋ ክፍል የመግደል ሙከራው ይደረግና ሌላ ሰው ቆስሎ ሻምበል ሚካኤል ይተርፋል።እሱ ተርፎ ሌላው ግለሰብ የተመታው ክፍሉን በመጀመሪያ የተከራየው ሻምበሉ ሲሆን አልተመቸኝም ብሎ ሌላ እንዲቀየርለት በማድረጉ የቆሰለው ሰው ሻምበሉ በመጀመሪያ ተከራይቶት በነበረው ክፍል ስለገባ በስህተት በጥይት ተመትቶ ይቆስላል።ሻምበል ሚካኤልበቆሰለውሰውበመጠርጠሩ ይታሰራል። ተጠርጥሮ ከታሰረ በኋላ ቁስኛው ከሞት በመዳኑ እሱ አይደለም የመታኝ ይለቀቅልኝ



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor

ብሎ ቃሉን በመስጠቱ ከእስር ነፃ ሊሆን ቻለ እንጂ ሞቶ ቢሆን ኖሮበእስርቤትገብቶእየማቀቀእንዲኖርሲያደርጉትምእንደነበርሚካኤ ልበለጠ ይናገራል።ድርጊቱ የተቀነባበረውና እሱን የመግደል ሙከራ የተደረገበት በመኢአድቀልፍ ሰዎች እንደሆነ በደብዳቤ ለኢንጂነር ኃይሉ ሻውል በማመልከቱ ኢንጂነሩ በዚህ ድርጊቱ ተቆጥተው ከነመጨረሻው ከድርጅቱ እንዲበረር ያደርጉታል።ይህ የተደረገው የምርጫ ዘጠና ሰባት ጉዳይ ኢትዮጵያን እያወዛገቡትና እያተራመሰት በነበረበት ወቅት ስለነበር ኢንጂነሩ ከሻምበሉ ይቀርቡ የነበሩትን አባሎችን ጭምር «የወያኔ ቅጥረኞች ናቸው» የሚልመግለጫበመስጠትሁሉንምከሻምበሉ ጋር ያባርሩዋቸዋል።

ኢንጂነሩ ይቅርታ ጠይቀው ከእስር እስከተፈቱበትና የቅሌት ካፓቸውን እስከ አጠልቁበት 2000 ዓ.ም ድረስ ያሉት ሁሉ ይደመጥላቸው ስለነበር በሰጡት መግለጫ ማንም አስት ነው ብሎ የተከራከረ አልነበረም። የሻምበል ሚካኤል መገድል ለመኢአድ ሰዎች ሁለት ወሳኝ ጥቅም እንደነበረው ሚካኤል በአንደበቱ ይናገራል።ስለሁኔታው ሲያብራራም «የኔ መገደል ለነዚህ ከአፍንጫቸው ባልዘለለ ለሚያስቡ ሰዎች በድርጅቱ ውስጥ ያለ አንድ ጠንካራ ሰው አስወግደው ከነደካማ አስተሳሰባቸው እንደልብ መንፏቀቅ ሲሆን ሌላው ኢህአዴግ ገደለው ብለው የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት የተወጠነ የተንኮል ተግባር ነበር።

የነሱ ቤተ መንግስት ያች ቸርችል ጎዳና የምትገኘዉ ቢሯቸው በመሆኗ ወደሷ የሚመጣ ማንኛውንም ሰው ጥሩም ሰራአልሰራ ጠላት ነውብለውያስቡታል።ከፍተኛ የገቢ ምንጫቸዉ ያችቢሮስለሆነች ስለ ሀገርና ወገን የሚቆረቆር ቀንደኛጠላታቸዉ ነዉ ይላል ሻምበል ሚካኤል በለጠ። እነዚህንና ሌሎችንም እያነሳን ከሻምበል ሚካኤል ጋር ለብዙ ሰዓት በብዙ ጉዳዮች ላይአወ.ርተናል።ዉድ አንባብያን ታሪኩ አላበቃምና በክፍል ሁለት እንገናኝ በአሁንወቅትሻምበልሚካኤል በለጠ በአንድ የውጭ ድርጅት ውስጥ ተቀጥሮ እየሰራ ነው።ሙሉ የምትባል ሚስትም አግብቶም የአንዲት የምታምር ሴት ልጅ አባት ሆኗል . . .



PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor



‹‹...በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ በሁሉም መልክና አቅጣጫ በአደጋ ላይ ትገኛለች፡፡ ስለሆነም በዚህ አደጋ ባንዣበበት ወቅት አማራው የቆየ ልምዱንና ትዕግስቱን ተጠቅሞ ለዘለቄታው የኢትዮጵያ ዕድልና ጥቅም በረጅሙ እንዲያስብ ስንጠይቅ ሌሎቹ ደግሞ በገዛ ዱራችን ዋሻዎችና መሬታችን እንዴት እንደምንሸፍትና እንዴት እንደምንዋጋ ሊያስተምሩንና በአጭሩ እንድናስብ ሊገፋፉን ይፈልጋሉ፡፡

እኛ ግን ሰለጦርነት ለአማራው መናገርና መገፋፋት ልጅ ለእናቷ ምጥ አስተማረቻት እንደማለት ነው እንላቸዋለን፡፡ ምክንያቱም አማራ መሣሪያውን ለምንና እንዴት እንደሚጠቀምበት፣ መቼ እንደሚያነሳውና በማን ላይ እንደሚሰነዝር ጠንቅቆ ያውቃልና ነው፡፡ ስለዚህ በኢትዮጵያዊነታችን የምንኮራ አማሮች ማንኛውንም ነገር በጥሞናና በትክክለኛነት በመገንዘብ በአሉባልታና ከዘመኑ የውሸት ፋብሪካ ምንጯ በሚነዛው የወሬ ውዥንብር ሣንታለልና ሣንፈታ በሁኔታውም ጨርሰን ተስፋ ሳንቆርጥ የአትንኩን ወኔያችንንም ጨርሰን ሳንተው የሌላውንም መብት ሣንነካ አርቀን በመመልከት በመጀመሪያ እንደማንኛውም የኢትዮጵያ ሕዝብ ሕጋዊ መብታችን እንዲከበር በጥሞና እንታገላለን እናሳስባለን...››

‹‹ኢህአዴጎች ጀግኖች ናቸውና በአላማቸው ባልወዳቸውም አከብራቸዋለሁ፡፡ የነሱ እናት ቀና ብላና በኩራት ትክሻዋን እየሰበቀችና ሽንጧን እያውረገረገች ትራመድ፡፡ የጀግና እናት መኩራት የጥንት ልማድ ስለሆነ ትኩራ፡፡ ሚስትም ልቧ በሐሴት ይሙላና ጉሮዋሸበዬ አንተን አንተን ይልሃል ግዳይ እያለች እሷም እንደ እማቷ ከጀግና ባሏ ጀግና ልጅ ለመውለድ ትማልል፡፡ የአንተ አለቃ እናትና ሚስት ግን.....››

ከመጽሐፉ የቀወሰደ

ዋጋው ብር 25
U.S.D. $ 15

ኖብል ማተሚያ ድርጅት ታተመ

PDF compression, OCR, web optimization using a watermarked evaluation copy of CVISION PDFCompressor